



# የሕዝብ አገልግሎቶች አሰጣጥ በአዲስ አበባ

አርታዒ

ሽፈራው በቀለ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

British Embassy
Addis Ababa





# የሕዝብ አገልግሎቶች አሰጣጥ
# በአዲስ አበባ


**አርታዒ**

**ሽፈራው በቀለ**



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
**Forum for Social Studies**

British Embassy
Addis Ababa

© 2007 ዓ.ም. ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

አዲስ አበባ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፡- ቆንጅት በለጠ

ISBN 13: 978-99944-50-53-4

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ 25864 code 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ: www.fssethiopia.org.et

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከብሪቲሽ ኤምባሲ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን ወይም አጋሮችን አመለካከት አያንፀባርቅም

# ጽዳት በአዲስ አበባ፣ ተግዳሮቶችና ተስፋዎች

*ወንድሙ አበጀ*

## 1. መግቢያ

በከተማ ጽዳት የከተማ ሕይወትን የሚያስጠብቅ/የሚያስቀጥል ወሳኝ አካል ነው፡፡ ጽዳት በከተማ ሕይወት ሂደት የሚመረቱ ቆሻሻና ለጤና ጎጂ የሆኑ ነገሮችን የሚያስወግድ ወይም/እና የሚያስተዳደር ነው፡፡ የጽዳት ችግር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ የተገኘው ከከተሞች ዕድገት ጋር ተያይዞ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ከከተሞች ዕድገት ጋር በተያያዘ የጽዳት ጉዳይ እጅግ በጣም ውስብስብ እየሆነ የመጣ ቢሆንም ጽዳት ባደጉ አገሮች ከተሞች በብቃት የሚከናወን ነው፡፡ በአዳጊ ሀገሮች ግን ጽዳት ትልቅ የከተሞች ጉድለት/ እንከን ሲሆን ይህም የሚስተዋለው ከሚገባው በላይ በሰፉ ከተሞች፣ በፕላን ባልተመሩ የከተማ አሰፋፈሮችና ከድህነት ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች ነው፡፡

የከተማ ሕይወትና እንቅስቃሴዎች የሚወሰኑት ከተማዋ በምትሰጠው የጽዳት አገልግሎት ደረጃ ነው፡፡ የከተማ የአካባቢ ብክለት ዋና ዋና ምንጮች የደረቅ ቆሻሻና ፍሳሽ ናቸው፡፡ ደካማ የጽዳት አገልግሎት ለውሃና ለአየር ከፍተኛ ስጋት ከመሆኑም በላይ የአፈር ብክለትን በማስከተል በተተኪው ትውልድ ሀብት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ ላለፉት አራት አስርተ ዓመታት ጽዳት የዓለም የዘላቂ ልማት አንገብጋቢ አጀንዳ ሆኗል፡፡ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ዓለምአቀፋዊና ሀገራዊ /አካባቢያዊ/ ጥረቶች በተለያየ ስም ሲደረጉ መቆየታቸውን፣ ከእነዚህም መካከል፣ 1980ዎቹ የውሃና ጽዳት አስርተ ዓመታት፣ አጀንዳ 21፣ የውሃ፣ የጽዳትና የጤና የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ ወ.ዘ.ተ… የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ሆኖም ለሚቀጥሉት ዓመታት ጽዳት የዓለም ዋና ተግዳሮቶች ሆኖ ይቀጥላል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2015 አንድ ሶስተኛው የዓለም ሕዝብ (ወደ 2.5 ቢሊዮን የሚጠጋ) የተሻሻለ የጽዳትን አገልግሎት የማያገኝ በመሆኑ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ማሳካት አይቻልም፡፡ (WHO/UNICEF, 2013) በአሁኑ ወቅት 15 ፐርሰንት የዓለም ሕዝብ መሠረታዊ የጽዳት አቅርቦት/አገልግሎት በማጣት በክፍት ቦታ ላይ ይፀዳዳል፡፡ (WHO/UNICEF, 2013)

አዲስ አበባ በጣም በማደግ ላይ ያለች ከተማ ስትሆን ነዋሪዎቿም ከሦስት ሚሊዮን ይበልጣሉ፡፡ ከተማዋ የጽዳት ችግር ያለባት ሲሆን ይህም በልማቷና በገፅታዋ ላይ ተፅዕኖ እያደረሰ ነው፡፡ በቂ ያልሆነው የጽዳት ሁኔታ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ፈርጀ ብዙ ሲሆን ከነዚህም መካከል የገጸ

ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ብክለት፣ ውሃ ወለድ በሽታዎች፣ የመልክአ ምድር ውበት ማጣት፣ የሙቀት መጠን የሚጨምር ጋዝ ልቀት በየጊዜው መጨመር እና አደገኛና የማይመለስ የሆነ የአፈር ብክለት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የከተማዋ የጽዳት ደረጃ ባለፉት አምስት ዓመታት የተሻሻለ ቢሆንም አጣዳፊና ዘለቄታዊ መፍትሔ የሚሹ ብዙ ችግሮች አሉት፡፡ የአፍሪካ ዋና ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ በጽዳት ደረጃ በምሳሌነት ልትጠቀስ የምትችል ከተማ መሆን ይገባታል፡፡ በሌላ በኩል ከተማዋ ሰፊ ከተማን የማደስና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ብዛት ያላቸው ረጃጅም ሕንፃዎችን በመገንባት ላይ ትገኛለች፡፡ እነዚህ ሁሉ የልማት ሥራዎች በአንድ ቦታ የሚያስተናግዱት የሕዝብ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ የተሻሉ የጽዳት መሠረተ ልማቶችን ይጠይቃሉ፡፡

የዚህ ፅሁፍ ዓላማ በአዲሰ አበባ የጽዳት አገልግሎት ላይ ሀሳቦችን ለመስጠትና ለማሻሻል የሚረዱ ግብዓቶችን ለመጠቆም ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ፅሁፍ የከተማዋን የጽዳት ሁኔታ ይተነትናል፡፡ የከተማዋ ገፅታና እንቅስቃሴ እንዲሁም ይህንኑ የሚያስተዳድረው ተቋም አደረጃጀት የሚዳሰሱ ይሆናል፡፡ በአዲስ አበባ ያለው የቆሻሻ ሥራ አመራር ልምድ እና ተግዳሮቶች በተለይም በደረቅ ቆሻሻና ፍሳሽ ዘርፍ ላይ በማተኮር ትንተና ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም ፅሁፉ የከተማዋን የደረቅ ቆሻሻና ፍሳሽ ሥራ አመራር ለማሻሻል ወሳኝ የሆነ የዘላቂ ጽዳት ግብዓቶችን ይሰነዝራል፡፡

## 2. የከተማ ልማትና ጽዳት

በማዕከላዊ የኢትዮጵያ ከፍታማ ቦታ የተቆረቆረችው አዲስ አበባ ከሰሜን እስከ ደቡብ ባለው የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የከፍታዋ መጠን ከ3000 ሜትር እስከ 2100 ሜትር ይደርሳል፡፡ የከተማዋ ስም «አዲስ አበባ» በአማርኛው ቃል እንደሚያመለክተው ከተማዋ ከሀገሪቷ የረጅም ዘመን ታሪክ ጋር ሲነፃፀር አዳጊ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ በ1887 (እ.ኤ.አ) የተመሠረተች ሲሆን ከ2ኛ የዓለም ጦርነት ወዲህ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ሕዝብ ዕድገት ያሳየች ቢሆንም ባለፉት አስርት ዓመታቶች ውስጥ የተመዘገበው የሕዝብ ብዛት ከፍተኛ ነው፡፡ የሕዝብ ብዛቱም በ1897፣ 30,000 ነዋሪዎች፣ በ1946 ደግሞ 180, 000፣ በ1964 ደግሞ ወደ 650,000፣ በ1984 ወደ 1.42 ሚሊዮን እና በ1994 ደግሞ 2.12 ሚሊዮን መድረሱን መረጃዎች ያሳያሉ (Berlan,1963, Wondimu, A & Alfakib E.; 1998)፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከተማዋ 3.1 ሚሊዮን የሚደርስ ነዋሪዎች ሲኖሯት (UN, 2012) ስፋቷ ደግሞ 540 ስኪዌር ኪሎሜትር ይሸፍናል፡፡

ሠንጠረዥ 1: በኢትዮጵያ ያሉ ከተሞች በክልል፣ በ2012 እ.ኤ.አ.

| ተራ ቁጥር | ክልል/አስተዳደር | የከተማ ክልል | በከተማው/በማዕከሉ የሚኖረው የሰው ብዛት | የከተማ ማዕከላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | 3 040 740 | 1 |
| 2 | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ | [1]387000 (ከተማ = 262884) | 1 |
| 3 | ትግራይ | መቀሌ ልዩ ዞን | 273 459 | 58 |
| 4 | አማራ | ባህር ዳር ልዩ ዞን | 266 432 (የከተማ ወረዳ 191016) | 204 |
| 5 | ኦሮሚያ | አዳማ ልዩ ዞን | 271562 | 366 |
| 6 | ደቡብ | ሐዋሳ | 212 665 | 176 |
| 7 | ሶማሌ | ጅግጅጋ | 147,482 | 82 |
| 8 | ሐረሪ | ሐረር | 110,457 | 1 |
| 9 | ጋምቤላ | ጋምቤላ | 59,393 | 12 |
| 10 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | አሶሳ | 37 365 | 23 |
| 11 | አፋር | አሳይታ<br>ሰመራ | 22548<br>3687 | 47 |
| | ጠቅላላ የከተማ ማዕከላት | | | 973 |

ምንጭ፡- CSA ትንበያ ለ 2012 እ.ኤ.አ.

አዲስ አበባ፣ በሀገሪቷ ካሉ ከተሞች ትልቋ ስትሆን በሠንጠረዥ 1 እንደተመለከተው በሁለተኛ ደረጃ ከተቀመጠው ከተማ በ10 እጥፍ የምትበልጥ ስትሆን በሚቀጥሉት ሃያ ዓመታት ፈጣን ዕድገት ይጠብቃታል፡፡ ይህ ልማት ቀጣይነት ባለው ዕቅድ በቅጡ ሊመራ ይገባል፡፡ የከተማ ፕላን ቀጣይ ልማትን በመቀየስ፣ በመተንበይ፣ ችግሮችን በመፍታት እና በመምራት ረገድ በከተማዋ የወደፊት ዕድገትና የከተማ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታን በተመለከተ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ባለፈው ክፍለ ዘመን ለከተማዋ በተዘጋጁ 10 ማስተር ፕላኖች ውስጥ የጽዳት ጉዳይ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነበር፡፡ አሁን ያለው የከተማው የስትራክቸር ፕላን በ2002 ተዘጋጅቶ ለ10 ዓመታት ያገለገለ ሲሆን፣ ትኩረቱ በፊዚካል ጉዳዮች ላይ ማለትም በመንገድ እና በመሬት አጠቃቀም

[1] ይህ አሀዝ የሚያሳየው የድሬዳዋና የገጠር አካባቢዋ ህዝብን ቁጥር ሲሆን፣ ሁለተኛው አሀዝ የሚያሳየው የድሬዳዋ ከተማ ህዝብን ቁጥር ነው።

ላይ ነው፡፡ ጽዳት የተገለፀው በጥቅሉ በመሆኑ አተገባበሩ ብዙ ችግሮች ገጥመውታል፡፡ ለምሳሌ፣ የደረቅ ቆሻሻን ብንወስድ፣ ለቆሻሻ ማከማቻ (Land fill) ከተጠቆሙት አራት ቦታዎች አንዳቸውም ለመተግበር አልቻሉም፡፡ በዚህ ምክንያት የተሻለ ቦታ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አስር ዓመታት ፈጅቷል፡፡

በከተማው ውስጥ የነበሩ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ቤቶችን መልሶ የማልማት ሥራ ባለፉት አምስት ዓመታት በከተማው በተወሰኑ ክፍሎች ማለትም በአራት ኪሎ፣ አሮጌው ቄራና ልደታ አካባቢዎች መከናወኑ በአሁኑ ወቅት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ቤቶች እንዲቀንሱ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ቆሻሻን ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ያለው የመንገድ ሽፋን በ1997 (AAAR,1997) ከነበረበት 3 ፐርሰንት በ2012 ወደ 14 ፐርሰንት በማደግ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ቤቶችን መልሶ የመገንባት ትላልቅ ፕሮጀክቶችም ሆኑ በኪስ ቦታዎች የተሰሩ ሥራዎች የቀበሌ ቤቶችን የተጨናነቀ ሠፈር እንዲቀንስ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ እነዚህም ቤቶች ባላቸው ባህሪያት ለጽዳት ችግሮች እጅግ በጣም የተጋለጡ አካባቢዎች ነበሩ፡፡

ባለፉት አስር ዓመታት በከተማ ውስጥ በተገነቡት የኮንደሚኒየም ቤቶችና አዲስ የሕይወት አኗኗር ዘይቤ ከፍተኛ የሆነ የቆሻሻ ምርትን የሚያስከትል ነው፡፡ ከየቤቱ የሚወጣው የደረቅም ሆነ የፍሳሽ ቆሻሻም ስለሚጨምር አፋጣኝ አሰባሰበን ይጠይቃል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ሦስት ደረጃ ያለው አስተዳደር ሲኖራት፣ እነሱም የከተማው (አስተዳደር)፣ 10 ክፍለ ከተሞች እና 116 ወረዳዎች (የበታች አስተዳደር) ናቸው፡፡ ከተማዋ ከአጎራባች የኦሮሚያ ከተሞች ጋር ከፍተኛ የሆነ የክልልና የከተማ ግንኙነት አላት፡፡ የከተማዋን ዓለማአቀፋዊ ሚና ይበልጥ የሚያጠነክረውና የሚያረጋግጠው ከተማዋ የአፍሪካ ሕብረት፣ የአፍሪካ የምጣኔ ሀብት ኮሚሽን እና ሌሎች አለምአቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶች መቀመጫ መሆኗ ነው፡፡ በከተማ ውስጥ ሦስት አካላቶች ስለቆሻሻ በዋናነት ኃላፊነት አለባቸው፣

- የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የመከታተልና የመቆጣጠር ሚናን በመያዝ፣
- የአዲስ አበባ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣ ለውሃ፣ ለፍሳሽ፣ ለህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ኃላፊ በመሆን፣

- የአዲስ አበባ የደረቅ ቆሻሻ የሥራ አመራር ኤጀንሲ እና የአዲስ አበባ የደረቅ ቆሻሻ መልሶ ማልማትና ማስወገድ ፕሮጀክት ቢሮ፣ ለደረቅ ቆሻሻ ሥራ አመራር ተጠሪ በመሆን[2] *

በሦስት ደረጃ ባለው አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎቶችን የማስተዳደር ሥልጣን ወደታችኛው የአስተዳደር እርከን ተከፋፍሏል፡፡ ሆኖም የፍሳሽ አገልግሎቶች የሚሰጡት በ8 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሲሆን እነዚህም በአዲስ አበባ ባሉ 10 ክፍለ ከተሞች የተለየ የራሳቸው የክልል ወሰን አላቸው፡፡

## 3. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ልምድና ተግዳሮቶች

የደረቅ ቆሻሻ ማለት ከተለያዩ ምንጮች በጠጣር መልክ የሚወገድ ቆሻሻ ነው፡፡ ደረቅ ቆሻሻ እንደየሁኔታው መሰረት በተለያየ መንገዶች መከፋፈል ይችላል፡፡ ክፍፍሉንም በስብጥር፣ በምንጭ እና በአወጋገድ ባህሪ መሠረት ማከናወን ይቻላል፡፡ እነዚህም ክፍፍሎች እንደገና በዝርዝር መከፋፈል ይቻላል፡፡ በስብጥር ረገድ የሚኖረው ክፍፍል ደግሞ ኦርጋኒክ እና ኦርጋኒክ ያልሆኑ ቆሻሻዎች በሚል የተከፋፈለ ነው፡፡ ምንጭን መሠረት ያደረገው ክፍፍል ደግሞ የሚመነጨውን ቆሻሻ ከቤት፣ ከተቋማት፣ ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከአገልግሎቶች እና ሌሎች ልዩ እና አደጋ አምጪ ቆሻሻ በሚል ይከፋፈላል፡፡ የአወጋገድ ባህሪን መሠረት በማድረግ በአብዛኛው የሚከፋፈለው የማዘጋጃ ቤት (የቤት፣ የተቋም፣ የተወሰኑ የንግድ፣ የመንገድ ቆሻሻ፣ ወ.ዘ.ተ...) እና አደጋ አምጪ (ተቀጣጣይ፣ የሚዝጉ ብረቶች፣ የሚፈነዳ ወይም መርዛማ) ቆሻሻዎች በሚል ይዘረዘራል፡፡

### 3.1 *የደረጃ ቆሻሻ ዓይነትና ስብጥር*

የአዲስ አበባ የደረቅ ቆሻሻ ዓይነት እስከዛሬ ድረስ ተጠንቅቆ አይታወቅም፡፡ በአሁኑ ወቅት ስለሚመነጨው ቆሻሻ የተደረጉ ጥናቶች የቆዩ ወይም ያልተሟሉ ናቸው፡፡ ስለሚመነጨው ቆሻሻ በ1997 የተደረገው (EHD,1997 እ.ኤ.አ.) ጥናት ሲሆን በተነጻጻሪም ሰፊ ይዞታ ያለው ነበር፡፡ ይህ ጥናት እስከአሁን ድረስ የሚሰራበት ቢሆንም ባለፉት አስርት ዓመታት የአኗኗር ሁኔታና የሚመነጨው ቆሻሻ በብዛት፣ በዓይነትና በምንጭ እጅግ በጣም ተቀይሯል፡፡ በ1997 ጥናት 76 ፐርሰንት ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤት፣ 18 ፐርሰንት ከተቋማት፣ ከቢዝነስ፣ ከኢንዱስትሪዎችና ከሆቴሎች፣ እንዲሁም 6 ፐርሰንቱ ደግሞ ከመንገድ ፅዳት የሚመነጩ እንደነበረ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የዚያን ጊዜ የቆሻሻ ስብጥር በአብዛኛው በአፂራና በአመድ

[2] እነዚህ ሁለቱ አካላት ከ1995 - 2001 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ የፅዳት፣ የውበት የፓርክ ልማት ኤጀንሲ ሥር ነበሩ፡፡

የተያዘ ሲሆን ይህም ከጠቅላላው የቆሻሻ ክብደት 60 ፐርሰንት ሲይዝ፣ ቀጣዩ ደግሞ ቅጠላ ቅጠሎችና ሳር ሲሆንም ከጠቅላላው 22.6 ፐርሰንት ይይዝ ነበር (EHD,1997 እ.ኤ.አ.)፡፡

ባለፉት ሃያ ዓመታት በከተማው የአኗኗር ዘይቤው በመቀየሩ በአብዛኛው ኦርጋኒክ ያልሆነው ቆሻሻ ማለትም ፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ ፕላስቲክ መያዣዎች፣ የልጆች የንፅህና መጠበቂያ፣ የምግብ ማሸጊያ ጣሳዎችና ፕላስቲኮች በመምጣታቸው በቆሻሻ ስብጥር ላይ ከፍተኛ ለውጥ ተከስቷል፡፡ ለውጡ ኦርጋኒክ ከሆኑት ቆሻሻዎች ውስጥ (እንደ አመድ ያሉት) እንዲቀንስ አድርጎ ሌሎቹ (ጫት ወ.ዘ.ተ...) እንዲጨምሩ አድርጓል፡፡ የአዲስ አበባ የቆሻሻ ማመንጨት መጠን በ1995[3] ከነበረው 1385 ሜትር ኪዩብ በቀን (0.17 ኪሎግራም /በነፍስወከፍ/ በቀን) ወደ 4052 ሜትር ኪዩብ በቀን[4] ደርሷል፡፡

በቅርብ ጊዜ የተካሄደው የIGNIS[5] ጥናት ከ2008 ጀምሮ በተወሰኑ ቀበሌዎች የመኖሪያ ቤት ቆሻሻን አስመልክቶ የተሰበሰበው መረጃ በተወሰነ ደረጃ አሁን ያለውን የመኖሪያ ቤት የቆሻሻ ስብጥር ስዕል የሚያሳይ ቢሆንም ሁሉን አቀፍ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡

በኢግኒስ መሠረት (IGNIS, 2010) ሳምንታዊ የመኖሪያ ቤት የቆሻሻ ማመንጨት ከ 0.89 - 3.77 ኪሎግራም /በነፍስወከፍ/ በሳምንት የሚደርስ ሲሆን የደረቅ ቆሻሻው ጠቅላላ ግምት ደግሞ 297, 079 ቶን/ በዓመት ነው (ሠንጠረዥ 2ን ይመልከቱ)፡፡ የመኖሪያ ቤት የቆሻሻ መጠን በገቢ ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም ከ0.17-0.54 ኪሎግራም /በነፍስወከፍ/ በቀን እንደሚደርስ ሲሆን በአማካይ ደግሞ 0.33 ኪሎግራም /በነፍስወከፍ/ በቀን ነው፡፡ የአዲስ አበባ የቆሻሻ ማመንጨት መጠን ከሌሎች በገቢ ከፍተኛና ዝቅተኛ ደረጃ ካሉ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው፡፡ በአውሮፓ ከተሞች እና በመካከለኛው ምስራቅ 1ኪሎግራም /በነፍስወከፍ/ በቀን ሲሆን በአፍሪካ ደግሞ 0.3-0.5 ነው፡፡ ዝቅተኛው የቆሻሻ ማመንጨት መጠን በሁለት ዋና ጉዳዮች ሊብራራ ይችላል፡፡ እነሱም የህገሬው ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆንና የዳበረ የእንደገና የመጠቀም ልምድ ናቸው፡፡

---

[3] Health bureau(1996)

[4] Addis Abeba Solid Waste Recycling and Disposal Project Office, 2012

[5] Income generation and Climate Protection valorizing municipal solid wastes in a sustainable way in emerging mega-cities (wondimu, 2000)

ሠንጠረዥ 2:- ሳምንታዊ የደረቅ ቆሻሻ የማመንጨት ድርሻ (ኪሎግራም/ በነፍስ ወከፍ/ በሳምንት)

| ድርሻ | ዝቅተኛ ገቢ | ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ገቢ | መካከለኛ ገቢ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ገቢ | ዝቅተኛ ደረጃ ኮንዶሚኒየም |
|---|---|---|---|---|---|
| ኦርጋኒክ ቆሻሻ | 0.43 | 0.72 | 0.92 | 2.30 | 1 |
| የእንጨት ቆሻሻ | *0.01* | 0 | 0.02 | 0.01 | 0 |
| ቆሻሻ ወረቀት | 0.05 | 0.04 | 0.1 | 0.15 | 0.07 |
| ቆሻሻ ፕላስቲክ | 0.04 | 0.05 | 0.1 | 0.15 | 0.08 |
| ቆሻሻብርጭቆ | 0.01 | 0.01 | 0.03 | 0.05 | 0.03 |
| ብረታ ብረት | *0.01* | 0.01 | 0.01 | 0.02 | 0.01 |
| ጨርቃ ጨርቅ | 0.05 | 0.05 | 0.04 | 0.03 | 0.02 |
| የማይንቀሳቀሱ ዕቃዎች | 0.02 | 0.05 | 0.01 | 0.04 | 0.02 |
| የንጽህና ምርቶች | 0.01 | 0.03 | 0.1 | 0.21 | 0.07 |
| አደገኛና ልዩ ቆሻሻ | 0 | 0 | 0.01 | 0.01 | 0.01 |
| የብስባሽ ስብስብ | 0 | 0 | 0.01 | 0.01 | 0.01 |
| ልዩ ልዩ | 0.01 | 0.01 | 0.01 | 0.03 | 0.01 |
| ከሰል | 0.02 | 0.02 | 0.04 | 0.05 | 0.04 |
| ረቂቅ ቆሻሻ | 0.22 | 0.36 | 0.35 | 0.69 | 0.19 |
| ድምር | 0.89 | 1.34 | 1.75 | 3.77 | 1.54 |

ምንጭ፣ IGNIS, 2010

የአዲስ አበባ ከተማ የቆሻሻ ስብጥር እየተቀየረ ሲሆን ኦርጋኒክ ያልሆነው ቆሻሻ እየጨመረ የመጣው በጣም በከፍተኛ መጠን ነው፡፡ የIGNIS ጥናት እንደሚያመለክተው የኦርጋኒክ ቆሻሻ ስብጥር ከ50 ፐርሰንት እስከ 62 ፐርሰንት ሲሆን ልዩነቱም በወርሀዊ ገቢ መጠን ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የኦርጋኒክ ቆሻሻ ከ1997 ከነበረበት መጠን 80 ፐርሰንት እጅግ በጣም ቀንሷል፡፡ በተቃራኒው ኦርጋኒክ ያልሆነው ቆሻሻ ከ1997 ከነበረበት 18 ፐርሰንት በ2008 ወደ 50 ፐርሰንት በመድረስ ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ሁሉንም የቆሻሻ ስብጥር ስንመለከት (በ IGNIS እንደተደረገው በመኖሪያ ቤቶች ቆሻሻ የተመለከተ ብቻ ሳይሆን) ኦርጋኒክ ያልሆነው

የቆሻሻ አይነት ድርሻ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ለዚህም ምልአት ባለው ጥናት ላይ ተመርኩዞ የደረቅ ቆሻሻ ክፍፍልን ማወቅ በአዲስ አበባ ደረጃ እጅግ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ለሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ግብዓቱ ለፖሊሲ ውሳኔና የዕለት ተዕለት የቆሻሻ አስተዳደር ተግባራትን ለማከናወን ይረዳል፡፡ የቆሻሻውም ዓይነት ሳይታወቅ የሚወሰደው እርምጃ ውጤታማና ቀጣይነት አይኖረውም፡፡

### 3.2 *የደረጃ ቆሻሻ አገልግሎቶች ሽፋን እና አሰባሰብ*

የደረቅ ቆሻሻ የከተማው ዋና አገልግሎቶች ሲሆን ውስብስብ የሚሆነው በከተማ ባህሪ እና ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር በተያያዘ ነው፡፡ የአዲስ አበባ የቆሻሻ አሰባሰብ አቅም ባለፈው አስር ዓመታት ከፍተኛ መሻሻሎችን አስመዝግቧል፡፡ በ1982 ከነበረበት 37 ፐርሰንት በ1999 ወደ 60 ፐርሰንት ሲደርስ በ2011 ደግሞ 92 ፐርሰንት ደርሷል (CSA, 2012)፡፡ የቤት ለቤት የቆሻሻ ማሰባሰብ ሥራ ለመኖሪያ ቤቶች በሕብረት ስራ ማህበራት እና ለተቋማት ደግሞ በግል ድርጅቶች መካሄዱ በቆሻሻ አሰባሰቡ ሽፋን እና መጠን ላይ ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ አስችሏል፡፡ አገልግሎቱ በሁሉም ቦታዎች ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን የመሰብሰቢያው ክፍያ ደግሞ ለመኖሪያ ቤቶች የውሃ ክፍያውን 20 ፐርሰንት ሲይዝ ለተቋሞች ደግሞ የውሃ ክፍያውን 42 ፐርሰንት ይይዛል፡፡ የቆሻሻ አሰባሰብ መጠን መሻሻል የከተማውን የጽዳት ሁኔታና ስነምህዳር ቢቀይርም እስካሁን ድረስ ወንዞች የቆሻሻ መጣያ ናቸው፡፡ በ1999 በተደረገ የዳሰሳ ጥናት 47 ፐርሰንት የሚሆኑ የፍሳሽ መስመሮችን፣ ክፍት ቦታዎችን እና ወንዞችን ለቆሻሻ መጣያ ይጠቀማሉ (wondimu, 2000)፡፡

ሠንጠረዥ 3:- በክፍለ ከተማና በወረዳዎች የሚገኙ የማጠራቀሚያ ገንዳዎችና ቅድመ አሰባሰብ

| ክፍለ ከተማ | የወረዳዎች ብዛት | ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች | | | ቅድመ ሰብሳቢዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚሰሩ ገንዳዎች | የማይሰሩ ገንዳዎች | አዲስ የተጨመሩ 2005 ዓ.ም. | ቅድመ ሰብሳቢ ማህበራት | የማህበራት አባላት | በየማህበራቱ ያሉ ገንዳዎች |
| ኮልፌ | 15 | 70 | 5 | 46 | 74 | 1000 | 2 |
| ልደታ | 10 | 47 | 7 | 77 | 37 | 416 | 1 |
| አቃቂ | 11 | 66 | 9 | 35 | 32 | 260 | 3 |
| ንፋስ ስልክ | 12 | 74 | 1 | 55 | 73 | 730 | 2 |
| ቦሌ | 14 | 115 | | 51 | 70 | 630 | 2 |
| የካ | 13 | 86 | 11 | 48 | 54 | 448 | 2 |
| ቂርቆስ | 11 | 55 | 5 | 28 | 48 | 471 | 2 |
| ጉለሌ | 10 | 72 | 2 | 27 | 49 | 490 | 2 |
| አራዳ | 10 | 47 | 7 | 27 | 41 | 551 | 1 |
| አዲስ ከተማ | 10 | 87 | 11 | 28 | 54 | 524 | 2 |
| ድምር | 116 | 719 | 58 | 372 | 532 | 5520 | |

***ምንጭ:*** Addis Ababa Solid Waste Recycling and Disposal Project Office, 2012

የመኖሪያ ቤቶችን የደረቅ ቆሻሻ የቅድመ አሰባሰብ ተግባር /ማለትም ከመኖሪያ ቤት እስከ የማጠራቀሚያ ገንዳዎች የሚከናወነው በማህበራት ሲሆን አብዛኛው አባላት ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም እንደ ጊዜያዊ ማከማቻ ያገለግላል፡፡ ከተማዋ ወደ 1091 የሚጠጉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ያላት ሲሆን እነዚህም ለ116 ወረዳዎች በሙሉ የሚያገለግሉ ናቸው (ሠንጠረዥ 3ን ይመልከቱ)፡፡ የማጠራቀሚያ ቦታዎችን መጨመር የሰብሳቢዎቹን የሥራ ሁኔታ እንዲሁም የአገልግሎቱን ሽፋን እንዲሻሻል አድርጓል፡፡ ሆኖም በብዙ ቦታዎች እንደሚታየው ገንዳዎች የሚቀመጡበት ቦታ ለመኖሪያ ቤቶች ቅርብ ሲሆን (አንዳንድ ጊዜ ከመኖሪያ ቤቶች ከ5 ሜትር ባልራቀ) ይህም በማናቸውም ሁኔታ ተቀባይነት ያገኙ መለኪያዎችን የሚቃረን ነው፡፡ ገንዳዎቹ በጊዜው በፍጥነት እንዲነሱ ስለማይደረግ በአካባቢው ለሚኖሩ ነዋሪዎች ከፍተኛ የጤና ስጋት ናቸው፡፡ ስለሆነም የቆሻሻ ማሰባሰብ ዋና ዓላማው የሕዝብ የጤና አገልግሎት ከመጥፎ ሽታና ከዝንቦች መራቢያ እንዲከላከል ለማድረግ ቢሆንም ገንዳዎቹ ከመኖሪያ ቤት

አጠገብ ስለሚቀመጡ በአካባቢው ባሉ ነዋሪዎች ላይ የጤና ስጋትን ያስከትላሉ፡፡ የሚገርመው ደግሞ አንዳንድ ገንዳዎች ለአረንጓዴ ቦታ በተተወ ቦታዎች ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ለተሻለ እና ለተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና ዝውውር ተገቢ የሆነ የማጠራቀሚያ ገንዳዎች ምርጫ ሊካሄድ ይገባል፡፡ የማጠራቀሚያ ገንዳዎቹም የዕቅድ መለኪያዎችን ያሟሉ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም የቦታ አመራረጡ ጥንቃቄና የከተማ ፕላንን ያስተዋለ ሊሆን ይገባዋል፡፡

ሁለተኛው የከተማዋ ቆሻሻ የማሰባሰብ ስርዓት (ገንዳዎችን ወደ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የማመላለስ) በትናንሽ መኪናዎች የሚከናወን ሲሆን ይህም የቅብብሎሽ ጣቢያ (Transfer Station) የለውም፡፡ ይህ አሠራር ከፍተኛ ወጪን ከመጠየቁ በላይ ብቃት የለውም፡፡ ምክንያቱም መኪናው 8 ሜትር ኪዩብ የሆነውን ገንዳ በደርሶ መልስ ለማመላለስ ወደ 40 ኪሎ ሜትር ስለሚጓዝ ነው፡፡ እነዚህ መኪናዎች በቀላሉ ወደ ነዋሪ ቤቶች በመግባት ቆሻሻውን ማንሳት ስለሚችሉ ቆሻሻን በመጀመሪያ ደረጃ ለማመላለስ ማገልገል ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አሁን ያለውን ስርጭት ለማሻሻል አሁን የሌሉ ሁለት ደረጃዎችን ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡ እነሱም፣ የቅብብሎሽ ጣቢያ (Transfer Station) ኖሮ ቆሻሻው የሚለይበትና የሚታሸግበት እንዲሁም ቆሻሻውን በትላልቅ መኪናዎች እስከ ማስወገጃ ስፍራ የማድረስ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4:- የመኪና ምልልስና የቀን የአሰባሰብ ብቃት

| ክፍለ ከተማ | የወረዳ ዎች ብዛት | የሚሰሩ ተሽከር ካሪዎች | የማይሰሩ ተሽከርካሪ ዎች | አማካይ የቀን ጉዞ በተሽከርካሪ (ጉዞ/በቀን/በተሽከ ርካሪ) | አማካይ የቀን የደረቅ ቆሻሻ ምልልስ በኪዩቢክ ሜትር |
|---|---|---|---|---|---|
| ኮልፌ | 15 | 9 | 7 | 7 | 700 |
| ልደታ | 10 | 3 | 7 | ? | 294 |
| አቃቂ | 11 | 5 | 4 | 7 | 336 |
| ንፋስ ስልክ | 12 | 5 | 7 | 16 | 576 |
| ቦሌ | 14 | 4 | 14 | 12 | 384 |
| የካ | 13 | 5 | 13 | 14 | 312 |
| ቂርቆስ | 11 | 5 | 12 | 12 | 422 |
| ጉለሌ | 10 | 5 | 6 | 6 | 336 |
| አራዳ | 10 | 5 | 10 | 7 | 307 |
| አዲስ ከተማ | 10 | 7 | 10 | 16 | 385 |
| ድምር/አ ማካይ | 116 | 53 | 90 | | 4052 |

*ምንጭ:* Addis Ababa Solid Waste Recycling and Disposal Project Office, 2012

ቆሻሻን በትራንስፖርት የማመላለስ አቅም በቀን 4052 ሜትር ኪዩብ ሲሆን ከፍተኛው በኮልፌ ቀራኒዮ ሲመዘገብ ይህም የሆነው በክፍለ ከተማው ብዙ ወረዳዎች ስላሉና (ከሌሎች ክፍለ ከተሞች በ50% ይበልጣል) ለቆሻሻ መጣያውም ስፍራ ቅርብ በመሆኑ ነው፡፡ አማካይ የቀን ምልልስ 10 ጉዞ/ በመኪና/ በቀን ነው፡፡ ይህም በሠንጠረዥ 4 ተመልክቷል፡፡

ለመንገድ ፅዳት 1700 ፅዳት ሠራተኞች ሲኖሩ፣ አገልግሎቱንም የሚሰጡት በዋና ዋና መንገዶች ነው፡፡ በከተማው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶችን ማየት የተለመደ አይደለም፡፡ ያሉትም ቢሆኑ (በሠንጠረዥ 5 እንደተመለከተው ለአዲስ አበባ በሙሉ 1500 እንደሚደርሱ) በአግባቡ ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቱን መጨመር ተገቢ ቢሆንም ግንዛቤን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግና በቆሻሻ መጣያ ቅርንጫቶች የመጠቀም ልምድን ለማዳበር የሚያስችሉ ዘመቻዎች ሊካሄዱ ይገባል፡፡ ንፁህ የሆነ መንገድ አለመኖር የውሃ መውረጃ መስመሮችን በመዝጋት በመንገዱ ላይ ከፍተኛ አደጋ ያደርሳል፡፡ እነዚህ አስፋልት መንገዶች

በከፍተኛ ወጪ ተሰርተው ከተመረቁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥገና እየጠየቁ ይገኛሉ፡፡

*ሠንጠረዥ 5:- የቆሻሻ ማጠራቀሚያ እና የመንገድ ፅዳት ሠራተኞች ብዛት በክፍለ ከተማና በወረዳ*

| ክፍለ ከተማ | የወረዳዎች ብዛት | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | | | የመንገድ ፅዳት ሠራተኞች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በሥራ ላይ | አዲስ | የተበላሸ | |
| ኮልፌ | 15 | 134 | 80 | 0 | 330 |
| ልደታ | 10 | 114 | 100 | 74 | 164 |
| አቃቂ | 11 | 27 | 75 | 11 | 46 |
| ንፋስስልክ | 12 | 32 | 80 | 0 | 162 |
| ቦሌ | 14 | 45 | 150 | 16 | 148 |
| የካ | 13 | 53 | 100 | 6 | 248 |
| ቂርቆስ | 11 | 299 | 10 | 74 | 213 |
| ጉለሌ | 10 | 50 | 19 | 20 | 30 |
| አራዳ | 10 | 228 | 0 | 125 | 195 |
| አዲስ ከተማ | 10 | 43 | 0 | 11 | 164 |
| ድምር | 116 | 1025 | 614 | 337 | 1700 |

***ምንጭ፣*** Addis Ababa Solid Waste Recycling and Disposal Project Office, 2012

አዲስ አበባ በየቀኑ 1220 ቶን ወይም 4052 ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ በከተማው ውስጥ ባለው ብቸኛ የማስወገጃ ዘዴ በቆሼ ረፒ መጣያ ጣቢያ ትጥላለች፡፡ ቆሼ ረፒ የቆሻሻ መጣያ ጣቢያ ወደ 30.5 ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን ከ1964 ጀምሮ ላለፉት አርባ ዓመታት እያገለገለ ይገኛል፡፡ ጣቢያው በየቀኑ የአፈር ሽፋን እንደማይደረግለት፣ መሬቱ እንዳይበከል የሚወሰድ እርምጃ እንደሌለ፣ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ እንደማይሰራ፣ የጋዝ መሰብሰብ እንደማይከናወን እና ምንም የሴል ዝግጅት እንደማይደረግለት መረጃዎች ይጠቁማሉ (ZTS, 2012)፡፡

ጣቢያው ባለፉት 30 ዓመታት በመኖሪያ ቤቶችና በሕዝብ ተቋማት (ትምህርት ቤትን ጨምሮ) የተጨናነቀ ሲሆን ይህም በአካባቢው፣ በማህበረሰቡ እና በመሬቱ ገፅታ ላይ አደገኛ/አስጊ የጤና ችግሮችን ይፈጥራል፡፡

የቆሻሻ መጣያው ጣቢያ ለብዙ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች የመስሪያ ቦታና የመኖሪያ ሰፈር ነው። በቅርብ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በጣቢያው

660 ሰዎች ከቆሻሻው ውስጥ የሚጠቅም ነገር ለማግኘት የሚለቅሙ ሲኖሩ እነዚህም ይህንን ጣቢያ እንደ መስሪያ ቦታቸው እንደሚጠቀሙበትና 73 ፐርሰንት የሚሆኑት ከ21-40 ዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ /ZTS, 2012/፡፡

የቆሻሻ መጣያ ጣቢያው ሙሉ ከመሆኑም በላይ በዝናብ ወቅት ተደራሽ አይደለም፡፡ አሁን ጣቢያው በመዘጋት ሂደት ላይ ሲሆን አዲሱ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እስከሚከፈት ድረስ የተወሰነው ክፍል ብቻ ለተወሰኑ ዓመታት አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል (ዝርዝሩን በምስል 1 ይመልከቱ)፡፡

ምስል 1፤ የረጲ ቆሻሻ መጣያ ጣቢያና እንደገና የመጠቀም ሃሳብ




*ምንጭ፡ Poyry, 2007*

አዲስ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ለመክፈት ላለፉት አስር ዓመታት ሙከራ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ ረጅም ሂደት ሊከሰት የቻለው በከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን (structure plan) ዕቅድ ላይ ጠንካራ የሆነ ይሁንታን ባለማግኘቱ ነው፡፡ ይህ ፕላን በአዲስ አበባ ጫፎች 4 ጣቢያዎችን ለመክፈት ሃሳብ ያቀረበ ሲሆን ይህም ጠለቅ ያሉ ጥናትና የፕላንና የዕቅድ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም፡፡ በአሁኑ ወቅት ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ በኦሮሚያ ክልል ልዩ ስሙ “ጨቤ ወረገኑ” በሚባል ቦታ አዲስ የቆሻሻ መድፊያ ጣቢያ ለመክፈት ከ2010 እ.ኤ.አ. ጀምሮ ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የዚህ የረጅም ጊዜ ሂደት ጥሩ ጎኑ በአዲስ አበባና በአጎራባች ከተሞች ያለውን ትብብር ለማጠናከር የፈጠረው ዕድል ነው፡፡ ይህ ትብብር የብዙ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እና /ወይም ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን

ብክለት ለመቀነስ እና በቆሻሻ አወጋገድ ሥራ አመራር ከስፋት ሊገኝ የሚታሰበውን ጥቅም የሚያስገኝ ይሆናል፡፡

### 3.3 *አደገኛ እና ልዩ ቆሻሻዎች*

*የማዘጋጃ ቤት ቆሻሻዎች በመባል ከሚታወቁት የመኖሪያ ቤት፣ የተቋምና የንግድ ቆሻሻዎች ውጭ ልዩና አደገኛ ቆሻሻዎች በመባል የሚታወቁ አሉ፡፡ እነዚህም ቆሻሻዎች ልዩ ትኩረት የሚሹት ከመርዛማነታቸውና ከዓመት ዓመት መጠናቸው እየጨመረ ከመምጣቱ አንጻር ነው፡፡ ከልዩና አደገኛ ቆሻሻዎች መካከል በዋናነት የኮንስትራክሽን፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የሕክምና፣ የኢንዱስትሪና የኬሚካል ቆሻሻዎች ይገኙበታል፡፡*

*በኢትዮጵያ ዛሬ እነዚህን ቆሻሻዎች አስመልክቶ የተለየ የመሰብሰብ ሥርዓት የለም፡፡ በአብዛኛው እነዚህ ቆሻሻዎች ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር በመዋሃድ የመርዛማነት ባህሪያቸው እየጨመረ ነው፡፡ ከኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች የትም ቦታ ተጥለው መንገዱንና ያለውን ክፍት ቦታ በማበላሸትና እንቅፋት በመፍጠር ላይ እንደሚገኙ በግልፅ የሚታይ ሃቅ ነው፡፡*

*የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም መጠኑ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን የመጣል/የማስወገድ ልምዱ ዝቅተኛ ስለሆነ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በቅርቡ የኤሌክትሮኒስ ቆሻሻዎችን እንደገና ለመጠቀም ከአዲስ አበባ 30 ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው አቃቂ የ* 'Demanufacturing Facilitiy (DMF)' *መከፈቱ ይታወቃል፡፡ ይህ ተቋም ኮምፒዩተሮችን፣ ታይፕራይተሮችን፣ የማተሚያና የኮፒ ማሽኖችን በመበታተን በተለያዩ የውጤት ዓይነቶች ማለትም ብረት፣ አሉሚኒየም፣ የአልሙኒየም ኬብል እና* "Printed wiring board" *እና ፕላስቲክ በመለየት ያዘጋጃል* (Manhart, et al, 2013)*፡፡ ይህ ተሞክሮ ተንቀሳቃሽ ስልኮችና ሌሎች መሳሪያዎች እንዲያካትት ቢደረግና ይህንንም ለመለየት እንዲቻል ግንዛቤ የመስጠትና የማነቃቂያ ሥርዓት ማበጀት ተገቢ ይሆናል፡፡*

*የሕክምና እና የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ከዚህ ዘርፍ የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለመሰብሰብና ለማስወገድ ቅርብ የሆነ ክትትልና ቁጥጥርን ይጠይቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለእንዲዚህ ዓይነት አደገኛ ቆሻሻዎች ልዩ የሆነ የማስወገጃ ቦታ የለም፡፡ በመሆኑም ልዩነት ሳይደረግ እንደዚህ ዓይነት ቆሻሻዎች በረጲ የመጣያ ስፍራ ይጣላሉ፡፡*

*የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ የከተማው አስተዳደር ዋነኛ ጉዳይ ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅና ያለውን ስነምሕዳር ሊቀለበስ /ሊቀየር ከማይችል ብክለት ለመጠበቅ ነው፡፡ በሀገር አቀፍና በከተማ ደረጃ የህክምና፣ የኢንዱስትሪና የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን*

ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስወገድና ለማስተዳደር ስትራቴጂዎች ሊቀረፁ ይገባል፡፡

### 3.4 *በደረጃ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሚና ያላቸው አካላት*

በአዲስ አበባ የደረቅ ቆሻሻ ዘርፉ የተለያዩ አካላትን ማለትም የግል፣ የመንግስት፣ የሕብረት ሥራ ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ ማህበረሰብ ወ.ዘ.ተ…የያዘ ነው፡፡ አገልግሎቶቹ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚከተሉት መልኩ ተከፋፍለው ይገኛሉ፡፡

| | |
|---|---|
| በወረዳ ደረጃ፤ | የመጀመሪያ ደረጃ ማሰባሰብ |
| በክፍለ ከተማ ደረጃ፤ | ሁለተኛ ደረጃ ማሰባሰብ |
| በከተማ ደረጃ፣ | ማስተባበር፤ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የቅብብሎሽ ጣቢያ |
| በክልል (አዲስ አበባና ኦሮሚያ) ደረጃ፤ | ለወደፊቱ በሚገነባው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጣቢያን አስመልክቶ ስለሚኖረው ትብብር |

የቅድመ መሰብሰብ ሥራን የሚያከናውኑ ማህበራት ሥራቸውን የሚያከናውኑት በእጅ በሚገፋ ጋሪ ሲሆን ወረዳውም ለተሰበሰበው ቆሻሻ በኪሎግራም ክፍያውን ይፈፅማል፡፡ ወደ አምስት የሚሆኑ የግል ድርጅቶች ከንግድና ከተቋማት ቆሻሻን የሚሰበስቡ ሲሆን ይህም በከተማዋ የሚሰበሰበውን ቆሻሻ 1/3ኛ ይሆናል፡፡

የደረቅ ቆሻሻ ንግድ የሚያካትታቸው እንደገና መልሶ የመጠቀም ሥራን የሚያከናወኑ በተለምዶ "ቆርቆሮሪያሌው" በመባል የሚጠሩት ሲሆኑ እነዚህም ፕላስቲክና ብረቶችን እንደገና ለመጠቀም የሚያደርጉት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይም የብረት ፍላጎት በመጨመሩ የእነዚህን ሰዎች ስራ እጅግ ሳቢና አጓጊ እየሆነ መጥቷል፡፡

## 4. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ልምድ እና ተግዳሮቶች በአዲስ አበባ

### 4.1 *የፍሳሽ፣ የሳኒቴሽን አገልግሎት*

ከምንጠቀመው ውሃ ውስጥ ከ70-80 ፐርሰንት ያህሉ የፍሳሽ ቆሻሻ የሚሆን ነው፡፡ በአጠቃላይ ፍሳሾች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እኒህም የቤት እና የኢንዱስትሪ ናቸው፡፡ የቤት ውስጥ ፍሳሽ የሚመጣው ከቤቶች፣ ከቢዝነስና ከተቋማት ነው፡፡ ይህ ፍሳሽ በአብዛኛው ኦርጋኒክ (ተፈጥሮአዊ) የሆነውን ቁስ የሚያካትት (በሌላ በኩል ኦርጋኒክ ያልሆኑ ከዕቃ ማጽጃ የሚመጡ ቢኖሩም)ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች፣ ከኢንዱስትሪው ዓይነት ጋር

በተያያዘ ይዘቱ የተለያየ ቢሆንም በአጠቃላይ ሲገለፅ መርዛማና በከባድ ማዕድኖች የተበከለ ነው፡፡

የፍሳሽ ቆሻሻ ችግር በአዲስ አበባ ባሉ ብዙ ቦታዎች በተለይም በቆዩና የዝቅተኛ ገቢ መንደሮች የሚስተዋል ዋነኛ ችግር ነው፡፡ ፍሳሽ ከቤት፣ ከከብት እርባታ፣ ከኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ቢዝነስ ተቋም በተናጠልእና ንፅህና በጎደለው መልኩ ይወገዳል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ያለው የፍሳሽ አገልግሎት ሽፋን ወደ 44.3 ፐርሰንት ብቻ ይገመታል (AAWSA, 2012)፡፡ በኢትዮጵያ የማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መረጃ መሰረት (CSA, 2012) በአዲስ አበባ የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት 94.7 ፐርሰንት ሲሆኑ በሀገሪቱ ከተሞች ደግሞ 66 ፐርሰንት ነው፡፡ ሆኖም ይህ መረጃ የመፀዳጃ ቤቱን የጥራት ደረጃ አያሳይም፡፡ ምክንያቱም ብዙዎቹ መፀዳጃ ቤቶች የጋራ የሆኑና ጥራታቸውም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሆኖም የከተማው የሳኒቴሽን ሁኔታ እየተሻሻለ መምጣቱን ለመረዳት በ1994 እና በ2007 የነበረውን መረጃ ስንመለከት፣ መፀዳጃ ቤት የሌላቸው ቤተሰቦች 24 ፐርሰንት እና 14 ፐርሰንት እንደቅደም ተከተላቸው መሆኑን የማዕከላዊ ስታስቲክስ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በግል የተያዙ የመፀዳጃ ቤቶች በተሻለ የተያዙና ሁልጊዜ (በመደበኛነት) የሚመጡ ናቸው፡፡ "የቀበሌ ቤቶች" ተብለው በሚጠሩት መኖሪያ ቤቶች ያለው የመፀዳጃ ቤቶች ግን በአብዛኛው በደካማ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ሲሞሉም ፍሳሹ የመነሳቱ ሁኔታ ድክመት ይስተዋልበታል፡፡ ስለሆነም በዝናብ ወቅት ሽንት ቤቱ የመሙላትና ከወለል በላይ በመሆን የመውጣት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

በአዲስ አበባ በአማካይ የውሃ ፍጆታ 401 ኪዩቢክ ሊትር በቀን ሲሆን፣ በቀን የሚመረተው ፍሳሽ ደግሞ 96, 000 ሜትር ኪዩብ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 22, 830 ሜትር ኪዩብ በቀን የሚሰበሰብና የሚጣራ ሲሆን ይህም 23 ፐርሰንት ያህል ብቻ ይሸፍናል (AWWSA, 2012)፡፡ በሽንት ቤት ጉድጓድ ውስጥ ያለው ፍሳሽ ቆሻሻ በየቀኑ መሰብሰብ ስለማያስፈልገውና የማጣራት ሂደትም ስለማይደረግለት የአገልግሎት ሽፋኑ ከ23 ፐርሰንት ያህል ብቻ ይሸፍናል ይበልጣል ማለት ነው፡፡

አብዛኛው ፍሳሽ ቆሻሻ የሚሰበሰበው በፍሳሽ ማንሻ መኪና ነው፡፡ ከ 2005 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት በፍሳሽ ማንሻ መኪናዎች የተመላለሰው ፍሳሻ ቆሻሻ በአማካይ 440, 175 ሜትር ኪዩብ በዓመት ነበር፡፡ የመጸዳጃ ቤቶችን ፍሳሽ የመምጠጥ አገልግሎት የሚሰጡ 99 የፍሳሽ ማንሻ መኪናዎች ያሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 67ቱ የመንግስት፣ 32 ደግሞ የግልና የተቋም ናቸው (AWWSA, 2010)፡፡

የፍሳሽ መስመር አገልግሎት በጣም ጥቂት የሆነውን የከተማ ክፍል ብቻ ይሸፍናል፡፡ የአዲስ አበባ የፍሳሽ ሥርዓት ከ1930ዎቹ ከተገነቡት ጥቂት በስተቀር የዝናብና የፍሳሽ መስመሩ የተለያየ ተብሎ የሚታመን ነው፡፡ ከተማዋ ቀደምትና ትላልቅ ጣምራ (የዝናብና የፍሳሽ) መስመሮች ያሏት ሲሆን ይህም በ1930ዎቹ የተገነቡ ናቸው፡፡ በከተማዋ በተለይም በስታዲየም አካባቢ ባለው ረባዳ ስፍራ ያለው የፍሳሽ መስመር ወርድና ቁመት 2.7 ሜትር በ2.8 ሜትር ይደርሳል (BECEOM, 1982)፡፡

የፍሳሽ መስመሩ ከቃሊቲ የማጣሪያ ጣቢያ ጋር የተመሠረተው በ1981 ቢሆንም እስካሁን ድረስ ብዙም እድገት አላሳየም፡፡ በ1997 የፍሳሽ መስመሩ ከ1600 ደንበኞች ጋር ብቻ የተያያዘ ሲሆን ይህም የከተማውን 0.5 ፐርሰንት ድርሻ ይይዛል (AAAR, 1997)፡፡ ዛሬ የፍሳሽ መስመሩ 51, 500 አባወራ እንዲሁም 2164 ሌሎች ደንበኞች አለው (AASWSA, 2012)፡፡ ማንም ሰው በቀላሉ ሊረዳው የሚችለው በከተማዋ ውስጥና በማስፋፊያ ቦታዎች የሚካሄደው የህንጻ ግንባታ ሥራዎች ለፍሳሽ መስመር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡

ለፍሳሽ መስመር ያለው ከፍተኛ ፍላጎት እስካሁን ድረስ አልተሟላም፡፡ ስለሆነም ብዙ ቤቶች በሕገወጥ መንገድ የራሳቸውን የፌሳሽ ማጠራቀሚያ (የሽንት ቤት ጉድጓድ) ከፍሳሽ መስመሩ ጋር በማያያዝ ይጠቀሙበታል፡፡ በ1996 በ Information Lemate-Ketema በተካሄደ ጥናት ወደ 20, 000 የሚሆኑ ቤተሰቦች ከፍሳሽ መስመሩ ጋር እንደተገናኙ የሚያሳይ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የተመዘገቡት ደንበኞች ግን 1600 ብቻ ነበሩ፡፡

በከተማው በተለይም በውስጥ ክፍሎቿ ወንዞች የፍሳሽ ቆሻሻ ለማስወገድ አንዱ መውጫ መንገዶች ናቸው። በዚህም ምክንያት በወንዞች ላይ የኦርጋኒክ ብክለት የሚደርስ በመሆኑ በብዙ ባክቴሪያና ቫይረስ የተበከለ ነው። ከጉርደሜ ወንዝ በተወሰዱ ሦስት ናሙናዎች ላይ በተካሄደ የባክቴሪዎሎጂካል ትንተና ያረጋገጠው ብዙ ዓይነት በሽታ አምጪ የሆኑ ህዋሳት (ለምሳሌ፣ klebsiella sp., E.coli, pseudomonas, entrobacter spp.and citrobacter spp.) እንዳሉበት ነው። በወንዙ ላይ በተደረገ የበሽታ አምጪ የሆኑ ህዋሳት ቆጠራ ከ21, 000 እስከ 3,110,000 ህዋሳት በሚሊ ሊትር የተገኘ ሲሆን ይህም ከመለኪያው ማለትም 161 ህዋሳት በሚሊ ሊትር ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው (Abdi et al,1990)።

### 4.2 የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች

በዓለም ላይ ያሉ ንፁህና ሳቢ የሆኑ ከተሞች ጥሩ የሆነ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች አሏቸው፡፡ ጥሩ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ከከተማ ውበት ጋር የተሳሰሩ

ሲሆን የሚሰጡትም አገልግሎት የአካል ጉዳተኞችንም የሚያካትት ነው፡፡ ከንጉሰ ነገስታት ዘመን ጀምሮ አዲስ አበባ የረጅም ጊዜ የሕዝብ መፀዳጃ አገልግሎት አላት፡፡ በፒያሳ የሚገኘው የሕዝብ መፀዳጃ ቤት (ከኢትዮጵያ ሲኒማ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘው) ለመሃል ከተሜው በቂ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ በኋላም የሕዝብ መፀዳጃ ቤት የመታጠቢያ ቤትና የልብስ ማጠቢያ አገልግሎቶች (ለምሳሌ፤ በመስቀል አደባባይ ይገኝ በነበረው የመፀዳጃ ቤት) ዝቅተኛ ገቢ ላላቸውና ቤት ለሌላቸው አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ይህ መፀዳጃ ቤት አካባቢውን እንደገና ለማልማት በተደረገው ለውጥ በአሁኑ ሰዓት የጠፋ ሲሆን በአካባቢው ወይም በሌላ ቦታ መፀዳጃ ቤቱ ሳይተካ ቀርቷል፡፡ በከተማው የገበያ ማዕከላትና አካባቢዎች የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች በከፍተኛ እጥረት ይታያል፡፡ ለምሳሌ፣ ከፒያሳ እስከ ሜክሲኮ፣ ከሜክሲኮ እስከ መገናኛ እና ከሜክሲኮ ቦሌ ድረስ ባሉበት ቦታዎች አንድም የሕዝብ መፀዳጃ ቤት የለም፡፡ የሕዝብ መፀዳጃ ቤት እጥረት በመኖሩ ክፍት ቦታዎች፣ የቀብር ቦታዎች፣ በወንዞች ዳር እና በከተማ ጎዳናዎች ላይ ብክለትን ያስከትላል፡፡

ከከተማ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በተቃራኒ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ቁጥርና ጥራት ባለፉት ሀያ ዓመታት ውስጥ አሽቆልቁሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ያለው 60 የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ብቻ ሲሆኑ ይህም እየሆነ ያለው ቁጥራቸው ቀላል የማይባል መንገድ አዳሪዎች ባሉባት ከተማ ነው፡፡ በፊት ከነበረው ያነሰ ነው፡፡ ምክንያቱም በ1997 የነበረው 72 ሲሆን በ1984 ደግሞ 48 ነበርና በከተማው ውስጥ የሚገኙ 760 የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ከ3 ሚሊዮን በላይ ለሆነው ነዋሪ እንዲሁም በከተማው መንገዶች ላይ ከሚተረማመሰው የሰው ብዛት ጋር ሲነፃፀር ምንም የለም ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ መፀዳጃ ቤቶች ጠቃሚን የማይጋብዙት በተለይም ለሴቶችና አካል ጉዳተኞች የማይመቹ ስለሆኑ ነው፡፡

የሕዝብ መፀዳጃ ቤት እጥረትና ያለመሟላት የከተማዋ ውበት እና ጤንነት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርስ ሲሆን የራሳቸው መፀዳጃ ቤትና መታጠቢያ ቤት የሌላቸው በመሆኑ የሕዝብ ቦታን ለመጸዳጃ መጠቀማቸው የማይቀር ነው፡፡ ችግሩ የከፋ የሚሆነው ከፍተኛ መጨናቅ ባለባቸው ቦታዎች ማለትም መንገድ፣ አደባባይ፣ ገበያ ቦታዎች፣ የቤተ እምነት ቦታዎች ሲሆኑ ይህም አጣዳፊ መፍትሔዎችን ይጠይቃሉ፡፡

የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ዝቅተኛ መሆን ምክንያቶች ብዙ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል የሚመለከታቸው ተቋማት በየጊዜው መለዋወጥ እንደ ዋና ምክንያት ሊጠቀስ ይቻላል፡፡ ይህም ለህዝብ መጸዳጃ ተገቢ ትኩረት ስላልተሰጠው ሊሆን ይችላል፡፡ ባለፉት 20 ዓመታት የእነዚህ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች አስተዳደር በተከታታይ ይለዋወጥ ነበር፡፡ ከ1980ዎቹ በፊት

የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ይተዳደሩ የነበሩት በማዘጋጃ ቤት ነበር፡፡ በ1990ዎቹ መጨረሻ ላይ ደግሞ በጤና ቢሮ ይተዳደሩ ነበር፡፡ ከ2005 እስከ 2010 ድረስ የሚተዳደሩት በጽዳትና ውበት ኤጀንሲ ነበር፡፡ ከ2010 ጀምሮ በአዲስ አበባ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ፍሳሽ ባለስልጣን ስር የተደራጁ ሲሆን የሕብረት ሥራ ማህበራት ክፍያን መሠረት ያደረገ አገልግሎት ይሰጡበታል፡፡ ክፍያውም 0.25 እና 0.5 ሳንቲም በአንድ አገልግሎት ነው፡፡

በአዲስ አበባ የገበያና የንግድ ማዕከላት የሽንት ቤት አገልግሎት የላቸውም፡፡ የምግብና የመጠጥ ቤቶች ውስጥ በቂ መጸዳጃ አለመኖር በመንገድ ላይ መፀዳዳትን አበረታተዋል፡፡ እነዚህ በገበያ ማዕከሎችና መጠጥ ቤቶች የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች የከተማውን የጽዳት ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

### 4.3 የኢንዱስትሪ ፍሳሾች

የሀገሪቷ ኢንዱስትሪዎች የተሰባሰቡት በአዲስ አበባና ወንዞቿን ተከተሎ በመሆኑ በየቀኑ በቂ ማጣራት ያልተደረገላቸውና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎችን የያዙ ፍሳሾች ወደ ወንዞቹ ይቀላቀላሉ፡፡ እዚህ ላይ መረዳት ያለብን ጉዳይ እነዚህ ወንዞች ከከተማው ውስጥም ሆነ ውጭ በግልና በማህበር ለመስኖ ሥራ ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የኢንዱስትሪ ፍሳሾች ወደ ወንዙ ከመግባታቸው በፊት በተለየ ሁኔታ ተይዘውና እና ተጣርተው ሊለቀቁ ይገባል፡፡ የኢንዱስትሪ ፍሳሾች በአካባቢው ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት መለኪያ ሊዘጋጅላቸውም ይገባል፡፡ እየጨመረ የመጣውን የኢንዱስትሪ ብክለት ለመከላከል የህግ ተግባራዊነት፣ መደበኛ ቁጥጥር እና ክትትል እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማህበረሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ ዋና ዋና ሥራዎች ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ የኢንዱስትሪ ልማት በፕላን በአግባቡ የተመራ አልነበረም፡፡ ከ230 በላይ የተለያየ መጠንና ዓይነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች የሚገኙት የከተማው ዋና መኖሪያ አካባቢ ነው፡፡ 18 የቆዳ ፋብሪካዎች፣ 132 የብረትና አሉሚኒየም፣ 44 የምግብና የመጠጥ፣ 27 የኬሚካልና የትንባሆ እና 13 የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙበት ቦታ በአብዛኛው የወንዝ መስመርን ተከትሎ በመሆኑ ብክለቱን የሚያባብሰው ከመሆኑም በላይ አስፈላጊውን ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡

## 5. ግንዛቤና አፈፃፀም

በጽዳት ረገድ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረም ቢመጣ ብዙ እንደሚቀር የሚታይ ነው፡፡ «በእኔ አካባቢ እስካልተፈፀመ» የሚል

አስተሳሰብ ገና አልተቀረፈም፡፡ ይህንንም ለማሻሻል ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ግንዛቤ ከመፍጠር በተጨማሪም ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የአቅም እጥረት ይስተዋልበታል፡፡

ግንዛቤ የማስፋቱ ተግባር ከተፈላጊ ደንቦች ጋር መሄዱ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በተለይም በደረጃ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ከፍተኛ ውጤት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከተማዋ ብዙ አዋጆችና ደንቦች አሏት፡፡ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር አዋጅ (ቁጥር 513/2007)፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ (ቁጥር 13/2004)፣ ደንብ ቁጥር 31/2001፣ አዋጅ ቁጥር 68/1971 እና 1995 ለፍሳሽ ቆሻሻ፣ የፍሳሽ መስመርን ስለማያያዝ የ 2009 ደንብ እና ብክለትን አስመልክቶ ሲቪል ኮድ ላይ የተመለከቱትን አንቀፆች እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ደንብ ቁጥር 13/2004 እንደሚያመለክተው ቆሻሻን በህገወጥ መንገድ የመጣል ተግባር መቀጫው ከብር 5-7000 የሚደርስ ሲሆን መቀመጫውም ግለሰቦችና ተቋማት ያካትታል፡፡ ሆኖም ከ2007 በኋላ ሕጉን የማስፈፀም ሥራ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ስለቅጣቱ እና የሕግ አግባብና ቆሻሻን የመለየት ጥቅሙና ሕገወጥ የሆነ አሰራርን አስመልክቶ የተሟላ መረጃ የለውም፡፡

## 6. ለዘለቄታዊ ጽዳት

ቀጣይነት ያለው የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በአዲስ አበባ ለማስፈን ለደረቅም ሆነ የፍሳሽ ቆሻሻዎች የሚሠራበትን ልማዳዊ ዘዴን እንደገና መፈተሽ ይጠይቃል በዘለቄታ ያለው ጽዳት የሚመጣው ሥርዓት የተከተለ አስተሳሰብ በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በህዝብ ውስጥ ሲሰርጽ ነው፡፡ የአንድ ጊዜ ተግባርም አይደለም፡፡ ይህም ተከታታይነት፣ ወጥነት ዕውቀትን የሚጠይቅ እርምጃ መውሰድን ይጠይቃል፡፡ አዲስ አበባን አስመልክቶ ከዚህ በላይ ከተነሱት ነጥቦች አንፃር የሚከተሉት መፍትሄዎች ለዘለቄታ ጽዳት አካላት በሚል ቀርበዋል፡፡

## 7. ቆሻሻን እንደ ሀብት መቁጠር


ቆሻሻ የሀይል፣ የጥሬ ዕቃዎችና በመጨረሻም የገንዘብ ምንጭ ነው፡፡ በከተማው ለረጅም ጊዜ የቆየው ቆሻሻን እንደገና የመጠቀም ሥርዓትና ልምድ በተለይም የቆርቆሪያሌዎችን ሥራ ማድነቅና ጉልህ ቦታ ልንሰጠው ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅት ማናቸውንም ብረታ ብረቶች እንደገና ለመጠቀም ያለው ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ የግል ዘርፉ ይህ የእንደገና መልሶ የመጠቀም ሂደት እንደ አንድ መልካም የንግድ ዕድል ሊያየው ይችላል፡፡

ቆሻሻን በሚፈለገው ሁኔታ የማደራጀት ባህል በነዋሪዎች ደረጃ ሊሰርፅ የሚገባው ልምድ ነው፡፡ "ሁሉንም አትቀላቅል" የሚለው መርህ ቆሻሻን ለማደስና ብቃትን ለማምጣትና ቀጣይነት ያለው የጽዳት ግቦችን ለማሳካት ያስችላል፡፡ በዚህ ረገድ የኮንዶሚኒየም የመኖሪያ ቤቶች ቆሻሻን በየአይነቱ ለመለየትና በተለያዩ ማስቀመጫዎች ለማስቀመጥ ያስችላል፡፡ ደረቅ ቆሻሻን ማቅለዝ በአንዳንድ ሁኔታዎች አዋጪ መስሎ ባይታይም መታየት ያለበት ከትርፍ አንፃር ብቻ ሳይሆን ደረቅ ቆሻሻን በመቀነስ አካባቢን ከመጠበቅና የከተማ ፓርኮችን አረንጓዴ ከማድረግ አንፃር የሚሰጠው ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል፡፡

## 8. ውጤታማ የቆሻሻ አስተዳደር

ብቃት ያለው የጽዳት አገልግሎት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ ጉዳዮች ሲኖሩ እነሱም፣ ምንጩን ከመቆጣጠር እስከ ቆሻሻውን ከመሰብሰብና ከማስወገድ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የቆሻሻ አስተዳደር ትልቁ ወጪ ቆሻሻውን ወደ መጣያ ስፍራ ከማጓጓዝ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ የሚሰራው ለሁለቱም ማለትም ለደረቅ ቆሻሻና ለፍሳሽ ነው፡፡ የደረቅ ቆሻሻን በተመለከተ አገልግሎቱን ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የቅብብሎሽ ጣቢያዎችና ብቃት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት መኖር ወሳኞች ናቸው፡፡ የቅብብሎሽ ጣቢያው ቆሻሻውን የመካኒካል ጭመቃን በመጠቀም መልሶ መጠቀም መቀነስ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ይህ አሰራር ከ30-50 ሜትር ኪዩብ የመጫን አቅም ያላቸውን ትላልቅ መኪኖች ለመጠቀም ያስችላል፡፡ ይህም ሃሳብ በምስል 2 ተመልክቷል፡፡ የቅብብሎሽ ጣቢያው በአግባቡ የተከፋፈለና ከአካባቢው የመሬት አጠቃቀም ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡

ምስል 2፣ ብቃት ያለው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ሃሳብ (adapted from Poyry, 2007)



ውጤታማ የደረቅ ቆሻሻ ሂደት — አሁን ያለው የደረቅ ቆሻሻ ሂደት

## 9. ጤናማ የቆሻሻ አወጋገድና ፕላን ተኮር የገንዳ ቦታዎች

ላለፉት 50 ዓመታት አዲስ አበባ ቆሻሻን በክፍት ቦታ ላይ በመጣል የምትጠቀም ሲሆን ይኸውም ለአካባቢ ንጽህና ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ነው፡፡ የደረቅ ቆሻሻ መድፊያ ቦታ ለአዲስ አበባና በአካባቢዋ ላሉ ከተሞች በአስቸኳይ የሚያስፈልግ መሠረተ ልማት ነው፡፡ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ምርጫና ልማት ከግምት ውስጥ ከሚያስገባቸው ነጥቦች መካከል ከመሬት አጠቃቀሙ ጋር ተስማሚ ስለመሆኑ፣ የንፋስ አቅጣጫ፣ የአቪዬሽን ክልል ጂኦሎጂና ሃይድሮ ጂኦሎጂ ጉዳዮች፣ መጥፎ ሽታን የምንከላከልበት ሁኔታ፣ በስፋት በመስራት ሊገኝ ስለሚችለው ጥቅም እና በማዘጋጃ ቤቶች መካከል ስለሚኖረው ትብብርና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የቆሻሻ መጣያ ቦታ በአግባቡ መዘጋት ይገባዋል፡፡ ሲዘጋም የአካባቢ ጥበቃና በአካባቢው ያሉ ቦታዎችን ደህንነት በመጠበቅ ሊሠራ ይገባዋል፡፡

የቆሻሻ መሰብሰቢያ ገንዳ የሚቀመጥበት ቦታ በአብዛኛው ከመኖሪያ ጋር የተጣጣመ ስለሆነ አስቸኳይ መፍትሔ ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ጉዳይ የከተማ ፕላን መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል እንጂ እንደ ቀላል የአስተደደር ውሳኔ ሊታይ አይገባውም፡፡

በአግባቡ የተዘጋጁና የተሰሩ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ዕቅዶች በአስቸኳይ የሚያስፈልጉ ሲሆን የፍሳሽ መስመርም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## 10. ምንጩን የመቆጣጠር ስትራቴጂዎችና የተቀናጀ ጥረት

የከተማው የጽዳት ዘርፍ ቀጣይነት ባለው ስትራቴጂ ላይ በመመስረት፣ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና ቀጣይነት ያላቸውን ግቦችን በማስቀመጥ ሊመራ ይገባል፡፡ ይህም ሊከናወን የሚችለው ምሉእነት ያለው የቆሻሻ ዓይነቶች ጥናት ውጤትን መሠረት ሲያደርግ ነው፡፡ የአዲስ አበባን ጽዳት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚከተሉት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ነጥቦች ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡

- ቆሻሻን ለማቅለዝ የሚያስችል ቅስቀሳና የገበያ ትስስር መፍጠር፣
- ባዮጋዝን ለመጠቀም የሚያስችል ቅስቀሳና ትግበራ፣
- ቆሻሻዎችን መለየትና ለቤተሰብ ግንዛቤ መስጠትና መቀስቀስ፣
- ጥቅጥቅ ባለሁኔታ በማደግ ላይ ያሉ አካባቢዎች ላይ የፍሳሽ አገልግሎትን ማስፋፋት፣ እና
- አሁን ያለውን ብረትን ሌሎች ኦርጋኒክ ያልሆኑ ቆሻሻዎችን እንደገና የመጠቀም ልምድ ላይ ማስፋፋት፣

የከተማዋ የጽዳት ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖረው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማንሳሳትና ማነቃቃት ተገቢ ነው፡፡ ከላይ የተመለከቱት ምንጭን የመቆጣጠር ስትራቴጂዎች የቆሻሻ አምራች የሆኑትን ማለትም የነዋሪዎች፣ የንግድ ተቋማት፣ ኢንዱስትሪዎችና የሌሎችንም አካላት ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ ትክክለኛ/ተጨባጭ የሆነ ተሳትፎና ቁርጠኝነት በተገቢው ቦታ እንዲገኙ ለማድረግ ተግባር ተኮር የሆነ ግንዛቤን የማስፋት ሥራዎችንና የማነቃቂያ ስልቶችን ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 11. ማጠቃለያ

አዲስ አበባ ወደ ጐንና ወደ ላይ በፍጥነት በማደግ ላይ ትገኛለች፡፡ በከተማዋ የውስጠኛው ክፍል የሚካሄዱት ትላልቅና የመልሶ ማልማት ሥራዎች በከተማዋ ቅርጽ ላይ ትልቅ ዘላቂ ለውጥ ያመጣሉ፡፡ የከተማ ሽቅብ ዕድገት የከተማውን ነዋሪ ቁጥር ከመጨመሩም በላይ የአኗኗር ዘዴውን ይቀይራል/ይለውጣል፡፡ ይህ ለውጥ ቀድሞ ታስቦ የሚሰራ የመሠረተ ልማትን በመጠየቅ ልማቱን ፍሬያማና የነዋሪዎቿን ሕይወት ጤናማ ያደርጋል፡፡

የፍሳሽ መሠረተ ልማትን ወደ ውስጠኛው የከተማ ክፍልና በተስፋፉት የከተማው አካባቢዎች ጋ የማድረስ የዘገየ እንቅስቃሴ ስለሆነ አስቸኳይ መፍትሄ ይጠይቃል፡፡ ይህን መፍትሄ መሠረት ማድረግ የሚገባው የከተማ ፕላን መስፈርቶችንና በቀጣይ የልማት መርሆዎች ላይ ነው፡፡ ማናቸውም የጽዳት መሠረተ ልማት ምርጫ የምሕንድስና ወይም የአስተዳደር ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ዋናው ቁምነገር ይህ የሥራ የፕላን ጉዳይ ሆኖ የከተማ ፕላን ባለሙያዎችን እንዲሁም የሳኒተሪ ባለሙያዎችን በማሳተፍ ሊሠራ ይገባዋል፡፡ ስለዚህ የተሻሻሉና የሁሉንም ዕይታ ያካተቱ የጽዳት መፍትሄዎች አሁን ከሚከለሰው የከተማው የስትራክቸር ዕቅድ ጋር ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ከተማዋ ሁሉን አቀፍ የሆነ የደረቅ ቆሻሻ ዓይነት ጥናትን መሰረት ያደረገ ብቃት ያለው የደረቅ ቆሻሻ ሥራ አመራር ንድፍ ማዘጋጀት ይኖርባታል፡፡ በአዲስ አበባና በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ ዓይነት ጥናት የሌላቸው መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የከተማው አስተዳደር በጥብቅ ሊይዛቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ሲሆን ይህም የዜጎችን ደህንነት ከመከላከልና ስነምሕዳሩን ሊቀለበስ ከማይቻል ብክለት ለመከላከል በማሰብ ነው፡፡ ዘላቂ የሆነ የሕክምና፣ የኢንዱስትሪና የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን በአግባቡ ለማስተዳደርና ለማስወገድ በሀገር አቀፍና በከተማ ደረጃ የሚያገለግሉ ስልቶች መዘጋጀት አለባቸው፡፡

አዲስ አበባ ንፁህና ጤናማ የከተማ ገፅታ ሊኖራት ይገባል፣ ለዚህም የተቀናጀና በደንብ ዲዛይን የተደረገ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶችን መስራት ወሳኝ ሲሆን እነዚህም ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በንግድ ማዕከላትና በቡና ቤቶች የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች "ክፊል የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች" ሆነው ለሁሉም አገልግሎት የሚሰጡበትን አሰራር ተፈጻሚ ማድረግ ለከተማ ውበትና ንፁህነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

በከተማ ጽዳት ረገድ ያለው ግንዛቤ በማህበረሰቡም ሆነ በባለሙያዎችና በውሳኔ ሰጪዎች አነስተኛ ነው፡፡ ግንዛቤ የማስጨበጡ ጥረት ካልተደገፈና በሕግ የበላይነት በተለይም በዋና በካዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ካልተሰራ የከተማዋ የጽዳት ቀጣይነቱ አይረጋገጥም፡፡

ዘላቂ (ቀጣይነት ያለው) ጽዳት የማህበረሰቡ፣ የግል ዘርፉ እና የመንግስት አካላት የስነ ዜጋ አመለካከት ውጤት ነው፡፡ ይህ የአንድ ጊዜ ድርጊት ሳይሆን ተከታታይና መላ ዕውቀትን፣ ጉልበትንና ሃይልን ለጉዳዩ ማዋልን ይጠይቃል፡፡ ይህም ዕቅድን መሰረት ያደረገ ቀጣይነት ያለው ድርጊት ማለትም ቆሻሻን እንደሀብት መቁጠር፣ የምንጩን የመቆጣጠር ስትራቴጂዎች፣ በቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ላይ ብቃትን በማምጣትና በደንብ የታቀደ የጽዳት መሠረተ ልማት በመገንባት የከተማውን ላይ ያለውን ልማት ማገዝ ይቻላል።

## 12. ዋቢ መጻሕፍት

AAAR (1997). Five year program of the Region 14 Administration (1997-2001). Addis Ababa.

Abdi Y., Bede B. and Wondimu A.(1990). Study of Addis Ababa Rivers: the case of Kurtume River. College of Urban Planning, Addis Ababa.

AAWSA (2010). Five year road map plan for Addis Ababa wastewater collection and disposal. Addis Ababa, Megabit 2003 EC.

AAWSA ( 2012). AAWSA: Abrief Profile. Addis Ababa Wtare supply and sewerage Authority.

Addis Ababa Solid Waste Recycling and Disposal Project Office, 2012. Annual Report 2004 EC.

BECEOM (1982). Flood protection and storm sewer system of Addis Ababa. Volume I-General Report, Addis Ababa.

Berlan E. (1963). Addis Abéba: la plus haute ville d'Afrique. Impremerie Allier, Grenoble.

CSO (1995). The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia: results for Addis Ababa. Volume I-Statistical Report, Addis Ababa.

CSA (2012), Ethiopian Welfare Monitoring Survey, Addis Ababa, 2012.

EHD (1997). A comprehensive overview on the Addis Ababa Municipality solid waste management and its environmental inspection services. Addis Ababa: Region 14 Health Bureau - Environmental Health Department, August 1997, 133p.

Health Bureau (1996). Annual report of health bureau. Addis Ababa, 1996.

IGNIS (2010). Waste Data Collection, Task Report , 2008-2010.

Manhart A, Tadesse A and Mehari Be (2013). E-waste Country Study Ethiopia. Öko and PAN, January 2013.

Poyry ( 2007). Complementary study: Addis Ababa Solid Waste Management Project. Poyry, 2007.

Techeste A. (1986). Basic planning principles and objectives taken in the preparation of the Addis Ababa Master Plan, past and present. In Proceedings of the International Symposium on the Centenary of Addis Ababa. Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa.

Wondimu A. & Alfakih E. (2001). Approach for sustainable urban storm water management in the context of developing countries. Proceeding of 4th International Conference on new technologies in storm drainage, NOVATEC, June 25-27, 2001, Lyon, France, p. 137-142.

WHO/UNICEF (2013), Progress on Sanitation and Drinking Water 2013 updates.

Wondimu A. & Alfakih E. (1998). Urban Drainage in Addis Ababa: existing situation and improvement ideas. In: Development in Urban drainage Modelling, Fourth International conference, London, pp. 823-830.

Wondimu A. (2000). La gestion durable des eaux pluviales urbaines par la gestion de l'espace et la subsidiarité: le cas d'Addis Abéba (Ethiopie). PhD thesis. INSA de LYON, 2000, 394p.

Wondimu (2012). Sustainable Urban Mobility Planning for coping challenges of Urban Transportation in the fast Urbanizing Ethiopia, the case of Addis Ababa, Paper under preparation for CODATU XV, October 2012.

ZTS (2012). Social Impact Assessment of Koshe Dump Site Closure and Reclamation Project, Addis Ababa, February, 2012.

# የጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ በአዲስ አበባ

*ጌትነት ምትኬ*

## 1. መግቢያ

የዚህ ፅሁፍ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ የጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ ሁኔታን አስመልክቶ የገለልተኛ ባለሙያ ዕይታን፣ በጽሑፉ ገምጋሚ የተሰጠውን አስተያየት እንዲሁም ነሐሴ 2 ቀን 2013 አዲስ አበባ በሚገኘው በጊዮን ሆቴል በተካሄደው ሕዝባዊ ውይይት ላይ የሚመለከታቸው አካላት የሰጡትን ግብዓቶች በማቀነባበር ለማቅረብ ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ ሕዝባዊ ውይይቶችን ለማበረታታትና በውይይቶቹ የተገኙ ውጤቶችንም በማስታወሻ መልክ ለማስቀመጥ በማሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡

ጥናቱ ዋና ዶክመንቶችን/ መረጃዎችን ማለትም የሥነ-ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናቶች፣ የጤና ዘርፍ የልማት ፕሮግራም፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ሪፖርቶችን፣ አዋጆችንና መመሪያዎችን ግምገማ አድርጓል፡፡

በዚህ ፅሁፍ የቀረቡትን ጉዳዮች ፍሰት ለመጠበቅና ተገቢውን ግንዛቤ ለማስፋት በማሰብ በእያንዳንዱ ርዕስ ስር አብዛኛው ውጤቶች እንዲብራሩ ተደርጓል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድ የሚገባው ይህ ፅሁፍ በማናቸውም ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ለመገምገም ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ ጥናቱ/ ሪፖርቱ በጤና አገልግሎት አቅራቢዎችና በተጠቃሚዎች የሚነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን ሸፍኗል፡፡ የጥናቱን ሚዛናዊነት ለመጠበቅ እንዲቻል በተጠቃሚዎች የሚነሱ ጉዳዮችን ለመመርመር በጤናው ቢሮ እንዲሁም በብሔራዊ ደረጃ የሚገኙ ሌሎች መረጃዎችና የዳሰሳ ጥናቶች እንዲመረመሩ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሪፖርት የጊዜውን ትክክለኛነት ለማስጠበቅ እንዲቻል አብዛኞቹ ከጤና ቢሮ የተገኙ መረጃዎች ቀኖች በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መሠረት የቀረቡ ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ ያለውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ከመመልከታችን በፊት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ያወጣውን የጤና ፖሊሲ እና ዋና ዋና አቅጣጫዎችን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የጤናው ፖሊሲ የሚከተሉትን አጠቃላይ አቅጣጫዎችን አካቷል[1]፡፡

[1]Health Policy of the Transitional Government of Ethiopia, 1993

- የጤና አገልግሎት ሥርዓቱን ዲሞክራሲያዊና ከማዕከላዊነት የተላቀቀ ማድረግ፣
- በጤና እንክብካቤ የማሻሻያና መከላከል ዘዴዎችን ማጎልበት፣
- ፍትሃዊና ተቀባይነት ያለው የጤና አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋትና ማስፋፋት፣
- በዘርፎች መካከል ያለውን የጋራ እንቅስቃሴ መደገፍና ማጠናከር፣
- በጤናው ዕድገት ውስጥ በአገር ደረጃ የራስን አቅም ማጎልበትና የውስጥና የውጭ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚረዱ ተስማሚ አመለካከቶችንና ድርጊቶችን ማስፋፋት፣
- የጤና እንክብካቤውን ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል እንደሚጠቀምበት ማረጋገጥ፣
- ከጎረቤት አገሮች እንዲሁም ከአህጉራዊና ከአለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ለጤና ዕድገት አስተዋጽኦ በሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ መተባበር፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣ ለጤና ጠንቅ የሚሆኑ ነገሮችን አብሮ መቆጣጠር፣
- በተጠኑ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት ተገቢ አቅምንና ብቃትን ማነፅና ማጎልበት፣
- አቅም ያላቸውን እንደችሎታቸው በማስከፈልና አቅም የሌላቸውን ደግሞ እገዛ በማድረግ ለማከም የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ለሕብረተሰቡ የጤና አገልግሎት መስጠት፣
- በጤናው እንክብካቤ የግሉን ዘርፍና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ተሳትፎ ማስፋፋት፡፡

በተጨማሪ የጤናው ፖሊሲ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣

1. የመረጃ፣ የትምህርትና የመገናኛ መርሐ-ግብሮች ይበልጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው የጤና እንቅስቃሴዎች መካከል ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎች፣ ከምግብ ማነስና ከዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ በሽታዎች፣ የሠራተኞችን ጤንነትና ደህንነት፣ የአካባቢ ደህንነት፣ የጤና መሠረተልማትን መልሶ ስለማቋቋም እና ተስማሚ የጤና አገልግሎት አመራር ስርዓት መቅረጽ፣
2. ፈዋሽና የማገገም አገልግሎቶች የአዕምሮ ጤንነትን ጨምሮ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣
3. ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ላተኮረ ተግባራዊ ምርምር ከፍተኛ ድጋፍ መስጠት፣
4. የአስፈላጊ መድኃኒቶች፣ የሕክምና ግብዓቶች፣ መሳሪያዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትን ማጠናከር፣

5. በጤና መስክ በቂና አግባብ ያለው የሰው ኃይልን ለማፍራት በግምባር ቀደምና በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠኑ በተለይም በሕብረተሰቡ ፍላጎት ያተኮሩና ለተግባር የተዘጋጁ የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን፣
6. ለሚከተሉት የሕብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ለቤተሰብ በተለይ ለሴቶችና ህፃናት፣ በግንባር ቀደምነት በማምረት ተግባር ላይ ለሚሳተፉ፣ እስከዛሬ ድረስ ተረስተው ለቆዩት ክልሎችና የህብረተሰብ ክፍሎች (አብዛኛው የገጠሩ ሕዝብ፣ ለከብት አርቢዎች፣ ለደሃ ከተሜዎችና አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሔረሰቦች)፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ለተጠቁ ልዩ ትኩረት መስጠት፣
7. የባህል መድሃኒቶችን ጠቃሚ ጎን ለማጎልበት ተገቢውን ትኩረት መስጠት፡፡

የሽግግር መንግስቱ የጤና ፖሊሲ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ የጤና ተግባራት እንደመሠረት አገልግሏል፡፡ በሌላ በኩል ፖሊሲው ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ ሁለት አሰርት ዓመታት ያሳለፈ በመሆኑ በተከታታይ ባሉት ዓመታት የተከሰቱ አዳዲስ ጉዳዮችን ለማካተት የሚያስችል ደጋፊ ወይም አጋዥ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መቅረፅን ይጠይቋል፡፡ ለምሳሌ፣ የኤችአይቪ/ ኤይድስ ፖሊሲ የወጣው በኋላ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ የሚታዩትን ፈጣን ለውጦች፣ የግንኙነት ውስብስብነት እና የልማት እንቅስቃሴዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት በጤናው ፖሊሲ ላይ በቂ ትኩረት ያልተሰጣቸውን ማለትም በከተማ ውስጥ የሚታየው አኗኗር መቀየርና የከተሜነት ባህሪይ ከበሽታዎች ስርጭት ሽግግር (የማይተላለፉ ከሚተላለፉ በሽታዎች አንፃር) አኳያ ልዩ ትኩረትና ስትራቴጂዎችን ይጠይቃሉ፡፡ በተጨማሪም በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የጤና ስጋቶች በቀላሉ ለአደጋ የሚያጋልጡ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ስለሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት በጤናው ፖሊሲ ላይ የተመለከተ ቢሆንም በአካባቢና በሠራተኞች ጤንነት ላይ ያሉ አስጊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡

## 2. የጤና አሰጣጥ መዋቅሮች በአዲስ አበባ

*ሥነ-ሕዝብ፡-*በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ግምት መሠረት በ2008 (Census, 2007) የተሻሻለው የአዲስ አበባ ሕዝብ ጠቅላላ ብዛት 3,384,569 ነው፡፡ በ2003 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ሕዝብ ግምት ደግሞ 2,975,608 ሲሆን ስብጥሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡- የተመረጡ የአመላካቾች ከመቶ ሲሰላ

| | |
|---|---|
| የፆታ ስብጥር | 0.91 |
| ከአንድ ዓመት በታች | 2.2% |
| ከ5 ዓመት በታች | 7.2% |
| ሴቶች (15-49) | 34.6% |
| የጥገኝነት መጠን | 37.6% |
| ዓመታዊ የዕድገት መጠን | 2.1% |

ምንጭ፡- CSA, Census, 2007

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ከሁለት አስርተ ዓመታት በፊት በ1985ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን[2] ቢሮው እንደገና በአዲስ መልክ የተደራጀው ከ10ዓመታት በኋላ በ1995 ዓ.ም ነበር። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሥር ከሚገኙት የሥራ ዘርፎች መካከል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ አንዱ ነው። በከተማው አስተዳደር ሥር አስር ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ሲሆን እያንዳንዳቸውም የጤና ጽ/ቤት አላቸው። በእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ሥር ደግሞ ወረዳዎች የተደራጁ ሲሆን እያንዳንዱ ወረዳም የጤና ጽ/ቤት አለው። ወረዳው ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከን የያዙ ቀበሌዎችን ይጨምራል። የቀበሌው አደረጃጀት የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ይጨምራል። የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በቤተሰብ ደረጃ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

## 3. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት

በአዲስ አበባ 11 የመንግሥት ሆስፒታሎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ስድስቱ በአዲስ አበባ ከተማ የጤና ቢሮ ሥር የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ሆስፒታሎቹም፣ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል፣ የካቲት 12 ሆስፒታል፣ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል፣ እና ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል። ይህ ሆስፒታል በቅርብ ጊዜ የተቋቋመ ነው፡፡

በተጨማሪም ከ10 የሚበልጡ የግል፣ ሌሎች መንግስታዊ የሆኑ (የፖሊስ ሆስፒታል እና የጦር ሠራዊት ሆስፒታል) እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (ደጃዝማች ባልቻ ሆስፒታል) ሆስፒታሎች ይገኛሉ፡፡ ከአስራ አንዱ ሆስፒታሎች ውስጥ አምስቱ በፌደራል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ሆኖም ሆስፒታሎቹ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችና

[2] Mohammed H. Addis Ababa City Administration Health Bureau, 2008

ከሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች በሪፈራል ለሚመጡት ሕመምተኞች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል አንዱ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ፅሁፍ የሚሸፍነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ሥር ያሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትና ሥራቸውን ነው፡፡

በጤና ቢሮው ሪፖርት መሠረት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚተገበረው የሆስፒታሎች የሪፎርም ሥራዎች መካከል በአዲስ አበባ የሆስፒታል አገልግሎቶችን ለማሻሻል ከተወሰዱ እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ምንም እንኳን አዳዲስ ሆስፒታሎች በከተማው ውስጥ በግንባታ ላይ ባይኖሩም፣ የሦስት ሆስፒታሎች የማስፋፊያ ሥራ የተካሄደ ሲሆን፣ በእነዚህም ሆስፒታሎች አዳዲስ ህንፃዎችና ተጨማሪ የመኝታና የመመርመሪያ ክፍሎች ግንባታ ተካሂዷል፡፡
- አዳዲስ የህክምና መሳሪያዎች ተገዝተዋል፡፡ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ መሳሪያዎችም ጥገና ተካሂዷል፡፡
- የክትትልና የቁጥጥር ተግባራት እንዲሁም የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት ተከናውኗል፡፡
- ለሠራተኞች ስልጠና የመሰጠት ዕድሎች/አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

ሠንጠረዥ1 የጤና ማዕከላትን ስርጭት በክፍለ ከተማ ደረጃ ያሳያል፡፡ ይህ ሠንጠረዥ የእያንዳንዱን ክፍለ ከተማ የሥራ አፈፃፀም ማለትም አዳዲስ የተገነቡ የጤና ማዕከላትን፣ ያለቁትንና ሥራ የጀመሩትን ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው ጥቂት ክፍለ ከተሞች ማለትም ልደታ፣ አዲስ ከተማ፣ አቃቂና የካ ከተገነቡት አዳዲስ የጤና ማዕከላት ጥቂቶቹ ብቻ በሥራ ላይ የሚገኙባቸው ክፍለ ከተሞች ናቸው፡፡ በተካሄደው የፓናል ውይይት ይህ ሁኔታ ሊከሰት ከቻለባቸው ምክንያቶች መካከል የጤና ባለሙያዎች እጥረት እና የመብራት ኃይል አቅርቦት አለመኖር በዋናነት ተጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም ሠንጠረዡ በርከት ያሉ አዳዲስ የጤና ማዕከላት መገንባታቸውን የሚያመለክት ሲሆን ይህንንም ለመረዳት የቀድሞው የጤና ማዕከላት አስተዋፅኦ ከጠቅላላው የጤና ማዕከላት ማለትም የቀድሞው፣ አዲስ የተሰሩና በመሰራት ላይ የሚገኙትን ጨምሮ 24.8 ፐርሰንት (26/105) ድርሻ ብቻ መያዙን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 2: የቀድሞውና አዲስ የጤና ማዕከላት ስርጭትበክፍለ ከተማ (2005ዓ.ም.)

| ክፍለ ከተማ | የቀድሞ | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | ድምር | የተጠናቀቁ | ያልተጠናቀቁ | አገልግሎት መሥጠት የጀመሩ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ የተሰሩ | | | | | | | |
| ጉለሌ | 2 | 1 | 4 | | | 8 | 8 | 0 | 7 |
| ቦሌ | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 9 | 6 | 3 | 6 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 2 | 4 | 3 | 1 | | 8 | 6 | 2 | 4 |
| አራዳ | 3 | 1 | 2 | 4 | | 7 | 4 | 3 | 4 |
| ልደታ | 4 | 1 | 0 | 4 | | 5 | 2 | 3 | 0 |
| ቂርቆስ | 3 | 1 | 4 | 0 | | 5 | 4 | 1 | 4 |
| አዲስ ከተማ | 2 | 2 | 2 | 4 | | 8 | 5 | 3 | 2 |
| አቃቂ ቃሊቲ | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 7 | 3 | 4 | 2 |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 2 | 7 | | 1 | | 8 | 6 | 2 | 4 |
| የካ | 3 | 6 | 2 | 5 | 1 | 14 | 7 | 7 | 3 |
| ድምር | 26 | 28 | 22 | 26 | 3 | 79 | 51 | 28 | 36 |

ምንጭ፡- Addis Ababa City Administration Health Bureau Report, April 2005 (9 Months)

ሆስፒታሎችን በማሳደግ/በማስፋፋት እና የጤና ማዕከላትን ቁጥር በመጨመር የጤና መሠረተ ልማት በከፍተኛ ደረጃ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ሆኖም በርካታ ቁጥር ያላቸው የጤና ማዕከላት በተለያዩ ምክንያቶች ለከተማው ነዋሪ አገልግሎት አይሰጡም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ከአገልግሎቶቹ መስፋፋት ጋር በተያያዘ ጥሩ የሆነና ተገቢነት ያለው ዕቅድ ማለትም የሰው ኃይል፣ በጀትና ሌሎች አገልግሎቶችን ለምሳሌ፣ የመብራት ኃይል ማዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡ የጤና ቢሮው የሥልጠና ተቋማትን መክፈቱ የሰው ኃይል ፍላጎቱን ለማሟላት የሚረዳው በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል፡፡ ሆኖም የሥልጠናውን ጥራትና የሠልጣኞች የብቃት ሁኔታ በአግባቡ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

## 4. የጤና ባለሙያዎች ብዛትና ዓይነት

በሠንጠረዥ 2 የጤና ባለሙያዎች ብዛት፣ ስብጥርና ስርጭት ከአዲስ አበባ ሕዝብ አንፃር ተመልክቷል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው ጠቅላላ የጤና ባሙያዎች ቁጥር 7520 ነው፡፡ ይህ አሃዝ በ2003 ዓ.ም. የነበሩትን የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን (1375) አይጨምርም፡፡ የዶክተሮች (የሕክምና ዶክተርና ስፔሺያሊስቶችን ጨምሮ) ብዛት ከጠቅላላው የከተማ ነዋሪ ጋር ሲጣመር 1፡17,607 ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በአዲስ አበባ ከተማ የአዋላጅ ነርሶችን ጨምሮ ወሳኝ የሆኑ የጤና ሠራተኞች እጥረት እንዳለ ነው፡፡ ሆኖም ከላይ በሪፖርቱ የተመለከተው አሃዝ በግል ክሊኒኮች የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎችን ይጨምር ወይ አይጨምር የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ሪፖርት ባይካተትም ከፍተኛ የሆነ የጤና ባለሙያዎች ፍልሰት (ከሥራ መልቀቅ) እንዳለ ከውይይቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 3: የጤና ባለሙያዎች ስርጭትና የጤና ባለሙያ-ሕዝብ ጥመርታ በአዲስ አበባ

| የባለሙያ ዓይነት | ብዛት | የጤና ባለሙያ-ሕዝብ ጥመርታ |
|---|---|---|
| የሕክምና ዶክተሮችና ስፔሺያሊስቶች | 169 | 1:17,607 |
| የጤና መኰንን | 259 | 1:11,489 |
| ፋርማሲስት (ዲፕሎማና ዲግሪ) | 284 | - |
| ነርስ (ቢኤስሲ ዲግሪ) | 981 | - |
| ክሊኒካል ነርስ | 1988 | - |
| አዋላጅ ነርሶች | 160 | 1:18,598 |
| ሁሉም ነርሶች | 3159 | 1:942 |
| ላቦራቶሪ (ዲፕሎማና ዲግሪ) | 274 | - |
| ራዲዮግራፈር | 23 | - |
| የራጅ ቴክኒሺያን | 15 | - |
| የአካባቢ ጤና ባለሙያ (ዲፕሎማና ዲግሪ) | 208 | - |
| ድምር | 7520 | - |

ምንጭ፡- Ministry of Health, Health and Health Related Indicators, 2003 E.C.

## 5. የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች

የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የሞዴል ቤተሰቦች እና የአንድ ለአምስት መሪዎች ሥልጠና አፈፃፀም ከዕቅድ አንፃር በሠንጠረዥ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው ክፍል ላይ እንደተመለከተው በ2003 ዓ.ም. በከተማው ውስጥ ጠቅላላ የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ብዛት 1375 ነው፡፡ የማህበረሰብ የጤና አገልግሎቶች የሚከናወኑት በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ነው፡፡ የከተማው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከማህበረሰቡ መዋቅሮች ማለትም በቅርቡ የጤና ልማት ሠራዊትን ለመመስረት ታስቦ በተደራጀው መዋቅር አማካኝነት በቀበሌ ደረጃ ለሞዴል ቤተሰቦች እና አንድ ለአምስት መሪዎች ሥልጠና በመስጠት በቅርበት ይሰራሉ፡፡

ሠንጠረዥ 4: የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ አፈፃፀም እና የአንድ ለአምስት መሪዎች በሰለጠኑና በተመረቁ ቤተሰቦች ብዛት

| ክፍለ ከተማ | በአንድ ለአምስት አደረጃጀት በስልጠና ላይ ያሉ ቤተሰቦች ብዛት | | በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ስልጠና የወሰዱና የተመረቁ ቤተሰቦች ብዛት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቅድ | አፈጻጸም | ዕቅድ | አፈጻጸም | % | |
| አራዳ | 12480 | 4788 | 12480 | - | - | |
| ጉለሌ | 11674 | 11674 | 6194 | 5363 | 87 | |
| አዲስ ከተማ | 34585 | 9261 | 34585 | - | - | በስልጠና ላይ |
| ልደታ | 500 | 254 | 250 | 20 | 8 | |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 15363 | 10400 | 15363 | 1613 | 10 | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 29000 | 17270 | 29000 | 19703 | 67 | |
| አቃቂ ቃሊቲ | 1128 | 825 | 1822 | 900 | 49 | |
| ቦሌ | 11928 | 5448 | 11928 | - | - | በስልጠና ላይ |
| ቂርቆስ | 10571 | 1342 | 10571 | 0 | 0 | |
| የካ | 24887 | 17942 | 9700 | 1575 | 16.7 | |
| ድምር | 152117 | 79204 | 168043 | 27599 | 39 | |

ምንጭ፡- Addis Ababa City Administration Health Bureau Report, April 2005 (9 Months)

በሠንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የሞዴል ቤተሰቦችና አንድ ለአምስት መሪዎች ኔትዎርክ/መረብ አጠቃላይ አፈፃፀም የሚያሳየው እንደቅደም ተከተሉ 88 እና 89 ፐርሰንት ነው፡፡ ከአራዳና ከልደታ ክፍለ ከተሞች በስተቀር ሌሎቹ ክፍለ ከተሞች የሞዴል ቤተሰቦችና የአንድ ለአምስት መሪዎች ኔትዎርክ/መረብ አፈፃፀም ከዕቅዱ ከሦስት አራተኛው በላይ መፈፀሙን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ የዕቅድ አፈፃፀም ትንተና በምንም ዓይነት መልኩ የክፍለ ከተሞቹን ሙሉ የአፈፃፀም ታሪክ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም ዝቅተኛ አፈፃፀም የታየባቸው ክፍለ ከተሞች ችግር ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

ሠንጠረዥ 5: የሞዴል ቤተሰቦችና የአንድ ለአምስት መሪዎች ኔትዎርክ/ መረብ ስርጭት በክፍለ ከተማ

| ክፍለ ከተማ | የተመረቁ ሞዴል ቤተሰቦች ብዛት 2005 /የ9 ወራቶች ሪፖርት/ | | | የአንድ ለአምስት መሪዎች ኔትዎርክ/ መረብ ብዛት 2005 /የ9 ወራቶች ሪፖርት/ | | | አንድ ለአምስት የተደራጁ ቤተሰቦች ብዛት 2005 /የ9 ወራቶች ሪፖርት/ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቅድ | አፈጻጸም | % | ዕቅድ | አፈጻጸም | % | ዕቅድ | አፈጻጸም | % |
| አራዳ | 3787 | 799 | 21 | 408 | 146 | 36 | 1632 | 584 | 36 |
| ጉለሌ | 16194 | 15251 | 94 | 10524 | 10524 | 100 | 52619 | 52619 | 100 |
| አዲስ ከተማ | 6120 | 2818 | 46 | 6917 | 5140 | 74 | 27668 | 21015 | 76 |
| ልደታ | 2300 | 1561 | 68 | 56 | 10 | 6.5 | 780 | 50 | 6.5 |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 10920 | 1359 | 12 | 18300 | 16995 | 93 | 91500 | 81925 | 89.5 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 10080 | - | - | 1335 | 1281 | 95 | 6675 | 5883 | 88 |
| አቃቂ ቃሊቲ | 5400 | 2199 | 41 | 8511 | 7378 | 87 | 35746 | 30987 | 86 |
| ቦሌ | 8280 | 6366 | 77 | 13273 | 10201 | 76.3 | 53032 | 40884 | 77 |
| ቂርቆስ | 5040 | 1047 | 20.7 | 8450 | 7848 | 100 | 8450 | 7847 | 100 |
| የካ | 9660 | 7567 | 78.33 | 1636 | 1425 | 87.1 | 6913 | 5625 | 81.9 |
| ድምር | 77781 | 38967 | 50 | 69410 | 60948 | 87.8 | 242356 | 216432 | 89 |

ምንጭ፡-Addis Ababa City Administration Health Bureau Report, April 2005 (9 Months)

በሪፖርቶቹ እንደተገለፀው ጤና ቢሮው የማህበረሰብ የጤና አገልግሎቱን በማስፋፋት ረገድ ማለትም የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን መርጦና አሰልጥኖ በመመደብና ለሞዴል ቤተሰቦችና አንድ ለአምስት መሪዎች ሥልጠና በመስጠት ትልቅ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ሆኖም በዚህ ረገድ አንዳንድ ቀበሌዎች የሚፈለገውን ያህል ምላሽ አልሰጡም፡፡ ይህም በነዋሪዎቹና በወረዳው የጤና ጽ/ቤት መካከል ሊፈፀም በሚገባው ጉዳይ ላይ ልዩነት ያለ በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ከነዋሪዎቹ ጋር መወያየትና የእያንዳንዱን ቀበሌ ነባራዊ ሁኔታዎች በማጤን የፍላጎቶቹን ዓይነት መፈተሽ ተገቢ ይሆናል፡፡ የሶሺዮኢኮኖሚ ሁኔታ/ደረጃ እና የጤና ፍላጎት ስርጭት ለሁሉም ቀበሌዎች ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል፡፡ የእያንዳንዱን ቀበሌ የነዋሪዎች ፍላጎት መለየት የማህበረሰብ የጤና መዋቅሮችን ትስስር እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች ሲለቁ የሚተኩበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

ሠንጠረዥ 5 የአዲስ አበባ ከተማ የጤና ቢሮ በእናቶችና ሕፃናት ጤና አገልግሎት ረገድ ያሳየውን የሥራ አፈፃፀም ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የቤተሰብ ምጣኔ አፈጻጸም ከ50 ፐርሰንት በታች ቢሆንም በሌሎች የእናቶችና ህጻናት ጤና አገልግሎት የማዋለድ አገልግሎትን ጨምሮ ከ87 ፐርሰንት በላይ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 6: ዋና ዋና በሆኑ የእናቶችና ሕፃናት ጤና ሥራዎች የ8 ወራት አፈፃፀም፣ 2005ዓ.ም

| የአገልግሎት ዓይነት | ዕቅድ (8 ወራቶች) | አፈጻጸም | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| ቅድመ ወሊድ ክብካቤ | 49565 | 57272 | 115.3 |
| ኤችአይቪ የተመረመሩ እርጉዝ ሴቶች | 57272 | 54354 | 94.9 |
| የማዋለድ አገልግሎቶች | 42208 | 37075 | 87.8 |
| ድህረ ወሊድ ክብካቤ | 26314 | 24570 | 93.4 |
| የቤተሰብ ምጣኔ | 405098 | 159851 | 39 |
| ዲፒቲ 3 | 45517 | 44741 | 98.3 |
| የኩፍኝ ክትባት | 45517 | 43413 | 95.4 |
| ሙሉ በሙሉ የተከተቡ | 45517 | 43003 | 94.5 |

**ምንጭ፡-**Addis Ababa City Administration Health Bureau Report, April 2005 (9 Months)

የእናቶችና የህፃናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ መሠረታዊ የሆኑ ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ የህዝባዊ ውይይት አስተያየትን በአካተተ መልኩ ሲታይ የጤና መስጫ ተቋማቶቹ የድንገተኛ አገልግሎቶች ማለትም የማለዋድ አገልግሎትን ለመስጠት ያላቸው አቅም እጅግ በጣም አነስተኛ ከመሆኑም በላይ አብዛኞቹ ደንበኞች በአገልግሎቱ አሰጣጥ እርካታ የላቸውም፡፡ በሆስፒታሎች የእናቶች ሞት ይስተዋላል፡፡ ይህም ችግር በአብዛኛው በድንገተኛ ክፍሎች ውስጥ የአዋላጅ ነርስና የማዋለድና የማህፀን ስፔሺያሊስቶች እጥረት/ማነስ ነው፡፡ በተጨማሪም የአቅርቦቶች ማነስ፣ የአገልግሎቶች አለመኖር፣ ተገቢ የሆነ ክህሎት/ችሎታ በባለሙያዎቹ ዘንድ ማነስ፣ የጤና ሠራተኞች ተነሳሽነት መጥፋት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ችግሮች ሲሆኑ እነዚህም ተገቢው መፍትሔ ሊበጅላቸው ይገባል፡፡ ተገቢ የሆነ የሰው ሃብት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ ቢደረግ ከላይ የተመለከቱትን አብዛኞቹን ችግሮች እንደሚቀርፍ ይታመናል፡፡

እስከአሁን ድረስ ክፍለ ከተሞቹ በ2005 ዓ.ም ያካሄዱትን የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች አፈፃፀም ከዕቅድ ጋር ተመልክተናል፡፡ ዕቅዱን ከአፈፃፀም አንፃር ምልከታ ሲደረግ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ብዙ ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፣ ተገቢ የሆነ ዕቅድ መኖር ወይም አለመኖር፣ የክፍለ ከተሞቹ ነባራዊ ሁኔታና ሌሎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በሚቀጥሉት አንቀጾች ዋና ዋና አመላካቾችን ከአፈፃፀሙ እና ከሌሎች የልማት ውጤቶች ጋር በማነፃፀር ትንታኔ ቀርቧል፡፡ የሥነ-ሕዝብና የጤና ዳሰሳ መረጃን (2000 እ.ኤ.አ.፣ 2005 እ.ኤ.አ. እና 2011 እ.ኤ.አ.) መሠረት በማድረግ አመላካቾችን ከጊዜና ከአጠቃላይ ብሔራዊ አሃዞች ጋር ለማነፃፀር ተሞክሯል፡፡ የአዲስ አበባን የጤና አመላካቾች ከብሔራዊ አሃዞች ጋር ለማነፃፀር ከባድ ነው፡፡ ምክንያቱም በሀገር ደረጃ ያለው መረጃ አዲስ አበባን እንዲሁም አብዛኛውን የሀገሪቱን ክልል የሚሸፍነውን የገጠር ማህበረሰብ የሚጨምር ስለሆነ ነው፡፡ ሆኖም ግኝቱ በተወሰነ ደረጃ አዲስ አበባ ከአመላካቾቹ አንፃር ያለችበትን ደረጃና የአፈፃፀሙ ዝንባሌን አስመልክቶ ፍንጭ ይሰጣል፡፡


## 6. የጤና አገልግሎቶች እና የጤና ሁኔታ አመላካቾች

### የመውለድ አቅም

በአዲስ አበባ በ2000፣ 2005 እና በ2011 እ.ኤ.አ. ያለው የአንዲት ሴት የመውለድ አቅም በምስል አንድ ተመልክቷል፡፡ በምስሉ ላይ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ የመውለድ አቅም በ2000 እ.ኤ.አ. ከነበረበት 1.9 ወደ 1.5 በ2011 እ.ኤ.አ. ዝቅ ብሏል፡፡ በአዲስ አበባ የተመዘገበው

የአንዲት ሴት የመውለድ አቅም ከብሔራዊ አሃዝ ጋር ሲነፃር በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ይህም በብሔራዊ ደረጃ የመውለድ አቅም በ2000 እና በ2011 እ.ኤ.አ. እንደ ቅደም ተከተላቸው 5.9 እና 4.8 ነበር፡፡

ምስል 1:




**የወሊድ መከላከያ ሽፋን**

በአዲስ አበባ ከተማ ከ2000 እስከ 2011 እ.ኤ.አ. ድረስ ያለውን የወሊድ መከላከያ ሽፋን በምስል 2 የተመለከተ ሲሆን ይህም ሽፋን ከብሔራዊ አሃዝ ጋር በተመሳሳይ ወቅት ተነፃፅሮ ቀርቧል፡፡

የወሊድ መከላከያ ሽፋን በጊዜ ሂደት ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ይታይበታል፡፡ የዘመናዊ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ሽፋን በ2000 እ.ኤ.አ. ከነበረበት 34.3 ፐርሰንት ወደ 56.3 ፐርሰንት በ2011 ደርሷል፡፡ ምንም እንኳን በብሔራዊ ደረጃ ከ2000 እስከ 2011 እ.ኤ.አ. ባሉት ጊዜያት ውስጥ ያለው አሃዝ የጨመረ ቢሆንም በአዲስ አበባ የታየው የወሊድ መከላከያ ሽፋን ከብሔራዊ አሃዝ በሁለት እጥፍ የጨመረ ነው፡፡ በአጠቃላይ መረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት የዘመናዊ የወለድ መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ሽፋን በኢትዮጵያም ሆነ በአዲስ አበባ በከፍተኛ ሁኔታ የጨመረ ሲሆን ይህም በተለያዩ ሪፖርቶች የተረጋገጠ ነው፡፡

**ምስል 2**





**የሕፃናት የሞት ምጣኔ**

የአዲስ አበባ የሕፃናት የሞት ምጣኔ ቅርፅ (ሁኔታ) በምስል 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ሁሉም የሕፃናት ሞት ምጣኔዎች ማለትም ከ5 ዓመት በታች ህፃናት የሞት ምጣኔ፣ ከ4 ዓመት በታች የሕፃናት የሞት ምጣኔ፣ ከ1ዓመት በታች የህፃናት የሞት ምጣኔ እና የጨቅላ ህፃናት የሞት ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ መጥተዋል፡፡ ሆኖም ከ2005 እስከ 2011 ባሉት ጊዜያት ውስጥ የጨቅላ ህፃናት ሞት ቅነሳ ከሌሎቹ የህፃናት ሞት ምጣኔዎች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡ የተለያዩ ሪፖርቶች ኢትዮጵያ ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች መካከል ከ4 ዓመት በታች የህፃናት የሞት ምጣኔና ከ1 ዓመት በታች የህፃናት የሞት ምጣኔን በመቀነስ ግቦቹን ማሳካት እንደምትችልና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶችንም ያስቀምጣሉ፡፡[3] ሆኖም ከ2005 ወዲህ የጨቅላ ህፃናትን ሞት በመቀነስ ረገድ ያለው እንቅስቃሴ ዝቅተኛ በመሆኑ ለዚሁ ክስተት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመለየት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

[3] Mitike G., Key Challenges in Meeting MDG4: Reduction of child mortality (Editorial). The Ethiopia J. of Health Development, 2012:26(2): 63-65

ምስል 3





### የኤች አይ ቪ ስርጭት ሽፋን

በሚቀጥለው ፅሁፍ የተቅማጥ፣ አጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ እና የኤች አይ ቪ ስርጭት አመላካች መጠኖችን እንመለከታለን። በምስል 4 እንደተመለከተው የኤች አይ ቪ ስርጭት ሽፋን በመጨረሻዎቹ ሁለት የሥነ-ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናቶች ላይ ተቀምጧል፡፡

የኤች አይ ቪ ስርጭት ሽፋን ከ15-49 ዓመት ዕድሜ ክልል ከሚገኙ ወንዶች ውስጥ በ2005 ከነበረበት 3 ፐርሰንት በ2011 ወደ 4.3 ፐርሰንት አድጓል። በሌላ በኩል የኤች አይ ቪ ስርጭት ሽፋን በሴቶች ብዙም ለውጥ ሳያሳይ በ2005 ከነበረበት 6.1 ፐርሰንት ወደ 6.0 ፐርሰንት በ2011 ደርሷል፡፡ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት ሽፋን በብሔራዊ ደረጃ በሴቶችና በወንዶች በ2005 እና በ2011 ምንም ለውጥ አላሳየም፡፡ ሆኖም በተመሳሳይ ወቅት የኤች አይ ቪ ስርጭት ሽፋን ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ጎልቶ ይታያል፡፡


ምስል 4




**የተቅማጥና አጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ በህፃናት**

ምስል 5 የተቅማጥ እና አጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ በአዲስ አበባና በኢትዮጵያ ያለውን የስርጭት ሽፋን ይዘትን ያመለክታል፡፡ የተቅማጥና አጣዳፊ የመተንፈሻ አካል በሽታ ስርጭት ሽፋን በጊዜ ብዛት በሁለቱም ማለትም በአዲስ አበባ (ከ10.4 ፐርሰንት ወደ 1.3 ፐርሰንት) እና በብሔራዊ ደረጃ (ከ24.4 ፐርሰንት ወደ 7 ፐርሰንት) ቀንሷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተቅማጥ ስርጭት ሽፋን በጊዜ ብዛት በአዲስ አበባ ከ12.2 ፐርሰንት ወደ 9.4 ፐርሰንት እንዲሁም በብሔራዊ ደረጃ ከ23.6 ፐርሰንት ወደ 10.4 ፐርሰንት ቀንሷል፡፡ ነገር ግን በ2005 በአዲስ አበባ የተቅማጥ በሽታ ስርጭት ከ2000 ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ እንደነበርና የበሽታውም ቅነሳ በብሔራዊ ደረጃ ካለው ቅነሳ ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ ይህንን በአግባቡ ለማብራራት ይከብዳል። ምክንያቱም በህፃናት ላይ የሚደርሱ የተቅማጥ በሽታዎች መንስኤዎች ብዙና የተሳሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡ በቀረበው መረጃ መሰረት ባለፉት አምስት አመታት በጣም ትልቅ ቅነሳ የተስተዋለ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ የሚነግረን የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ መሻሻል ያለ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም በአዲስ አበባ ያለው መሻሻል በብሔራዊ ደረጃ ካለው ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ምክንያቶቹ በቅጡ ሊፈተሹ ይገባል፡፡

ምስል 5




ምስል 6 የክትባት አገልግሎት ሽፋን በአዲስ አበባና በብሔራዊ ደረጃ ያለውን ይዘት ያመለክታል፡፡ ለሁሉም የክትባት ዓይነቶች የክትባት ደረጃው በአዲስ አበባ ከ73.8 ፐርሰንት ወደ 78.7 ፐርሰንት በጥቂት መሻሻልን አሳይቷል፡፡ ሆኖም በብሔራዊ ደረጃ በ2000 ከነበረው 14.3 ፐርሰንት ወደ 24.3 ፐርሰንት በ2011 ደርሷል፡፡

ምስል 6




በዓለም ባንክ ጥናት ሪፖርት መሰረት በዝቅተኛው ደሃና በባለፀጋው መካከል ያለው ልዩነት በአዲስ አበባ ያለው ከብሔራዊው አሃዝ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ

ነው፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ያለው በዝቅተኛውና በባለፀጋው መካከል ያለው ልዩነት ብር 37 እና ብር 137 ሲሆን በብሔራዊ ደረጃ ደግሞ ብር 15.8 እና ብር 50.9 ነው፡፡ በእያንዳንዱ የበሽታ ንክኪ በአቅራቢው የሚወጣው ወጪ በአዲስ አበባ ብር 95 ሲሆን በኢትዮጵያ ደረጃ ደግሞ ብር 23.5 ነው፡፡[4]

በሠንጠረዥ 6 እንደተመለከተው የበጀት አጠቃቀሙ በጣም ትንሽ ሲሆን ይህም በአብዛኛው ከ50 ፐርሰንት በታች ነው፡፡ ይህም በጤና ቢሮው ደረጃ የታወቀ መሆኑንና ያለውን ሀብት በአግባቡ የመጠቀም ደካማነት እንዳለ ነው። የዚህ ችግር መንስኤ በተቋማት ዝቅተኛ ብቃት ብቻ ሳይሆን ከመስሪያ ቤቱ ውጭ ባሉ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ተፅዕኖዎች ስለሚደርስበት ነው፡፡ የከተማው የጤና ቢሮ ዝቅተኛ የበጀት አጠቃቀም ሊኖርበት የቻለበትን ምክንያት በግልፅ ለይቶ ወደፊት አፈፃፀሙን ለማሻሻል የሚያስችለውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

[4] World Bank, World Bank Report, 2004.

## ሠንጠረዥ 7: በአዲስ አበባ የጤና ቢሮ የበጀት አጠቃቀም (9 ወራቶች፣ 2005 ዓ.ም.)

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የወጪ ሪፖርት | | | |
| ተ.ቁ | ሥራዎች | | የዓመቱ ዕቅድ (2005) | ከሐምሌ 1 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2005 | | | |
| | | | | የ8 ወራቶች ዕቅድ | አፈጻጸም | ባላንስ | % |
| 1 | ደመወዝ | 6100 | 8,191,873.00 | 6,143,917.30 | 4,352,717.67 | 1,791,199.63 | 71 |
| 2 | መደበኛ በጀት | 62/63/00 | 11,420,952.00 | 9,327,146 | 2,088,056.61 | 7,239,089.39 | 22 |
| | ድምር | | 19,612,825.00 | 15,471,063.3 | 6,440,774.28 | 9,030,289.02 | 46.5 |
| | | | | የገቢ ሪፖርት | | | |
| ተ.ቁ | ሥራዎች | | የዓመቱ ዕቅድ (2005) | የ8 ወራቶች ዕቅድ (ከሐምሌ 1 እስከ መጋቢት 30, 2005) | | | |
| | | | | ዕቅድ | አፈጻጸም | ባላንስ | % |
| 1 | 1489 | | | 240,000.00 | 554,881.07 | | 231.20 |
| | ድምር | | | 240,000.00 | 554,881.07 | | 231.20 |
| | | | | ከለጋሾች ተገኝቶ የወጣ ወጪ | | | |
| ተ.ቁ | ሥራዎች | ከ 2003 እና 2004 | ገቢ 2005 | ድምር | ወጪ | ቀሪ ባላንስ | % |
| 1 | ከተለያዩ ለጋሾች | 3,031,543.80 | 12,432,111.39 | 15,463,655.19 | 7,535,581.32 | 7,928,073.87 | 48.73 |
| | ድምር | 3,031,543.80 | 12,432,111.39 | 15,463,655.19 | 7,535,582.32 | 7,928,072.87 | 48.73 |

ምንጭ:- Central Statistic Agency and ORC Macro, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Demographic and Health Survey, 2011.

## 7. አዋጆች፣ ደንቦች፣ የሥነ-ምግባርና የአሠራር ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮው የተቋቋመው በአዋጅ ሲሆን አዋጁም በ2008 ተሻሽሏል፡፡ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 8/2008 ነው[5]፡፡አዋጁ ከሚዳስሳቸው ጉዳዮች መካከል፣ የሕክምና አገልግሎት መርሆዎች፣ የጤና ቢሮው ኃላፊ ሥልጣን፣ የጤና አገልግሎት አስተዳደር መዋቅሮች፣ የሆስፒታሎችና የጤና ማዕከሎች ህጋዊነት፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ስለ ሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፣ ስለጤና ጣቢያዎች ከፍተኛ ሥራ አመራር፣ የሥራ አመራር ቦርድ እና ከፍተኛ የሥራ አመራር አካላት በጤና ጣቢያዎች ያላቸውን ሥልጣንና ተግባር፣ የሆስፒታልና የጤና ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባራት፣ የሥራ አመራር ቦርድና ከፍተኛ የሥራ አመራር ተጠያቂነት፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የአሠራር ደንብ፣ የሪፈራል ስርዓት፣ በሆስፒታሎች የግል የሕክምና ክፍል ስለማቋቋም፣ ከክፍያ ነፃ የሆኑ የጤና አገልግሎቶች፣ የሆስፒታሎችና የጤና ጣቢያዎች የገንዘብ ምንጭ፣ የሀብት አጠቃቀም፣ የጤና አገልግሎት ክፍያ፣ የጤና ኢንሹራንስ፣ የገቢ አጠቃቀም፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ ዓላማዎች፣ በዕቅድ ረገድ ስለሚኖረው ተሳትፎ፣ የግልና የመንግስት ትብብር፣ የድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት፣ የሥራ አካባቢን ስለማሻሻል፣ የምክክር ፎረም፣ ስለድጋፍ፣ የመረጃ መሠረትን ስለማጠናከር፣ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እና የተሻሩ ህጎች ይገኙበታል፡፡ ይህ የሚያሳየው የአዲስ አበባ አስተዳደርና የጤና ቢሮው አገልግሎቶችን፣ መዋቅሮችን፣ ሥራ አመራሩን፣ የማህበረሰቡን ተሳትፎን፣ የፋይናንስ ሁኔታና የህግ ማዕቀፎችን ለማስቀመጥ ረጅም ርቀት መሄዳቸውን ያመለክታል፡፡

አዋጁን መሠረት በማድረግ ዝርዝር የትግበራ መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የአዲስ አበባ የጤና ቢሮ የጤና አገልግሎቶችን ስለመስጠትና ስለጤና አስተዳደርና አጠባበቅ ብዙ ዝርዝር መመሪያዎችንና ደንቦችን አዘጋጅቷል[6]፡፡ ከደንቦቹ  ዋና ዋና ነጥቦች መካከል፣ አመራርና ስራ አመራር፣ ገቢ ስለማመንጨትና ስለመጠቀም፣ ክፍያን ስለማስቀረት፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ የግሉ ክንፍ፣ የጤና አገልግሎት ያልሆኑትን ስራዎች

[5]Addis Ababa City Council, A Proclamation to amend the Addis Ababa City Government Health Service Delivery, Administration and Management, Addis Negarit Gazeta of the City Government of Addis Ababa, Proclamation No. 8/2008, Addis Ababa

[6] Addis Ababa City Government Health Bureau, Regulation for Health Service Delivery & Health Facility Administration and Management, No 1/2001, January 2001 E.C. Addis Ababa City Government Health Bureau, Regulation for Health Service Delivery & Health Facility Administration and Management, No 26/2001, November, 2001 E.C

በሌሎች አካላት እንዲሰሩ ስለማድረግ እና ሌሎች ደንቦች ማለትም የስራ አመራር ቦርድ አመሠራረት ይገኙበታል፡፡

በኛ ዳሰሳ በሚከተሉት ጉዳዮች ማለትም የአሰራር ደንብ፣ የሙያ ስነ-ምግባር እና እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ በምን ዓይነት መልኩ ከሙያ ማህበራት ጋር በትብብር ሊፈቱ ስለሚችሉበት ሁኔታ ውስን መረጃና ሪፖርቶች ብቻ ተገኝተዋል፡፡

## 8. የደንበኞች እርካታ

የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል ከተቀረፁት የሆስፒታሎች ሪፎርም ፕሮግራም አካል በመሆኑ፤ የጤና ቢሮው የደንበኞች እርካታን ማረጋገጥ ከአመላካቾቹ አንዱ እንደሆነ በመገንዘብ በየጊዜው/በመደበኛነት ክትትል ያደርጋል፡፡ ክትትሉ የሚካሄደው ህመምተኞች ከሆስፒታሉ ሲለቁ ነው፡፡ የሆስፒታሎችን ሥራ ለመለካትና ውጤታቸውንም ከጊዜ አንፃር እንዲሁም በሆስፒታሎች መካከል ንፅፅር ለማካሄድ ቁልፍ የሆኑ የአፈፃፀም አመላካቾች አሉ፡፡ ይህ ጉዳይ በሚመለከታቸው አካላትና ደንበኞች ሁልጊዜ ቅሬታ የሚቀርብበት ነው፡፡ አብዛኞቹ ቅሬታዎች የሚነሱት ከመድሃኒትና ሌሎች አቅርቦቶች እጥረት፣ በተለይ ተኝተው ለሚታከሙ አልጋ ለማግኘት ረጅም ጊዜ መጠየቁ፣ በጤና ባለሙያዎች የሚስተዋለው የደከመ ግንኙነት፣ የመረጃ እጥረት፣ የደከመ የሪፈራል ስርዓት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የጤና ቢሮው አብዛኛውን ቅሬታዎች የሚያውቃቸው በመሆኑ በዕቅዱ ውስጥ ለማካተት ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በቅርቡ በሶስት ሆስፒታሎች ተኝተው በሚታከሙ ህሙማን ላይ በተደረገው የእርካታ ዳሰሳ ህመምተኞች በከፍተኛ ደረጃ እርካታን እንዳገኙ (83 ፐርሰንት) ጥናቱ ያመለክታል (Yakob Seman, 2013)፡፡ ዋቢ መፅሐፍት ባይገኙም፣ በሽተኞች ታክመው ከህክምና ተቋማት ሲወጡ በተደረገ ውይይት ከ79-85 ፐርሰንት የሚሆኑ ደንበኞች በአገልግሎት አሰጣጡ መርካታቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም በደንበኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ደንበኞች የሚያጋጥማቸውን እውነተኛ ችግር ላይገልፁ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ደንበኞች አብዛኛውን ጊዜ እርካታን ከሚገባው በላይ ለጥጠው ሊለኩት ስለሚችሉ ነው፡፡

## 9. በጋራ የመስራትና ትብብር

ምንም እንኳን ከአዲስ አበባ አስተዳደር የጤና ቢሮ ጋር በትብብር የሚሰሩ ከ60 በላይ ተባባሪዎችና አጋሮች ቢኖሩም፣ የእነዚሁኑ ድርጅቶች ዝርዝር፣ የትብብር መስክ እና የክትትል አመላካቾችን የሚያሳዩ መረጃዎች የሉም፡፡ ይህ ትልቅ አቅም ስለሆነ ያሉትን መረጃዎች በስርዓት መያዝና የተደረገውንም ጥረት ሪፖርት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 10. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

በአጠቃላይ፣ በአመላካቾቹና በሪፖርቶቹ መሠረት የጤና ቢሮው መዋቅሩን እስከ ቤተሰብ ድረስ ማድረሱ፣ የማህበረሰቡን ተሳትፎ ማጎልበቱ፣ ተግባራትን ማስፈፀሙ፣ የጤና አገልግሎቱን ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለማዳረስ የጤና መስጫ ተቋማትን ማስፋፋቱ በዋናነት የሚጠቀሱ ተስፋ የሚጣልባቸው መሻሻሎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ከሆስፒታሎች የሪፎርም ፕሮግራም ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ የጤና ክብካቤ ጥራትን ለማሻሻልና የደንበኞችን እርካታ ለማረጋገጥ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

ምንም እንኳን የጤናው ፓሊሲ ብዙ ጉዳዮችን የያዘ ቢሆንም የከተማውን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ በተለምዶ ባለው የበሽታዎች ስርጭት (ለምሳሌ፣ ተላላፊ ያልሆኑ ብዙ የሚቆዩ በሽታዎች ከተላላፊ በሽታዎች አንፃር) በቅጡ ያልተዳሰሱ የአገልግሎቶች ፍላጎት በየጊዜው እየጨመረ የመጣ ስለሆነ የጤና ቢሮው በተለይ ሊመለከታቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። በጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ፬[7] ሰነድ ላይ ስለጥንካሬ፣ ስለደካማ ጎን፣ ስለ መልካም አጋጣሚዎችና ስለ ስጋቶች የቀረበው ትንታኔ ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ በሽታዎች ትኩረት አናሳ እንደነበርና እነዚህም በሽታዎች ለከፍተኛ የሞት ምጣኔ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡ ከአካባቢና ከስራ ደህንነት ጋር የተያያዙ የጤና ችግሮች (አደጋዎች/ጉዳቶች፣ የመተንፈሻ አካልና የልብ ችግሮች) እየጨመሩ የመጡ ስለሆነ እነዚህንም ለመቅረፍ በጣም ጥሩ የሆኑ ስትራቴጂዎችን መቅረጽ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የፓሊሲው ጉዳዮች የከተሞችን በተለይም የአዲስ አበባን ልዩ ሁኔታ በተሟላ መልኩ ለማስተናገድ ስለማይችሉ እንደገና ቢፈተሹ የተሻለ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳን በጤናው ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ፬ ላይ ተግባራዊ ምርምር እየጨመረ የመጣ እንደሆነ ቢያመለክትም፣ ተግባራዊ ምርምር እና መረጃን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ የበለጠ ሊበረታታ እንደሚገባና በጤናው ፓሊሲ ላይ ተመልክቶ ተግባራዊ ሳይደረግ የቀረውን ጉዳይ ለመተግበር ጠቃሚ የሆኑ የጥናት ውጤቶችን ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት ተገቢ ነው፡፡ የላብራቶሪና ምርምር ማዕከል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ስር እንዲተዳደር መደረጉ የጥናት ስራዎችን ይበልጥ ለማከናወን ጥሩ እምቅ ሀብት ነው፡፡ በተጨማሪም ምርምር የመስራትን አቅም ለማዳበር እንዲቻል ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትብብር መመስረት ተገቢ ነው፡፡

[7]Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Health, Health Sector Development Program IV, 2010/11-2014/15

ሠራተኞችን ማሳተፍ፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ማገዝና የባለቤትነት ስሜት እንዲዳብር ማበረታታት የጤና ክብካቤ አገልግሎት አፈፃፀምን ለማሻሻል በተለይም ጥራትን ለማረጋገጥና የደንበኞችን እርካታ ለመጨመር ያግዛል፡፡

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተደረገው ህዝባዊ ውይይት በጤና ዘርፍ ከሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መካከል፣ የመድሃኒትና የሌሎች አቅርቦቶች እጥረትና ከፍተኛ ዋጋ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረትና ከፍላጎት ጋር ያልተጣጣመ ውስን የሆስፒታል አልጋዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በሆስፒታል ተኝቶ ለመታከም የሚጠይቀው ረጅም ጊዜ እንደሚታወቀው ስር ሰዶ የቆየ ችግር ሲሆን እስካሁን አልተፈታም፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ዕቅዱን በአግባቡ ሊተገብር ይገባል፡፡

በአዋጁም ሆነ በጤናው ፓሊሲ የመንግስትና የግል ዘርፍ ቁርኝትን ማበረታታት አስፈላጊ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም በሪፖርቶቹ ሆነ በተደረገው ውይይት የግል ዘርፉ ተሳትፎ በግልፁ ካለመታወቁም በላይ በሪፖርቶቹ ላይ አልተመለከተም፡፡ የግል ዘርፉ የጤና አገልግሎቶችን በመስጠትና የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የሠልጣኞችን ችሎታና የስልጠናውን ጥራት በየጊዜው ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡

የጤና ቢሮው መድሃኒትና ሌሎች አቅርቦቶችን እጥረት ለመፍታት በየጊዜው የሚጠፉትን መድሃኒቶችና ሌሎች አቅርቦቶች በመለየትና ተገቢውን የክምችት መጠንና የተሻሻለ የሎጂስቲክስ ሥራ አመራር ለመዘርጋት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግርን ለመቅረፍ የጤና ቢሮው የጤና ኮሌጆችን በመክፈት በተለያዩ የነርስ ሙያዎች ማለትም አዋላጅ ነርስ፣ የራጅ ሠራተኛ፣ የላብራቶሪ ቴክኒሺያን፣ የፋርማሲ ቴክኒሺያን፣ የህክምና ዶክተሮች እና ሌሎች በብሔራዊ ስርዓቱ እጥረት ያለባቸውን ሙያዎች በማካተት ስልጠና ይሰጣል፡፡ የስልጠናውን ጥራት የማሻሻልና የክትትል ስርዓቶችን መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት

Addis Ababa City Administration Health Bureau Report, April 2005 (9 months)

Addis Ababa City Council, A Proclamation to amend the Addis Ababa City Government Health Service Delivery, Administration and Management, Addis Negarit Gazeta of the City Government of Addis Ababa, Proclamation No. 8/2008, Addis Ababa.

Addis Ababa City Government Health Bureau, Regulation for Health Service Delivery and Health Facility Administration and Management, No.1/2001. January 2001 E.C.

Addis Ababa City Government Health Bureau, Regulation for Health Service Delivery and Health Facility Administration and Management, No.26/2001. November 2001 E.C.

Central Statistic Agency and ORC Macro, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Demographic and Health Survey 2000 Addis Ababa and Maryland, USA,

Central Statistic Agency and ORC Macro, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Demographic and Health Survey 2005, Addis Ababa and Maryland, USA.

Central Statistic Agency and ORC Macro, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Demographic and Health Survey 2011, Addis Ababa and Maryland, USA,.

Central Statistic Agency, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Census 2007.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health Sector Development Program IV, 2010/11-2014-15.

Health Policy of The Transitional Government of Ethiopia, 1993

Ministry of Health, Health and Health related indicators, 2003 E.C.

Mitike G, Key Challenges in Meeting MDG4: Reduction of child mortality (Editorial). The Ethiop. J. of Health Dev. 2012; 26 (2):63-65.

Mohamed H. Addis Ababa City Administration Health Bureau, 2008.

World Bank, World Bank Report 2004.

Yakob Seman, “Assessment of the Level of Patient Satisfaction and its Determinants among Admited Patients in Selected Public Hospitals of Addis Ababa, Ethiopia,” (MPH thesis Submitted to School of Public Health, Addis Ababa University, 2013)

# የቤቶች ሁኔታ በአዲስ አበባ

*ደመቀ ኃይሌ*

## 1. *መግቢያ*

### 1.1 *ስለቤቶች ዘርፍ*

*በተባበሩት መንግሥታት የሃቢታት ተቋም በተሰበሰበው መረጃ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ አንድ ቢሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚኖረው በደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ባልሆኑ ቤቶች ሲሆን ይህም ሁኔታ በየቀኑ እያደገና እና እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠቁማል፡፡ ይህ ችግር ከሁሉም በላይ በቂ ባልሆኑ የቤት ፖሊሲዎች፣ የከተሞች መስፋፋትና ዕድገት እየጨመረ መምጣትና ከዚህም የተነሳ አካሄዱን መቆጣጠር ያለመቻል እና በከተማ የሚገኝን መሬት ለአብዛኛው የከተማ ነዋሪ ተደራሽ ማድረግ ያለመቻል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በ*1996 *የወጣው የሃቢታት አጀንዳና የኢስታንቡል ዲክላሬሽን ከዚህ ጋር ሲታይ የአጋጣሚም አልነበረም፡፡ ይህ ዲክላሬሽን “በቂ መጠለያ ለሁሉም” የሚለውን ዓለም አቀፍ ዕቅድ ወደተግባር ለመውሰድ የታሰበ ነበር፡፡ ይህ የሃቢታት አጀንዳ መንግሥታት መጠለያን ለሁሉም ለማዳረስ፣ ሁሉም ሊሳተፍበት በሚችል ዋጋ ለማቅረብ፣ ተደራሽ ለማድረግ እና የቤቶች አቅርቦትን ቀላል ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነበር፡፡*

*የህዝብ እድገት እና እየጨመረ የመጣው የመሬት፣ የቤቶች እና የመሠረተ ልማት ፍላጎት የክልልና የብሔራዊ መንግሥታት ትልቁ ፈተና እየሆነ ይገኛል፡፡ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት የሃምሳ ዓመታት ልምድ እንደሚያሳየው በሃገራቱ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በበቂ ሁኔታ ለመፍታት ያስቻሉ አልነበሩም፡፡ በብዙ መንግሥታት በከፍተኛ ሁኔታ በመንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑ የቤቶች አቅርቦት ፕሮግራሞች በስፋት ተግባራዊ ቢሆኑም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ቤቶችን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኙ የማድረጉን ችግር መፍታት አልተቻለም፡፡ እንደአማራጭ ተግባራዊ የተደረጉት ከተለመደው ወጣ ያሉና የቤቶቹንም ደረጃ ዝቅ በማድረግ በራስ አገዝ፣ የጋራ የእገዛና የማህበር መርህን መሠረት ያደረጉ የቤቶች ፕሮግራሞች፣ቀ ዝቅ ባለ ዋጋ የተለያዩ ግብዓቶችን ማለትም መሬትን፣ የሰው ሃይልን እንዲሁም መሠረተ ልማትን በማቅረብ በተወሰነ ደረጃ ችግሩን ለመቅረፍ ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ካለው የቤቶች ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር ያላቸው አስተዋጽኦ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንኑ ለመቅረፍ የመሬት መጠንን በህግ ወስኖና*

የመሠረተ ልማት ዝርጋታውን ቀስ በቀስ በማካሄድ የተወሰደው ቀጣይነት ያለው የመሬት ልማት ፕሮግራም ያለውን ችግር ለመቅረፍ ያስቻለ አልነበረም፡፡

ቤቶችን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ላሉ ቤተሰቦች ማቅረብ ያለመቻልና አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል መሬት በቀላሉ ማግኘት ያለመቻል ከህግ ውጭ የሆኑ ቤቶች እንዲስፋፉ ማድረጉ ችግሩ ማብቂያ እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ ፖሊሲ አመንጪዎችም የዚህን ችግር መሠረታዊ መንስኤ በትክክል መለየት አልቻሉም፡፡ ይህ ከህግ ውጭ የሆነ የቤቶች መስፋፋት ደግሞ በብዙ ከተሞች ለበርካታ ዜጎች የቤት ማግኛ ዋና ዘዴ እየሆነ ይገኛል፡፡ ከህግ ውጭ የሆኑ የመሬት ሠፈራዎች፣ በከተሞች ዳርቻ ባልለሙ መሬቶች ላይ የሚሰሩ የጨረቃ ቤቶች፣ ለአደጋ ተጋላጭ በሚባሉ አካባቢዎች የሚከናወኑ ሠፈራዎች በሙሉ የከተሞች ዕድገትን መውጫ የሌለው አዙሪት ውስጥ እንዲኖር አድርገውታል፡፡ የምዕተ ዓመቱ ስምምነት (2000) እና በ2005 የተከለሰው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ተራ ቁጥር 7 ኢላማ 11፣ እስከ 2020 ድረስ ቢያንስ የ100 ሚሊዮን ከህግ ውጭ የሆኑ ኗሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እና አዳዲስ ከህግ ውጭ የሚሰሩ ቤቶች እንዳይኖሩ አማራጮች የፖሊሲ ምላሾችን ለመስጠት ያለመ ነው። ይህ ሃሳብ ሁለት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሠረታዊ ጉዳዮችን ያነሳል። አንደኛው ጉዳይ በየከተሞች ከህግ ውጭ የሚሰሩ ቤቶችን መኖርና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጁ ከመሬት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎች ይህን ሁኔታ በማሻሻል የከተሞችን መስፋፋት ስርዓት ባለው ሁኔታ መምራት እንዲያስችሉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው። ሌላው ጉዳይ ደግሞ በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ቤተሰቦች ተደራሽና አቅምን ያገናዘቡ የቤቶች ልማት አማራጮች ለመስጠት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መንደፍ አስፈላጊና መሠረታዊ መሆኑን ነው። እነዚህ እርምጃዎች ደግሞ በበርካታ ታዳጊ ሃገሮች የሚገኙ ከተሞችን ዕድገት እየጎተተ ያለውን ህገወጥ የሆኑ የቤቶች መስፋፋትን ለማስቀረት ያም ባይሆን ለማረጋጋት ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል።

## 1.2 *የጥናቱ ግብ፣ ውሱንነትና ስልት*

ግብ፣ የዚህ ጥናት ግብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያለውን የቤቶች ሁኔታ መቃኘት ነው፡፡ይህ የጥናት ወረቀት በመካሄድ ላይ የሚገኘውን የቤቶችን ልማትና ወሳኝ በሆኑ ቦታዎች እየተከናወነ ያለውን የመልሶ ማልማት ሁኔታ ይተነትናል፡፡ በመጨረሻም አሁን በሥራ ላይ ያሉ ከመሬት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መመሪያዎችን በማሻሻል አዳዲስና አሁን ያለውን ሁኔታ ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ፖሊሲዎችን፣

ህጎችንና መመሪያዎችን ለማሻሻል ሊያግዙ የሚችሉ ኃሳቦችን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች መልሶ ማልማት ሂደት ውስጥ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎችና እርምጃዎችን በተመለከተ ሊወሰዱ የሚገባቸው የማሻሻያ ኃሳቦች ቀርበዋል፡፡ የከተሞች የመኖሪያ ቤቶች ልማትና በመሃል ከተማዎች የሚካሄዱ መልሶ ማልማት ሥራዎች መሻሻል ከጥናቱ የሚጠበቅ ውጤት ነው፡፡

***ወሰንና ውሱንነት፣*** የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ስላለው የመኖሪያ ቤቶች ልማትና መልሶ ማልማት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የጥናት ወረቀት በቤቶች ልማት መስክ ባለፉት 20 ዓመታት በሚመለከታቸው የተለያዩ አካላት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን ያሳያል፡፡ በዋናነት በከተማዋ ያለውን የቤቶች ችግር፣ ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችንና እስከአሁን ባለው ሁኔታ የተመዘገቡ ውጤቶችን ለይቶ ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም በወሳኝ አካባቢዎች እየተከናወነ ያለው የመልሶ ማልማት ሥራ አጠቃላይ የሥራው ሂደት ወደሌላ ቦታ ማስፈርና ካሳ ክፍያን ጨምሮ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተገኙ ውጤቶችን ሶስት ፕሮጀክቶችን በምሳሌነት በመውሰድ ይተነትናል፡፡ በተጨማሪም የዳሰሳ ጥናቱ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማትንና የመልሶ ማልማትን በተመለከተ ከህዝብ የተሰበሰበ አስተያየት በመደገፍ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### *የጥናቱ ስልት*

***የመረጃ ምንጭ፣*** ጥናቱ ሁለቱንም የመረጃ ምንጮች ማለትም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ተጠቅሟል፡፡ በዋናነት እንደዋነኛ የቀጥተኛ መረጃ ምንጭ የሆኑት በአዲስ አበባ የመሬት ልማት ኤጀንሲና በአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት የሚሰሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሲሆኑ በተጨማሪም በተወሰኑ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የአካል ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ እንደ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ከቤቶች ልማትና መልሶ ማልማት ጋር የተያያዙ የተለያዩ የጥናት ወረቀቶች፣ ሪፖርቶችና አግባብነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ ጽሁፎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በቁጥር ሊገለጹ የሚችሉትን መረጃዎች መሠረታዊ የሆኑ የስታቲስቲካዊ መንገዶችን በመጠቀም መረጃዎች እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡

በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ዋና የመረጃ ምንጭ የነበሩት መሥሪያ ቤቶች የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና ግንባታ ቢሮ፣ በአዲስ አበባ መስተዳድር የመሬት ልማት ኤጀንሲ የሚያገለግሉ የተለያዩ የሥራ ሂደት ኃላፊዎች እና

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በተጨማም የበርካታ አጥኝዎች የጥናት ወረቀቶች ለጥናቱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

***የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች፣*** በዚህ ጥናት ዝግጅት ወቅት በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋሉት መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ከአዲስ አበባ የመሬት ልማት ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ቢሮ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ለሚያገለግሉ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅና የፎከስ ግሩፕ ውይይት፣ በመረጃ መረብ የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ ከቤቶች ልማትና አቅርቦት እንዲሁም መልሶ ማልማትና የቤቶች ማፍረስ ጋር የተያያዙ የተለያዩ የጥናት ወረቀቶች፣ ሪፖርቶች፣ ሌሎች ጽሁፎች ዳሰሳም በዋና የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገድነት አገልግለዋል፡፡

***የመረጃ ትንተናና አቀራረብ፣*** ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች በመግለጫ፣ በሠንጠረዦች፣ በቻርቶች፣ በግራፍና በስዕል እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎቹ በቁጥር ሳይሆን በገለጻ መልክ በመዘርዘር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### *1.3 ከተማና የቤቶች ሁኔታ*

ወደከተማነት መቀየር ሲባል ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎች በተመጣጣኝ ሁኔታ አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች በመስፈር ከተሞችና ትንንሽ ከተሞች የሚፈጠሩበት ሂደት ነው፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም መሠረት

| | | |
|---|---|---|
| በ 1800 | 3% | (ከኢንዱስት አብዮት በፊት) |
| በ 1980 | 40% | ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ |
| በ 2000 | 50% | ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ |
| በ 2050 | 90% | ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ |

ከላይ ከቀረበው መረጃ እንደሚታየው ከ 36 ዓመታት በኋላ 70% የሚሆነው የዓለማችን ህዝብ የሚኖረው በከተሞች ይሆናል ወይም ከተሜ ይሆናል። የከተሞች እድገትም በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ከዚህም የተነሳ አብዛኛዎቹ እንቅስቃሴዎች ከከተማ ጋር የተያያዙ ይሆናሉ፡፡ ይህም የከተማ ቤቶች ሁኔታ ትኩረት ማግኘት እንዳለበት ያመላክታል፡፡

**በኢትዮጵያና በአዲስ አበባ የከተሜነት ሁኔታ**

*በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ የሚኖረው የከተማ ሕዝብ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ወደ* 1000 *በሚጠጉ የከተማ ማዕከላት ይኖራል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ወደከተማነት የመለወጥ ደረጃ በአጠቃላይ በአፍሪካ ሃገሮች ካለው የከተሞች ዕድገት አንጻር በግማሽ ያነሰ ቢሆንም በአጠቃላይ በሃገሪቱ የከተማ ኗሪዎች ብዛት* (*ማለትም* 11,199,013) *ግን በአህጉሪቷ ትልልቅ ከተሞች ጎራ እንድትሰለፍ አድርጓታል፡፡ ይህ* 11.2 *ሚሊዮን የሆነው የከተማ ነዋሪም ባልተመጣጠነ ሁኔታ በሃገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቶ ይኖራል፡፡ አዲስ አበባ የሃገሪቱ ዋና ከተማና ቀዳሚ ከተማ እንደመሆኗ መጠን ከሃገሪቱ የከተማ ኗሪ* 26% *ስትይዝ ይህም በኦሮሚያ ክልል ከሚኖረው* 30% *ቀጥሎ በዚች ከተማ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በላይ አዲስ አበባ በህዝብ ብዛት ከሃገሪቱ ቀዳሚ ከተማ ናት፡፡ የህዝብ ብዛቷም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በሁለተኛ ከተማ ከምትገኘው የድሬዳዋ ከተማ በአስራ አራት እጥፍ የሚበልጥ የህዝብ ብዛት አላት፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ አበባ በአፍሪካ ከሚገኙ ካላደጉ ከተሞች አንዷ ስትሆን በከፍተኛ ደረጃ ከሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መካከል የከተማ ድህነትና የደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ያልሆኑ ቤቶች ይገኙበታል፡፡*

*በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት የአዲስ አባባ ከተማ ኗሪ ብዛት በ*2005 *ዓ.ም፣* 2,887,000*፣ በ*2010 *ደግሞ* 3,328,000 *ተገምቶ እንደነበርና በ*2015 *ደግሞ* 3,792,000 *ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡*

### *1.4 የከተማ ቤቶች ጽንሰ ኃሳብ*

**የዋና ዋና ጽንሰ-ሀሳቦች ትርጉም**

**ቤት**፣ *ቤት ማለት መኖሪያ፣ ህንጻ፣ ወይም መዋቅር ሆኖ ለሰዎች ወይም ለሌሎች ፍጥረታት ለመኖሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡ ቤት የሚለው ሃሳብ ከትንሹ ከአርብቶ አደሩ ከሚሰራው ጎጆ ቤት እስከ ውስብስብ የሆነውና የተለያዩ ስርዓቶች የተዘረጉለት መኖሪያ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፡፡ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች የትኛውንም ዓይነት ህንጻ መኖሪያ በማለት ይጠሩታል፡፡*

**ቤተሰብ** (*ሃውስሆልድ*)፣ *በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቤተሰብ ይባላሉ፡፡ ቤተሰብ ብዙ ጊዜ የአንድ ቤተሰብ አባላትን የሚይዝ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ቤተሰብ ያልሆኑ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦችን ሊይዝ*

ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ ቤተሰብ የሚለው አባባል በአንድ ቤት ውስጥ በቡድን ሆነው የሚኖሩና የቤት ወጪዎችን የሚጋሩ (አብረው የሚያበስሉ) ሰዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

**ሕዝብ፣** በዚህ አገላለጽ መደበኛ ነዋሪ ሕዝብን የሚመለከት ሲሆን ተቋማትን፣ የመከላከያ ሃይሎችን እና በአብዛኛው ተማሪዎችን አይመለከትም።

**በቂ መጠለያ፣** ማለት ራስን ከመከለያ ጣሪያ ከመከላከል የበለጠ ነገር ነው፡፡ በተጨማሪም በቂ መጠለያ ሲባል በቂ የግል ነጻነት፣ በቂ ቦታ፣ ብዙ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ቦታ፣ በቂ ደህንነት፣ የባለቤትነት ነጻነት፣ የቦታው ዘላቂነትና ጥንካሬ፣ በቂ ብርሃን፣ ሙቀት ንፋስ እና መሠረታዊ የሆኑ መሠረተልማት ያለው ማለት ነው፡፡

**መኖሪያ ቤት፣** መኖሪያ ቤት ማግኘት ለሰው ልጅ አንዱ መሠረታዊ ፍላጎት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የሰው ልጆች ፍላጎት ማሟላት በሃገሪቱ የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ይወሰናል፡፡ ይህም ሲባል መኖሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን የመኖሪያው አካባቢ፣ መሠረተ ልማቱና ያሉት አቅርቦቶችን ያካትታል።

**የቤት ፍላጎት፣** አዳዲስ ቤተሰቦችን ለማስተናገድ፣ የተበላሹ ቤቶችን ለመቀየርና በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖረውን የሰዎች ጭንቅንቅ ለማስቀረት የሚያስፈልጉ በተፈለገው ደረጃ ያሉ መኖሪያ ቤቶች ብዛት ማለት ነው።

**ቤት የማግኘት መብት፣** ማለት በቂ ቤትና መጠለያ የማግኘት ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብት ነው፡፡ ይህም መብት በብዙ ሃገራት ህገ መንግስትና በዓለምአቀፍ ሰብዓዊ መብት ዲክላሬሽን እና በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህል ዓለማቀፋዊ ኮንቬንሽንም ላይ ተጠቅሷል፡፡

**የከተማ መልሶማልማት፣** በከተማ አካባቢ የሚታዩ ችግሮችን ለማቃለል፣ የኗሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ውጤታማ የሆነ የመሬት አቀማመጥ በከተማ እንዲኖር ለማድረግ የከተማን ሁኔታን ማሻሻል እና የከተማ ቦታን ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ መለወጥ ማለት ነው፡፡

**የከተማ ማደስ፣** በከተማ ማዕከል ውስጥ የሚገኙ ያረጁ፣ የተበላሹና የወደቁ የመኖሪያ ቤቶችና ህንጻዎች በማፍረስ ቦታውን ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች መጠቀም ማለት ነው (Miller, 1959) ፡፡

**ከተማን ማሻሻል/ማሳደግ፣** ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ አገልግሎችንና መሠረተልማቶችን በማቅረብ በደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች ላይ የቤቶችን አካላዊ ሁኔታ በማሻሻል ያለውን ቤት ሳያፈርሱ ለመኖሪያና ለሌሎች አገልግሎቶች ምቹ አካባቢን በመፍጠር የሚካሄድ ጣልቃገብነት ነው፡፡

**ካሳ፣** ባለው ህግ መሠረት አዲስ የከተማ ልማት ተግባራዊ በመሆኑ ወይም የልማት ሥራዎች በመሠራታቸው ምክንያት በንብረታቸው ወይም በሃብታቸው ላይ ለደረሰባቸው ኪሳራ በገንዘብ ወይም በቁሳቁስ የሚከፈል ማካካሻ ነው፡፡

**ኮንዶሚኒየም/ኮንዶ፣** ማለት የቤት ባለቤትነት እና ሌላ የሚጨበጥ ንብረት ዓይነት ሲሆን ከኮንዶሚኒየሙ የተወሰነ ክፍል በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት የተያዘ ሆኖ ሌሎች የጋራ የሆኑ ፋሲሊቲዎች ማለትም መገልገያዎች፣ ኮሪደሮች፣ ማሞቂያዎች፣ ሊፍቶች እና በግቢው ውስጥ ያሉ ቦታዎችን የመጠቀም ከሕግ መብቶች ጋር የተያያዘ የግለሰብ ባለቤትነት ሲሆን ቁጥጥሩ የሚካሄደው ግን የሁሉንም አካላት በጋራ ባለቤትነት በሚወክለው የባለቤቶች ማህበር ነው።

"ኮንዶሚኒየም" የሚለው ቃል በአሜሪካና በርከት ባሉ የካናዳ ክልሎች በስፋት ጥቅም ላይ የዋለ የሕግ አግባብ ነው፡፡ በአውስትራሊያ፣ በኒውዝላንድ እና በካናዳዋ የብሪቲሽ ኮሎምቢያ ግዛት ኮንዶሚኒየም የተከፋፈለ ባለቤትነት በመባል ይታወቃል። በኪዩቤክ ደግሞ ኮንዶሚኒየም የሚለው ጥቅል ስም እንዳለ ሆኖ "የተከፋፈለ የጋራ ኃብት" (በፈረንሳይኛ 'ፕሮፐሪቴ ኢንዴቪስ') ብለው ይጠሩታል፡፡ በፈረንሳይ ደግሞ በአብዛኛው እነሱ ሲንዲክ በሚሉት የሚተዳደር ሆኖ ለኮንዶሚኒየም የተሰጠው ስያሜ የጋራ ባለቤትነት ነው፡፡ በአብዛኛው የስፓኒሽ ግዛቶች ደግሞ የተለመደው '*propiedad horizontal*' የሚለው መጠሪያ ነው። በደቡብ አፍሪካ የዚህ ዓይነት ባለቤትነት "sectional title" በመባል ይታወቃል (http://en.wikipedia.org,2013) ፡፡

**ፍላጎት፣ (Demand)** ይህ የምጣኔ ኃብት ጽንሰ-ሃሳብ ሲሆን የሚያንጸባርቀውም ህዝቡ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነባቸውን ቤቶች ብዛት የሚያመለክት ነው፡፡
**ውጤታማ ፍላጎት፣** (Effective Demand) በሰዎች የመክፈል አቅምና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህም ፍላጎት በገቢና ቤተሰቡ ሊከፍል በተዘጋጀው ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

**የሚያስፈልግ** (**Need**)፣ ይህ ቃል ይገባል የሚለውን የሚያንጸባርቅ ሲሆን፣ ይህም የሚወሰነው ማዕከላዊ መንግሥት የሕዝቡን አቅምና ፍላጎት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በሚያስቀምጠው ዝቅተኛ መለኪያዎች/ መስፈርቶች ነው።

**ከቦታ ማስነሳት**፣ (**Eviction**) ባልተፈቀዱ ቦታዎች ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ከፍላጎታቸው ውጭ ከለመዱት አካባቢ ማስነሳት ማለት ነው፡፡

**ተሳትፎ**፣ የሚመለከታቸው አካላት በአንድ አካባቢ ላይ ስለሚደረገው መሻሻል ወይም አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ባለው አጠቃላይ ሂደት ላይ በውሳኔ አሰጣጥና አተገባበር ላይ ያላቸው ተሳትፎ ሲሆን በዚህም በጉዳዩ አካሄድና ውጤት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ማለት ነው፡፡

**እንዲያንሰራሩ ማድረግ**፣ ማለት በአካባቢያችን ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ የሆኑ ኃብቶችን የመጠበቅ፣ የመጠገን፣ እንደገና እንዲያንሰራሩ የማድግን ሂደትን ይይዛል (Miller, 1959)፡፡

**ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር**፣ ማለት ሰዎች ከለመዱትና ሲኖሩበት ከነበረው አካባቢ ወደሌላ አዲስ አካባቢ ማስፈር ነው፡፡

**ሠፈራ**፣ ማለት ወደሌላ ቦታ የተዛወሩ የከተማ ኗሪዎችን በከተሞች ውስጥ በሌላ ቦታ/ቤት እንዲያገኘ ማድረግ ነው፡፡ (**Demeke H, 2008; and** Wikipedia, the free encyclopedia, accessed in Nov. 2013).

**ዋና ዋና ኃሳቦች**

የዓለምአቀፉ የሰብአዊ መብት ዲክላሬሽን አንቀጽ 25 ቤት የማግኘት መብትን ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ እንዲኖር የማድረግ መብት አንድ አካል አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡

ሁሉም ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና አኗኗር ምቹ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ እንዲኖር መብት አለው፡፡ ይህ ሲባል ምግብ፣ ልብስ፣ ቤት፣ ህክምና የማግኘት መብትን ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ይይዛል፡፡ በተጨማሪም ከሥራ ማጣት፣ ከህመም፣ አካል ጉዳተኝነት፣ በፍቺ ጉዳይ፣ በእርጅና እና ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሁኔታዎች ለሚያጋጥሙ ችግሮች ያለውን የማህበራዊ ደህንነት መብት ያጠቃልላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮቬናንት አንቀጽ 11 (1) ቤት የማግኘት መብትን በቂ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ ከመኖር መብት እንደ አንዱ አካል አድርገው ይወስዱታል፡፡

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ ላይ ቤት የማግኘት መብት ለሁሉም እኩል የሆነ ተደርጎ ተቀምጧል፡፡ ይህ ሃሳብ በ1991 በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህል ኮሚቴ አራተኛው አስተያየት ላይ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ አጠቃላይ አስተየየቱም ቤት የማግኘት መብት በህግ ለሁሉም ሰው የተፈቀደ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

እንደ ተባበሩት መንግሥታት የቤቶችና የከተማ ልማት ጊዜያዊ ኮሚቴ ኤክስፐርቶች 'ቤት' የሚለው ቃል መጠለያ ማግኘት ወይም መኖሪያ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ኗሪዎችን ከሌሎች ጎረቤቶቻቸው ጋር የሚያገናኙ አገልግሎቶችንም ይጨምራል፡፡ ሌሎች ደግሞ ቤትን የቤት ህንጻ መኖሩን ብቻ ሳይሆን ለአንድ ግለሰብና ቤተሰቡ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ የመኖሪያ አካባቢን፣ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን፣ ፋሲሊቲዎችን፣ ቁሳቁሶችን የያዘ ነው ይላሉ (Habitat, 1971, as citeed in Demeke, 2008.)፡፡

ብሔራዊ የከተማ ዕቅድ ኢንስቲትዩት (2000) የመኖሪያ ቤትን በዋናነት ለብዙ አገልግሎት የሚውል አንድ ክፍል፣ የግል ወይም የጋራ መጸዳጃና መታጠቢያ ክፍል፣ የግል ወይም የጋራ ማብሰያ ክፍልን፣ የግል ወይም የጋራ የኤሊክትሪክ መብራት፣ የግል ወይም የጋራ የቧንቧ ውሃና በዋና አካባቢዎች 4 ሜትር፣ በአማካይ አካባቢዎች 6 ሜትር እንዲሁም በማስፋፊያ አካባቢዎች 10 ሜትር መንገድ ያለው ነው በማለት ያስቀምጠዋል፡፡

እንደኬንያ ያሉ ሃገራት ደግሞ መኖሪያ አካባቢን እንደሚከተለው ይተረጉሙታል፡፡ ሊሰፋ የሚችል ባለ አራት ክፍል ዋና ቤት (ሁለት መኝታ ክፍል፣ አንድ ማብሰያ ክፍል፣ እና አንድ ሳሎን) ሆኖ ስፋቱ በትንሹ 50 ስኴር ሜትር የሆነ፣ ግድግዳው በተቃጠለ ሸክላ ወይም በብሎኬት ወይም በጭቃ ሆኖ በሲሚንቶ የተገረፈ፣ ወለሉ በሲሚንቶ በጥሩ ሁኔታ ያለቀ፣ ጣራው በቆርቆሮ ወይም በሌላ ንጣፍ የተሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በከተማ ያሉ ሁሉም ቤቶች የውሃ፣ የፍሳሽ፣ የመብራት፣ ተደራሽ መንገድና የዝናብ ውሃ መውረጃ አገልግሎቶች ሊኖሩት ይገባል።

በሌላ በኩል ዚምቧቤ ደግሞ የመኖሪያ ቤቶችን ደረጃ በእያንዳንዱ መኖሪያ ሊኖር የሚገባውን ሁኔታ እንደሚከተለው ታስቀምጣለች፡፡ አስራ ሁለት ኗሪዎች ላሉት እያንዳንዱ የመኖሪያ ክፍል ከአንድ ያላነሰ የውሃ ቧንቧ ወይም የመጸዳጃ ቤቱ ከውሃ ወለድ ማስወገጃ ጋር ያልተያያዘ፣ ስምንት ኗሪዎች ላሉት ከአንድ ያላነሰ የመጸዳጃ ቤት፣ በቂ የሆነ የውሃ አቅርቦት እና ከአንድ ያላነሰ የውሃ ነጥብ እያንዳንዱ አስራ ሁለት ኗሪዎች፣ እነዚህ ሁሉ

በቀላሉ ሊደረስበት በሚችል ቦታ መኖር እንዳለበት ያስቀምጣሉ (Demeke, 2008) ።

"...በቂ መጠለያ ማለት አንገት ማስገቢያ ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ከአንገት ማስገቢያነት በተጨማሪም ከመኖሪያና መሠረታዊ ከሆኑ ፍላጎቶች አንጻር የሚከተሉትን በዋናነት የያዘ እንደሆን ይገለጻል፡፡ እነሱም፣ በቂ የግል ነጻነት፣ በቂ ቦታ፣ ብዙ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ቦታ፣ በቂ ደህንነት፣ የባለቤትነት ነጻነት፣ የቦታው ዘላቂነትና ጥንካሬ፣ በቂ ብርሃን፣ ሙቀትና አየር የሚያገኝ፣ በቂና መሠረታዊ የሆኑ መሠረተ ልማት ያለው ማለትም የውሃ አቅርቦት፣ ንጽህና መጠበቂያ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ፣ ጥራቱን የጠበቀ አካባቢያዊና ከጤናና ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች የተሟሉለት እና በቂና ተደራሽ የሆነ አካባቢ ሲሆኑ፣ ሁሉም በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገኙ የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው ያስገነዝባል" (The Istanbul Declaration and The Habitat Agenda, UNCHS, 1997: 35, በ Demeke, 2008 እንደተጠቀሰው) ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች እንደምንረዳው የመኖሪያ ቤት የምንለው ኃሳብ የመኖሪያ አካባቢ ሆኖ ከመኖሪያነት በተጨማሪ አካባቢው ያለበትን ከባቢያዊ አቀማመጥ፣ የአካባቢውን ኗሪዎችና ማህበረሰቡን፣ የህዝብ አገልግሎቶችን፣ ህጎች፣ ደንቦችና ስርዓቶች፣ ለመኖሪያ ምቹ መሆኑና ተደራሽነቱ፣ መብትና ኃላፊነቶችና ትርፉን ኪሳራን ጨምሮ የሚይዝ ነው፡፡

- በተጨማሪም ቤቶች የሚለው ጽንሰሃሳብ የሚከተሉትን ይይዛል፣
- የቤቱ አካላዊ ቅርጽ፣ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችና ቦታው፣
- የህንጻ ጥበብ፣ ቁሳቁስና የሙሥራት ክህሎት፣
- ህንጻው በተጠቃሚው ምርታማነት እና የምጣኔ ሀብት ላይ የሚኖረው ዋጋና ተጽዕኖ፣
- ከህግ ጋር በተያያዘ የት እና እንዴት መሰራት እንዳለበት የሚያሳይ፣ እና
- ለኢንቨስትመንትና ለትርፍ ማግኛነት ሊያገለግሉ የሚችሉባቸው መንገዶች እና በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኗሪዎች የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱት የቤቶች ሁኔታዎች ትርጉምና ኃሳቦች እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሃገራት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ላይሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም ውድድር በበዛበት ሁኔታ ክፍያውን ፈጽመው የተጠቀሰውን ዓይነት የቤት ባለቤት ሊሆኑ የማይችሉ በርካት ዜጎች ያሉ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ ማለት በአብዛኛው የተሰሩ የመኖሪያ ቤቶች ከላይ

በባለሙያዎች እንደተጠቀሰው ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች አሟልተው የተሠሩ አይደሉም፡፡ ይልቅስ የሚሠሩ ቤቶች የባለቤቶችን የኑሮ ደረጃና የአካባቢውን ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የቤቶች ትርጉምና ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃዎች በሁሉም ሃገር ተግባራዊ ማድረግ ሊያስቸግር ይችላል፡፡

በሁሉም ዘንድ ግን መስማማት ላይ የሚያደርስ አንድ እውነታ አለ፡፡ ይሄውም ቤት ለሁሉም ሰው የሚያስፈልግና የኑሮ ሁኔታ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ቤት በሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ላይ ትልቅ አሻራ የሚያስቀምጥ ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ቤቶች የሚለሙበትና ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሸጋገሩበት መንገድ ደግሞ በአጠቃላይ ሊደረስበት በሚፈለገው የልማት ግብ፣ የአካባቢ ጥበቃና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን ከመከላከል ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው፡፡ የቤቶች አሠራርና የአካባቢ ሁኔታም የኗሪዎችን እሴትና ባህል የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ የቤቶች ግንባታ በሥራ ፈጠራ ረገድ ያለው አስተዋጽኦ በአለም አቀፍ ደረጃም የታወቀ ነው፡፡

## 1.5 *በዓለም ደረጃ የከተማ ቤቶች ችግሮች፣ ከተሜነትና ድህነት*

ቤት ለማንኛውም ሰው ለመኖር መሠረታዊ የሆነ ፍላጎት ቢሆንም የሚሰሩ ቤቶች ዓይነት እና ደረጃ ግን በሃገራት የኢኮኖሚ ደረጃ ይወሰናል፡፡ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገራት ከቤቶች ጋር በተያያዘ በዋናነት ሦስት ፈታኝ ሁኔታዎች አሉባቸው፡፡ እነሱም፣ በሚያስደነግጥ ሁኔታ እያደገ ያለው የህዝብ ቁጥር፣ ድህነትና እያደገ ያለው ወደከተማነት የመለወጥ ሁኔታ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ በእስያ፣ አፍሪካና ላቲን አሜሪካ የሚገኙ በርካታ ኗሪዎች ወይ ቤት አልባ ናቸው ወይም በቂ የቤት አገልግሎት እያገኙ አይደሉም፡፡ ይህ ሁኔታም በሰዎቹ የኑሮ ሁኔታና በአጠቃላይ የሀገራቱ የዕድገት ደረጃ ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

በፍጥነት እያደገ ያለው ወደከተሜነት የመለወጥ ሁኔታ ያመጣቸው የቤት እጥረትና ደካማ የቤቶች ሁኔታ ሕይወትን በከፍተኛ ደረጃ የሚፈታተን ጉዳይ ነው፡፡ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኗሪዎች በዝቅተኛ ዋጋ ቤት ለማቅረብ ያለመቻልና ቦታ የማግኘት ችግሮች መውጫ በሌለው ሁኔታ የደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ያልሆኑ ቤቶች እንዲበዙ አድርጓል፡፡ የምዕተ ዓመቱ ዲክላሬሽን (2000) እና በ2005 የተከለሰው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ቁጥር 7 ኢላማ 11 እንደሚያስቀምጠው፣ 100 ሚሊዮን ለሚሆኑ በደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ባልሆኑ ቤቶች የሚኖሩ ኗሪዎችን

የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ሌሎች አዳዲስ ተመሳሳይ መኖሪያዎች እንዳይሰሩ አማራጮችን በማቅረብና የፖሊሲ ምላሽ በመስጠት ለማከናወን እስከ 2020 ዕቅድ ተይዟል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የሰዎች አሰፋፈር ማዕከል በመጋቢት 1996 ባወጣው ዓለማቀፋዊ የሰዎች አሰፋፈር ሪፖርት መሠረት በዓለማችን 500 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ቤት አልባ ወይም በቂ የሆነ ቤት የሌላቸው እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ የሃቢታትና የተባበሩት መንግሥታት የሰዎች አሰፋፈር ኮንፈረንስ ሴክሬታሪ ጀነራል የሆኑት ዶ/ር ዋሊ ኒዶው እንደሚሉት "በሚቀጥለው ምዕተ ዓመት በዓለማችን የሚጋጥሙ አንገብጋቢ የሆኑ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የምናስተውለው በከተሞች ይሆናል፡፡" ቤት አልባነትና ዝቅተኛ የሆነ የቤቶች ሁኔታ የእነዚህ ችግሮች ሁሉ መነሻ ነው፡፡ ከተሞችም እዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በቂ ሃብት አላቸው ምክንያቱም በአብዛኛው ባልለሙ ሃገራት ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ውስጥ ከ 50 እስከ 80 ፐርሰንቱን የሚሸፍኑት ከተሞች ስለሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ከተሞችን ወደኋላ እያስቀራቸው ያለው ነገር ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚውለው የከተማ ሃብትና ብክነት ነው፡፡

በከተሞች እያጋጠመ ያለው ችግርም በፍጥነት እያደገ ባለው የህዝብ ዕድገት ምክንያት እየተባባሰ ይገኛል፡፡ ይህ የከተሞች እድገት በ1995 ወደ 2.4 ቢሊዮን የነበረው በ2025 ደግሞ ወደ 5 ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን የከተሞች የህዝብ ብዛት ዕድገት በገጠር ካለው የህዝብ እድገት ጋር ሲነጻጸር በ2.3 እጅ የበለጠ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮችና ፈታኝ ሁኔታዎች እያሉባቸውም ከተሞች የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አከባቢያዊ ዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተሮችና ለድሆች መልካም ዕድሎች ፈጣሪ መሆናቸውን ይቀጥላሉ (Habitat, 1996)፡፡

ስለከተሞች ስናስብ በቅድሚያ የሚመጡት ቤት አልባ ሰዎች ሲሆኑ፣ እነዚህም በከተሞች ያለውን የቤቶች ችግር የሚያሳዩ ቀዳሚ አመልካቾች መሆናቸው ትክክል ነው፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም ሁኔታ ፊት ለፊት የሚታይ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ የናረ የቤቶች ዋጋ የመገናኛ ብዙሃን መነጋገሪያ እንደሆነና የወለድ ምጣኔውም ለውጥ የሌሎች በርካታ አካላትን ቀልብ የሳቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አሁን ያለው ዝቅተኛ የቤቶች ሁኔታና ችግር በሚታሰበው ደረጃ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ያልታወቀ ቢሆንም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎችን ችግሮችን፣ በብድር ምክንያት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያሉ የቤት ባለቤቶችን ሁኔታና በሕዝብ አገልግሎት ዘርፉ ቤቶችን ለማደስ የተከማቸ ያልተሰራ ሥራን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ መሠረታዊ የሆነው የመጠለያ ፍላጎት በቤቶች ጥራትና ብዛት ረገድ ያለውን ችግር ግልጽ ያደርገዋል፡፡ እንደተፈለገው ተዘዋውሮ ሊታይ የሚችል በቂ ቤትና ደረጃውን የጠበቀ ቤት አለን ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ በዚህ ረገድ ያለውን የማህበራዊና የባህል ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ ቢሆንም ብዛትና ጥራት የቤት ችግሮች ዋነኛ ክፍሎች ናቸው (Malpass and Murie, 1990) ፡፡

ከማህበራዊ ጉዳዮች አንጻር በድህነት፣ በኑሮ አለመመጣጠን እና ደረጃውን ባልጠበቁ ቤቶች መካከል ስላለው ግንኙት ይታወቃል፣ ጥናትም ተደርጎበታል፡፡ ሌሎች ማህበራዊ ልዩነቶች ማለትም ጾታ፣ ዕድሜ እና አካል ጉዳተኛነት ከቤቶች ፖሊሲ በተለይም ለቤት ሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ተደራሽ ከመሆን፣ የንብረት ባለቤትነት መብት ባህሪና ክፍፍል፣ የቤቶች ዲዛይንና መሥሪያ ቦታና መሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ ግንኙነቱም የሁለት ወገን ነው፡፡ በቂ የሆነ የቤቶች አቅርቦት ያለመኖርና ለቤቶች ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በእኩል ሁኔታ ያለማግኘት በሰዎች መካከል በማህበራዊ አኗኗራቸው ምክንያት ያለውን ልዩነት ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በማህበራዊ ዋስትና ረገድ የተጎዱ ማህበረሰቦችን በተመለከተ እየተከናወነ ያለው ሁኔታ እነዚህ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱና በቤቶች ረገድ ያላቸውን ልዩ ፍላጎት እንዲሟላ ለማድረግ ተችሏል፡፡ የማህበራዊ ችግሮች መጨመር ለተጎዱ ወገኖች ቤቶችን የማዳረስ ሥራን አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ደረጃውን ያልጠበቀ የቤቶች ሁኔታ መኖር በከተሞች ውስጥ ረብሻ፣ ወንጀል፣ መገለልና ሰላም ማጣት እንዲከሰቱ ከማድረግ አንጻር አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሜክሲኮ ከተማ ከህግ ውጭ የሆነ የመሬት ሽያጭ ደላሎች መብዛት እንደ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ "በቂ" የቤቶች አቅርቦት የሚለውን ሁኔታ በዓለም ደረጃ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ማየት አስቸጋሪ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ "በቂ" የሚለው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ሊወሰንም ይገባዋል (UN-HABITAT, 2008)፡፡

## 1.6 የአዲስ አበባ የምሥረታ ታሪክ

በህዳር 1886 እ.አ.አ አጼ ሚኒሊክ በሃገሪቱ ሩቅ ክፍል በነበሩበት ወቅት ባለቤታቸው ከነበሩበት ከፍታ ሥፍራ አዲስ አበባ ወደምትገኝበት ቦታ መጥተው ሠፈሩ፡፡ እቴጌ ጣይቱ የእንጦጦን ቤተ-መንግሥት በመተው አሁን ፍልውሃ ያለበት ቦታ የሄዱትም በእንጦጦ አካባቢ በነበረው ቀዝቃዛ አየርና ምቹ ያልሆነ ሁኔታ የተነሳ እንደሆነ ይነገራል (Bahru, 1991)፡፡

አዲስ አበባ ተስማሚ ከሆነው የአየር ሁኔታዋ በተጨማሪ ለመስፋፋት የነበራት ምቹ ሁኔታ ጥሩ ነበር፡፡ በእንጦጦ የነበረው ሁኔታ በተወሰነ ቦታ ላይ የታጠረና አጼ ሚኒሊክ የሚያስቧትን ዓይነት ከተማ ለመመሥረትና ለመስፋፋትም ብዙም እድል የሌለው ነበር፡፡ በተጨማሪም የእንጦጦ ተራራ ለውሃ አቅርቦት እና ለንግድ ምቹ አልነበረም፡፡ ሚኒሊክም ከሄዱበት ሲመለሱ በአዲሱ ቦታ በጣም ስለተሳቡ በ1892 የሰፈሩበትን ቦታ 'አዲስ አበባ' ብለው የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ከተማና መቀመጫ እንድትሆን ወሰኑ (ibid)፡፡

ፎቶ1፣ በ1897 የነበረው የአዲስ አበባ ገጽታና የቤቶች ዓይነት



ምንጭ፣ Demeke, 2012

በአዲስ አበባ የመጀመሪያዎቹ የምስረታ ዓመታት በፍልውሃ አካባቢ የነበሩት ቤቶች በዋናነት የድንኳን ቤቶች ነበሩ፡፡ ይህም ለሁሉም ማለትም ለንጉሱ፣ ለባላባቶች፣ አሽከሮችና ወታደሮች ጭምር ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰፋፈርም ቀስ በቀስ በተለያዩ ዕውቅ ሰዎች እየተሰየሙ ሠፈር እየተባሉ በተጠሩ አካባቢዎች እየተስፋፉ ሄዷል፡፡ ቀስ በቀስም እነዚህ ድንኳኖች በጭቃና በእንጨት ቤቶች እየተተኩ ሄደዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ የአዲስ አበባ የቤቶች ሁኔታ እስከ አጼ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ የቀጠለ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም የየራሱን ቤት ቢሰራም በሌሎች እየታገዘ ነበር።

**ፎቶ 2፣ በጣልያን ወረራ ወቅት በተወሰኑ የአዲስ አበባ ክፍሎች በገነት ሆቴልና በካምቦሎጆ የነበሩ ቤቶች ገጽታ**




*ምንጭ፡* Demeke, 2012

## አዲሲቷ አዲስ አበባ፣ እያደገ የመጣ ህዝብና የከተማ ክልል

**አዲስ አበባ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና ከተማና የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ በመሆኗ ምክንያት የአፍሪካ የዲፕሎማቲክ መዲና የሆነች ከተማ ናት፡፡ በዓለም ደረጃ በፍጥነት እያደጉ ከሚገኙ ከተሞች ውስጥም አንዷ ናት፡፡ እ.አ.አ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባ የህዝብ ብዛት በሦስት እጥፍ አድጓል (ከታች ያለውን ምስል ይመልከቱ)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የከተማው ስፋትም በጣም እያደገ ይገኛል፡፡ በ1973 እ.አ.አ የተነሳው የጎግል የምድር የሳተላይት ፎቶ እንደሚያሳየው የከተማ ቦታ በ12 እጥፍ ያህል ተስፋፍቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የከተማ ቦታው መስፋፋት ካለው የህዝብ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር በአራት እጥፍ ይበልጣል (ምስል 2)** (UN Habitat, 2008)፡፡

ምስል 1፣ (በስተግራ) የአዲስ አበባ የህዝብ ዕድገት ከ1950 - 2025
ፎቶ 3፣ (በስተቀኝ) ሰዎች በሚበዙበት ሰዓት በአንድ የአዲስ አበባ መንገድ ያለ ሁኔታ






ምስል 2፣ የአዲስ አበባ የከተማ ቦታ ዝግመታዊ ለውጥ፣ ከ1973 እስከ 2010




*ምንጭ፣* UN Habitat, 2008

## ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ

አዲስ አበባ ከባህር ወለል በላይ በ7,546 ጫማ (2,300 ሜትር) ከፍታ ላይ የምትገኝ ሳር የበዛባት ከተማ ስትሆን፣ በ9° 1’ 48” ሰሜን በ38° 44’ 24” ምስራቅ ትገኛለች። ከተማዋ ከእንጦጦ ተራራ ግርጌ ትገኛለች፡፡ በደቡብ

በቦሌ አካባቢ ከሚገኘውና ከባህር ወለል በላይ 2326 ሜትር (7631 ጫማ) ከሆነው የከተማዋ ዝቅተኛ ሥፍራ ተነስቶ በሰሜን 3000 ሜትር (9800 ጫማ) እስከ እንጦጦ ተራራ ይዘልቃል፡፡

**የአየር ሁኔታ**

አዲስ አበባ የሰብ ትሮፒካል ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚታየው የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባት ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ እንደ ቦታው ከፍታና የንፋስ አካሄድ በአማካይ እስከ 10 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ልዩነት ያላቸው ቦታዎች ስላሏት የደጋና የወይናደጋ የአየር ሁኔታን አጣምራ ትይዛለች፡፡ ከተማዋ በከፍተኛ ቦታ ላይ መገኘት ዓመቱን ሙሉ ተመጣጣኝ የሆነ የአየር ሁኔታ እንዲኖራት አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ለምድር ወገብ ያላት ቅርበት የአየር ሁኔታው ከወር እስከ ወር የተመጣጠነ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከህዳር አጋማሽ እስከ ጥር ድረስ ያለው የበጋ ወራት ነው፡፡ የከፍተኛ ቦታዎች የአየር ንብረት ደረቃማ ሲሆን አዲስ አበባም ይሄው ዓይነት የአየር ንብረት ያላት ናት፡፡ በነዚህ ደረቃማ የበጋ ወራት በቀን ያለው ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 23 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ አይሄድም፡፡ በማታ የሚኖረው የሙቀት መጠን ደግሞ በጣም ቀዝቃዛ ሊሆን ይችላል፡፡ ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ያለው ጊዜ የመኸር ዝናብ የሚዘንብበት ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት የሚኖረው የቀንና የማታ የሙቀት መጠን በዓመቱ ውስጥ ባሉት ሌሎች ወራት እንደሚኖረው የጎላ ልዩነት የላቸውም፡፡ በነዚህ ጊዜያት የሚኖረው ዝቅተኛው የሙቀት መጠን ከ 10 እስከ 15 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በእነዚህ ጊዜያት ከተማዋ ምቹ የሆነ የሙቀት መጠንና በቂ ዝናብ ታገኛለች፡፡ ረዥሙና ዝናባማ የሆነው ወቅት ከሰኔ እስከ መስከረም አጋማሽ ያለው ጊዜ ነው፡፡ ይህ ወቅት የክረምት ወቅት ቢሆንም በተደጋጋሚ በሚዘንበው መጠኑ የበዛ ዝናብ፣ ደመናና በረዶ ከሌላው ጊዜ ያጠረ የፀሐይ ብርሃን ስለሚኖር የአየር ሁኔታው ከሌላው ጊዜ የቀዘቀዘ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ቀንና ሌሊቱ ጨለማ፣ ቀዝቃዛና እርጥበት የበዛባቸው ናቸው፡፡ በመቀጠልም የበጋውና የክረምቱን ወቅት የሚያገናኘው የጸደይ ወቅት ነው፡፡

**የከተማው ዕንብርት**

በብዙ አዳጊ ሃገራት እንደሚታየው በአብዛኛው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የተወሰኑ የግል ህንጻዎች የሚገኙበት የከተማ ዕንብርት ይኖራል፡፤ እንዲህ ዓይነቱ አካባቢ ብዙ ጊዜ ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩበትና ያረጁ ቤቶች የሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ በአዲስ አበባ በእነዚህ

አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ በሌሎች አካባቢዎች ከሚኖረው ህዝብ በብዙ እጥፍ ይበልጣል፡፡ (ቀጣይ ፎቶዎችን ይመልከቱ)

ፎቶ 4፣ በከተማዋ ዕምብርት ያለ የተደበላለቁ ቤቶች ሁኔታ




*ምንጭ*፡ Author's collections

ዋና ዋና የመንግስት ቢሮዎችና ባህላዊ የሆኑ ቦታዎችም በዚህ የከተማዋ ዕንብርት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ፓርላማ፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ብሔራዊ ሙዚየም፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለስላሴ

የተቀበሩበት የቅድስት ስላሴ ካቴድራል፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያንና ትልቁ መስጊድ በዚሁ አካባቢ ይገኛሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዳርቻ ያሉ አካባቢዎች ላይ የማስፋፋት ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተካሄደ ነው፡፡ እንዲያውም አዲስ አበባ በመሃል ከተማዋ እራሷን እያደሰች ይመስላል፡፡ ከማሃል ከተማዋ በሶስት አቅጣጫዎች ትላልቅ ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በምስል 3 እንደተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ክልል ወሰን በሚገርም ሁኔታ እየሰፋ በ1997 ዓ.ም 530 ስኩር ኪሎሜትር ሲሆን ይፋዊ የሆነው የከተማው ዞን ግን 290 ስኩር ኪሎሜትር ነው። አሁን ያለው የከተማዋ ስፋት 540 ስኩር ኪሎሜትር ይገመታል። ሆኖም ይፋዊ የሆነው የከተማው ዞን 300 ስኩር ኪሎሜትር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

ምስል 3፣ የከተማ መስፋፋት ዝንባሌ በአዲስ አበባ (ከ1886-1997)



*ምንጭ፣* Dominique C. & Daniel S. 2003

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ አዳዲስ የንግድ ህንጻዎች፣ የመንግሥት መስሪያ ቤት ህንጻዎች፣ የህዝብና የግል ኮንዶሚኒየሞች እንዲሁም በከተማዋ ዳርቻዎች በርካታ የግል መኖሪያ ቤቶች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

በምዕራብ በዋናነት በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ እስከ አምስት ፎቅ ድረስ የሚደርሱ በርካታ ኮንዶሚኒየሞች እየተገነቡ ይገኛል፡፡

## 2. የቤቶች ሁኔታ

### 2.1 *ዳራ*

አዲስ አበባ ከሃገሪቱ የከተማ ነዋሪ 26% የያዘች ከተማ ናት፡፡ በየዓመቱ 120,000 አዳዲስ ነዋሪዎች ወደከተማዋ ይቀላቀላሉ፡፡ ይህ መጠኑ የሰፋና የማያቋርጥ ፍልሰትም በከተማዋ ያለውን የቤቶች ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያባባሰው ይገኛል፡፡ ምክንያቱም በከተማዋ ያለው የቤቶች ሁኔታ ያለውን የነዋሪዎች ዕድገት የመሸከም አቅሙ አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በተለይ አንቀጽ 1 እና 7 ን ከማሳካት አኳያ መንግሥት የተለያዩ ህጎች፣ ደንቦችና ስትራቴጂዎችን በማውጣት በሃገሪቱ ያለውን የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ቁሳዊ ሁኔታን ለማስተካከል ጥረቶች እያደረገ ይገኛል፡፡

ሁሉን አቀፍ የሆነ ልማትን በከተሞች ለማምጣትና የተመጣጠነና የተፋጠነ የከተሞች እድገት እንዲመጣ መንግሥት በ2005 እ.አ.አ የከተማ ልማት ፖሊሲን በማውጣት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህም ፖሊሲ በሂደት የቤቶች ልማት ፖሊሲ (ቤልፖ) እ.አ.አ በ2006 እንዲወጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይህም ፖሊሲ በዋናነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙና በደቀቁ ሠፈሮች ለሚኖሩ ሰዎች ምቹና በቂ የመኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው ለማድረግና ሥራን በመፍጠር ኢኮኖሚያቸው እንዲያድግ ታስቦ እየተከናወነ የሚገኝ ተግባር ነው (UN HABITAT, 2008)፡፡

በፍጥነት በሚያድገው የህዝብ ዕድገትና እያደገ በመጣው የከተሜነት ሁኔታ ምክንያት የቤቶች ጉዳይ ለአዲስ አበባ ከተማ አሁንም ሆነ ከዚህ በፊት ፈታኝ ከሚባሉ ጉዳዮች ዋነኛው ነው፡፡ በተለይ የከተማዋን 80% ለሚይዙ በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ኗሪዎቿ ስር የሰደደ ችግር ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ የከተማዋን የቤት ፍላጎት ማሟላት ውስብስብ ጉዳይ አድርጎታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ 70% የሚሆነው ኗሪ በደቀቁ፣ ለሰው ልጅ መኖሪያነት ምቹ ባልሆኑና ለጤና አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች ይኖራል (ibid)፡፡

በተመሳሳይ በከተማዋ ያለው የሥራ አጥነት ደረጃ 40% ነው፡፡ የከተማዋ ኢኮኖሚ ደካማ በመሆኑ በፍጥነት ቁጥሩ እያደገ ለመጣው የከተማዋ ኗሪ ያለውን የቤቶች ፍላጎት ለማሟላት፣ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን በሚፈለገው ሁኔታ ለማሟላትና የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚከናወኑ ሥራዎች አዳጋች አድርጓቸዋል፡፡ አሁን ባለው ገበያ በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው ቤት ለብዙ ኗሪዎች በማቅረብ የቤቶችን ፍላጎት ለሚሟላት የሚያስችል አይደለም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መንግሥት እነዚህን ከቤቶች

አቅርቦት ጋር የተያያዙ ፈታኝ ሁኔታዎች በመገንዘብና ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ ካለው ፍላጎትና ቁርጠኝነት በመነሳት የተለያዩ አዳዲስ መንገዶችን በመቀየስ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ እነዚህን ስትራቴጂዎች በዋናነት በዝቅተኛና በመካከለኛ የኑሮ ሁኔታ ላሉ ሰዎች ቤቶችን ለማዳረስ በ2004 የተቀየሰው የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡

በተመጣጣኝ ዋጋ፣ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች ያሉትና የተሟላ ቤት የማግኘት ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህም ፍላጎት የመነጨው በአንድ በኩል አሁን ካለው የቤቶች እጥረት የተነሳ በሌላ በኩል ደግሞ በቀበሌ ሥር ያሉት የመንግሥት ቤቶች እርጅናና ለመጠገን አስቸጋሪ ከመሆቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ውጤታማ ፍላጎት አነስተኛ ነው፡፡ የኗሪዎችን ገቢና ወጭ በሚመለከት፣ የቁጠባ ባሕልና ለቤቶችና ለሌሎች ጉዳዮች ቅድሚያ ከመስጠት ጋር በተያያዘ በቂና አስተማማኝ መረጃ ባለመኖሩ ውጤታማ ፍላጎትን ለመለካት አስቸጋሪ ቢሆንም አብዛኛው የከተማዋ ኗሪ በግል ሴክተሩ የሚቀርቡ ቤቶችን ለመግዛት አቅም እንደሌለው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልገው (Need) በተመጣጣኝ ዋጋ ቤቶችን ማቅረብ ነው፡፡

**የባለቤትነት ሁኔታ**

*ሠንጠረዥ 1፣ በአዲስ አበባ የቤቶች የባለቤትነት ሁኔታ*

| ተ.ቁ | ባለቤት | 1994 እ.አ.አ | 2007 እ.አ.አ |
|---|---|---|---|
| 1. | ከግለሰቦች በኪራይ የተያዙ | 16.70% | 35.36% |
| 2. | በባለቤቶች የተያዙ | 34.42% | 32.62% |
| 3. | ከቀበሌ በኪራይ የተያዙ | 37.92% | 23.63% |
| 4. | ከኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ በኪራይ የተያዙ | 2.48% | 1.81% |
| 5. | ከሌሎች ድርጅቶች በኪራይ የተያዙ | | |
| 6. | ከኪራይ ነጻ የሆኑና በሌላ ሁኔታ የተያዙ | 8.48% | 6.58% |
| | ጠቅላላ የቤቶች ብዛት | 100% (347,742) | 100% (628,986) |

*ምንጭ፡* Elias Yitbarek. et al, 2011

ከባለቤትነት ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ቤቶች ሁለት ዓይነት ማለትም የመንግሥትና የግል ሲሆኑ በመንግሥት ባለቤትነት የሚገኙት ከአጠቃላዩ 32.02% ሲይዙ፣ በግል የተያዙት ደግሞ 67.98% ናቸው (ሠንጠረዥ 1ን

ይመልከቱ)፡፡ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በ2007 ባወጣው መረጃ መሠረት በግል ባለቤትነት ከሚገኙት 67% ቤቶች ውስጥ 35.36% በኪራይ ያሉ ሲሆን ቀሪዎቹ 32.62% ደግሞ በባለቤቶቹ የተያዙ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግሥት ከተያዙት 32.02% ቤቶች ውስጥ 23.63%ቱ የቀበሌ ቤቶች፣ 1.8% በመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የሚከራዩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 6.58% ደግሞ ከኪራይ ነጻ የሆኑ ናቸው፡፡

**ህጋዊ ሁኔታና የመሃል ከተማ የቤቶች ሁኔታ**

የቤቶችን ህጋዊ ሁኔታ ስናይ በከተማዋ ዳርቻ ያለው ህጋዊ ያልሆኑ ቤቶች መስፋፋት እንዳለ ሆኖ ወደ 60,000 የሚሆኑ ቤቶች (በአጠቃላይ ካሉ ቤቶች 20% የሚሆኑት) ወደ 300,000 የሚሆኑ ሰዎችን ያየዙ ቁመታቸው አጭርና ምቹ ያልሆኑ ቤቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በከተማዋ የልማት ዕቅድ ሪፖርት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ከ18% (42,840) በላይ የሚሆኑት የከተማዋ ቤቶች ያረጁ፣ ለመውደቅ የደረሱና ጥገናና መተካትን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ሪፖርቱ በተጨማሪም የተጨናነቀውን የከተማዋን ክፍል ማስተካከል የሚቻለው የታፈነውን በመበተን (de-densification) እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ይህ የተጨናነቀውን የከተማዋን ክፍል ጭንቅንቅ ለመፍታት ወደ 50,300 አዳዲስ ቤቶችን መገንባትን ይጠይቃል (Demeke H. 2012) ፡፡

**የቤቶች የፋይናንስ ምንጭ**

ለቤቶች ግንባታ በዋናነት ብድር የሚሰጠው ተቋም የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ነው፡፡ ይህ ባንክ የቤቶችና ቁጠባ ባንክ በመባል በአነስተኛ የወለድ ምጣኔ ማለትም ለማህበራት በ4.5 % ለግለሰቦች ደግሞ በ7.5% ለቤቶች ግንባታ ብድር ይሰጥ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ የወለድ ምጣኔው 16% በመድረሱ ለቤቶች የሚወሰድን ብድር በማያበረታታ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የወለድ ምጣኔ ማደግ ዋናው ምክንያት በመንግሥት በኩል በቤቶች ዘርፍ በተለይ ለግል ቤት ግንባታ ይሰጥ የነበረውን እገዛ ወይም ማበረታቻ ለማስቀረት የተወሰደ እርምጃ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በከተማዋ ውስጥ ከብድር ውጭ የራሳቸው የገቢ ምንጭ በሌላቸው ነዋሪዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ይሁን እንጂ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ለቤት ሥራ ፋይናንስ የሚሰጥ አዲስ ድርጅት የተቋቋመ ቢሆንም ራሱን በማደራጀትና ለስራ የሚያስፈልገውን ማዕቀፍ በማዘጋጀት፣ የሥራውን ስፋትና ኃላፊነቱን በማጥራት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉና ተደራጅተው ለኮንዶሚኒየም የቤት ስራ የሚያገለግል የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ለሚያቀርቡ ግን በቂ የሆነ እገዛ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሰዎች በሚያከናውኑት ሥራ ምክንያት

የሚያገኙትን ገቢ የቤት ዕጣ ሲወጣላቸው የቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም የሚያግዛቸው ቢሆን እንደ ቤት ብድር ለመውሰድ ግን ያስቸግራል፡፡

## 2.2 የቤቶች ችግር

በአሁኑ ጊዜ በከተማይቱ ከቤት ጋር የተያያዙ ችግሮች በሦስት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነሱም፡

1. የቤት እጥረት፣
2. ዝቅተኛ የቤቶች የጥራት ሁኔታ፣ እና
3. የቤት አልባነት ናቸው፡፡

**የቤት እጥረት፣** በ2011 የአዲስ አበባ ከተማ የልማት ዕቅድ የአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት መሠረት እያደገ የመጣውን የህዝብ ብዛት ለመሸከም እንዲቻል ሲንከባለል የመጣ የ172,400 እና ተጨማሪ 276,400 ቤቶች እጥረት ይታይበታል፡፡ የቤቶች እጥረትም በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያትና ወደከተማት በፍጥነት ከመለወጥ ጋር ተያይዞ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይገኛል፡፡

እየተንከባለለ የመጣው የቤቶች ፍላጎት ሊከሰት የቻለው በቂ የሆነ መሬት ባለመኖሩ፣ እየጨመረ የመጣ የኪራይ ገቢ፣ እያደገ የመጣው የካፒታል እድገት ታክስ (capital gain tax)፣ እንዲሁም በመንግስት በኩል ለቤቶች ሥራ በቂ የሆነ ሃብት ካለመኖር ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ሲሆን፣ ይህንንም እየተንከባለለ የመጣውን የቤቶች ፍላጎት ማሟላት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ከ15 ዓመታት በፊት ቢሆንም በ1996 በተደረገው የቤት ለቤት ጥናት መሠረት የአዲስ አበባ የየዓመቱ የቤቶች ፍላጎት በአማካይ በየዓመቱ 22,000 ቤቶች እንደሚሆን ተገምቶ ነበር፡፡ በከተማዋ አዳዲስ ቤቶችን የመገንባቱ ሁኔታ እየቀነሰ በመሆኑ አሁን ያለው የቤቶች እጥረት እንደሚጨምር ይገመታል፡፡

ከ2003 ጀምሮ በከተማዋ ያለውን የቤቶች እጥረት ለማቃለል የከተማው መንግሥት የኮንዶሚኒየም የቤቶች ልማትን የጀመረ ቢሆንም በፕሮግራም የተመዘገቡ ደሪዎች ብዛት 453,000 ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የነበረው ዕቅድ በየዓመቱ በ1.2 ቢሊዮን ብር 50,000 ቤቶች ለመገንባት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ፕሮግራሙ ምላሽ የሰጠው 111,000 ለሚሆኑ ተጠቃሚዎች ነበር፡፡ ቀሪዎቹ 300,000 ደሪዎች ዘጠኝ ዓመታትን እንዲጠብቁ ተገድደዋል፡፡

**የቤቶች እርጅና፣** ከቤቶች ማርጀት፣ ጥራት መውረድና ምቹ ያልሆነ አካባቢ ጋር በተያያዘ የከተማዋ 80 ፐርሰንት የደቀቁና ለኑሮ ምቹነት የሌላቸው

ሲሆኑ ይህም ከከተማዋ አጠቃላይ ቤቶች 60 ፐርሰንቱን ይይዛል፡፡ በዚህም የተነሳ የቤቶች እጥረት ለመቀነስ ለኗሪዎቿ በቂ የሆነ፣ ለመክፈል የሚችሉትና ለመኖር ምቹ የሆነ ቤት ማቅረብ የቤቶች ልማት ስትራተጂ ቀዳሚ ዓላማ ነው፡፡

በቀበሌ የተያዙ ቤቶች በቂ የሆነ ጥገና ባለማግኘታቸው ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ቤቶች ወርሃዊ የኪራይ ዋጋ ከሚያስፈልጋቸው የጥገና ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ በመሆኑ የቤቶችን ጥገና አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ቤቶች ወርሃዊ የኪራይ መጠናቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማዋ ኗሪዎች የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡ በከተማዋ ያለው አማካይ ወርሃዊ የኪራይ መጠን 40.98 ብር ሲሆን 76.87% የሚሆኑ የኪራይ ቤቶች ከ50 ብር በታች የተከራዩ ናቸው፡፡ በከተማዋ ያለው ይህን የመሰለው የኪራይ ሁኔታ እንዲሁም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የከተማ ኗሪዎች የየራሳቸውን ቤት እንዲገነቡ የሚያበረታታ ፖሊሲ ባለመኖሩ ጭምር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 70% የሚሆኑት የኪራይ ቤቶች አንድ ክፍል ብቻ ያላቸው ሲሆን በአንድ ሰው በአማካይ አምስት ስኴር ሜትር ወይም በአንድ ክፍል አራት ሰዎች ይኖሩበታል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም አብዛኞቹ ያረጁ ቤቶች ናቸው፡፡

ፎቶ 5፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ ያረጁ ቤቶች ምሳሌዎች







*ምንጭ፣* AAHDPO, 2012; Berhanu & Mesfin, 2012; and Ethio-Reporter website

በተመሳሳይ ሁኔታ የመንገድ ተደራሽነት፣ ውሃ፣ የፍሳሽ ማስወገጃና የሳኒቴሽን ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህም መሠረታዊ የልማት ሥራን ይጠይቃል። አሁን ካሉት ቤቶች ውስጥ 71.4 ፐርሰንት የቧንቧ ውሃ አቅርቦት ሲኖራቸው ከዚህ ውስጥ 22 ፐርሰንቱ የራሳቸው የቧንቧ ውሃ አላቸው። በተመሳሳይ 67.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ቤቶች የመጸዳጃ ቤቶች አቅርቦቶች አሏቸው።

ቤት አልባነት፣ በአዲስ አበባ ከተማ በዋናነት ያለውን የቤቶች እጥረት፣ የቤቶች ደረጃ መውረድና የቤቶች እርጅና ያን ያህል የገዘፈ አይሆንም እንጂ ከድሃም ደሃ በሆኑት፣ ወላጅ አልባ በሆኑትና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በተጎዱትም ቤት አልባነት የጎላ ችግር ነው፡፡ እነዚህ ቤት አልባዎች በመንገዶች ዳርቻ፣ በፕላስቲክ መጠለያዎች፣ በጊዜያዊ መጠለያዎች፣ በአውቶቡስ ፌርማታዎች፣ በቤተክርስቲያን አካባቢዎችና ሌሎች ጥጎች ይኖራሉ፡፡ በአንዳንድ ጥናቶች እይታ የአዲስ አበባ ቤት አልባዎች በሁለት ቡድኖች ይከፈላሉ። እነሱም፣ በፕላስቲክ ቤቶች የሚያድሩና የፕላስቲክ መጠለያ የሌላቸውና ውጭ የሚያድሩት ናቸው፡፡ እነዚህ ውጭ የሚያድሩት በተለምዶ "በረንዳ አዳሪዎች "የሚባሉት ናቸው፡፡ በፕላስቲክ መጠለያዎች የሚኖሩት በመንገዶች ዳርቻ በጨርቅ፣ በፕላስቲክና በወዳደቁ አሮጌ ነገሮች በተሰሩ መጠለያዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ቤት አልባዎች በቀን የሚኖሩበት ቋሚ ቦታ ስለሌላቸው ትክክለኛ ቁጥራቸውን መገመት ያስቸግራል፡፡

ፎቶ 6፣ ቤት አልባ የሆኑ ዜጎች በመኝታ ላይ በአዲስ አበባ መንገድ



በ1993 በተገኘ መረጃ በፕላስቲክ መጠለያዎች የሚኖሩት ኗሪዎች 3,479 እንደሚደርሱ ይገመታል፡፡ ይሁን እንጂ በተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችና በመንግሥትና በዕርዳታ ድርጅቶች በተወሰዱ የራስን መቻል ፕሮግራሞች የተነሳ ይህ ቁጥር እየቀነሰ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህም ሆኖ የቤት አልባነት አሁንም የከተማዋ ዋና ጉዳይ ነው፡፡

## 2.3 *የከተማዋ የቤት ችግሮች ዋና ምክንያቶች*

**የህዝብ ቁጥር መጨመር**

በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት የአዲስ አበባ የህዝብ ቁጥር በ2010 3,328,000 እንደሚደርስ ተገምቶ የነበረ ሲሆን፣ የ2.1 የዕድገት መጠን መሠረት በማድረግ ከአንድ ዓመት በኋላ በ2015 የኗሪዎቿ ቁጥር 3,792,000 እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ይህም እድገት ከተማዋ በተፈጥሮ ማደግ ካለበት አካሄድ ይልቅ በዋናነት በዓመት 1.69 ፐርሰንት በሆነው ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት ምክንያት የሚመጣ ነው፡፡ በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት ከሚያሳዩት ተፈጥሯዊ የከተማ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር አዲስ አበባ በጣም ዝቅ ያለ ዕድገት ይስተዋልባታል (UN HABITAT 2007) በ (Elias Y., Yonas A. et al, 2011) እንደተገለጸው፡፡ ከከተማ ወደ ከተማና ከገጠር ወደከተማ ያለው ፍልሰት ለከተሞች በፍጥነት ማደግ እንደዋና ምክንያት ይወሰዳል፡፡ ይህ የከተሞች በፍጥነት ማደግ ደግሞ ከሚፈጥረው የቤቶች እጥረት በተጨማሪ ከመጠን ያለፈ መታፈግን፣ ያልታቀደ ከተሜነትን፣ እንዲሁም ከተሞች ሊስፋፉ በሚያስቡበት አካባቢ ያለዕቅድ

የሚከናወን ሠፈራን ያባብሳል፡፡ በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የህዝብ ቁጥር መብዛት በአዲስ አበባ ያለውን የቤቶች እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ አባብሶታል፡፡

**ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የመሬት አቅርቦት አናሳ መሆን**

በኢትዮጵያ የከተማ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይገኛል፡፡ የመሬት ባለቤትነት ከግል ወደህዝብ የተዛወረ ቢሆንም የመኖሪያ ቦታ ማግኘት በዝቅተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላሉ ኗሪዎች አስቸጋሪ ነው፡፡ ለከተማ ኗሪዎች መሬት ማግኘት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በክልል 14 የወጣው የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 3/94 በከተማዋ ውስጥ ቦታ ስለሚያዝበት በተገቢው ሁኔታ ያብራራል፡፡ ቦታን ከማግኘት ጋር የተያያዙት ሁኔታዎች ቦታን ማግኘት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኗሪዎች አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም ለመወዳደር ለሚፈልጉ ኗሪዎች ለምዝገባ 250 ብር እንዲሁም የግንባታውን 20% በቅድሚያ ለማስያዝ ስለሚያስቸግር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለከተማዋ ደሃዎች አስቸጋሪ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሊዝ ለመያዝ የተመረጡት ቦታዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ የከተማዋ የመሬት አሰጣጥ ሁኔታ አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ካለው የቤት ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር አቅርቦቱ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በዓመት የመሬት አቅርቦቱ ብዛት 1100 ቦታዎች ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ያለው የመሬት አቅርቦት በቂ ቢሆንና ዋጋውም ተመጣጣኝ ቢሆን በአጠቃላይ ካለው የቤቶች ፍላጎት አንድ አምስተኛውን ሊያቃልል ይችል ነበር፡፡ የሊዝ ፖሊሲው ያለውን የቤቶች ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ የቤቶች ዋጋ በፍጥነት እንዲያሻቅብና የቤቶችን ግንባታ ወጭ ያላግባብ እንዲያድግ አድርጎታል፡፡

**በቤቶችና መሬት አሰጣጥ ላይ እየሰፋ ያለው ሙስና**

በ2012 በዓለም ባንክ በታተሙ ሪፖርቶች መሠረት ከመሬት ሊዝ ጋር በተያያዘ ግልጽ ህግና መመሪያዎች ባለመኖራቸው የተነሳ በአዲስ አበባ ከተማ ያለጉቦ የከተማ ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ ይሄው ሪፖርት በተጨማሪ በሙስናና በዝምድና በሚሰጡ ህጋዊ ያልሆኑ የመሬት ባለቤትነት ካርታ መበራከት ምክንያት ህዝቡ በመሬት መረጃ ላይ ያለውን እምነት እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ የተጠያቂነት ስርዓት ያለመኖር አንዳንድ በዘርፉ ያሉ ባለስልጣኖች ያሉትን ክፍተቶች በመጠቀም ራሳቸውን ሃብታም እንዲያደርጉ በር ከፍቶላቸዋል፡፡

በሃገሪቱ መሬት በመንግሥት እጅ ላይ ይገኛል፡፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በ2009 ባወጣው ሪፖርት መሠረት እያደገ በመጣው የመሬት ዋጋ ምክንያት ለባለሃብቶች በረዥም ጊዜ ሊዝ መሬት ለመስጠት የሚወሰደው ጉቦ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳደገ ጠቁሟል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ባለስልጣኖችና በግል ሴክተሩ መካከል ያለመግባባቶች እንደተፈጠሩ በርካታ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ፡፡ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት በተጨማሪም በመሬት ማልማት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶችም በሙስና ምክንያት እንደተከሰሱ አስቀምጧል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከመኖሪያ ቤትና ቦታ ጋር በተያያዙ ዋና ዋና የሙስና ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ከመሬት ሊዝ ጋር የተያያዙ ሙስናዎች**

- የመሬት የሊዝ አዋጁ፣ ህጎቹና ደንቦቹ ግልጽ ባለመሆናቸው የተከሰቱ ሙስናዎች፣
- የመሬት ሊዝ ጨረታ አሸናፊዎች ከታወቁ በኋላ የተሰረዙ የመሬት ሊዝ ጨረታ ውጤቶች፣
- በህጋዊ መንገድ በሊዝ ጨረታ ያሸነፉትን በመካድ፣ ለሌሎች አልሚዎች ህጋዊዎቹ ካሸነፉበት ዋጋ ባነሰ መደራደር፣
- በሊዝ አዋጁ በተቀመጠው መሠረት በ1ኛና በ2ኛ ደረጃ ተጫራችነት የተቀመጡ እያሉ በ3ኛ ደረጃ ለተቀመጡ ተጫራቾች መሬት መሸጥ፣
- የሊዝ ጨረታ ኮሚቴው ሃላፊነትና የአገልግሎት ዘመን ግልጽ ያለመሆንና የሊዝ ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር የጥቅም ግጭት ማጋጠሙና ይህም ወደሙስና ማምራቱ፣
- የመሬት ሊዝ ጨረታ መመሪያው ከስነምግባርና ከሙስና ጋር በተያያዘ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የዲስፒሊን እርምጃዎች ግልጽ መመሪያ ያለመኖር፣
- ለተለያዩ ሰዎች የአንድ መሬት የባለቤትነት መታወቂያ መስጠት፡፡ (FEACC and Transparency Ethiopia, 2009)

**ለቤት ማህበራት መሬት ከመስጠት ጋር የተያያዙ የሙስና ጉዳዮች**

ከ2005 በኋላ ለማህበራት መሬት መስጠት የተቋረጠ ቢሆንም የነበረው አሰጣጥ ሂደት ግን በከፍተኛ ሁኔታ በሙስና የተጨማለቀ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ በበርካታ የከተማዋ አካባቢዎች ብዙ ማህበራት መሬት ህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ ሁኔታ በዕጣ እንዲወስዱ ሲደረግ ነበር፡፡ ለዚህ ከህግ ውጭ ለሆነ አሰራር በዋናነት ተጠያቂዎች ስነምግባር የጎደላቸው የክፍለ ከተማ

*ሠራተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሠራተኞች ቦታ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ላላሟሉ አንዳንዶም በአካል ላልተገኙ ማህበራት ቦታ ይሰጡ ነበር፡፡ አንዳንዶቹም በህጋዊ መንገድ ማህበራትን ሳያደራጁ ቦታውን ለራሳቸው ይወስዱ ነበር፡፡ በህጋዊ መንገድ እንደወሰዱት ሁሉ ከህግ ውጭ ለሆኑት ማህበራት የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ይሰጡ ነበር፡፡ ሥነምግባር ከጎደላቸው የክፍለ ከተሞች ሠራተኞች ጋር የጥቅም ግንኙነት ያላቸው አንዳንድ ግለሰቦች ለማህበራት ፍላጎት ሊውል ይገባው የነበረውን መሬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህንንም በማህበራት እንደተደራጁ በማስመሰልና የሌሉ ግለሰቦችን ዝርዝር በማያያዝና የባንክ አካውንት በመክፈት፣ በማህበራት የሚጠየቀውን የማህበራት መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ ነበር፡፡ መሬቱንም ከወሰዱ በኋላ ለመግዛት ፍላጎት ያላቸውን ግለሰቦች በመጥራት እንዲገዙ አድርገዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በተለይ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተሞች ታይተዋል* (FEACC and Transparency Ethiopia, 2009)፡፡

*በፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንና ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ የ*2009 e.c. *ሪፖርት መሠረት የክፍለ ከተማ ሠራተኞች ስለጉዳዩ በቂ ዕውቀት ቢኖራቸውም ለጉዳዩ ግን ጀርባቸውን ሰጥተዋል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መረጃዎች ሲደርሳቸው እንኳን ተገቢውን ትኩረት አይሰጡም ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ግለሰብ ራሱን በማህበራት በማደራጀት መሬት መውሰድና መሸጥ ቀላል ነበር፡፡*

*በሌላ በኩል ደግሞ በህጋዊ መንገድ ተደራጅተውና የሚፈለገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው የሚመጡ ማህበራት ቦታ ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድን ማለፍ የሚጠበቅባቸው ሲሆን አንዳንዴም ቦታ የለም የሚል መልስ ተሰጥቷቸው ፋይላቸው ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ነበር፡፡*

*በአጠቃላይ እነዚህ ችግሮች የታዩት ከአምስት ዓመታት በፊት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ምክንያት የተወሰኑ ጉዳዮች ተሻሽለዋል፡፡ ይሁን እንጂ የመሬት አሰጣጥ ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ተቃለዋል ወይም የመሬት አሰጣጥ ስርዓቱና አፈጻጸሙ ከችግር ነጻ ነው ማለት አይቻልም፡፡* (FEACC and Transparency Ethiopia, 2009)፡፡

**ከሪል ስቴት አልሚዎች ከሚቀርበው መሬትና ሰርተፊኬት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ የሙስና ጉዳዮች**

- *በሪል ስቴት አዋጅና በመሬት ሊዝ አሰጣጥና አፈጻጸም መመሪያ መካከል ያለው ተቃርኖ ባስከተለው ክፍተት ምክንያት የሪል ስቴት አልሚዎች የወሰዱትን መሬት ሳያለሙ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ፣*
- *መንግሥት በከተማዋ ያለውን የቤቶች እጥረት ለመቅረፍ መሬትን በድርድር የማሸጋገር ሂደት ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የራሳቸውን የግል ፍላጎት ለማሟላት በሚራወጡ ስግብግብና ከፍተኛ ገንዘብ ለመሰብሰብ በሚራወጡ የመሬት አልሚዎች መገታቱ፣*
- *ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እንዲፈጠሩ በዋናነት ምክንያት የሆነው በማዕከልና በክፍለ ከተማ ደረጃ ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና የክትትል ስራ ባለመሰራቱ ነው፡፡*
- *በሌላ በኩል ደግሞ በአልሚዎች የሚመጣውን ለእያንዳንዱ ይዞታ በተናጥል የባለቤትነት ሰርተፊኬት የማግኘት ጥያቄ በተመለከተ ግልጽ የሆነ መመሪያ ያለመኖሩ ለሙስና በር ከመክፈቱም በተጨማሪ በክፍለ ከተሞች መካከል ተመሳሳይ አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፣*
- *የከተማዋን ይዞታ በተመለከተ የሚያገለግል ካርታ ባለመኖሩ አንድ ቦታ ለሁለት ግለሰቦች እንዲሰጥ ማድረጉ፣*
- *ፈጣንና ውጤታማ የሆነ የመሬት መረጃ ስርዓት ባለመኖሩ የተነሳ የተፈጠረው ውጣ ውረድና የአገልግሎት ምላሽ ለማግኘት ረዥም ጊዜ መውሰዱ፣*
- *ከመሬት ጋር የተያያዙ መረጃዎችና ፋይሎች መጥፋትም ለሙስና በር እንዲከፈት አድርጓል፣*
- *የመሸጫ ዋጋን በድርድር እንዲወሰን መደረጉ በነበረው የገበያ ልዩነት ምክንያት መንግስት ከመሬት ዋጋ ሊያገኝ ይገባው የነበረውን ገቢ እንዳያገኝ ማድረጉ፣*
- *ክፍለከተሞችና የከተማዋ ጽ/ቤት ሁለቱም በመሬት አሰጣጥ ላይ መሳተፋቸውም ለሙስና በር ከፍቷል፣*
- *በየደረጃው በመሬት አሰጣጥ ላይ በሚሳተፉ አካላት መካከል መናበብ ያለመኖርና በመሬት ሊዝ አሰጣጥ ረገድ በወጡ መመሪያዎችና ደንቦች መካከል ተመሳሳይነት ያለመኖር ለሙስና ሥራ ምክንያቶች ሆነዋል፣*
- *በማዕከልም ሆነ በክፍለከተሞች ደረጃ ተጠያቂነት ያለመኖር የሙስና ምክንያት መሆኑ በአጥኝዎች ከታዩ ጉዳዮ ውስጥ አንዱ ነው፡፡*

**ከቀበሌና ከኮንዶሚኒያም ቤቶች ጋር በተያያዙ የተከሰቱ ጥቂት የሙስና ጉዳዮች**

- ለቀበሌ ቤት ባለቤቶች የባለቤትነት ሠርተፊኬት ከመስጠትና ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግ ጋር የተያያዘ፣
- በተወሰኑ የቤት ሥራ ተቋራጮች ለቤት ስራ የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ በሚያዛባና የቤቶችን ዘላቂነት ችግር ውስጥ በሚከት ደረጃ ለቤቶቹ ግንባታ የተሰጡ የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶችን በመስረቅ ደረጃውን ያልጠበቀ ስራ መሰራቱ፣
- ግልጽነት በጎደለው የኮንዶሚኒየም እጣ አወጣጥ ጋር በተያያዘ የዕጣ አሸናፊዎችን ዝርዝር ወዲያውኑ ማውጣት ሲቻል በመዘግየቱ የተነሳ የህዝቡን እምነት ማጣት፣
- ለኮንዶሚኒየም ከረዥም ጊዜ በፊት የተመዘገቡት እያሉ ከሠራተኞች ጋር ባላቸው ቅርበት የተነሳ በአጭር ጊዜ ተመዝግበው እጣ ያገኙ ሰዎች እንዳሉ ጭምጭምታዎች መኖራቸው፣ ያሸነፉ ሰዎች ዝርዝርም በወቅቱ ያለመውጣት ለሚፈልጓቸው ሰዎች እስኪደለድሉ ነው የሚለውን ጥርጣሬ አጠናክሮታል፡፡

**በከተሞች የሚኖሩ ነሪዎች ገቢ አነስተኛ መሆን**

በአዲስ አበባ ከተማ የቤቶችን ችግር እያባባሱ ከሚገኙ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የኗሪዎቿ ገቢ አነስተኛ መሆን ነው፡፡ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ኗሪዎቿ ቁጥርም በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በከተማዋ የልማት ዕቅድ (2003-2010) መሰረት ከከተማዋ አጠቃላይ ኗሪዎች ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት 4% ብቻ ናቸው፡፡ 16% የሚሆኑት መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሲሆኑ ቀሪዎቹ 80% ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ናቸው (Elias et al, 2011)፡፡ ከዚህ በመነሳት የከተማዋ የቤቶች ችግር ከገቢ ጋር የተገናኘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ፖሊሲ አውጭዎችም የገቢ ሁኔታ አነስተኛ መሆን ለቤቶች እጥረት ምክንያት እንደሆኑ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማዋ ኗሪዎች ገንዘብ ሊኖራቸው የሚችለው መሠረታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ነው፡፡ በጣም ውድ የሆኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ብዙውን ገቢያቸውን ይሻማቸዋል፡፡ ቤት ደግሞ ለብዙ ቤተሰቦች ውድ ከሚባሉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለቤት የሚያወጡት ወጭ ከዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማዋ ኗሪዎች ከፍተኛ የሆነውን ወጪያቸውን ይወስድባቸዋል፡፡

ሥራ አጥነት በከተማዋ በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋ ጉዳይ ነው፡፡ ከተማዋ ያለው የስራ አጥነት ሁኔታም 29% እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ሥራ አጥነት በዝቅተኛ ገቢ ሁኔታ ጋር ተደርቦ የቤቶችን ችግር አስከፊ አድርጎታል፡፡

**የቤቶች ደረጃና ደንብ**

ሃርዲ (1981) እንዳመለከተው "…የጥራት ደረጃዎች በአካባቢው ካሉ ሃብቶች ጋር ተመጣጣኝ፣ እያደጉ የሚመጡ፣ ካለው ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር በበቂ ሁኔታ ሊመጋገቡ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን በርካታ ለሚሆነው ህዝብ ቤትን ለማግኘት የሚያስችለው በራስ ተነሳሽነት ቤቶች የመገንባትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡" አሁን በከተማዋ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የቤቶች ደረጃ በከተማዋ ውስጥ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማዋ ኗሪዎች የመክፈል አቅም ጋር የማይጣጣምና ከከተማዋ የህንጻ ግንባታ ጋር የማይመጣጠን ነው፡፡ የተቀመጡት የቤቶች ደረጃ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አብዛኞቹ የከተማዋ ኗሪዎች እነዚህን ቤቶች ለመስራት በሚችሉበት ደረጃ ላይ አይደሉም፡፡

የመንግስት መመሪያዎችም የቤቶችን ዋጋ ከፍ እንዲል አድርገዋል፡፡ በዚህም ለድሆች ቤት የማግኘት ጉዳይን አስቸጋሪ በማድረግ ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ የቤቶችን የጥራት ደረጃ ከፍ ማድረግ ለዋጋው ከፍተኛ መሆን አስተዋጽኦ አለው፡፡ በእርግጥም መንግስታት የቤቶችን የጥራት ደረጃ ከፍ በማድረግ ብዙ ቤተሰቦች ከሚፈልጉት በላይ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሲታይ የመንግስት ዋጋ ህብረተሰቡ ከሚደርስበት የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡ መመሪያዎች ማህበረሰቡን ቢጎዱም የተወሰኑ ክፍሎችን የሚጠቅሙ ቢሆንም ከጥራት ባሻገር ባሉ ሁኔታዎች ሊደግፏቸው ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የቤቶች አቅርቦትን በመቀነስ ከመሬት ጋር የተያያዘው መመሪያ የመሬትና የቤቶችን ዋጋ እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ልማት ያለመኖር**

በአዲስ አበባ ከተማ ካሉ ችግሮች ዋናዎቹ ከአረጁና ለመኖሪያ ምቹ ካልሆኑ አካባቢዎች ጋር የተያያዘ ናቸው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የልማት ዕቅድን መሰረት በማድረግ ወይም በማስተር ፕላን ላይ የተመሰረተ ልማት ባለመኖሩ የተነሳ ነው፡፡ ይህም ያረጁና ደረጃቸውን ያልጠበቁ እንዲሁም የታፈጉ የመኖሪያ አካባቢዎች እንዲኖሩ አድርጓል፡፡

**የቤቶች ፋይናንስ**

*የቤቶች ልማትን በተመለከተ ውስን የሆነ የፋይናንስ ሁኔታ መኖሩ አንዱ እንቅፋት ነው፡፡ ይህም ችግር ከመንግስትና በኗሪዎች በኩልም የሚታይ ነው፡፡ በሃገራችን ያሉ የፋይናንስ ተቋማት አቅም አነስተኛ በመሆኑ የተነሳ ቋሚ ደመወዝ ኖሯቸው ቤት ለመስራት ወይም ለመግዛት ለሚፈልጉ ኗሪዎች ብድር የመስጠት ሁኔታ ደካማ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በከተማዋ ያሉ ኗሪዎች የኑሮ ደረጃ አናሳ መሆን በቋሚነት ለቤት ስራ ገንዘብ የመቆጠብ ሁኔታን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡*

**ይዞታን ማስከበር**

*ይዞታን የማስከበር ጉዳይ ይህ ባለመኖሩ ስጋት ላይ ያሉ አካላትን ብቻ ሳይሆን የማዕከልና የክልል መንግሥታትንም የሚጠቅም ነው፡፡ በጣም በርካታ ምሳሌዎች እንደሚያሳዩት ሰዎች የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሲያገኙ ገንዘባቸውን በማውጣት ቤታቸውንና አካባቢውን ለማልማት ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ማግኘት ለመጠለያዎች መሻሻል፣ የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ በማህበረሰቡ መገለልን ለመቀነስ፣ ለከተማ አገልግሎቶች ተደራሽ መሆን፣ በማህበራትና በግለሰቦች ኢንቨስት ለማድረግ ያለውን ፍላጎት በአግባቡ ለመጠቀም እና የከተማዋን ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በአዲስ አበባ የይዞታ ባለቤትነት ማግኘትና አለማግኘት ከቤቶች ጋር በተያያዘ ላሉ ችግሮች በተለይም ለመሃል ከተማዋ ማርጀትና በከተማዋ ዳርቻ ለሚገኙ ከህግ ውጭ ለሚሰሩ ቤቶች መሠረተ ልማት አለመስፋፋት አንዱ ምክንያት ነው፡፡*

*በአጠቃላይ በአዲስ አበባ ቤቶች ጋር ለተያያዙ ችግሮች ዋነኛ ምክንያቶች የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ያለማግኘት፣ የቤቶች ደረጃና መመሪያዎች፣ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ልማት ያለመኖር፣ የቤቶች ፋይናንስ እጥረትና የባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ያለመኖር ናቸው፡፡*

## 2.4 *በአዲስ አበባ የቤቶች ፍላጎት*

*በጽንሰ ኃሳብ ደረጃ ሲታይ አጠቃላይ የቤቶች ፍላጎት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ እነሱም፣ ለአዲስ ቤተሰቦች የሚያስፈለግ ቤት፣ ያረጁና የደቀቁ ቤቶችን መተካት፣ የተጨናነቁ ሠፈሮችን ማስተካከልና ለቤት አልባ ሰዎች ቤት እንዲያገኙ ማድረግን ይይዛል፡፡*

የአዲስ አበባ ከተማ የቤቶችን ችግር ከጥራትና ከቁጥር አንጻር ማየት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን በተለያዩ አካላት የተለያየ ጥረት ቢደረግም በአዲስ አበባ ያለው የቤቶች ሁኔታ ያለውን የነሪዎቿ ፍላጎት ለማሟላት በቁጥርም ሆነ በጥራት በቂ አይደለም፡፡

በከተማዋ የነበረው የቤተሰብ ብዛት 588,235 ሲሆን፣ በ3% የህዝብ ዕድገት መጠን ሲሰላ በ2010 ሊኖር የሚችለው የቤተሰብ ብዛት ደግሞ 702,382 እንደሚደርስ ይገመት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ2004 የነበረው የቤቶች ቁጥር 471,429 የነበረ ሲሆን በ2.3% የቤቶች ግንባታ መጠንን መሠረት በማድረግ በ2013 የሚኖሩ ቤቶች መጠን 569,015 ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡ የ2.3% የዕድገት መጠን እስከ አሁን የተገነቡትን 108,482 ኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታን የማያካትት በመሆኑ እነዚሁኑ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ስንደምርባቸው በአዲስ አበባ በ2013 የሚኖሩ ቤቶች 677,497 ይደርሳሉ፡፡

ስለዚህ ከዚህ በመነሳት 251,987 የሚሆኑ የደቀቁትን ወይም መተካት ያለባቸውን ቤቶች ካለው ጠቅላላ የቤቶች ቁጥር ላይ ሲቀነስ የሚኖሩት የቤቶች ቁጥር 425,510 ይሆናል፡፡ መተካት ያለባቸው ቤቶች ተቀንሰው አሁን ያሉት ቤቶች ሊይዙ የሚችሉት ከከተማዋ ነሪዎች 2,212,652 ብቻ ነው፡፡ በ2007 በወጣው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሪፖርት መሠረት አሁን ያለው የአዲስ አበባ የህዝብ ብዛት ቁጥር አሁን ባለው የ2.1% የዕድገት ምጣኔ መሠረት 3,189,000 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ አባላት አማካይ ቁጥር 5.2 እንደሆነ ተወስዶ ከ2010 እስከ 2013 የሚኖረውን ተጨማሪ የህዝብ ብዛት ለማስተናገድ ተጨማሪ 152,308 ቤቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሦስቱን መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶች ማለት አዲስ ቤተሰብ መመስረትን፣ መተካት ያለባቸውን ቤቶችና መሰራት የነበረባቸው ቤቶችን (የሪል እስቴት ፈላጊዎችን ሳይጨምር) ጨምሮ እስከ 2013 የሚያስፈልገው ጠቅላላ የቤቶች ፍላጎት 571,897 ነው፡፡ ይህም የቤቶች ፍላጎት ግምት የከተማዋ አስተዳደር ከሰኔ እስከ ነሐሴ 2013 ባደረገው ምዝገባና ከዚህ ቀደም ከተመዘገቡት ጋር ተደምሮ ካስቀመጠው የ600,000 ሰዎች ብዛት ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡

በቅርብ ባለው የ2013 መረጃ መሠረት በተለያዩ የቤቶች ግንባታ ፕሮግራሞች የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር በጠቅላላው 1,176,472 ይደርሳል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 22,324ቱ ነዋሪዎች ለ10/90 እና 758,148 ነሪዎች (ከዚህ ውስጥ 132,151 ከዚህ ቀደም የተመዘገቡ ሲሆን 625,997 አዲስ ተመዝጋቢዎች) ደግሞ ለ20/80 ተመዝግበዋል፡፡ ከከተማዋ ነሪዎች ውስጥ

164,000 ደግሞ ለ40/60 የተመዘገቡ ሲሆን 232,000ዎቹ ነዋሪዎች ደግሞ ለማህበራት ተመዝግበዋል፡፡ በተጨማሪም እንደ ቴሌ፣ ባንክ፣ አየር መንገድና የመሳሰሉት የልማት ድርጅቶች በተተወላቸው የ100/0 ፕሮግራም ቁጥሩ በውል ያልታወቀ ፍላጎት አለ፡፡ ይህም ከ2010 በኋላ የ100/0 ፕሮግራምን ሳይጨምር ለሁሉም ፕሮግራሞች ተጨማሪ 723,472 ቤቶች ያስፈልጋሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለ10/90 እና ለ20/80 ፕሮግራሞች ብቻ 411,896 ቤቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከከተማዋ የቤቶች ልማት ኃላፊዎች እንደተስተዋለው ይህ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች መቆጠብ ያለባቸውን የገንዘብ መጠን ለመቆጠብ ባለመቻላቸው ምክንያት ይህ ቁጥርም እየቀነሰ እንደሚሄድ ይገመታል፡፡ ሌላው ምክንያት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች በየወሩ እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸውን ወርሃዊ መዋጮ መጠን በተመለከተ መቻልና አለመቻላቸውን ብዙ ሳያስቡበት መብታቸውን ለመጠቀም ብቻ የተመዘገቡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች አካባቢ ለኪራይ ቤቶች ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ለሚገኙ ነዋሪዎች የኪራይ ቤት ማግኘት አንዱ አማራጭ ነው፡፡ አሁን ያለው የመሬት ልማት ዕቅድና የመሬት አሰጣጥ እንዲሁም የቤቶች ፖሊሲ ለመንግሥት የኪራይ ቤቶች ያለውን ፍላጎት የተገነዘበ አይመስልም፡፡

ሠንጠረዥ 2፣ በ2013 የኮንዶሚኒየም ፍላጎት በፕሮግራም ዓይነት

| የፕሮግራም አይነት | ሴት | ወንድ | ጠቅላላ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 10/90 | 12,677 | 9,647 | 22,324 | |
| 20/80 (አሁን ያለ) | 44,974 | 87,177 | 132,151 | ይህ በ2003 እንደገና ምዝገባ ከተደረገ በኋላ ያለ ቁጥር ነው በፊት የተመዘገቡት ሰዎች ቁጥርም ወደ 453,000 ይጠጋል፡፡ |
| 20/80 (አዲስ) | 270,603 | 355,394 | 625,997 | |
| 40/60 | - | - | 164,000 | |
| ማህበራት | - | - | 232,000 | |
| 100/0 | የለም | የለም | የለም | ለልማት ድርጅት ሠራተኞች የተዘጋጀ ፕሮራም |
| ጠቅላላ | 328,254 | 452,218 | 1,176,472 | |

ምንጭ፣ Developed based on AAHDA, 2013

## 2.5 ባለፉት ሃያ ዓመታት የቤቶች ልማትና አሰጣጥ ጥረቶች

**የግል ቤቶች (የሪል ስቴት፣ ግለሰብና የማህበራት አልሚዎች)**

የሪል ስቴት ልማት ዕድገት በመጀመሪያዎቹ ዘመናት በጣም ፈጣን ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ፈጣን ዕድገት በብዙ ምክንያቶች ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ለተቀዛቀዘው የሪል ስቴት ዕድገት ምክንያት ሆነው ከሚጠቀሱት መካከል፣ የተሳሳቱ ግምቶች፣ ከፋይናንስ ድርጅቶች ጋር ያለው ደካማ ግንኙነት፣ ቀርፋፋ የመሬት አሰጣጥ ስርዓት፣ ከአልሚዎች በኩል የኪራይ ሰብሳቢነት ባህሪ መኖር የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በከተማዋ መስተዳድር በተደረገው ጥናት መሠረት አንዳንድ የሪል እስቴት አልሚዎች የሚታለል ባህሪ ለምሳሌ፣ የወሰዱትን ቦታ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፣ ቦታዎችን ሳያለሙ ለረዥም ጊዜ አጥሮ ማስቀመጥ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የማህበረሰቡ ክፍሎች ቤቶችን መስራት ያለመቻላቸው፣ በትክክል የሪል ስቴት አልሚነት ባህሪን ሳይሆን የኮንስትራሽን ሥራን ብቻ መስራት፣ ያልተፈቀዱ ክፍፍሎችን መፍጠር፣ ከፍተኛ ትርፍ ለማካበት ሲባል ያሉትን የህግ ክፍተቶች መጠቀም የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ፎቶ 7፣ የቤቶች ልማት በግል (በሪል እስቴትና በግለሰብ) አልሚዎች












ምንጭ፣ From different sources

በአልሚዎች በኩል ከተጠቀሱ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ በመስተዳደሩ በኩል ቀርፋፋ የመሬት አሰጣጥ ስርአት፣ የብድር አቅርቦ አለመኖር፣ የግንባታ እቃዎች ዋጋ ማሻቀብና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ያሉ ቢሆንም በነዚህ አልሚዎች የተሠሩ ቤቶች ጨምረዋል፡፡ ስለዚህ ይህ ውሱን የሆነ ጥረት የከተማዋን የቤቶች ቁጥር እንዲያድግ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በግል ገንቢዎች የሚሰሩ ቤቶችን በተመለከተ ብዙም አልተሠራም (Elias Y., Yonas A. et al 2011)፣ (AAHDPO, 2012)፡፡

በሌላ በኩል የግልና የማህበር ቤት ገንቢዎች በአዲስ አበባ በአጠቃላይ የገነቧቸው ቤቶች ብዛት 46,021 ሲሆን ቤቶቹም የተያያዙና ያልተያያዙ ናቸው፡፡

*ምስል 4፣* የግል ቤቶች የሚገኙባቸው ሳይቶች *ምስል 5፣* የሪል እስቴት የሚገኙባቸው ሳይቶች





SOURCE: Elias Yitbaredk, et al (2011)

በአጠቃላይ ሲታይ የሪል ስቴት፣ የግልና የማህበር አልሚዎች አስተዋጽኦን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡

- ወደ 5,000 የሚሆኑ ቤቶች በሪል ስቴት አልሚዎች ተገንብተዋል፣

- በግልና በማህበራት የቤት ገንቢዎች 46,021 ቤቶች የተገነቡ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ለቤቶች ቁጥር አስተዋጽኦ አድርጓል፣
- በርካታ ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድሎች ተፈጥረዋል፣
- የአንዳንድ የሪል ስቴት አልሚዎች የብቃት ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ከፍ ብሏል፣
- የከተማዋ አንዳንድ አካባቢዎች ገጽታ በጥሩ ጎኑ ተለውጧል፣
- ይሁን እንጂ እነዚህ ሁኔታዎች አዳዲስ ችግሮችን ፈጥረዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ዘግተው የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችንና በኢኮኖሚ ከሌላው ተለይተው የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተፈጥረዋል፡፡
- ሰፊ ቦታ ለሪል ስቴት አልሚዎች በመሰጠቱ በግል አልሚዎች በኩል ያለመደሰት መፈጠሩ፡፡

**በአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የቤቶች ልማትና አሰጣጥ**

በከተማዋ ሁሉን አቀፍ የሆነ ልማትን ለማምጣት ሲባል የአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጅክት ጸ/ቤት የተቋቋመው በ2003 ነው፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ ገቢን በማሳደግ፣ የከተማዋ ኗሪዎች ያለባቸውን ችግሮች በመፍታት ትልቅ ሚናን ተጫውቷል፡፡ የአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ያከናወናቸው ዋና ዋና ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ፎቶ 8፣ ያረጀው መሃል ከተማና የአዳዲስ ቤቶች ልማት በአዲስ አበባ**



ምንጭ፣ From various sources

**የኮንዶሚኒየም ፍላጎትና አቅርቦት**

በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም መሠረት የኮንዶሚኒየም ቤቶችን የማስተላለፉን ሥራ ለማፋጠን ለኮንዶሚኒየም ቤት ፈላጊዎች የመጀመሪያ ምዝገባ የተካሄደው በእ.አ.አ. 2005 ነበር፡፡ በዚህም መሠረት 453,287 ቤት ፈላጊዎች ተመዝግበው መረጃዎቻቸው በኮምፒዩተር የመረጃ ቋት እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ ከተመዘገቡት ውስጥ 278,578ቱ ወይም 61.46% ወንዶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 174,709 ወይም 38.54% ደግሞ ሴቶች ናቸው (የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ) (AAHDPO, Amharic version report, 2012)፡፡

ሠንጠረዥ 3፣ በ2005 የነበረው ፍላጎት[1] በቤቶች ዓይነት

| ተ.ር | የቤቶች አይነት | ተመዝጋቢዎች በጾታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ሴቶች | ወንዶች | ጠቅላላ |
| 1 | ስቱዲዮ | 59,856 | 42,431 | 102,287 |
| 2 | ባለአንድ መኝታ ቤት | 127,504 | 74,465 | 201,969 |
| 3 | ባለሁለት መኝታ ቤት | 73,310 | 44,931 | 118,241 |
| 4 | ባለሶስት መኝታ ቤት | 17,908 | 12,882 | 30,790 |
| | **ጠቅላላ** | **278,578** | **174,709** | **453,287** |
| | **ድርሻ በመቶኛ** | **61.5** | **38.5** | **100** |

**ምንጭ፣** AAHDPO. 2012, as translated by the author

ከላይ በሠንጠረዡ ላይ እንደቀረበው በ2012 ብቻ የቤቶች ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ80,245 ኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታን አጠናቅቋል፡፡ ከነዚህ ቤቶች ውስጥ 5,592 (7%) ለንግድ አገልግሎት የዋሉ ናቸው፡፡ ቤቶቹ የተገነቡት በከተማ መስተዳድሩ 10 ክፍለ ከተሞች በሚገኙ 117 ሳይቶች ላይ ነው፡፡

[1] ፍላጎት ማለት የተመዘገቡ ሰዎች ብዛት ነው፡፡


ሠንጠረዥ 4፣ በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽቤት እስከ 2012 ድረስ በ117ቱ ሳይቶች ላይ የተገነቡት ቤቶች አድራሻ

| | ከተማ | የሳይቶች ብዛት | የብሎኮች ብዛት | የቤቶች ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 17 | 1033 | 29,438 | 36.69 |
| 2 | ቦሌ | 12 | 722 | 20178 | 25.16 |
| 3 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 9 | 237 | 8390 | 10.46 |
| 4 | አቃቂ ቃሊቲ | 5 | 203 | 5887 | 7.34 |
| 5 | ቂርቆስ | 15 | 137 | 4242 | 5.29 |
| 6 | የካ | 16 | 136 | 4303 | 5.36 |
| 7 | ልደታ | 7 | 89 | 3261 | 4.06 |
| 8 | አራዳ | 19 | 61 | 2116 | 2.64 |
| 9 | ጉለሌ | 9 | 48 | 1325 | 1.65 |
| 10 | አዲስ ከተማ | 8 | 33 | 1105 | 1.38 |
| | ጠቅላላ ድምር=10 | 117 | 2699 | 80,245 | 100 |

*ምንጭ፣* Developed based on AAHDPO, 2012

ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ የኮንስትራክሽን ሳይቶች ከ120 በላይ የደረሱ ሲሆን አዳዲስ እና የተለያየ አማራጭን የያዙ እንደ 10/90 እና 40/60 የመሳሰሉት ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው፡፡

ምስል 6፣ (በግራ በኩል) ከ2003 እስከ 2011 ባሉት ጊዜያት ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ብዛትና አጠቃቀም




ምንጭ፣ Developed Based on (AAHDPO, 2012)

ፎቶ 9፣ (በቀኝ በኩል) በኮንዶሚኒየም ብሎኮች ለንግድ ሥራ የዋሉ የምድር ቤቶች



ምንጭ፣ UN Habitat, 2011

ከላይ በተመለከተው ምስል መሠረት ከቤቶች ልማት ፕሮጀክት በጠቅላላው ከተገነቡና ለዕድለኞች ከተላለፉ 80,245 የኮንዲኒየም ቤቶች ውስጥ እስከ 2011 ድረስ 93 ፐርሰንቱ ለመኖሪያ ቤቶች ቀሪው 7 ፐርስንት ደግሞ ለንግድ አገልግሎቶች ውለዋል።

**ፎቶ 10፣ (በግራ በኩል) በአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተገነቡ ኮንዶሚኒየሞች**



*SOURCE*: AAHDPO, 2012

**ምስል 7፣ (በቀኝ በኩል) የኮንዶሚኒየም ፕሮጀክቶች ሳይቶች**




*SOURCE*: Elias Yitbarek. Et al, 2011

**የመኖሪያ ቤቶችን ያገኙ 74,653 ተጠቃሚዎች በገቢ ደረጃ ሲነጻጸሩ (ከታች ያለውን ምስል ይመልከቱ)፣**

- **12,968 (17.37%) ስቱዲዮ ቤቶች በዝቅተኛ የገቢ ክልል ውስጥ ለሚገኙ እንደተላለፈ፣**

- 31,169 (41.75%) አንድ የመኝታ ክፍል ያላቸው ቤቶች በመካከለኛ የገቢ ክልል ለሚገኙ እንደተላለፈ፣
- 23,430 (31.39%) ሁለት መኝታ ክፍሎች ያሏቸው ቤቶች ደግሞ በተነጻጻሪ በጥሩ የገቢ ደረጃ ለሚገኙ እንደተላለፈ፤
- 7,086 (9.49%) ሦስት መኝታ ክፍሎች ያሏቸው ቤቶች ደግሞ በተነጻጻሪ በጥሩ የገቢ ደረጃ ለሚገኙ እንደተላለፈ፤


ምስል 8፣ እስከ 2012 የተጠናቀቁና የተከፋፈሉ የኮንዶሚኒየም ዓይነቶች




**ምንጭ፣** Developed based on (AAHDPO, 2012)

በሌላ በኩል እስከ ስድስተኛው የቤቶች የዕጣ ክፍፍል ድረስ ከቀረቡት ቤቶች ውስጥ 63,677 ቤተሰቦች ቤታቸውን የተረከቡ ሲሆን ወደ 21.23% የሚሆኑት ተጠቃሚዎች ግን እስካሁን ድረስ ቤቶቹን አልተረከቡም። ለዚህ ሁኔታ ከሚቀርቡ ምክንያቶች አንዱ የፋይናንስ እጥረት ሲሆን ሌሎችም ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በሌላ በኩል ቤቶቹን ለመረከብ ካልቻሉት ውስጥ 56.25% የተመዘገቡት ለስቱዲዮ ቤቶች ሲሆን 42.35% ደግሞ አንድ የመኝታ ቤት የሚፈልጉ ቤት ፈላጊዎች ናቸው። ከተጠቃሚዎቹ መካከል የገቢ መጠናቸው ሳይታይ 56% ሴቶች ሲሆኑ 44% ደግሞ ወንዶች ናቸው።

ምስል 9፣ ከ2003 እስከ ታህሳስ 2013 ድረስ ጠቅላላ የኮንዶሚኒየም ቤቶች አቅርቦት




ምንጭ፣ Developed based on (AAHDPO, 2012 )

የአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትን የኮንዲኒየም ቤቶች ግንባታን አፈጻጸም በተከታታይ ጊዜያት ሲታይ (ከላይ ያለውን ምስል ተመልከት) እስከ 2005 ድረስ 32,220 ቤቶች የተገነቡ ሲሆን፣ እስከ 2007 ደግሞ 27,705 ቤቶች፣ እስከ 2010 ድረስ 18,347 ቤቶች እንደተገነቡ፣ እስከ 2012 ድረስ ደግሞ 1973 ቤቶች መገንባታቸው እና እስከ 2013 ደግሞ 28,237 ቤቶች ተገንብተዋል። በጠቅላላው እስካሁን ድረስ 108,482 ቤቶች የተገነቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥም ወደ 100,000 የሚጠጉ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ተላልፏል።

ሆኖም ይህ አቅርቦት ከፍላጎቱ ጋር ሲነጻጸር (453,287 የኮንዲሚኒየም ቤት ፈላጊዎች በተጠባባቂ ሊስት ላይ ይገኛሉ) ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በተከናወኑት ሥራዎች 100,00 ቤተሰቦች ተጠቃሚ ሆነዋል። ይህም ማለት እስከዚህ ዓመት ድረስ የፍላጎቱ 22 ፐርሰንት ብቻ ተሳክቷል ማለት ነው። በነገራችን ላይ ይህ ንጽጽር በቅርቡ በተዘጋጀው የቤቶች ዕቅዶች ላይ የተመዘገቡትን ሰዎች (ከነሐሴ - ነሐሴ 2013) አያካትትም።

ፎቶ 11፣ በአዲስ አበባ የተገነቡ ጥቂት የኮንዶሚኒየም ብሎኮች




ስለሆነም በቅርቡ 28,237 የኮንዲሚኒየም ቤቶች ቀድመው ለተመዘገቡ ዕድለኞች ተጠቃሚዎች በይፋ የሎቶሪ ዕጣ የተሰጠውን ጨምሮ እስካሁን ድረስ በጠቅላላው 108,482 ቤቶች ተገንብተዋል። በኮንስትራክሽን ላይ ያሉ ወደ 95,000 ቤቶች ይገኛሉ። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መሠረት የአንድ ቤተሰብ ጠቅላላ መጠን በአማካይ 5 በመሆኑ ከተገነቡት 108,482 የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ከ500,000 በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚዎች ናቸው። በተጨማሪም ከ2012-2013 ባሉት ጊዜያት ውስጥ በግንባታ ላይ ያሉት ቤቶች ሲጠናቀቁ፣ የቤቶች ልማት ፕሮግራም በጠቅላላው 419,475 ዜጎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

**የኮንዲሚኒየም ቤቶችን ስለማስተላለፍ**

በአሥር ክፍለ ከተሞች በሚገኙ 120 የተለያዩ ሳይቶች ላይ ተገንብተው ያለቁ የኮንዲሚኒየም ቤቶችን ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ በተከታታይ ዘጠኝ ይፋ

የሆነ የሎቶሪ ዕጣዎች ተካሂደዋል። የመጀመሪያው ዙር የተካሄደው በ2005 ሲሆን የመጨረሻው እና 9 ኛው ዙር የሎቶሪ ዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት የተካሄደው በ2013 ነው።

ፎቶ 12፣ የሎቶሪ አሸናፊዎች ከሚገለጽባቸው ዘዴዎች አንዱ



SOURCE: UN-Habitat, 2011

ለዘጠኙ የሎቶሪ ዕጣዎች የተዘጋጁትን ጠቅላላ የተገነቡ ቤቶችን ክፍፍል ስንመለከት፣ በመጀመሪያው ዙር----18,988፣ በሁለተኛው ዙር----15,031፣ በሦስተኛው ዙር----11,005፣ በአራተኛው ዙር----15,034፣ በአምስተኛው ዙር----10,769፣ በስድስተኛው ዙር----10,000፣ በሰባተኛው ዙር----7,300፣ በስምንተኛው ዙር----10,653 ቤቶች፣ እና በመጨረሻም፣ ዘጠነኛ ዙር----10,257 ቤቶች ተላልፈዋል። ሆኖም ዕጣው ደርሷቸው ኮንትራት ያልፈረሙና ቤቶቹን ያልተረከቡ ተጠቃሚዎች አሉ።

ዝርዝር ጥናትን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ከአዲስ አበባ ቤቶች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በተደረገ የፎከስ ግሩፕ ውይይት በምክንያትነት የተጠቀሱት ጉዳዮችም፣

- የቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም የገንዘብ እጥረት፣
- ትልቅ የቤተሰብ አባላት ያላቸውን ቤተሰቦች ለማስተናገድ የሚችል የመኖሪያ ክፍሎች ብዛት በቂ አለመሆን፣

- የቀበሌ ቤት ያላቸው አንዳንድ ተጠቃሚዎች በቤቱ መጠን እና በሌሎች ጉዳዮች በቀበሌ ቤቶች መኖርን ይፈልጋሉ[2]

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች እና ሌሎች ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች፣ ሁሉም ቤቶች ለመጀመሪያ ተጠቃሚዎች አልተላለፉም። በመሆኑም ቤቶቹ ለሚቀጥለው ዙር የሎቶሪ ዕጣ እንዲወጣባቸው ይደረጋል። ይህ ዓይነት ሁኔታ በእያንዳንዱ የሎቶሪ ዕጣ ዙሮች ተከስተዋል። ባለቤት ያላገኙት ቤቶችም እስከሚቀጥለው የሎቶሪ ዕጣ ድረስ ክፍት ይሆናሉ ማለት ነው። ይህ ሁኔታ ለዕጣው የቀረቡ ጠቅላላ የቤቶች ብዛት እና ለዕድለኛ ተጠቃሚዎች የተላለፉ ቤቶች ላይ ልዩነት ይፈጥራል።

ፎቶ 13፣ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ኮንዲሚኒየሞች የውስጥና ውጭ ዕይታዎች





[2] አንዳንድ በእንደገና ልማት ሳይቶች እንዲነሱ የተደረጉ ሰዎችም ተተኪ 2 ወይም 3 መኝታ ቤቶች በተለዋጭ ካላገኙ ቤታቸውን ለመልቀቅ ፍላጎት የላቸውም።


 

**መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን ማስተላለፍ**

አሁን ባለው ደንብ መሠረት፣ መደበኛው ዝውውር ከተፈጸመ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ተጠቃሚዎች ቤታቸውን ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችሉም። በዚህም ተጠቃሚ ነዋሪዎች የእያንዳንዱን ቤቶች ሙሉ ወጪ የሚጨርሱበት ጊዜ እንደሆነና በመጨረሻም የቤቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሕጋዊ ሰነድ ይቀበላሉ።


ሆኖም ብዙ ተጠቃሚዎች ቤቶቻቸውን ወደ ሦስተኛ ወገን ያስተላልፋሉ ወይም መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ይሸጣሉ። ተጠቃሚዎቹ ያገኙትን ዕድል የሚያስተላልፉበት እውነተኛ ምክንያቶችን ለማግኘት ዝርዝር ጥናት ማካሄድን ይጠይቃል። ሆኖም ይህ ሁኔታ በከተማዋ በግልጽ የሚታይ /የሚስተዋል ነው። ምንም እንኳን መንግሥት ይህ ሁኔታ እንዳይከሰት ቢፈልግም፣ ሰዎች ይህንን ድርጊት የሚያከናውኑት ገዢው ሰው ለሻጩ ሰው ገንዘብ እንዳበደረ ተቆጥሮ ክፍያውን ይፈጽማል። በህጋዊ መንገድ መደበኛ ያልሆነው ገዢ ከሻጩ ሙሉ የውክልና ሥልጣን ይኖረዋል። አንዳንድ ተጠቃሚዎች ወዲያዉኑ ዕድላቸውን መደበኛ ላልሆኑ ገዢዎች ያዘዋውራሉ። ይህንን የሚያደርጉትም የቅድሚያ ክፍያውን ለመፈጸም የገንዘብ እጥረት አጋጥሟቸው እና የተሻላ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት አስበው ሊሆን ይችላል።

**ምስል 10፣ አሁን ባለው የቤቶች ልማት ላይ የሚሳተፉ ዋና ተዋናዮች አስተዋጽኦ**




**ምንጭ፣** Demeke, 2012.

**ምስል 11፣ በአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ዋና ተዋናዮች ያሉበት ሥፍራ (እስከ 2012)**



**ምንጭ፣** Elias Yitbarek, et al 2011

## 2.6 *የኮንዶሚኒየም ቤቶች ጽንሰ ሃሳብ*

**ትርጉም**

***ኮንዶሚኒየም ወይም ኮንዶ ማለት የቤት ባለቤትነት እና ሌላ የሚጨበጥ ንብረት ዓይነት ሲሆን ከኮንዶሚኒየሙ የተወሰነ ክፍል በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት የተያዘ ሆኖ ሌሎች የጋራ የሆኑ ፋሲሊቲዎች ማለትም መገልገያዎች፣ ኮሪደሮች፣ ማሞቂያዎች፣ ሊፍቶች እና በግቢው ውስጥ ያሉ ቦታዎችን የመጠቀም ከሕግ መብቶች ጋር የተያያዘ የግለሰብ ባለቤትነት ሲሆን ቁጥጥሩ የሚካሄደው ግን የሁሉንም አካላት በጋራ ባለቤትነት በሚወክለው የባለቤቶች ማህበር ነው*** (The free encyclopedia, 2013) ፡፡

**የኮንዶሚኒየም ባለቤትነት ምን ማለት ነው?**

በኮንዶሚኒየም ውስጥ ያሉ ቤቶች በግለሰቦች፣ በቤተሰቦች፣ በድርጅቶች ወይም በከተማ መስተዳድሩ የተያዙ ናቸው፡፡ በኮንዶሚኒየም ውስጥ ያሉ ቤቶች ወይም የንግድ ድርጅቶች (ሱቆች፣ ቢሮዎች እና የመሳሰሉት) ቤቶች ተብለው ይጠራሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት እና በቤትነት ያልተወሰዱት "የጋራ ሃብት" ተብለው ይወሰዳሉ፡፡ እነዚህ የጋራ ሃብቶች በህንጻው ውስጥ ባሉ ሰዎች በጋራ የሚያዙ ናቸው፡፡ በብዙ ህንጻዎች እነዚህ የጋራ ሃብቶች የሚባሉት ጣራዎችን፣ ደረጃዎችን፣ የውጭ ግድግዳዎችና መስኮቶችን፣ የህንጻው መሠረት፣ እንደ ቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ ገመዶችና የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም በህንጻው አካባቢ ያለው መሬት ማለትም የአትክልት ሥፍራ ካለ፣ መጫዎቻ ቦታዎችን ጨምሮ የኮንዶሚኒየም ኗሪዎች በጋራ ኃብትነት የሚያዙ ናቸው፡፡

**የባለቤትነት ድርሻ**

ከላይ እንደምንረዳው እያንዳንዱ የኮንዶሚኒየም ኗሪ ካሉት የጋራ ቤቶች የባለቤት ድርሻ አለው ማለት ነው፡፡ ለእያንዳንዱ የኮንዶሚኒየም ባለቤት የተቀመጠው ይሄው ባለቤትነት "የባለቤትነት ድርሻ" የሚባል ሲሆን ስሌቱም እንደሚከተለው ነው።

የባለቤትነት ድርሻ = የአንዱ ዩኒት ጠቅላላ ስፋት/ የሁሉም ዩኒቶች ጠቅላላ ስፋት የባለቤትነት ድርሻ ብዙ ጊዜ በፐርሰንት ይገለጻል፡፡ የጋራ ሃብት ጠቅላላ ስፋት የሁሉም ዩኒቶች ጠቅላላ ስፋትን አይጨመርም፡፡ የባለቤትነት ድርሻ ክፍፍሉ የሚያገለግለው በኮንዶሚኒየሙ የጋራ ሃብት ላይ ብቻ ነው፡፡ በልዩ ህግና መመሪያ እስካልተገደበ ድረስ እያንዳንዱ የኮንዶሚኒየም ኗሪ ያለበትን

ቤት በተመለከተ ሙሉና ያልተገደበ ነጻነት አለው። የኮንዶሚኒየም ኗሪዎችን የባለቤትነት ነጻነት ከሚገድቡ ህጋዊ ምክንያቶች እንደምሳሌ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል። (ሀ) የቤቱ አጠቃቀም ላይ ለውጥ ሲኖር ለምሳሌ፣ ከመኖሪያነት ወደ ንግድ ሲለወጥ፣ (ለ) የኮንዶሚኒየም ቤቱ ሲከፋፈል። የባለቤትነት ድርሻ ክፍፍል ለኮንዶሚኒየም ባለቤቶች በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ይህ የባለቤትነት ድርሻ ክፍፍል የጋራ የሆኑ የኮንዶሚኒየም ቦታዎችን ለመጠበቅና ለማደስ/ለመጠገን የሚወጡ ወጭዎችን እንዲሁም የባለቤቶች ማህበር የሥራ ማስኬጃ ወጭን በተመለከተ የሚወጣውን የወጭ ድርሻን ለማሳወቅ ስለሚያስችል ነው።

**የባለቤቶች ማህበር፤ አደረጃጀትና ተግባሩት**

በኮንዶሚኒየም ውስጥ የባለቤቶች ማህበር የሚባለው የግል፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። ግለሰብ የኮንዶሚኒየም ባለቤቶች ኮንዶሚኒየሙን ሲገዙ የማህበሩ አባላት ይሆናሉ። የኮንዶሚኒየም ባለቤት መሆንና የማህበር አባል መሆን አይነጣጠሉም። አንድ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤት ቤቱን ለሌላ ሰው ሲሸጥ በማህበሩ ያለውንም ባለቤትነት ለአዲሱ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤት እንዲሁም አባልነቱንም ያስተላልፋል። የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች ማህበር ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማህበር ነው።

ፎቶ 14፣ በኮንዶሚኒየም የሚገኙ አንዳንድ የጋራ ይዞታዎች ገጽታ







***የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጥቅሞች***

በትክክል በሚሰራ የቤቶች ገበያ ጥሩ የሆነ ኮንዶሚኒየሞች ውስጥ የሚኖሩ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች ብዙ ጥቅሞች አሏቸው፡፡

**ከሥጋት ነጻ የሆነ የይዞታ ባለቤትነት**

ንብረቶች ወደ ግል ይዞታነት ከመተላለፋቸው በፊት ብዙ ሰው በሚኖርባቸው ህንጻዎች የሚኖሩ ሰዎች ከስጋት ነጻ የሆነ የይዞታ ባለቤትነት ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ በግል የቤቶች ንግድ ይህ ከስጋት ነጻ የሆነ የይዞታ ባለቤትነት በህግ በተሰጣቸው ባለቤትነትና በሊዝ የተገደበ ነው፡፡ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች የኮንዶሚኒየሙን ህግ እስከአከበሩ ድረስ ከስጋት ነጻ የሆነ የይዞታ ባለቤትነት አላቸው፡፡ ማንም ኗሪነታቸውን ሊቀማቸው አይችልም፡፡

**የቤቶች ነጻነት ዋጋ ያለው ኢንቨስትመንት ነው**

የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች ቤታቸውን የመጠቀም፣ የማከራየት ወይም የመሸጥ ልዩ ነጻነት አላቸው፡፡ ከቤቶች የሚገኝ ማንኛውንም ገቢ በነጻነት መጠቀም ይችላሉ፡፡ የቤቶች ገበያ ባደገ ቁጥር ደግሞ የቤቶች ኢኮኖሚያው ዋጋም እያደገ ይመጣል፡፡ በየትኛውም የንብረት ገበያ ላይ እንደሚታየው ቤቶች ያሉበት አካባቢ፣ ጥራትና ዓይነት ዋጋቸውን ይወስነዋል፡፡ የቤቶች ባለቤቶችና አጠቃላይ ማህበሩ ኮንዶሚኒየሞችን በአግባቡ ለመያዝና ለመጠገን ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉላቸው ኮንዶሚኒየሞች ይህን ከማያገኙት የኮንዶሚኒየም ቤቶች የተሻለ ዋጋ ያወጣሉ፡፡

አንድ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤት ከዚያ ኮንዶሚኒየም መውጣት ቢፈልግ ሊያከራየው ወይም ሊሸጠው ይችላል፡፡ በደንብ የተያዙ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን መሸጥ ወይም ማከራየት ትልቅ፣ የተሻለ ወይም በተሻለ አካባቢ የሚገኝ ቤት ለመግዛት ያስችላል፡፡

ፎቶ 15፣ በዝቅተኛና በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች አዲሱን ኑሯቸውን ሲያጣጥሙ









**የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች ኪራዩ አይከፍሉም**

የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች በራሳቸው ሃብት ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ፡፡ ቤት ተከራዮች በቤት ኪራይ ጭማሪ ላይ ብዙም ነጻነት የላቸውም ወይም ከኪራይ ገንዘቡ ምን ያህሉ ቤቱን ለማሻሻል እንደሚውል ወይም ምን ያህሉ ባከራዩ ኪስ ውስጥ እንደሚገባ መወሰን አይችሉም፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤቶች በራሳቸው ቤት ላይ ነው ኢንቨስት የሚያደርጉት፡፡ ዋጋ የመወሰን ሙሉ ነጻነትም አላቸው፡፡ እንዲሁም ካላቸው ገቢ ምን ያህሉን ለቤቱ ማሻሻያ እንደሚውል የሚወስኑትም እነሱ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ገንዘቡ ምን ላይ መዋል እንዳለበት የሚወስኑት እነሱ ናቸው ፡፡

## 2.7 *በአዲስ አበባ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ልምድ*

**የኮንዶሚኒየም ቤቶች የአድራሻ መረጣ**

የመጀመሪዎቹ የኮንዶሚኒየም አድራሻ መረጣ በ1997 የአዲስ አበባ የማስተር ፕላን መሠረት ነበር፡፡ በዚህም አዳዲስ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን ለመስራት ምቹ የሆኑ ቦታዎች ያሉትን አረንጓዴና ቡናማ ሜዳዎችን በማየት ተመርጠዋል፡፡ አማካሪዎችም ተቀጥረው ስለቦታዎቹ የመያዝ ችሎታ፣ የአካባቢው ሁኔታ፣ የውሃ አቅርቦት፣ የመንገድ ሁኔታ፣ ከብክለት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንዳሉ፣ የአካባቢው ነዋሪ ኮንዶሚኒየም ለመኖር ያለው ፍላጎት፣ እና ያለውን የኢኮኖሚያውና አካባቢያው ሁኔታ እንዲያጠኑ ተደርጓል፡፡ እነዚህ አማካሪዎች በተጨማሪም ትልልቅ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሲካሄድ በአካባቢው ባለው ማህበራዊ ሁኔታ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በተመለከተ ጥናት እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡ በነዚህ ጥናቶች አካባቢዎቹ ለኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ምቹ መሆናቸው ሲረጋገጥ ቦታውን ለመጠቀም እንዲቻል በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ለሚመራው የመሬት ቦርድ ጥያቄ ይቀርባል፡፡

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት አንዱ ዓላማ የደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን ማሳደግ ቢሆንም፤ እስከአሁን በአዲስ አበባ የተከናወኑት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታዎች በባዶ ቦታዎች ወይም ለሌላ ተግባር በተያዙ ሌሎች አካባቢዎች ላይ ነው፡፡ ይህ የተደረገበት ዋናው ምክንያት የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን ለማንሳት ሲታሰብ የሚመጣውን ማህበራዊ ዋጋ ለመቀነስ ነው፡፡

ይሁን እንጂ መሃል ከተማዋን ማልማት አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ መንግሥት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ በከተማዋ ዳርቻ የሚሰሩ አዳዲስ ቤቶችን ማገዱ ነው። የዚህ አካሄድ ዋና አላማም ምጥን ያለ የከተማ ዕቅድን ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን ይህም የመሠረተ ልማትን ለመገንባት የሚወጣውን ወጭ ለመቀነስ ያስችላል። ለምሳሌ፣ አሁን ያለው የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓት የከተማዋን 3 በመቶ ብቻ ነው የሚሸፍነው።

**የመጀመሪያዎቹ የኮንዶሚኒየም ሠፈሮችና የቤቶች ዲዛይን**

የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ቢሮ በተመረጡት የቤቶች ልማት አካባቢዎች ለሚሰሩ ህንጻዎች ዲዛይን እንዲቀርብ ውድድር አውጥቶ ነበር። የቤቶቹ ብሎኮች በአብዛኛው የተወሰኑ ቢሆንም (ማለትም የቤቶች አይነት ቁጥርና የፎቅ ብዛትና የመሳሰሉት) የወጣው ውድድር ለቤቶች ዲዛይን፣ ለብሎኮች አቀማመጥና ክፍት የሚተው ቦታዎችን ያካትታል። በውድድሩ አሸናፊዎች ከተመረጡ በኋላ ዲዛይኑን እንዲሰሩ ተደርጓል። የተሰሩት ዲዛይኖች የግል ኮንሰልታንቶችና የመንግሥት አርክቴክቶች ላሉበት የገምጋሚ ቡድን ቀርቦ ማስተካከያዎች ተደርገውበታል።

ምስል 12፣ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ዲዛይን ዓይነት





በአዲስ አበባ የመጨረሻው የዲዛይን ለውጥ የተደረገው በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ቢሮ ነው። ይሁን እንጂ ሥራውን የማደራጀት ሂደት የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ቅርንጫፎች ነው።

**መሬት ማጽዳት፣ ካሳ ክፍያና ጊዜያዊ መልሶ ማስፈር**

በአረንጓዴና ቡኒ ሜዳዎች/አካባቢዎች የካሳ ክፍያና መልሶ ማስፈር ብዙም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ለታሰበው ልማት የተመረጠው ቦታ በቀበሌ ቤት የተያዘ ከሆነ ከኗሪዎች ጋር ስለኮንዶሚኒየም ልማት ሰፊና ግልጽ ውይይት ለማድረግ ዕቅድ ይይዛል፡፡

በኮንዶሚኒየም ልማት ምክንያት ወደሌላ ቦታ መዛወር የነበረባቸው ቤተሰቦች አንድም ወደሌላ ቀበሌ ቤት እንዲዛወሩ ተደርገዋል፣ የካሳ ክፍያ እንዲያገኙ ወይም ከአዲሱ ኮንዶሚኒየም እንዲወስዱ የቅድሚያ ዕድል ተሰጥቷቸዋል፡፡ የኮንዶሚኒየም ቤት ለመግዛት ከተስማሙ ኮንዶሚኒየሙ ተሰርቶ እስኪያልቅ ድረስ በጊዜያዊነት በተሰሩ የእንጨት ወይም በቆርቆሮ በተሠሩ ቤቶች እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡

ፎቶ 16፡ በልደታ የነበሩ ያረጁ ቤቶችን መልሶ ለማልማት የአካባቢ ማጥራት ሥራ ሲከናወን





**የህንጻ ሥራ ተቋራጭ ማሰማራት**

በኮንዶሚኒየም ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ ለመሳተፍ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተመዘገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የትኞቹ ድርጅቶች እንደሚሳተፉም ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ የኮንስትራክሽን ድርጅቶችም እንደአላቸው ልምድ በደረጃ የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ ደረጃ ስድስት ከፍተኛው ሲሆን በቂ ልምድ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ የግንባታ ተቋራጮች የኮንዶሚኒየም ብሎክ ግንባታን ለመውሰድ ቢያንስ ደረጃ 5 ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው የኮንዶሚኒየም ብሎክ ስራ ለመውሰድ ይጠየቅ የነበረው የአስራ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ አስቸጋሪ በመሆኑ ወደ አራት አመት ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮጀክቶችን ለመኮናተርም ኢንጂነሮች ቢያንስ ሶስት ዓመት የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የእያንዳንዱን ብሎክ ስትራክቸር ለመገንባት የተለዩ የህንጻ ተቋራጮች እንዲቀጠሩ ተደርጓል፡፡ ቀሪዎቹን የኮንዶሚኒየም ሥራዎች ማለትም ክፍሎቹን መሙላት፣ የቧንቧና የኤሌክትሪክ ሥራ፣ የመጨረሻውን ሥራ መስራት ለጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ይህም አነስተኛ ሥራዎችን ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች መስጠት ዓላማውም የእነዚህን ድርጅቶች ብቃት ለማሳደግ፣ የሚወጣውን ወጭ ለመቆጠብ፣ የግንባታውን ጥራት ለማሳደግ በሚያስችል ሁኔታ ውድድርን ለማምጣትም ጭምር ነው፡፡ የግንባታዎችን ጥራት ለመቆጣጠርና ለማስጠበቅም አማካሪዎች ተቀጥረዋል፡፡
የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅም ነበር፡፡ ጽ/ቤቱ ለእያንዳንዱ የፕሮጀክት ኮንትራክተር ሥራዎችን ይደለድል ነበር፡፡ እያንዳንዱ ተጫራች ኮንትራክተሮችም ከጽ/ቤቱ ጋር በስፔሲፊኬሽኑ ላይ

በመነጋገር በመንግሥት በተቀመጠው ዋጋ ሥራውን ለመስራት ፈቃደኛነታቸውን እንዲወስኑ ይደረጋል፡፡ ኮንትራክተሮች በተቀመጠው ዋጋና የዕቃዎች ዋጋ ላይ ከተስማሙና ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ የመጨረሻው ደረጃ የሚሆነው ኮንትራክተሮቹ ለቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስምምነታቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ሲጽፉ ይሆናል፡፡

የኮንዶሚኒየም ብሎኮችን ግንባታ ለማከናወን የተለያዩ ተቋራጮች የተለያየ ድርሻ/ፐርሰንት እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ ብዙ ጊዜ ደረጃ 6 ተቋራጮች ሁለት ብሎኮችን፣ ደረጃ 5 ተቋራጮች ሶስት ብሎኮችንና ደረጃ 4 ተቋራጮች ደግሞ አራት ብሎኮችን እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

**የግንባታ ደረጃ**

የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ አንዱ ልዩ ባህሪው የግንባታ ቁሳቁሶች ማዕከላዊ በሆነ ሁኔታ ለፕሮጀክቶቹ መሰጠቱ ነው፡፡ የዕቃዎቹን ጥራትና ዋጋ ለመጠበቅ ሲባል ሁሉንም ዕቃዎች በጅምላ ማለትም ሲሚንቶ፣ አርማታ ብረት፣ የኤሌክትሪክና የቧንቧ ዕቃዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የሚገዛው የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በተቋራጮች ሊያጋጥም ይችል የነበረው የቁሳቁሶች ማለቅ አልተከሰተም፡፡

የግንባታው ጥራትም በየሳይቶች በመገኘት ፍተሻ በሚያደርጉ አማካሪዎች ይረጋገጣል፡፡ የነበረው የጥራት ደረጃም ዝቅ ብሎ ከታየ አዳዲስ ኮንትራክተሮች ይቀጠራሉ፡፡

ፎቶ 17፡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ግንባታ ደረጃዎች



**የግንባታ ጥራት**

ከኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ጋር በተያያዘ ብዙ የሚወራለት ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ከስትራክቸር፣ ከቧንቧና የጽዳት ዕቃዎች አገጣጠም እና አጨራረስ ጋር የጥራት ጉድለት መኖሩን ነው። ይሁን እንጂ ይህ የጥራት ችግር ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል። ከጥራቱ መሻሻል እንዲሁም የቤቶች እጥረት ካመጣው አመለካከት ጋር ተያይዞ አሁን የኮንዶሚኒየም ኗሪዎችም ሆኑ ሌሎች በኮንዶሚኒየም ቤቶች ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ነው። አሁን በተጠባባቂነት ያሉትም ሆነ ያልተመዘገቡ ግን ኮንዶሚኒየም ቤት እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ሰዎች ምኞት እድለኛ ሆነው አንድ ቤት እንዲኖራቸው ነው (Demeke H, 2012.)።

**የቤቶች ክፍፍልና ድልድል**

ከላይ በተገለጸው መሠረት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ደረጃ 80 ፐርሰንት ሲደርስ ሎቶሪ ለማውጣት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ምዝገባ እንደሚጀመርና በቀጣይም ዕጣ እንዲወጣ ይደረጋል። የዕጣው ውጤትም በኢንተርኔት፣ በጋዜጣና በቀበሌዎች ማስታወቂያ ሰሌዳዎች እንዲወጣ ይደረጋል። ዕጣ የወጣላቸው ባለዕድሎችም በቤቶች ማስተላለፊያ አስተዳደር ቢሮ በመቅረብ ለመጀመሪያ ደረጃ ሽግግር "ፎርም ቁጥር 3"ን በመሙላት ኮንትራት እንዲገቡ ይደረጋል። ባለዕድሎች ከባንክ ብድር መውሰድ የሚፈልጉ ከሆነ ይህንን ፎርም ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመውሰድ የብድር ጥያቄያቸውን ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ፎርም ለባንኩ ዕጣው የደረሳቸው ሰዎች ባለዕድሎች መሆናቸውንና ከቤቶች ልማት ጽ/ቤት ጋር ኮንትራክት መግባታቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ከዚያም በቤተሰቡ መከፈል ያለበትን 20 ፐርሰንት ተቀማጭ እንዲከፍሉ ይደረጋል። ይህ ከተከፈለ በኋላ ባንኩ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ ይህንን ደረሰኝ እና ፎርም ቁጥር 3ን በማያያዝ ለቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በማቅረብ የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ይጠይቃሉ።

የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለባለዕድሎች የስምምነት ፎርም በማቅረብ እንዲፈርሙ ያደርጋል። ከዚያ በኋላ ፎርሙ ለመሬት አስተዳደርና ለባንክ እንዲላክ ይደረጋል። በተጨማሪም ባለዕድሎቹ 200 ብር ወይም 15 የአሜሪካ ዶላር እና የብድራቸውን 1.03 ፐርሰንት የቴምብር ቀረጥ ለመሬት አስተዳደር እንዲከፍሉ ይደረጋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከደንበኛው ጋር ይህንን የብድር ስምምነት ከፈረሙ በኋላ ፎርሙን የቤቱን ቁልፍ ለሚያስረክቡት የክፍለ ከተማ ጽ/ቤቶች ይላካል።

ብዙ የኮንዶሚኒየም ባለዕድሎች በቤቶቹ ላይ ሊከሰት የሚችለውን ስርቆት ለመከላከል ሲሉ ወደቤታቸው የሚገቡት የቤቶቹ ሥራ ከመጠናቀቁ በፊት ነው።

ፎቶ 18፣ የኮንዶሚኒየም ባለዕድሎች አዲሱን ኑሮ ለመጀመር ወደ ኮንዶሚኒየም ቤቶቻቸው ሲገቡና ከገቡ በኋላ











**ወደ ኮንዶሚኒየማቸው ከገቡ በኋላ ያለው ሁኔታ**

አንዴ ነዋሪዎቹ ወደቤታቸው ከገቡ፣ ፕሮጀክቱ አለቀ ማለት ነው። ወደ ኮንዶሚኒየም ከተገባ በኃላ የተለያዩ ሁኔታዎች የተከሰቱ ቢሆንም የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ነዋሪዎች አዲሱን የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሕይወት እንዲለማመዱ ለማድረግ ሁለት የተጻፉ መመሪያዎችን አዘጋጅቷል። የመጀመሪያው መመሪያ የአሠራር ሥነምግባር ሲሆን፣ ሁለተኛው በዩኒቱ መሠረታዊ የጥገና ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው የሚዘረዝር ነው። ከዚህ ሌላ መንግሥት ፕሮጀክቶቹን የሚከታተልበትና የሚገመግምበት ሁኔታ የለም።

## *2.8 በኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ትክክለኛው ተጠቃሚ ማነው?*

በ2005 የተደረገው የመጀመሪያው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ምዝገባ ተመዝጋቢዎችን በኑሮ ደረጃ የለየ አልነበረም እንዲያውም ሌላ ቤት ያላቸውና ከአንድ በላይ ቤት ያላቸውም እንዲመዘገቡ ተደርጓል። የሪል እስቴት ባለቤቶች ሆነው ከቤቶች ሽያጭ ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ የኮንዶሚኒየም ቤት ለማግኘት የተመዘገቡ ሰዎችም ይኖራሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በከተማዋ የቤቶች ሽያጭ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ዋጋው ከፍ እንዲል ያደረጉ የቤት ሽያጭ ደላሎች እንዲበራከቱ አድርጓል። ይህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶችን ችግር ለመቅረፍ እያደረጋቸው ያሉ ጥረቶች እንዳሉ ሆኖ በተለያየ መልክ ይንጸባረቅ ነበር። ለምሳሌ፣ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ኪራይና ሽያጭ መጨመር። በዚህ መንገድም የሚደረገው የቤቶች ኪራይና ሽያጭ በህጋዊ መንገድ የሚደረገውን የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሽያጭና ኪራይ በከፍተኛ ሁኔታ ጎድቶታል። ሌላው ከዚህ ጋር የተያያዘው ጉዳይ ደግሞ ህጋዊ ባልሆነው የኮንዶሚኒየም ሽያጭ ላይ በደህና የኢኮኖሚ ደረጃ የሚገኙ ኗሪዎች መሳተፋቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ወይ ከውጭ ገቢ አላቸው ወይም ደግሞ ገቢያቸውን ከፍ ለማድረግ በከተማዋ ውስጥ በተለያዩ ሥራዎች የተሰማሩ ናቸው። ይህ ሁሉ ከኮንዶሚኒየም ቤቶች ጋር በተያያዘ ያጋጠመው ከህግ ውጭ የሆነ ሂደት የጎዳው የኮንዶሚኒየም ቤት ባለዕድል ያልሆኑትንና እያደገ በመጣው የግል ቤቶች የኪራይ ማደግ የተማረሩትን በዝቅተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉና የመንግሥት ሠራተኞችን ነው።

የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የቤቶች እጥረት ለማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም ሃብታሞችና በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችም የቤቶችን ገበያ እንደፈለጉ በማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጠቀሙ አድርጓቸዋል።

ፎቶ 19፣ በተሻለ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ተጠቃሚ ነዋሪዎች



በሌላ በኩል ደግሞ የኮንዶሚኒየም ቤታቸውን የተሻለ ገቢ ለማግኘት ሲሉ በማከራየት በከተማዋ ዳርቻዎች በአነስተኛ ዋጋ ቤት በመከራየት የሚኖሩ ባለእድሎች በርካታ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ገቢያቸውን ከፍ በማድረግ ፍላጎቶቻቸው ለማሟላት አስችሏል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሁኔታ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችና ታዛቢዎች በኮንዶሚኒየም ቤቶች አካባቢ የሚታዩትን በርካታ የሳተላይት ዲሾችና የመኪናዎች ብዛት በማየት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ለዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ ላሉ ነዋሪዎች ሳይሆን በተሻለ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እዚህ ያገኙትን የኮንዶሚኒየም ቤት ዕድል ለፋይናንስ ጥቅም ሲሉ ለሌሎች በመሸጣቸው ያጋጠማቸውን ወርቃማ ዕድል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጥተዋል፡፡

በከተማዋ ውስጥ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከሚታዩት እውነታዎች አንዱ በርካታ የሶማሊያ ዜግነት ያላቸው ዜጎች በተለያዩ የኮንዶሚኒየም ሳይቶች ላይ ለምሳሌ "ቦሌ መድሃኒያለም" "መብራት ሃይል" መኖራቸው ነው። ሌሎች ደግሞ በአብዛኛው በተከራዮች መያዛቸው ነው። ሆኖም የመጀመሪያዎቹ የኮንዶሚኒየም ባለዕድሎች በዝቅተኛና በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ አይደሉም ማለት አይደለም። አሁንም ቢሆን ግን ይህ የባለዕድሎች ሽያጭና ኪራይ ሁኔታ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ፕሮጀክት ተጠቃሚ ያደረገው ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ኗሪዎች ነው የሚለውን አመለካከት በብዙዎች ዘንድ ይስተዋላል።

ሠንጠረዥ 5፣የኮንዶሚኒየም ባለዕድሎች የክፍያ ሁኔታ በዓይነት

| የቤት አይነት | ቅድሚያ ክፍያ | የወለድ ምጣኔ | የእፎይታ ጊዜ | የመክፈያ ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| ስቱዲዮ | 10% | 0% | 6 ወራት | 20 ዓመት |
| አንድ መኝታ ቤት | 10% | 2% | 3 ወራት | 10 አመት |
| ሁለት መኝታ ቤት | 30% | 7.5% | - | 15 ዓመት |
| ሦስት መኝታ ቤት | 30% | 7.5% | - | 10 ዓመት |
| የንግድ | 100% | - | - | - |

*ምንጭ*: Berhanu & Mesfin, 2012.

ከላይ ካሉት እውነታዎች በተጨማሪም የሪል ስቴት ቤቶችና የኮንዶሚኒየም ቤቶች የጥራት ደረጃ ብዙም ልዩነት ባይኖረውም የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሽያጭ ከሪል ስቴት ቤቶች ሽያጭ በጣም ያነሰ ነበር። ለምሳሌ፣ በአንድ ሪል ስቴት ውስጥ ያለ ቤት በሜትር ስኴር ብር 15,000 ቢያወጣ፣ የኮንዶሚኒየም ቤት ግን ከብር 2000 እስከ 2500 በሜትር ስኴር ያወጣል። ይህም እውነታ ብዙ ሃብታም ሰዎችን በመሳብ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በርካታ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛት የኪራይ ዋጋን ከጊዜ ወደጊዜ ከፍ በማድረግ በቤቶች ገበያ ወሳኝ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ያሉት ሁኔታዎች እንደሚያሳዩት የቤቶችን ቁጥር ከመጨመር አንጻር የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ የከተማዋ የቤቶችን ቁጥር ከመጨመር አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም፣ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ፕሮጀክት ዋና ዓላማ የነበረው የዝቅተኛና መካከለኛ ኗሪዎችን የቤት ችግር ከመቅረፍ አንጻር 100 ፐርሰንት የተሳካ ነው ለማለት ግን አይቻልም። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ምክንያት እያደገ ያለው የቤቶች ኪራይ መጠን እንኳን ዝቅተኛ ገቢ

ያላቸውን ይቅርና የተሻለ ገቢ ያላቸውን የመንግሥት ሠራተኞችን እየተፈታተነ ይገኛል፡፡ ይህም ካለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በከፊል የተገናኘ ነው፡፡

## 2.9 ከኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ጋር በተያያዘ ያሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ማጠቃለያ

- እንደሲሚንቶና የአርማታ ብረት ዓይነት የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶች ዋጋ መናር፣
- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች ያልተሻሻለ የቅድሚያ ክፍያ፣
- በተግባር ላይ ላለው ከዕጣ ጋር የተያያዘ ሽግግር አማራጭ አነስተኛ መሆን፣
- በጣም ዘግይቶ ከመስተካከሉ በፊት ግልጽና አስተማማኝ የዕጣ ስርዓት ያለመኖር፣
- የራሳቸው ቤት ያላቸውንና ቤት የሚያስፈልጋቸውን በትክክል ሊለይ የሚችል ውጤታማ የሆነ የመመረጫና መለያ ስርዓት ያለመኖር፣ (ይህ በአዲሱ የምዝገባ ስርዓት እንዲስተካከል ተደርጓል)፣
- የአገልግሎቶች አሰጣጥ መዘግየት፣
- የግንባታው ሂደት መዘግየት፣
- ከዕጣ መውጣት በኋላ ለባለዕድሎች ቤቶችን የማስተላለፍ ሂደት መዘግየት፡፡

## 3. የቤቶች ፖሊሲዎች ዳሰሳ

በግንቦት 1991 የተካሄደውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ለሽግግር ጊዜው የሚያገለግል አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በህዳር 1991 አውጥቶ ነበር፡፡ የዚህ ፖሊሲ አንቀጽ 8 በሽግግሩ ወቅት ስለሚኖረው የከተማ መሬትና የቤቶች ግንባታ የሚናገር ነው፡፡ ይህ ፖሊሲ መንግስት የከተማ ቤቶችን ወደግል በማዞር የቤቶችን ገበያ ለማሻሻል ያለውን ፍላጎት ያንጸባርቃል፡፡ አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ 8.1.1 እስከ 8.1.4 ከከተማ ቦታና ቤት ጋር በተያያዘ የመንግሥትን ሚና በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ንዑስ አንቀጾቹ የሚከተሉትን አስቀምጠዋል፦

- የከተማ ቦታ ባለቤትነት በመንግሥት እጅ ይሆናል ሆኖም ቤት ለመገንባት ለሚፈልጉ ያለመድልኦ እንዲከፋፈል ይደረጋል፣
- መንግስት ሰዎች ቤቶቻቸውን በመገንባታቸው ሊያገኙ የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ መመሪያዎችንና ደንቦችን ያወጣል፣ ምቹ ሁኔታዎችንም ይፈጥራል፡፡

- አቅም በፈቀደ መጠን የመንግስት ኤጀንሲዎች ዝቅተኛ ወጭ የሚያስወጡ ቤቶችን ለኪራይና ለሽያጭ ይገነባሉ፡፡
- መንግስት በቤት ባለቤቶችና በተከራዮች መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት መመሪያ ያወጣል፡፡

የፖሊሲው ንዑስ አንቀጹ 8.2 የግል ኢንቨስተሮችን በከተሞች ልማትና በግንባታው ሴክተር ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ አስፈላጊነት ያስቀምጣል፡፡ የግሉ ሴክተር ትልቁን ሚና መጫወትን አስፈላጊነት ያሰምርበታል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 ዝርዝር አፈጻጸሙን አስቀምጠዋል፡፡ ቤቶችን ለመኖሪያነት ወይም ለሌላ አገልግሎት መገንባት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ባለው የመንግስት መመሪያ መሠረት ቦታ ሊያገኝ ይችላል፣ የይዞታ ባለቤትነትም ይሰጠዋል፣ በዚህም ቤቱን መሸጥ፣ ማከራየት፣ ለሌሎች ማስተላለፍና ሌሎች የተያያዙ ጉዳዮችን ማካሄድ ይችላል፡፡ ፖሊሲው ቤቶችን በግል ወይም በጋራ ለመገንባት የሚቻል መሆኑን ያስቀመጠ ሲሆን የማህበራት ቤቶች ግንባታንም ያበረታታል፡፡ በመንግስት የተወረሱ ቤቶችን መሸጥ የተፈቀደ ሲሆን የቀድሞው የቤቶቹ ባለቤቶች ወደፊት በሚካሄድ ጥናት መሠረት የካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው እንደሚችል ተመልክቷል (Tadesse, G.G, 2000)፡፡

በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው መንግሥት በዝቅተኛ ወጪ የሚሰሩ ቤቶችን ግንባታ ይደግፋል፡፡ በተጨማሪም አዋጁ ህዝብን በቀጥታ ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ማህበራዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች ያለ ሊዝና ያለጨረታ እንደሚሰጥ ተቀምጧል፡፡ ይህ አበረታች የሆነ ሁኔታ ቢኖርም የግሉ ሴክተር በቤቶች አቅርቦት በተለይ ደግሞ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ከመጥቀም አንጻር የነበረው አስተዋጽኦ አርኪ አልነበረም (Tadesse, 2000) ፡፡

ከ1991 ጀምሮ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በነጻ ኢኮኖሚ ስርዓት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ መሬትን በተመለከተ ያለውን እጥረትም መሠረት በማድረግ መሬት በመንግሥት ባለቤትነት ተይዟል፡፡ ይህም ሁኔታ አዲስ የቤቶችና የመሬት ፖሊሲ እንዲወጣ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ረገድ ዋናው ለውጥ በብሔራዊ ደረጃ የመሬት ሊዝ ፖሊሲ ተግባራዊ መደረጉና ከዚህ ቀደም ለቤት ማህበራት ይሰጥ የነበረው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲቀር መደረጉ ነው፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ የአዲስ አበባ ክልል መስተዳድር በ1993 የመሬት ሊዝ ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ ይህ ፖሊሲ ለግል አገልግሎት ዝቅተኛው 73 እና ከፍተኛው 175 ስኴር ሜትር እንዲሆንና የመጨረሻው የሊዝ መክፈያ ጊዜ ደግሞ 99 ዓመታት እንዲሆን ወስኗል፡፡ ብዙ ቦታዎችም በዕጣ ለአመልካቾች እንዲከፋፈሉ ሲደረግ፣ የዓመት ኪራዩ 0.5 ብር

በሜትር ካሬ እንደነበረና በኃላም 3 ብር በሜትር ካሬ ሆኗል። አሁን ያለው የመሬት ክፍፍልና የቤቶች ግንባታ ፖሊሲ 20 በመቶ በቅድሚያ መክፈልን የሚጠይቅ በመሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ኗሪዎች እንዳይሳተፉ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም ከ2001 ጀምሮ ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኘው 2ኛው ብሔራዊ የልማት ዕቅድ መሠረት አሁን ያለው መንግሥት ለቤቶችና ለከተማ ልማት ከፍተኛ ትኩረትን ሰጥቷል፡፡ በተለይም ትኩረት የሰጠው ለሪል ስቴት አልሚዎች፣ ለግል አልሚዎች እና በዝቅተኛ ዋጋ ለሚገነቡ ኮንዶሚኒየሞች ነው፡፡ አሁን ያለው ትኩረት በቤቶች ግንባታ ላይ ብቻ ያተኮረ አልነበረም፡፡ ከሌሎች የልማት ፕሮግራሞች ጋርም ቅንጅትን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የቤቶች ግንባታ ከጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ጋር በማቀናጀት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህም ለቤቶች ግንባታ እንደግብዓት ከማገልገሉም በላይ ሌሎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እንዲያድጉ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም የቤቶችን ግንባታ ከሌሎች ሥራዎች ጋር ማቀናጀት ለሙያ ትምህርት ቤት ተመራቂዎችና ሌሎች የግንባታ ሠራተኞች ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዕድልን ፈጥሯል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አካሄድ በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ ለሚሰሩት የግንባታ ሠራተኞች የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት አስችሏል፡፡ ይህ የሥራ ላይ ሥልጠናም የሠራተኞች የሥራ ፍጥነት ለማሻሻልና የቤቶችንም ጥራት ለመጨመር አስችሏል፡፡

### *3.1 ፖሊሲ፣ የህግ ማዕቀፎችና ተዋናዮች መጠለያን በማቅረብ*

ከረዥም ጊዜ በኋላ በጥር 2013 በብሔራዊ ደረጃ ሁሉን አቀፍ የሆነ የቤቶች ፖሊሲ ወጥቷል፡፡ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ የፌዴራል መንግሥቱ በከተማ ልማት ፖሊሲውና ተያይዘው በወጡ መመሪያዎች ላይ በከተሞች ያለውን የቤቶች ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ ተቀምጧል፡፡ አሁን በከተማዋ ያለው የቤቶች መርህ በሃገሪቱ ከ1991 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው ለግል ባለሃብቶች በተለይም ለሪል እስቴት አልሚዎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረውን የነጻ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም በከተማዋ ያለውን የቤቶች እጥረት በ50 ፐርሰንት ለመቀነስ የከተማዋ አስተዳደር በ2004 ዓ.ም የአምስት ዓመት የቤቶች ልማት ፕሮራም አዘጋጅቷል፡፡ ይህ ፕሮግራም ቀዳሚ ዓላማውም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የከተማዋን ኗሪዎች የቤቶች ችግር መቅረፍ ነበር፡፡ ይህ ፕሮግራም እስከ አራት ፎቅ የሚደርሱ የኮንዶሚኒየም ቤቶች እንደሚይዝና ዝቅተኛ የመገንቢያ ሥፍራው ደግሞ 22 ሜትር ካሬ ሲሆን ይህም በዝቅተኛ የገቢ መጠን ላይ

የሚገኙ ቤተሰቦች እንዲጠቀሙ በማሰብ በዝቅተኛ ወጭ የሚገነቡ ቤቶች ናቸው፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ አፈጻጸም የከተማዋ የልማት ዕቅድ ባሰበው መልክ ግን አልነበረም፡፡ የከተማ ልማት ፖሊሲው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ በዋናነት በግል ሴክተሩ እንዲገነባ ያሰበ ቢሆንም የሆነው ግን የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ የተከናወነው በመንግሥት በመሆኑ ነው (Elias Yitbarek. et al, 2011)፡፡

የከተማዋ መስተዳድር 150,000 የሚሆኑ የተወረሱ 'የቀበሌ' ቤት በመባል የሚታወቁ ቤቶችን በወር ከ11.11 ዶላር በታች በሆነ ዋጋ ያከራያል፡፡ በተጨማሪም የከተማ መስተዳድሩ በአነስተኛ ወጭ ቤቶችን የማቅረብ ሃላፊነት ያለበት ቢሆንም ከ1996 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ወደ 7,409 ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

በግል የተያዙም ሆነ የተከራዩ መጠለያዎችን በማቅረብ ሂደት ዋነኛዎቹ ተዋንያን መንግስትና የግል ሴክተሩ (የቤት ማህበራት፣ ግለሰቦችና የሪል ስቴት አልሚዎች) ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህ ተዋንያን ከቤቶች ግንባታና ከገበያ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ ትልቁን ሚና እየተጫወቱ ያሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ቀርፋፋ የሆነ የመሬት አሰጣጥ ስርዓት እና ከአቅም በላይ እየሆነ የመጣው የግንባታ ቅድመ ሁኔታዎችና ወጭ የግል ቤቶች አቅርቦትን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በ1995 በዕጣ የተከፋፈለው የቤት መስሪያ ቦታ ብዛት 10,202 ብቻ ነበር፡፡ በ2004 እና በ2005 በተሻለ ሁኔታ በ2,000 የቤት ሥራ ማህበራት በመደራጀት 60,000 የሚሆኑ አባላት ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ አግኝተዋል፡፡

ሌላው ችግር ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው ግለሰቦችና ማህበራት ቦታ ለማግኘት ከአጠቃላዩ የመኖሪያ ቤት የግንባታ ወጭ 20 ፐርሰንት በዝግ አካውንት ተቀማጭ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን የሪል ስቴት አልሚዎች ተሳትፎ ከ1998/99 በኋላ እያደገ የመጣ ቢሆንም እነዚህ በግል የተያዙ ድርጅቶች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኘው የህብረተሰቡ ክፍል ቤት ለማቅረብ ጉዳያቸው አልሆነም፡፡ ጥናቱ እንደሚያሳየው አሁንም ቢሆን በሪል ስቴት አልሚዎች የሚገነቡ ቤቶች በከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉት አካላት ተደራሽ ናቸው (Berhanu A. & Mesfin T/ G., 2012)፡፡

### 3.2 የመሬት አሰጣጥና አስተዳደር

ሌላው በ1993 የወጣው አዋጅ መሬት የህዝብ ሃብት እንደሆነ ተይዞ የሪል ስቴት ስርአትን ተግባራዊ በማድረግ የመሬት ዋጋ ከገበያና ከጊዜ ጋር እንዲያያዝ አድርጓል፡፡ ከሊዝ ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የወጡ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የቤት ፈላጊዎችን መሬት የማግኘት ችግር የበለጠ ውስብስብ አድርጎታል፡፡ በዚሀም የተነሳ በርካታ ኗሪዎች ከህግ ውጭ ቦታዎችን በመያዝና ለመኖሪያ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎች እንዲመሰረቱ አድርጓል፡፡

የከተማዋ መስተዳድር የለማ መሬት መስጠት ባለመቻሉ ያልተነካ መሬት ለመስጠት ተገዷል፡፡ በዚህም የተነሳ በበርካት አካባቢዎች የቤቶች ግንባታ ከተጠናቀቀም በኋላ በመሠረተ ልማቶች አለመሟላት የተነሳ ለረዥም ጊዜ ሰዎች ሳይገቡባቸው ቆይተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለከተማዋ መስተዳድር ፈታኝ ሁኔታዎችንና ተጨማሪ ወጭን እያስወጣ ይገኛል፡፡

### 3.3. የመሬት ሊዝ ፖሊሲ በቤቶች ሁኔታ ላይ ያለው ተጽዕኖ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የመሬት ሊዝ ፖሊሲን በአዋጅ ቁጥር 80/1993 አውጥቷል፡፡ ይህም ፖሊሲ መሬትን በባለቤትነት ከያዘው መንግስት ወደግል ባለሃብቶች የሚዛወርበትን ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን ከግል ባለሃብቶች ወደሌሎች የሚተላለፍበትን መንገድም አስቀምጧል፡፡ ይህ ፖሊሲ የሚከተሉትን ዓላማዎች በመያዝ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል፡፡

- የገበያ መርሆዎችን በመከተል በመንግሥት የተያዙ ቦታዎችን በማስተዳደርና በመረጃ ወይም በእውነታ ላይ ያልተመሠረተ ግምትን ማጥፋት፣
- ፈጣንና ውጤታማ የሆነ የከተማ መሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ በማድረግ የከተማዋን ያለአግባብ መሥፋፋት መቆጣጠር እና ከዚህም የተነሳ ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ የድንበር አለመግባባቶችን መከላከል፣
- ለመሠረተ ልማትና ሌሎች የህዝብ አገልግሎቶች ማስፋፊያ የሚውል ፋይናንስን ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የአዋጁ አፈጻጸም ደረጃ እንደተጠበቀው አልነበረም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር መመሪያዎችን በማውጣት ቀዳሚ ነበር፡፡ በየዓመቱ የሚከፈለው የመሬት ግብር መጠን ብዙ ጊዜ ያልተከለሰና አነስተኛ ነበር፡፡ (ለምሳሌ በመጀመሪያው የመሬት ሊዝ ዋጋ በሜትር ካሬ 0.50 ብር ነበር) ሆኖም ከዚህ በኋላ ወደ 3.00 ብር በሜትር ካሬ እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

ከመሬት ሊዝ ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ከተለዩ ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የከተማ መስተዳድሩ ፖሊሲውን በማስፈጸም እንዲገኙ ከታሰቡ ጥቅሞች ይልቅ ገቢ በማስገኘት ላይ ማተኮሩ፣
- ከተማ አቀፍ የሆነ ወቅታዊ ማስተር ፕላን (በኋላ ተከልሷል) እና የአካባቢዎች ዝርዝር ዕቅድ ያለመኖር፣
- በአቅም ችግሮች ምክንያት የሚፈለገውን መጠንና ቅርጽ ያላቸውን ቦታዎች በሚፈለገው መጠንና አካባቢ ለማቅረብ ያለመቻል፣
- መሬት በሚሰጡ አካላትና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን በሚሰጡ አካላት መካከል ደካማ ቅንጅት መኖር፡፡

ሠንጠረዥ 6፣ ለተለያዩ ዓይነት የቤቶች ልማት የተከፋፈለ የመሬት መጠን

| ዓመት | የቤት ዓይነት | | | | | | ጠቅላላ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አፓርትመንት | | ሪል ስቴት | | የግል መኖሪያ (ዕጣ፣ድልድል እና ሽልማት) | | | |
| | የቦታ ብዛት | የቦታ ስፋት (በሄክታር) | የቦታ ብዛት | የቦታ ስፋት (በሄክታር) | የቦታ ብዛት | የቦታ ስፋት (በሄክታር) | የቦታ ብዛት | የቦታ ስፋት (በሄክታር) |
| 1995 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1996 | - | - | - | - | 450 | 6.8 | 450 | 6.8 |
| 1997 | - | - | - | - | 221 | 3.3 | 221 | 3.3 |
| 1998 | 5 | 0.3 | 2 | 195.1 | 184 | 2.8 | 191 | 198.2 |
| 1999 | 53 | 2.8 | - | - | 689 | 10.3 | 742 | 13.10 |
| 2000 | 27 | 2.1 | 2 | 35.6 | 1690 | 26.8 | 1,719 | 64.5 |
| 2001 | 65 | 8.3 | - | - | 2173 | 32.6 | 2,238 | 40.9 |
| 2002 | 61 | 4.0 | - | - | 4131 | 61.9 | 4,192 | 65.9 |
| 2003 | 98 | 16.2 | 1 | 5.8 | 1451 | 21.8 | 1,550 | 43.8 |
| 2004 | 186 | 119.9 | 5 | 67.0 | 359 | 4.7 | 550 | 191.6 |
| 2005 | 177 | 13.3 | 15 | 66.1 | 13 | 2.7 | 205 | 82.1 |
| 2006 | - | - | 94 | 293.4 | 30 | 68.9 | 124 | 362.3 |
| **አጠቃላይ ድምር** | **672** | **166.9** | **119** | **663** | **9411** | **242.6** | **10,202** | **1,073.40** |

**ምንጭ:** Computed based on AA Land development Agency, 2013

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር መሬትን የማስተላለፍ ሂደት ሎተሪ ማውጣትን እንዲሁም ሎተሪ ከወጣ በኋላ ለአገልግሎት ዋጋ 20 ፐርሰንት ማስከፈልን ያካትታል። በዕጣው ፕሮግራም ለመሳተፍ የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።

- የከተማዋ ኗሪ መሆን አለበት፣
- 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው መሆን ይኖርበታል፣
- ቦታና መሬት የሌለው መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፣
- የተወሰነውንና የማይመለሰውን የምዝገባ ወጭ መክፈል ይኖርበታል፣
- ከፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ ወጭ 20 ፐርሰንት በዝግ አካውንት ማስቀመጥ ይኖርበታል፣
- ዕጣ የደረሰው መሆን አለበት።

ብዙ ጊዜ ያለው የቦታ መጠን ከአመልካቾች ብዛት በጣም ያነሰ ነበር። አሸናፊዎች ቀደም ብሎ በተገለጸ ቦታና ጊዜ በሚወጣ ዕጣ ይታወቃሉ። በመጀመሪያ ዕጣ ባይሳካላቸው አመልካቾች የመመዝገቢያውን ክፍያ በመክፈል ለሁለተኛ ጊዜ ሊሞክሩ ይችላሉ።

አመልካቾች ተቀማጭ ካደረጉት ገንዘብ ግማሹን የቤቱን መሠረት ከገነቡ በኋላ ይለቀቅላቸዋል። ቀሪው ገንዘብ የህንጻው መዋቅር ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ ነው የሚለቀቅላቸው። አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶች (የቦታ ባለቤትነትና የቤት ካርታ እና ሌሎች) ተሟልተው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ግንባታ ካልተጀመረ መሬቱ ይወሰዳል። ግንባታው በሶስት ዓመታት ውስጥ ካልተጠናቀቀ የመሬት ባለቤትነት የሚሰረዝ ሲሆን ቦታው ለጨረታ እንዲቀርብ ተደርጎ 10 ፐርሰንት ተቀንሶ የተገኘው ገንዘብ ለባለቤቱ ይመለስለታል። ይሁን እንጂ ይህ እርምጃ እስከአሁን ተግባራዊ አልተደረገም።

### *3.4 በአዲስ አበባ ያሉ የቤቶች ደረጃ፣ ተመጣጣኝነትና ግንባታ ፈቃድ መመሪያዎች*

በአዲስ አበባ ከተማ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የመሬት መጠንና ወለል ስፋት ደረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል። በአሁኑ ጊዜ የመኖሪያ ቤት የመሬት መጠን ከ73 እስከ 175 ሜትር ካሬ የሚደርስ ሲሆን ወለል ስፋት ደግሞ ከ 56 እስከ 175 ሜትር ካሬ ይደርሳል። ከ1994 እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምድር ቤትንና ባለ አንድ ፎቅ ቤቶችን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን፣ የግንባታ ወጪያቸውም እንደቅደም ተከተላቸው የአሜሪካን ዶላር

3889 እና 6667 ድረስ እንደነበርና ይህንንም ከፍለው መሥራት የሚችሉት ወርሃዊ ደመወዛቸው እንደቅደም ተከተላቸው የአሜሪካን ዶላር 167 እና 222 የሚያገኙትን ቤተሰቦች ብቻ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ የማስተር ፕላን ማሻሻያ ጽ/ቤት በተካሄደው የቤቶች ዳሰሳ ጥናት በ (Berhanu & Mesfin 2012) እንደተጠቀሰው 92 ፐርሰንት የሚሆነው የከተማዋ ህዝብ ወርሃዊ ገቢው ከ167 የአሜሪካን ዶላር ያነሰ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አብዛኛው የከተማ ኗሪ መመሪያው የሚጠይቀውን መስኪያ በማሟላት መኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችል ብቃት የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ አሁንም የግንባታ ወጭ ያሻቀበ በመሆኑ ያለ እውነታ ነው፡፡

የተቀመጠውን የቤቶች ደረጃ በመጠበቅ ለመገንባት ወጭው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ቤተሰቦች የሚችሉት አይደለም፡፡ ይህም ሁኔታ እንደሚያሳየው ቤቶችን ለመገንባት የማይችሉ ቤተሰቦች ብዛት ከፍ እያለ እንደሚመጣ ነው፡፡ ስለዚህም የከተማዋ የቤቶች ደረጃ አብዛኛው መጠለያ ፈላጊ ሊሰራ ከሚችልበት አቅም ጋር የሚመጣጠን አይደለም፡፡ በቤቶች አቅርቦትና በቤት ፈላጊዎች መካከል ያለመመጣጠን መኖር አንዱ ምክንያትም የቤቶች ደረጃና የግንባታ መመሪያዎች ናቸው፡፡


አሁን ባለው የቤቶች ግንባታ መመሪያ የሚከተሉት በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ የቤቶችን ግንባታ ከህዝቡ ደህንነት፣ ንጽህና፣ ጤንነት ጋር በማመጣጠን መስራትን፣ ቀላል የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ከማስቀመጥ፣ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች ከማስቀመጥ፣ ፈጣንና አስተማማኝ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ከመዘርጋት፣ ግንባታዎችን ከመጠናቸው፣ ከውስብስብነት፣ ከተግባርና ቅድመ ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ መስራትን በሚሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡

### *3.5 የከተማ ፕላን ልምድና በከተማዋ የቤቶች ሁኔታ ላይ ያለው ተጽዕኖ*

የከተማ ፕላኖች የከተሞች የመሬት አስተዳደር ምን መሆን እንዳለበት ማዕቀፍ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዓላማ የሚፈቀዱ የመሬት አጠቃቀም ሁኔታዎችን ማለት ለመኖሪያ ወይም ለንግድ ወይም ለማህበራዊ አገልግሎ ወይም ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ቦታዎችን ለመለየት ነው፡፡ በተጨማሪም መሬትን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል፣ እንዲሁም ያለውን መሠረተ ልማት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ስራ ላይ ለማዋልና አጠቃላይ የአካባቢውን ውበትና ልዩ ሁኔታ ለመጠበቅ ያስችላል፡፡

የከተማ ፕላን ዘመናዊ በሆነ መንገድ የተጀመረው በጣሊያን ወረራ ጊዜ ነው። የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የተዘጋጀው ከ1984 እስከ 1986 ባለው ጊዜ ውስጥ በኢትዮ ጣሊያን የልማት ኮርፖሬሽን ሲሆን፣ በዚህ ጊዜ የተዘጋጀው የማስተር ፕላን ከዚህ ቀደም ከነበረው ሰፋ ብሎ የተዘጋጀ ነው። ይህ የማስተር ፕላን በቅርብ ጊዜ ተከልሶ የከተማዋን ልማትና መሬት አስተዳደርና ሥራ አመራርን በተመለከተ ህጋዊ ዶክመንት ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።


*ምስል 13፣* በአዲስ አበባ የነበሩ ከተማ አቀፍ እና አካባቢያዊ የልማት ዕቅዶች ልምድ (የመጀመሪያው በ1986፣ የተዘጋጀ ማስተር ፕላን፣ ሁለተኛው - አሁን ያለው የስትራክቸራል ዕቅድ እና ከ3ኛው እስከ 5ኛው- ናሙና አካባቢያዊ የልማት ዕቅዶች)











በአዲስ አበባ የነበሩት የከተማ ፕላኖች ያረጁ ሠፈሮችን መልሶ ከማልማት ይልቅ በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው በመስፋፋት ላይ ነው፡፡ እንዲያውም ከተማዋን ወደውስጥ የማልማት ሥራዎች ዘግይተው ቢመጡም የተስፋፉት ግን ገጠሩን ወደከተማ ከመለወጥ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችና የሕግ የበላይነትን በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ለማዛመድ ካለ ፍላጎት ተያይዞ ነው፡፡

በቅርቡ የከተማዋን ማስተር ፕላን ለመከለስ በተደረገው እንቅስቃሴ ከዕቅዱ ጀምሮ በርካታ መድረኮችን በመፍጠር የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሞክሯል። በተለይም ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ በከተማዋ ማስተር ፕላን ዝግጅት ወቅት

የሚመለከታቸውን ማሳተፍ የሚገባና አስፈላጊ ቢሆንም እንደመርካቶ ላሉ አካባቢዎች የተዘጋጁ የአካባቢ የልማት ዕቅዶችም የኗሪዎችን ተሳትፎ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

የአካባቢ የልማት ዕቅዶች ከከተማዋ ስትራክቸራል ዕቅድ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ፣ የአካባቢውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታና የአካባቢውን ኗሪ አስተያየት አሳታፊ በሆነ ሁኔታ በመሰብሰብ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተካሄዱት የአካባቢ ልማት ዕቅዶች በባለሙያዎች የተዘጋጁና በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ከማስቀመጥ አንጻር ለማስተካከል በር የማይከፍቱ ናቸው፡፡ በቅንጅት የመስራት ጠቀሜታው በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም በአጠቃላይ ሲታይ ግን የከተማ ቦታን ለመኖሪያነትና ለንግድ ከመደልደል ጋር በተያያዘ የቅንጅት ጉድለት ይታያል፡፡

በከተማዋ መስተዳድር ለተወሰነ አካባቢ የአካባቢ የልማት ዕቅዶችን ወይም የከተማ ዲዛይንን ማውጣት የአካባቢውን ማህበረሰብና የግል ሴክተሩን ተሳትፎ በዕቅድ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአተገባበር ደረጃ ጭምር ተሳትፎን ባረጋገጠ ሁኔታ አሳታፊ የሆነ የከተማ ዕቅድ አሰራርና ሂደትን የሚጠይቅ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት አካሄዶችም የጸደቁ የልማት ዕቅዶች አሁን ካለው የከተማ ልማት ዕቅድ ጋር መሄዳቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

በአዲስ አበባ የልማት ዕቅድ ግምገማ መሠረት ከተሰባሰቡት ካርታዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ሲታይ በአዳዲስ የቤቶች ፕሮጀክቶች የተሸፈነው የከተማ ቦታ 2,977 ሄክታር ነው፡፡ ይህንንም መጠን ከታሰበው 10,048 ሄክታር ጋር ሲወዳደር መልማት ካለበት 30 ፐርሰንቱ ብቻ ነው፡፡ ቀሪው 70 ፐርሰንት የሚሆነው መሬት ባዶ ነው ወይም ለሌሎች ጥቅሞች እንዲውል ተደርጓል፡፡ በቤቶች የተሸፈነው ቦታ ከተሰሩ ቤቶች ጋር ሲወዳደር አነስተኛ መሆኑ በትንሽ ቦታ ላይ የተወሰነ ልማት ያለ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይህም በዋናነት በርካታ ብዙ ፎቆች ያሏቸው ኮንዶሚኒየም ቤቶች ከመገንባታቸው ጋርም ይያያዛል፡፡

ሌላው የከተማዋን ማዕከል ከማልማት ጋር በተያያዘ ከልማት ዕቅዱ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ በተሳትፎ ላይ የተመሠረተ አካሄድ እንዲኖርና ያለውን የቤቶች ደረጃና የዕቅድ ህጎች በማሻሻል አግባብ ያላቸውና ተግባራዊ የሚሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በቅርቡ የከተማ አዋጅ ቁጥር 574/2008 ወጥቷል፡፡ የአዋጁ ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ከዕቅድ ውጭ የሆኑ የከተማ አካባቢዎችን ማስተካከል፣
- በከተማ ልማት ዕቅድ፣ ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚመለከታቸውን የህዝብና የግል አካላት ለማሳተፍ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣

- የሚካሄዱ የልማት ፕሮግራም ሥራዎች ለህዝብ ደህንነትና ለተፈጥሮ ሀብት አደጋ በማይሆን ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ መከታተል፣
- የዕቅዱን ሂደት አሁን በሃገሪቱ ካለው ያልተማከለ አስተዳደር ጋር አብሮ እንዲሄድ ማድረግ።

በአብዛኛው እንደታየው የቤቶችን ደረጃ መቀነስ ማለትም አነስተኛ ቦታን መጠቀም፣ አማራጭ የግንባታ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ አማራጭ ዲዛይንን መጠቀም፣ ለምሳሌ በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ ክፍሎችን መሥራት፣ የድሃ ድሃ የሆነውን ማህበረሰብ በተመለከተ ያለውን ህግ ቀለል እንዲል የማድረግ ሥራዎች አልተሰሩም።

የቤቶች ሥራ ከመሬት ስርጭትና ልማት ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ እውነታ በመነሳት የልማት ዕቅዱ አገልግሎት ላይ የዋለ መሬትን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ከማልማትና መሬትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ በርካታ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፏል። ወደ ጎን እየሰፋ የሚሄደውን ሁኔታ ለማስቀረትና የተፋፈነውን ከተማ ከማፍታታት ጋር በተያያዘ ውጤታማ ለማድረግ በዋናነት ሁለት ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተዋል። አንደኛው የኮንዶሚኒየም ህግና የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ሲሆን ሌላው ደግሞ በመንግስት ቤቶች ኤጀንሲና በቀበሌ የተያዙ ቤቶችን በርካታ ቤቶች በሚይዙ ህንጻዎች መተካት ነው።

ኮንዶሚኒየም ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግና በመንግስት የተያዙ ቤቶችን ወደ ፎቅ ቤቶች የመለወጥ ስራ በአብዛኛው ተግባራዊ ሆኗል። የኮንዶሚኒየም ቤቶችን አተገባበር ህጋዊ ማዕቀፍ ለመስጠት የኮንዶሚኒየም ቤቶች አዋጅ ቁጥር 370/2003 (በ1995 ዓ.ም) ወጥቷል። በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የከተማ ልማትና የከተማ መልካም አስተዳደር ዕቅድ ድህነትን ለማጥፋት የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ (2005/06 እስከ 2009/10) አካል ሲሆን ዕቅዱም ውጤታማና በትንሽ ወጭ የሚሰሩ ቤቶችን መሥራት ላይ ያተኮረ ነው። ቀጣይነት ያለው የከተማ ልማት ዕቅዱም ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይም ትኩረት ያደርጋል። እነሱም፣ ወጭ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ ቤቶችን መሥራትና ያረጁ ቤቶችን ወጭ ቆጣቢ በሆኑ አዳዲስ ቤቶች መተካት ነው (Elias Yitbarek. et al, 2011) ።

የሪል ስቴት ልማትን በተመለከተ ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው የሪል ስቴት አልሚዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። ከተማዋ ያለባትን የቤቶች ችግር ለማቃለል ለሪል ስቴት አልሚዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንዲያገኙ

ተደርጓል። ለምሳሌ፣ መሬትን በቅናሽ የሊዝ ዋጋ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ማበረታቻዎችን እንዲያገኙ የተደረገ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ከህግ ውጭ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ተገኝተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በአዲስ አበባ የሽግግር መንግሥት የሪል ስቴት መመሪያ ቁጥር 20/2005 (1995 ዓ.ም) ወጥቷል፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት የሪል ስቴት አልሚ ማለት 50 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ቤቶችን የሚገነባ ነው፡፡ በሪል ስቴት ልማት ላይ የተሰማሩ አልዎች በርካታ በመሆናቸው ከዚህ ቀደም መንግሥት ይሰጥ የነበረውን ማበረታቻ እንዲቆም አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ፣ ከዚህ ቀደም ከሊዝ ነጻ ሆኖ ይሰጥ የነበረው 50 ሜትር ካሬ ቦታ መስጠት እንዲቆም ተደርጓል፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ፐርሰንት ለማልማት ከሚፈልጉት ጋር ድርድር በማካሄድ የተሰራ ሲሆን ለሪል ስቴት ከተያዙ ቦታዎች ውጭ የሚሰጡ ቦታዎችን በተመለከተ ግን ከፍተኛ የሆነ የጨረታ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ በተጨማሪም 70 ፐርሰንት የኮንዶሚኒየም ቤቶችን እና 30 ፐርሰንት ቪላ ቤቶችን እንዲገነቡ በማድረግ ውጤታማ የሆነ የመሬት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

የኪራይ ቤቶችን አቅርቦት ከማሳደግ አንጻር የልማት ዕቅዱ ያስቀመጠው የመንግሥት ቤቶችን ወደግል የማዞር ዕቅድ ግን ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ በአሁኑ ወቅት በመንግስት ቤቶች የተያዙ 20,000 ቤቶችና በቀበሌዎች የተያዙ 150,000 የመንግስት ቤቶች አሉ፡፡ በተጨማሪም የሪል እስቴት አልሚዎች በከፊል የሚከራዩ ቤቶችን ስለሚገነቡበት ሁኔታ መታየት ያለባቸው አማራጮች አልተቃኙም፡፡ የሪል ስቴት አልሚዎች ለኪራይ የሚሆኑ ቤቶች ለመገንባት ዝግጁ ያልሆኑበት ምክንያት የሚያወጡትን ወጭ ለመሸፈን የሚያዳግታቸው በመሆኑ ነበር፡፡

## 3.6 አሁን ያሉ ሠፈራዎችን ለማሻሻል ያሉ ፖሊሲዎች

ቦታን ለቤቶች ልማት ለማዋልና ለማስራጨት የሚከናወኑ ተግባራት ያለውን የሠፈራ ሁኔታ ባቀናጀ መልኩ ሊከናወን ይገባዋል፡፡ በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱ ሁለት የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡ ከህግ ውጭ የሚካሄደውን ሠፈራ ማስተካከልና የከተማዋን መሃል እንደገና ማልማት ናቸው፡፡ ከህግ ውጭ የሚካሄዱ ሠፈራዎችን ከማስተካከል ጋር በተያያዘ ቦታዎችን ማስተካከልና የባለቤትነት ካርታ መስጠትን ያካትታሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የከተማዋን መሃል ከማልማት ጋር በተያያዘ የመንግስት ቤትን ወደግል ማዞርንና ከተማዋን ማሳደግን ያካትታል፡፡ የመንግስት ቤቶችን ወደግል ማዞር በሽያጭ ወይም ወደባለቤታቸው በመመለስ ሊሆን ይችላል፡፡ ቤቶችን ወደባለቤታቸው በመመለስ ሂደት ከዚህ በፊት በነበረው መንግስት ያለአግባብ የተወሰዱ ቤቶችን ወደትክክለኛ ባለቤታቸው ወይም ህጋዊ ወራሾቻቸው መመለስን ያካትታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሽያጭ ሲባል አሁን በቤቶቹ ለሚኖሩ ሰዎች በተመጣጣኝ ዋጋ በሽያጭ ማስተላለፍን ያካትታል፡፡ ይህ ፕሮፖዛል በተጨማሪም ወደሌላ የማስፈር ፖሊሲን፣ አሳታፊ የሆነ ፖሊሲ፣ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የከተማ ዕቅድ ስታንዳርዶችንና የከተማዋን መሃል መልሶ-ለማልማት የሚያስችሉ ህጎችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያካትታል (Elias, et al, 2011)፡፡ ይሁን እንጂ የልማት እቅዱን አፈጻጸም ስንመለከት ብዙዎቹ ፕሮፖዛሎች ተግባራዊ አልተደረጉም፡፡ ከዚህም በመነሳት የልማት ዕቅዱ በፕሮፖዛሉና በአተገባበሩ መካከል ያለመጣጣም ይታይበታል፡፡

ህጋዊ ያልሆኑ ቤቶችን ወደህጋዊነት ለመለወጥ የታሰበው ፕሮፖዛል በተወሰነ ደረጃ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የመሬት አያያዝና አስተዳደር መመሪያ 2/2010 (Memeria 2/2002EC) በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት አስተዳደርና ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በአተገባበር ሂደት ያሉትን ቦታዎች ከማስተካከል ይልቅ ህጋዊ ማድረግና ለባለቤቶቹ የቦታ ካርታ በመስጠት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ህጋዊ ያልሆኑ ቤቶችን ህጋዊ ከማድረግ ጋር በተያያዘ በ1996 ዓ.ም 150,203 ጉዳዮች ተመዝግበዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 24,000 የሚሆኑት ጉዳዮች በከተማዋ መስተዳድር የተስተናገዱ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በየክፍለ ከተሞቹ ተከፋፍለዋል፡፡

## *3.7 የአዲሱ የቤቶች ፖሊሲ ተስፋዎች*

### የቤቶች ልማት ፕሮግራሞች

መንግሥት በተለያየ የኢኮኖሚ ደረጃ ላሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በተመጣጣኝ ዋጋ በቂ የሆኑ ቤቶችን ዲዛይን በማድረግ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህንንም ለማከናወን በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም መሠረት መንግስት የመኖሪያ ቤቶችን ገንብቷል፡፡ ይሁን እንጂ ለበርካታ ዓመታት በተጠራቀመው ችግር ምክንያት መንግሥት ብቻውን ችግሩን በበቂ ሁኔታ ሊፈታው የሚችል አይደለም፡፡ ስለዚህም በከተማዋ በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኗሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ለማቅረብ፣ በተለይም ደግሞ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ልዩ ትኩረት በመስጠትና የቤቶች ገበያ በአግባቡ እንዲሰራ በማድረግ መንግስት የቤቶችን አቅርቦት በተመለከተ ሦስት ክፍሎች ያሉት አማራጭ የያዘ ዶክመንት ያዘጋጀ ሲሆን፣ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምስል 14፣ አዲስ የቀረቡ የቤት ዕቅድ ዲዛይኖች ዓይነት (10/90፣ 20/80 እና ማህበራት)



















1. **በመንግሥት አስተባባሪነት የሚገነቡ ቤቶች**
    1.1. በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ቡድኖች የሚገነቡ (10/90)
    1.2. የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ (20/80)
    1.3. በተሻለ የገቢ ደረጃ ላሉ የሚገነቡ ቤቶች (40/60)
    1.5. ለኪራይ አገልግሎት በመንግስት የሚገነቡ ቤቶች (ያልጸደቀ)
    1.6. ለዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ ለፕሮጀክትና ፋብሪካ ሠራተኞች የሚገነቡ ቤቶች

2. **የግል ዘርፉ የቤቶች ልማት**
    2.1. ለሽያጭና ለኪራይ በሪል ስቴት አልሚዎች የሚገነቡ ቤቶች
    2.2. በግለሰቦች የሚገነቡ ቤቶች (ለግል መጠቀሚያና ለኪራይ አገልግሎት የሚውሉ)
3. **በቤት ማህበራት የሚከናወኑ የቤቶች ልማት (100/0)**

ምንጭ፣ (MUDC, 2012)

በአዲሱ የቤቶች ፖሊሲ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተለያዩ አማራጮችን አቅርቧል፡፡ በዶክመንቱ እንደተጠቀሰው ዋናዎቹ ተዋናዮች

መንግሥት፣ የግሉ ሴክተር (ሪል ስቴቶች)፣ ግለሰቦችና የቤት ማህበራት ናቸው። አዲሱ የቤቶች ፖሊሲ ስምንት ንዑስ ክፍሎች አሉት።

## 4. የከተማ መልሶ ማልማት

**በከተማዋ የውስጥ ክፍል ስለሚገኙ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን በተመለከተ ያሉ ጽንሰ ኃሳቦችና ምሳሾች**

### *4.1 የደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ጽንሰ ኃሳብ*

"የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች" (slum) እንደሚከተለው ይተረጎማል። "አካባቢውና ማህበራዊ ሁኔታው የወደቀ ከመሆኑ የተነሳ አርኪ የሆነ የቤተሰብ ኑሮ ለመኖር ምቹ ያልሆኑ የመኖሪያ አካባቢዎች ማለት ነው።" ጥሩ ያልሆኑ ቤቶች ለእንደዚህ ያሉ አካባቢዎች መገለጫዎች ናቸው። "Slum" የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል አስቸጋሪ ቃል ነው። ቃሉ አጭር፣ ቀላል እና ለመተካት አስቸጋሪ ነው። በዚህም የተነሳ በብዙ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ቃሉ በተሳሳተ ሁኔታ ጥቅም ላይ ይውላል። "Slum" ማለት በጣም ያረጀና የወደቀ የመኖሪያ አካባቢ ማለት ነው። ቃሉ በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው ከዚህ ቀደም በጣም የተከበሩና ብዙ ሰዎች ሊኖሩባቸው የሚፈልጓቸው አካባቢዎች ሆነው በኃላም በሂደት የቀድሞ ኗሪዎቻቸው ወደተሻሉና አዳዲስ አካባቢዎች በመዛወራቸው ቀስ በቀስ የወደቁና የደቀቁ አካባቢዎች ናቸው። ድሮ በጣም የተከበሩ የሚባሉ አካባቢዎች ተከራዮች የበዙባቸውና በእያንዳንዱም ቤት በርካታ ኗሪዎችን ያያዙ አካባቢዎች ናቸው። እንዲህ አይነት አካባቢዎች ለአብዛኛው የከተማ ድሃ በመጠለያነት የሚያገለግሉ ናቸው። አዳዲስ የሚፈጠሩ ድሃዎችና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የከተማዋ ኗሪዎች በነዚህ ደረጃቸው በወረደ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ።

የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ትርጉም ከቦታ ቦታ ይለያያል። በደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ዓይነትና ባህሪ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ይህም በአንድ ከተማ ውስጥና ከከተማ ከተማ ይለያያል። ብዙ ጊዜ ታማኝና የተረጋገጠ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። በዚህም የተነሳ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረውን ህዝብ ቁጥር በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል። የተባበሩት መንግሥታት ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በደቀቁና ለኑሮ ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች እንደሚኖሩ ይገልጻል። ይህም ሲሰላ በዓለማችን ካለው ህዝብ ከስድስቱ አንዱ በእንደዚህ ዓይነት አካባቢዎች እንደሚኖሩ ያሳያል። በተጨማሪም በ2030 ይህ ቁጥር ወደ 2 ቢሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል።

በነዚህ በደቀቁና ለኑሮ አመቺ ባልሆኑ አካባቢዎች ያለው የኑሮ ሁኔታ የከተማ ድህነትን ከሚያሳዩ መንገዶች አንዱ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ግለሰቦችና ማህበረሰቦች ፈታኝ የሆኑ አደገኛ ሁኔታዎችን ተጋፍጠው ይኖራሉ። የእያንዳንዱ አካባቢ ሁኔታ የተለያየ ቢሆንም እነዚህ ኗሪዎች ለጎርፍ፣ ለመሬት መንሸራተት፣ ለበሽታ፣ አደገኛ ለሆኑ የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች ተጋላጮች ናቸው። መንገዶች ያለመኖር፣ የእግረኛ መንገዶች ያለመኖር፣ የመንገድ መብራቶች ያለመኖር፣ የፍሳሽ መውረጃ አለመኖር፣ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ያለመኖር፣ የቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓት ያለመኖር፣ እና ሌሎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች መጓደል ጥቂቶቹ ችግሮቻቸው ናቸው። በተለይም ሴቶችና ህጻናት በንጽህና ጉድለት፣ በአየር ብክለት እና ማገዶ ለመሰብሰብ በሚወስድባቸው ጊዜ ከሁሉም በላይ ተጠቂዎች ያደርጋቸዋል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ችግሮች ማለቂያ የሌላቸውና እንደአዙሪት መልሰው መላልሰው የሚያጋጥሙ ናቸው።

የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች/አካባቢዎች አካላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ከቦታው ዕድሜና ካሉበት የከተማዋ አካባቢ ጋር ተይይዞ ይለያያል። በመሃል ከተሞች የሚገኙ "የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ባረጁ ቤቶች፣ ለረዥም ጊዜ በኖሩ ብዙዎቹ ተከራይ በሆኑ ኗሪዎችና በተጨናነቀው አካባቢያቸው ይታወቃሉ። በሌሎች አካባቢዎችም አልፎ አልፎ እንዲህ ዓይነት ቦታዎች ይገኛሉ። እነዚህም ቤቶች በህዝብ መሠረተ ልማቶች ላይ የተገነቡ ሲሆን መልሶ ማስፈርን ይጠይቃሉ።

በከተሞች ዳርቻ ላይ ያሉ ሠፈራዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጡና በብዛትና በትፍግፍግም አነስተኛ ናቸው። በአብዛኛው ከሌሎች ከተሞች በመጡ ኗሪዎች እንደየ ኃይማኖታቸውና ክልላቸው በሠፈሩ ሰዎች የተያዙ ናቸው። እነዚህም ሰዎች በእነዚህ አዳዲስ የንግድና የኢንዱስትሪ አካባቢዎች ሥራ ለመፈለግ የመጡ ናቸው። ብዙዎቹ ራሳቸው በሠሯቸው መጠለያዎች ሲኖሩ ጥቂቶች ደግሞ በኪራይ የሚኖሩ ናቸው።

## *4.2 የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ባህሪያትና የፖሊሲ አካሄድ*

የጉዳዮች የተለያዩ መሆንና ውስብስብነት ከላይ ወደታች የሚወርድ አጠቃላይ አካሄድን ወደ መሠረዝ አስገድዷል።

### ስደቀቁና ስኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች የተሰጡ ምላሾች

ለደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን በተመለከተ የተሰጡ የፖሊሲ ምላሾችን ስንመለከት መንግሥት ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል በአራት

መንገዶች ተጠቅሟል። እነርሱም፣ በኃይል ማስነሳት፣ ከቦታው በማንሳት በሌሎች አካባቢዎች ማስፈር፣ ከቦታው በማንሳት ያንኑ አካባቢ እንደገና ማልማት እና ባሉበት አካባቢ ቦታዎችን ማሳደግ ናቸው።




ከእነዚህ አራቱ አካሄዶች አንዱ ኗሪዎችን ማስነሳት ነው። በደቀቁና ለኑሮ ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎችን ምንም አይነት አማራጭ ሳይሰጡ በግዴታና በኃይል ማስነሳት በብዙ ቦታዎች የተለመደ አሠራር ነው። በእንደዚህ አይነት አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ኑሯቸውን ለመግፋት ካሉበት ትግል ጋር ተያይዞ ድንገት ሳያስቡት ከቦታቸው እንዲነሱ መደረጋቸው የመኖራቸውን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይከትባቸዋል። በተጨማሪም ያላቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሃብቶቻቸው ላይ ያላሰቡት ችግር ሲመጣባቸው ከፍተኛ የሆነ የሥነልቦናዊ ቀውስ ይገጥማቸዋል። "የቤቶች መብትና ማስወገድ ማዕከል" እንደገመተው በየዓመቱ 5 ሚሊዮን ሰዎች የዚህ ችግር ሰለባዎች ናቸው (Geurts, 2013) ።

ፎቶ 20፣ መጠለያዋ የፈረሰባት ሴት ስታለቅስ



ምንጭ: (UNHSP, 2003)

ከቅርብ ጊዜ በፊት ማለትም ግንቦት 2005 በዚምባብዌ 'Operation Murambatsvina,' በሚል ዘመቻ መንግስት በመላው ሃገሪቱ በርካታ ቤቶችን፣ የንግድ ቦታዎችንና የመንገድ ላይ ንግድ ቦታዎችን አጥፍቷል፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የመረጃ ፍለጋ ተልዕኮ ሪፖርቶች መሠረት 700,000 የሚሆኑ ዜጎች የመኖሪያ አካባቢያቸውንና ኑሯቸውን አጥተዋል፡፡ ወደ 2.4 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በተለያየ ደረጃ ተጎድተዋል፡፡ ሠፈሮች በመፍረሳቸው ምክንያት በኤች አይ ቪ ኤድስ በጽኑ የታመሙ ሰዎች ካለምንም የህክምና እገዛ ሜዳ ላይ ቀርተዋል፣ ተማሪዎች ያለትምህርት ቀርተዋል፣ እንዲሁም ያለምግብ፣ ውሃ፣ ንጽህናና መጠለያ ቀርተዋል፡፡ በእንዲህ አይነት መፈናቀሎች ይበልጥ የሚጎዱት ደግሞ ሴቶችና ህጻናት ናቸው፡፡

ሁለተኛው የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን ለመለወጥ የሚወሰደው እርምጃ ከነበሩበት ቦታ በማንሳት በሌላ ቦታ ማስፈር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች ብዙ ጊዜ በነዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ከመሃል ከተማዎች በማንሳት ከመሃል ከተማዎች በጣም በሚርቁ አካባቢዎች ማስፈርን ያካትታል፡፡ ኗሪዎቹ ከተነሱ በኋላም እነዚያ አካባቢዎች በከፍተኛ ዋጋ ለእንደገና ማልማት ይከፋፈላሉ፡፡ የእንዲህ ዓይነቱ አሠራር መሠረታዊ ችግር እንደገና እንዲሰፍሩ የተደረጉት ሰዎች በሰፈሩባቸው አካባቢዎች ሥራ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ምክንያት እንደገና ወደከተማዋ ሌሎች የደቀቁ አካባቢዎች መመለሳቸው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተፈናቀሉት ሰዎች ቃል የተገባላቸውን ሠፈራዎች የማያገኙበትም ሁኔታ አለ፡፡

ፎቶ 21፣ ከመሃል ከተማ የተፈናቀሉ ኗሪዎች ወደሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ ሲጠይቁ የሚያሳይ (የሌላ ሀገር ምሣሌ)



ምንጭ: (UNHSP, 2003)

ብዙ ጊዜም በጉልበት የሚደረግ መፈናቀል በእንደገና ማስፈር ሊሸፈን ይችላል፡፡ ለእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ምሳሌዎችም፣

- አካባቢያዊ አደጋ ያለባቸው ዞኖች
- የህዝብ የመመላለሻ አካባቢዎች

ሰዎችን ከነበሩበት ቦታ በማንሳት ወደሌላ ማስፈር አስፈላጊ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች የሚገኙበት ቦታ አካባቢያዊ አደጋ ያለባቸው ዞኖች ከሆነ፣ የሠፈሩበት አካባቢ በመንገዶች መተላለፊያ አካባቢ ከሆነ (በባቡርና መንገዶች መተላለፊያ ላይ ሲሆን)፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን ይህ አማራጭ ሆኖ ባይወሰድ ይመረጣል (Geurts, 2013) ፡፡

በፖሊሲ አውጭዎች በሦስተኛ መንገድነት የተቀመጠው ደግሞ ከቦታው በማንሳት በዚያው ላይ የእንደገና መልሶ ማልማትን ማካሄድ ነው፡፡ ይህም በደቀቁትና ለኑሮ ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩትን ሰዎች ለጊዜው ማስነሳትን፣ ቦታውን ማጽዳትንና በቦታው ላይ አዳዲስ ህንጻዎችን መገንባትን ያጠቃልላል፡፡

ለንግድ የሚውል ቦታ ካለውና ይህም ለመኖሪያነት የሚያገለግለውን ቦታ ወጭ ለመሸፈን የሚያስችል ሆኖ ሲገመት በርካታ ፎቆች ያሉት ህንጻ መስራት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ የንግድ ቤታቸውን በምድር ቤት አድርገው ኑሯቸውን በፎቆች ላይ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ባለብዙ ፎቅ ቤት መስራት አዋጭ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም በምድር ቤት ያሉት የንግድ ሱቆች

ኪራይ ህንጻውን ለመስራት የወጣውን ወጭና ህንጻውን ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን ስለማይችል ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን መተፋፈግ ለመቅረፍ ብዙ ፎቅ ያላቸውን ህንጻዎች መስራት ጥሩ አማራጭ ነው፡፡ እንዲህ አይነት አማራጮች በራሳቸው ውጤታማ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች በርካታ ቢሆኑም የራሳቸው የሆኑ ችግሮች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በጣም ትልልቅ ህንጻዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኗሪዎች በምድር ቤት የራሳቸውን ትናንሽ የቢዝነስ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉ አይደለም፡፡ ይህም ለብዙ ቤተሰቦች ብቸኛው የገቢ ምንጭ የሚሆንበት ጊዜ በርካታ ነው፡፡ በደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ባልሆኑ አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎች በጋራ ችግሮቻቸውን የሚነጋገሩበትና ስሜቶቻቸውን የሚጋሩባቸው ምቹ ሁኔታ ያለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ብዙ ጊዜ ብዙ ፎቆች ባሏቸው ህንጻዎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ግን ወደ መበታተንና አለመገናኘት ያመራሉ (Guerts, 2013)፡፡

አራተኛው የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን ከማስተካከል ጋር በተያያዘ ያለውና በብዙ ማህበረሰብም ተመራጭ የሆነው አማራጭ አካባቢውን ማሳደግ ወይም ማሻሻል ነው፡፡ ይህም ያሉትን መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች አጥጋቢ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ማሻሻልንና የይዞታ ባለቤትነትን ማስተካከልን ያካትታል፡፡ የዚህ ዓይነት መፍትሄ ዋናው ጠቀሜታ የማህበረሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አለማቃወሱ ነው፡፡ ሌላው ይህ አማራጭ ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን ክፍሎች በትክክል ተጠቃሚ የሚያደርግም አማራጭ ነው፡፡

**የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት የሃቢታት ተቋም ዕይታ**

የይዞታ ባለቤትነት ጉዳይ በከተማ የሚገኙ ድሃ ማህበረሰቦች በሂደት ከከተማዋ ጋር ለመቀላቀል እንዲችሉ የሚጠየቅ አንዱ ተፈላጊ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም የይዞታ ባለቤትነት የቤቶች መብት አንዱ መሠረታዊ አካል ነው፡፡ በበርካታ ዓለምአቀፋዊ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎችና ስብሰባዎች ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ሁሉም ሰዎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከመፈናቀል የሚጠብቃቸው የይዞታ ባለቤትነት ይፈልጋሉ፡፡ የይዞታ ባለቤትነት ጉዳይ በዚህ የተነሳ ችግር ይገጥመናል ብለው ለሚያስቡት ብቻ ሳይሆን በገንዘብ እጥረት አደጋ ላይ የወደቁ የማዕከልና የአካባቢ መንግስታትንም ይጠቅማል፡፡ ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች የይዞታ ባለቤትነት ሲኖራቸው ያሉባቸውን ቤቶችና አካባዎችን ለማሻሻል ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ለማውጣት ደስተኞች

ናቸው፡፡ ለዚህም ነው እንደ ተባበሩት መንግሥታት የሃቢታት ተቋም አገላለጽ የይዞታ ባለቤትነት መስጠት በጣም የተረጋጋ ማህበረሰብ እንዲኖር ለማድረግ፣ የተሻለ ሁኔታ ላይ ያሉ መጠለያዎች እንዲኖሩ ለማስቻል፣ ማህበራዊ መገለልን ለመቀነስ፣ ለከተማ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ለማሳደግ፣ በድርጅትና በግለሰብ መዋለንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚፈልጉ አካላትን ለማበረታታትና በአጠቃላይ የከተማውን አካባቢ ለማልማት ያስችላል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የሰዎች አሠፋፈር ፕሮግራም በ2003 የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን ለመለካት እንዲቻል ትርጉሙን ከአካባቢያዊና ከህጋዊ ጉዳዮች ጋር ብቻ በማያያዝ ያቀርበዋል፡፡ እንደ ተባበሩት መንግሥታት የሃቢታት ተቋም የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ሲባል ንጹህ ውሃ፣ ለንጽህናና ለመሠረተ ልማቶች አመቺ ያልሆኑ፣ የቤቶቹ የጥረት ደረጃ የወረደ፣ በጣም የተጨናነቁና በስጋት ላይ ያለ ኑሮ የሚኖርባቸው በማለት ያስቀምጣቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ትርጉም የሚያተኩረው በአሃዛዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ነዋሪዎችን አስመልክቶ ያሉ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ማለትም ፍትሃዊ ያልሆነ የሃብት ክፍፍል፣ ልዩነቶችና ብቃትን ለመጠቀም ያለመቻል ሁኔታዎችን አያካትትም (Elias Yitbarek, 2008)፡፡ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ለበርካታ የማህበራዊ ችግሮች መፈልፈያ ቦታዎች ናቸው፡፡ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች የሚኖሩ ነዋሪዎች በተለይም ንጹና አደገኛ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ሰዎች ለብዙ በሽታዎች ተጋላጭ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድህነትና ከፍተኛ የሥራ አጥነት መጠን ሰዎችን ተስፋ እንዲቆርጡና ለማህበራዊ ጭንቀቶች፣ ወንጀለኝነት፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ የአልኮል ሱሰኝነት፣ እና ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ውስጥ እንዲገቡ ሊመራቸው ይችላል (UNHSP፣ 2003)፡፡

### የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች መኖር አይቀሬ ነውን?

ሁሉም ከተሞች የራሳቸው የሆኑ የደቀቁና ለመኖሪያ ምቹ ያልሆኑና ከህግ ውጭ የሆኑ ሠፈሮች አሏቸው፡፡ የነዚህ ሠፈሮች ስፋት፣ መጠንና ባህሪ እንደየሃገሮቹ ህጋዊ ሁኔታና የገቢ መጠንና የህግ አፈጻጸም ሁኔታ ከከተማ ከተማ ይለያያል፡፡ በሚገርም ሁኔታ ብዙ ጊዜ የእንደዚህ ዓይነት ሠፈሮች መፈጠር ከህጎች ያለመኖር ወይም የአፈጻጸም ችግር ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን ህጉ መኖሩ በራሱ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች እንዲገደቡ የሚያደርገውን ጥረቶችን ሊያባብሰው ይችላል፡፡ የደቀቁና ለመኖሪያነት

ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎች በከተሞች ሊቀሩ የማይችሉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የአንድ ከተማ ስኬታማነትና ዕድገት ምልክቶችም ናቸው፡፡ ለውጥ የማያሳዩት ዕድገታቸውን ባቆሙና ብዙም በማይንቀሳቀሱ ከተሞች ብቻ ነው፡፡ ይህም ሲባል ግን ሁሉም ከተሞች የዕድገት፣ የውድቀትና የመልሶ ማደግን ሂደት የግድ ማለፍ ይኖርባቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በሆነ ጊዜ የተሻለ ዕድገት የሚያሳዩ ከተሞች አሉ፡፡ በዚህ ጊዜም አዳዲስ እድገቶችን ያሳዩ እና እንደገናም የታደሱ ከተሞች አሉ፡፡

የወደቁ የሚለው እንደሁኔታው የሚለያይ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ከተሞች ደግሞ የደቀቁና ለመኖሪያነት ምቹ አይደሉም የሚባሉ ሠፈሮች ከሌሎች ሠፈሮች የተሻሉ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎችም አሉ፡፡ በአንዳንድ ከተሞች የሚታየው የውድቀትና እንደገና የማንሰራራት ሁኔታ አንዳንዴ ቀስ በቀስ ይሆንና ልዩነቱ በውጭ ባሉ ሰዎች ብዙም ላይታይ ይችላል፡፡ አንዳንድ አካባቢዎች ምንም እንኳን የተለወጡና እንደገና የተሰሩ ቢሆንም የነበራቸውን ልዩ ሁኔታዎች እንደያዙ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

የደቀቁና ለኑሮ አመቺ ያልሆኑ ሠፈሮች በከተሞች ውስጥ መፈጠራቸው የማይቀር ቢሆንም እንዲህ ዓይነት ሠፈሮች በአብዛኛው በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ባሉ ከተሞች ላይ ይፈጠራሉ፡፡ የነዚህ ዓይነት ሠፈሮች መፈጠር ጥሩ ያለመሆኑን ብንወስድም መፈጠራቸው ግን የአንድ ከተማ ዕድገትን ያሳያሉ፡፡ የእንዲህ ዓይነት ሠፈር ነዋሪዎች አሁን ከሚያወጡት በላይ ለቤት ማውጣት ስለማይችሉና አንዳንዴም ስለማይፈልጉ ርካሽና ደስታን የሚሰጣቸው በመሆኑ የሚጫወቱት ሚና በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች በተጨማሪም ከገጠር ወደ ከተማ ለሚመጡ ሰዎች ወደ ከተማ ህይወት እንደመሸጋገሪያ ያገለግላሉ፡፡ ከቤቶች ጋር በተያያዘ ምንም አማራጮች በሌሉበት ሁኔታ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች የሌሉበት ከተማ መፍጠር ብሎ መንቀሳቀስ ለከተማ ልማት ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ቡድኖችን ማለትም የገጠር ተሰዳጆችን ኑሮ የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

### *4.3 የደቀቁ ሰፈሮችን ማንሳት ታሪካዊ አመጣጥ*

የደቀቁ ሠፈሮችን በታቀደና በታሰበ ሁኔታ የቤቶቹን ሁኔታ ለማሻሻል ማስነሳት መቼ ተጀመረ? ትክክለኛ ጊዜያቶቹ ከከተማ ከተማ የሚለያይ ቢሆንም የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በብዙዎቹ ከተሞች በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የተጀመረ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ በትክክል የተጀመረበት ጊዜ ከከተሞች የህዝብ ዕድገት መጨመር እና የቤቶችን ችግር ለመቅረፍ

ከማስፈለጉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡ በአንዳንድ የሦስተኛው ዓለም ሃገራት የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን ማንሳት በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ እንደተጀመረ ይገልጻል፡፡ እነዚህን ሠፈሮች የማንሳት ሥራ በአብዛኛው በቅኝ ገዢዎች ተግባራዊ የተደረጉ ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዘው የተከናወኑ ጥናቶችም እንደሚያሳዩት የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን ማስነሳት የቤቶችን ሁኔታ ማሻሻል ተስኖት እንዲያውም ለነዚህ ቡድኖች የነበራቸው የቤቶች አማራጭ በማጥፋት የቤቶችን ችግር በማባባስ የታሰበውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ አለማስቻላቸውን ነው፡፡ ጥናቶቹ በተጨማሪ እንደሚያሳዩት እንዲህ አይነት እርምጃዎች በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ሁኔታዎችን እንዲባባሱ አድርገዋል፡፡ ምክንያቱም የተፈናቀሉት ሰዎች ወደሌሎች ህጋዊ ወዳልሆኑ አካባቢዎች ስለሚሄዱ ነው፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ሠፈሮች የሚነሱ ሰዎች ከተለያዩ ቤተሰቦች፣ ጓደኞችና ከሚያውቋቸው ሰዎች ጋር ያላቸውን ግኑኝነት በተመለከተ ያሉ ትስስሮች ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ሊጤን ይገባዋል፡፡ ብዙ ጊዜ እነዚህን የሚፈናቀሉ ሰዎች እንደገና ወደሌላ ሠፈሮችና ቤቶች የማስፈር ሁኔታን መንግስት ብዙም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ በመንግስት የሚወሰደው እርምጃ ለተፈናቀሉ ሰዎች ከከተሞች የራቁና ያልለሙ ቦታዎችን መስጠት ነው፡፡

እንዲህ አይነት የቦታ ምደባዎች የፈጠሯቸው ችግሮች በዶክመንት መመዝገብ የተጀመሩት ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ1963 መጨረሻና በ1964 መጀመሪያዎች ላይ 90,000 ሰዎች ከማኒላ ከተማ ተነስተው ከከተማዋ 37 ኪሎ ሜትር በምትርቀው ሳፓንግ ፓላይ በሚባል አካባቢ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል፡፡ በ1965 መጨረሻ ወደ አዲሱ ሠፈራ ከሄዱት ውስጥ የቀሩት 17,000 ሰዎች ብቻ ነበሩ (Juppernlatz, 1970)፡፡ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ እንዲህ ዓይነት ሠፈራዎች ለሠፋሪዎቹና ለቤተሰቦቻቸው ከቦታው ምቹነት፣ ስራ ከማግኘት፣ የመሠረተ ልማቶትና ሌሎች አገልግሎቶችን ከማግኘት አንጻር ችግር እንዳለባቸው ይገልጻሉ (Drakakis-Smith 1981)፡፡

በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ መንግስት ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን ተፈናቃዮች በመንግስት ቤቶች የሚያሰፍሩበትም ሁኔታ አለ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ቤታቸው በቡልዶዘር ለፈረሳባቸው ተፈናቃዮች በ1950ዎቹ በተገነቡ ባለብዙ ፎቆች በካራካስና ቬንዜዌላ የተከናወኑት የመልሶ ማስፈር ሥራዎች ይጠቀሳሉ፡፡

### *4.4 የመፈናቀል ምክንያቶች*

*ብዙ ጊዜ መንግሥታት ካሉት ሶስት ምክንያቶች አንዱን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡*

*ብዙ ጊዜ የሚቀርበው የመጀመሪያው ምክንያት ከተማዋን ለማስዋብና ለማስጌጥ ሲባል ነው፡፡ በማኒላና በሴኦል ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚፈናቀሉት በከተማዎቹ የሚከናወኑ ትላልቅ ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች ሲኖሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በማኒላ የወይዘሪት ዩኒቨርስ ውድድር ሲካሄድና የጳጳሱ ጉብኝት ከመጀመሩ በፊት በሴኦል ደግሞ ከ*1988*ቱ የሴኦል ኦሎምፒክ በፊት የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት የኢንድራ ጋንዲ ልጅ ሳንጃይ ጋንዲ በንቃት የተሳተፉበት በዴልሂ ከተማ ከ*1975 *እስከ* 1977 *የተካሄደው መፈናቀል ከተማዋን የማስዋብ ፕሮግራም አካል ነበር፡፡ በተጨማሪም ዴልሂ የህንድ ዋና ከተማ መሆኗ በ*1960*ዎቹ በሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦችን በከተማዋ ዳርቻ በሚገኙ በመሸጋገሪያ ጣቢያዎችና የከተማ መንደሮች ለማስፈር እና ለመልሶ ማልማት እንደምክንያት ቀርቧል* (Juppenlatz 1970) ፡፡

*ዴሞክራሲያዊ ከሆኑ መንግስታት ይልቅ ኦቶሪቴሪያን የሆኑ መንግሥታት ብዙ ጊዜ ከተሞችን የማስዋብና የማፈናቀል ሥራን ያከናውናሉ፡፡ በመፈናቀል ላይ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በሪኦዴጄኔሮ በ*1960*ዎቹና በ*1970*ዎቹ መጀመሪያ የተከናወኑ የማፈናቀል ተግባራት የተከናወነውን ሥራ በመንግስትና በህዝቡ እንዲሁም በመስሪያ ቤቶቻቸው መካከል ምንም ዓይነት ውይይት ሳይደረግ፣ የህዝቡ አስተያየት በመንግስት በኩል ሳይወሰድና የተነሱ ተቃውሞዎችን በማፈን የተከናወነ እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም መታየት ያለበት ሁኔታ በቅርቡ የተካሄዱ የማፈናቀል ሁኔታዎች የተከናወኑት በህጋዊ መንገድ ሥልጣን ላይ ባልወጡ መንግስታት ሲሆን፣ ለምሳሌ፣ የአርጀንቲና ወታደራዊ መንግሥት ከ*1977 *እስከ* 1980 *ባሉት ጊዜያት የማፈናቀል ተግባራት ተፈጽሟል። በዴልሂ ከ*1975 *እስከ* 1977 *ድረስ የተካሄደው የማስወገድ ፕሮግራም የተካሄደው ጠቅላይ ሚኒስትሯ ዲሞክራሲያዊ ህግን ባገዱበት ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም በሴኦል የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን ለማፈናቀል በ*1970*ዎቹና በ*1980 *የተካሄዱት ምሳሌዎች ናቸው፡፡*

*በእርግጥም በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት የሚካሄዱ ያረጁ አካባቢዎችን የማልማት ተግባራት በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የሃብት እጥረት፣ የተቋማት ብቃት ማነስ እና የሌሎች ጉዳዮች አንገብጋቢነት የተነሳ ካደጉ ሃገሮች ጋር የሚወዳደር አይደለም፡፡*

ሌላው ለደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን ለማንሳት የሚቀርበው ሁለተኛ ምክንያት እነዚህ ሠፈሮች የወንጀለኝነት ማዕከሎች ስለሆኑና ብዙ ወንጀለኞችም ስለሚኖሩባቸው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ እነዚህን ሠፈሮች ማንሳት ከተማዋን ከማስዋብ በተጨማሪም የወንጀለኝነትን ማዕከልን እንደማጥፋትም ይወሰዳል፡፡ በ1982 አጋማሽ ላይ በማኒላ አዲስ ሰዎችን የማፈናቀል ስራ ሲጀመር፣ የከተማዋ ከንቲባ ኢሜልዳ ማርቆስ ስለ "ሙያዊ ሕገወጥ ሠፋሪዎች" (professional squatters) ሲገልጹ "ደግና ሰው ወዳጅ የሆነውን ማህበረሰብ ያላግባብ የተጠቀሙ መሬት ቀሚዎች" በማለት ነው፡፡

መንግሥታት በደቀቁና ለኑሮ ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች ያለውን የጤና ችግርም ለመፈናቀል እንደምክንያትነት ይወስዳሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በናይጀሪያ በ1950ዎቹ ለተካሄደው መፈናቀል በምክንያትነት ቀርቧል፡፡ የሚገርመው ግን የጤና ችግር ለመፈናቀላቸው ምክንያት የሆነው እነዚያ ሰዎች የነበራቸው ማህበራዊ ቁርኝት በመቋረጡና ከነበሩበት በበለጠ በተፋፈገ አካባቢ ለመኖር በመገደዳቸው የጤንነት ችግራቸው እየባሰ መሄዱ ነው፡፡

ሦስተኛው ለመፈናቀል እንደምክንያት የሚቀርበው የመልሶ ማልማት ነው፡፡ መሃል ከተሞችና ስትራቴጂያው የሆኑ አካባቢዎች (ለምሳሌ፣ በአይሮፕላን ማረፊያዎች አካባቢዎች) ለከተሞች እድገት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ በብዙ የሦስተኛው ዓለም ሃገራት ርካሽ የሆኑ መኖሪያዎች በብዙ ከተሞች ውስጥ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ አጋማሾች ላይ ተሰርተዋል፡፡ ከቅርብ ምዕተ ዓመታት ጀምሮ ግን መሃል ከተሞች ለቢሮዎችና ለሌሎች የተሻለ ገቢ ለሚያስገኙ ሥራዎች ለመጠቀም ሲባል መልሰው እንዲለሙ ተደርገዋል፡፡ አሮጊዋ ዴሊሂን፣ ካራቺን፣ ባንኮክን፣ ሳንቲያጎን፣ ሊማን ጨምሮ በብዙ የሦስተኛው ዓለም ሃገራት በመሃል ከተማዎች በተካሄዱ የንግድና የመኖሪያ ልማቶች በነዚህ አካባቢ የነበሩትን ርካሽ የሆኑ ቤቶችን፣ ማደሪያዎችን እና ሌሎች ርካሽና በመሃል ከተማ የሚገኙ ማደሪያዎች መተካታቸውን የ (UNCHS, Habitat, 1984) ጥናትን በመጥቀስ (Geurts, 2013) ገልፃለች፡፡

ቤቶች በህጋዊ ሁኔታ የተያዙባቸው አካባቢዎች እንደገና ሲለሙ ኗሪዎች ካሳ እንዲያገኙ ይደረጋል (ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ካሳ የነበሩበትን ቤት ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ቤት ለመግዛት የሚያስችል ባይሆንም)፡፡ ተከራዮች ግን ብዙ ጊዜ ካሳ አይከፈላቸውም፡፡ በሴኦል በተከናወኑ ብዙ የመፈናቀል ተግባራት የቤት ባለቤቶች ምንም እንኳን አዲስ ቤት ለመግዛት የሚያስችላቸው ባይሆንም ካሳ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም የሚያሳየው

ተከራዮች ሃብታምና የራሳቸውን ቤት ለመግዛት ከሚችሉት በተለየ ሁኔታ እንደሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩና ያላቸውም ነጻነት የተገደበ መሆኑን ነው (Geurts, 2013)፡፡

## *4.5 በአዲስ አበባ የመሃል ከተማ መልሶ ማልማት*

**በአጠቃላይ በኢትዮጵያና በአዲስ አበባ ያለው ሁኔታ**

በኢትዮጵያ መንግሥት በወጣው የዕቅድ ሕግ ማለትም የከተማ ልማት አዋጅ ቁጥር 574/2008 እና የከተማ ልማት ስትራቴጂ (MWUD, 2005) መሠረት በሀገሪቱ የሚገኙ ብዙ የከተማ ማዕከሎችና ከተሞች አዲስ አበባንም ጨምሮ ፕሮግራሙን ለማስፈጸም ተገቢ የሆኑ ተቋማት እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ሆኖም አሁን ያለው አሠራር እንደሚያሳየው በተለይም በአዲስ አባባ የሚካሄዱት የመልሶ ማልማት ሥራዎች የኗሪዎቿን ደህንነት ከማስጠበቅና ከመመለስ ይልቅ የከተማዋን ገጽታ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

የከተማ መልሶ ማልማት የማይቀር ጉዳይ ሲሆን በከተሞች ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት በቁርጠኝነት፣ በግልጽነት እና በተጠያቂነት መርሆዎች የሚሰሩ ተቋማትን ይፈልጋል፡፡

ከላይ በተመለከተው የዕቅድ ሕግ መሠረት የከተሞች መልሶ ማልማት ጥያቄ ከመንግሥት፣ ከማህበረሰቡ ወይም ከግለሰቦች ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህንን ተግባራዊ የማድረጉ ሂደት ግን በህዝብ ተሳትፎ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ላይ በመመስረት የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያሟላ በሚስችል መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

በ1991 ጀምሮ ተግባራዊ ከተደረገው የቅይጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ከተማ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ውስጥ ተጉዛለች፡፡ ከተካሄዱት ለውጦች ውስጥ በግል ዘርፉ የተከናወነው ኢንቨስትመንት አንዱ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ በርካታ የመልሶ ማልማት ሥራዎች በመሃል ከተማዋ ተከናውነዋል፡፡

በከተማዋ የሚገኙ የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮች ከዕቅድ ውጭ ያሉ ሠፈሮች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ በአብዛኛውም በኪራይ የተያዙ የመንግስት ቤቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 80 ፐርሰንቱ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ ሲሆን ብዙ ጊዜም የቀበሌ ቤቶች በመባል ይጠራሉ፡፡ አብዛኞቹ የቀበሌ ቤቶችም አንድ ክፍል፣ በጭቃና በእንጨት የተሰሩና ከ40 ዓመት በላይ ያገለገሉ ናቸው (CSA, 1999)፡፡

*በአሁኑ ጊዜ በነዚህ ቤቶች በአብዛኛው የሚኖሩት በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ሲሆኑ፣ ቤቶቹም ተገቢው ዕድሳት ስለማይደረግላቸው አርጅተውና ሊወድቁ ደርሰው ይገኛሉ፡፡*

*እንዲህ ዓይነት ያረጁና የወደቁ ለአካባቢውም ጤንነት ጥሩ ያልሆኑ አካባቢዎችን እንደገና የማልማቱ ሥራ የተጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይህንን የደቀቁና ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ ሠፈሮችን እንደገና የማልማቱን ሥራ የከተማዋን ገጹታ በሚለውጥ መልኩ ለማከናወን መጠነ ሰፊ ሥራዎችን ጀምሯል፡፡ በዚህም የተነሳ በግልጽ የሚታዩና ከተማዋ የነበራትን መጥፎ ገጽታ የለወጡ ሥራዎች ተሰርተዋል። አሁንም በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሚካሄዱት ፕሮጀክቶች የህዝብ ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ የሌለባቸውና የህዝቡን ኑሮ ያናጉና በርካታ ነቀፋ የደረሰባቸው ናቸው፡፡*

## *4.6 በአዲስ አበባ የተከናወኑ ዋና ዋና የመልሶ ማልማት ሥራዎች*

### **የሸራተን አዲስና የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን**

*በሸራተን አዲስና በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የተከናወኑት የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በሸራተን አዲስ የተካሄደው መልሶ ማልማት ባለአምስት ኮከቡን የሸራተን አዲስ ሆቴል ለመገንባት ሲሆን የመልሶ ማስፈሩ ሥራ የተጀመረው በ*1992 *ቢሆንም ብዙ ሰዎችን የማስፈር ሥራው ግን በየዓመቱ በቀጣዮቹ ዓመታት ተከናውኗል፡፡ በዚህ ሂደት* 707 *ቤተሰቦች ወደሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ መልሶ የማስፈሩ ሂደት ሙሉ ወጭ የተሸፈነው በአልሚው ነበር፡፡ አልሚው ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት በተሰጠው ቦታ ቤት የመስራትና ቤተሰቦቹን የማስፈር ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ ሂደት ኗሪዎቹ ቦታዎችን እንደሚለቁ ተነግሯቸዋል። በሂደቱም የህዝብ ተሳተፎ አልነበረም፡፡ የተከናወነው መልሶ ማስፈር ከነበሩባቸው ያረጁና ለኑሮ ምቹ ካልነበሩት ቤቶች የተሻለ ቤት እንዲያገኙ የተደረገ ቢሆንም ሥራ አጥነትና የገቢ መቀነስ ግን በብዙዎች ዘንድ ያጋጠመ ችግር እንደነበር የ*(Lishan Seyoum 2010) *ጥናትን በመጥቀስ* (Ezana, 2011) *አስቀምጧል፡፡*

### **ሁለተኛው በከተማዋ የውስጠኛ ክፍል የተካሄደ በጣም አስፈላጊ መልሶ ማልማት**

*ሁለተኛ በከተማዋ የውስጠኛ ክፍል የተካሄደው መልሶ ማልማት በካሳንቺስ አካባቢ የተካሄደው መልሶ ማልማት ነው፡፡ ይህ ፕሮግራም* 150 *ሄክታር*

የሚሆን መሬትን የሸፈነ ሲሆን የተካሄደውም የሁለተኛው የአዲስ አበባ የአስር ዓመት የከተማ ልማት ዕቅድ ከተዘጋጀ በኋላ እንደተካሄደ የ (Mesay Tefera 2008) ጥናትን በመጥቀስ (Ezana, 2011) ገልጿል፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ የንግድና የቢዝነስና እንቅስቃሴዎች የሚስተዋሉበት ዓለማቀፋዊ የከተማ ማዕከል ለመፍጠር ነበር፡፡ በአካባቢ ልማት ዕቅዱ የኗሪዎች ተሳትፎ አልነበረም። ይልቅስ ፕሮጀክቱ ያተኮረው በሥፍራው የነበሩ ኗሪዎችን ወደሌላ ቦታ በማስፈር ቦታውን ነጻ ማድረግ ላይ ነበር፡፡ የአካባቢ ልማት ዕቅዱም የተዘጋጀው ኗሪዎቹ ከማስፋፊያው ከተነሱ በኋላ ነበር (Ezana, 2011)፡፡ እነዚህ ሁለት ፕሮጀክቶች የሚያሳዩት በአዲስ አበባ መሃል ከተማ የተካሄዱ የመልሶ ማልማት ፕሮግራሞች በዋናነት በግል ኢንቨስተሮች አነሳሽነት የተካሄዱና ፕሮጀክቱ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ያልነበረበት መሆኑን ነው፡፡

በዚህም የተነሳ የ (Gebre Yintiso, 2008, p. 53) ጥናትን በመጥቀስ (Ezana, 2011) ተፈናቃዮቹ የነበራቸውን የንግድ ግንኙነት ማጣታቸውን፣ ለመኖራቸው ወሳኝ የሆኑ መደበኛ ያልሆኑ ትስስሮችን ማጣታቸው፣ የነበሩበትን ቦታ አንጻራዊ ጠቀሜታና ሥረወቻውን ማጣታቸው እና ከፍተኛ ለሆነ የትራንስፖርት ወጪ መጋለጣቸውን አመልክቷል። የአብዛኞቹ ሠፋሪዎች ገቢም አሽቆልቁሏል። በተጨማሪም አብዛኞቹ ተፈናቃዮች ከውሃ አቅርቦት፣ ንጽህና፣ ትምህርትና ጤና ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች አጋጥሟቸዋል፡፡

**በስልቱ ላይ የተፈናቃዮችና የመንግሥት ባለስልጣናት አስተያየት**

ፕሮጀክቱ ተጽዕኖ ላደረሰባቸው የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያየ ውጤት ነበረው፡፡ ለአንዳንዶቹ ኗሪዎች ህጋዊ የሆነ ቤት እንዲያገኙ ረድቷቸዋል፡፡ በተፈጠሩት አዳዲስ ሥራዎችና በአዲሶቹ ሠፈራዎች ምክንያት ህጋዊ እና የራሳቸው የሆነ ጥሩ የመኖሪያ ቤቶች እንዲያገኙ ረድቷቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ወደሌላ የመንግሥት ኪራይ ቤቶች የተዛወሩት ተፈናቃዮች ኑሮ አሽቆልቁሏል፡፡ ይህም የፕሮጀክቱ ሽፋን የተለያየ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የ(Oakley, 1991) አባባል በመጥቀስ (Ezana, 2011) እንዳሰፈረው አሳታፊ የሆነ ሂደት መኖሩ ሁሉንም የሚያቅፍ ተመሳሳይ ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ሆኖም ፕሮጀክቱ ሁሉንም በእኩል ደረጃ ከመጥቀም አንጻር የተሳካለት አልነበረም፡፡

በጥናቱ ላይ በተሳተፉ በርካታ አስተያየት ሰጭዎች እንደተጠቀሰው ፕሮጀክቱ ፍላጎትን መሠረት ያላደረገ እና የተደረጉት ውይይቶችም የነሱን

ፍላጎትና ስጋቶች ያላካተቱ በመሆኑ ጥቅም ያላመጡ ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በርካታ የጥናቱ ተሳታፊዎች ፕሮጀክቱ እንዲያመጣ የታሰበውን የተሻለ ህይወት ከማምጣት ይልቅ ህይወታቸውን እንዳተራመሰባቸው ገልጸዋል፡፡ በተቃራኒው በቃለመጠይቁ የተሳተፉ ሁሉም የመንግሥት ባለስልጣናት ፕሮጀክቱ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ፣ በጊዜ የተጠናቀቀ፣ እና የታቀደለትን የኗሪዎችን ህይወት ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ውጤታማ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከኗሪዎችም ይህ ዓይነት አስተያየት የነበራቸው ነበሩበት፡፡ ምንም እንኳን ሁሉንም የማይወክል ቢሆንም ግኝቶቹ በፕሮጀክቱ ላይ የመንግሥት ባለስልጣናትና ኗሪዎች ያላቸውን የአስተያየት ልዩነቶች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሂደቱን በተመለከተ ፍላጎትን መሠረት ያላደረገ፣ ምክክር ከማድረግ አንጻርም መዘግየት የነበረበት፣ ውጤታማነቱ አነስተኛና አሉታዊ እንደነበረ ይገልጻሉ፡፡ የ (Oakley 1991, Imparato, Ruster 2003) ጥናትን በመጥቀስ (Ezana, 2011) እንደገለጸው ውጤቶቹ ጥሩና ትክክለኛ የሆነ ተሳትፎ የነበረበት ሂደት ባህሪያትን አያንጸባርቁም፡፡

**በቅርቡ በአዲስ አበባ የተካሄደ የመልሶ ማልማት ሥራ፡-የልደታ ፕሮጀክት**

በከተማዋ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት በ2009 በተካሄደ ጥናት መሠረት ከልደታ አካባቢ የተነሱ 963 ቤተሰቦች ወደኮንዶሚኒየም ቤቶች፣ 183ቱ ደግሞ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ወደሚገኙ ወደቀበሌ ቤቶች እንዲዛወሩ ተደርጓል፡፡ የመልሶ ማስፈሩ ዝርዝርም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ፎቶ 22፣ ቀድሞ የነበሩ ቤቶች፣ ሳይቱን የማጥራት ሥራ እና አዳዲስ የተገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች



ወደሌላ ሠፈር እንዲሰፍሩ የተደረጉ ሰዎች ብዛት = 8520

- የአካባቢው ጠቅላላ ስፋት---------------------------------------- 26 ሄክታር
- ለኮንዶሚኒየም የዋለ ---------------------------------------------- 8 ሄክታር
- ለመሬት ለውጥ የዋለ ---------------------------------------------- 2 ሄክታር
- ለማህበራዊ አገልግሎት የዋለ------------------------------------- 3 ሄክታር
- ለንግድ የዋለ---------------------------------------------------------- 5 ሄክታር
- ለአረንጓዴ ሜዳዎችና ለመንገዶች የዋለ ---------------------- 8 ሄክታር

**በመልሶ ማስፈሩ ላይ ያለ መረጃ፣**

- 932-------የቀበሌ ቤቶች
- 117-------የቀበሌ ንግድ ቤቶች
- 48-------- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ቤቶች
- 330-------የግል ቤቶች
- 15-------- የመንግሥት መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ት/ቤቶች

በጠቅላላው 1442 ህንጻዎች እንዲፈርሱና ነዋሪዎቹ ወደሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ተደርጓል።

**ካሳ፣ ምትክ ቤትና መሬት**

- 766--------ወደ ኮንዶሚኒያም የተዛወሩ
- 166--------ወደ ምትክ የቀበሌ ቤቶች የተዛወሩ
- 129--------በቀበሌ ቤቶች የነበሩ ደባሎች እና 25 በግል ቤቶች ይኖሩ የነበሩ የኮንዶሚኒየም ቤት ተሰጥቷቸዋል
- 44--------የግል ቤቶች በምርጫቸው መሠረት ወደኮንዶሚኒየም ቤቶች እንዲዛወሩ ተደርገዋል
- 55--------ሰዎች በሽርክና እንዲደራጁ ተደርጎ 25 ሜትር ካሬ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በቤቶች ልማትና ዝውውር ቢሮ በተጠናው ጥናት መሠረት በልደታ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ተፈናቃይ ነዋሪዎች በከተማዋ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ተሰራጭተዋል፡፡ ዝርዝሩም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

*ሠንጠረዥ 7፣ ለተፈናቃዮች በተለዋጭ የተሰጡ የኮንዶሚኒየምና የቀበሌ ቤቶች ያሉባቸው አካባቢዎች*

| ክፍለ ከተማ | ወደ ኮንዶሚኒየም | ወደቀበሌ የኪራይ ቤቶች | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| ልደታ | 74 | 161 | |
| ን/ላፍቶ | 457 | 10 | |
| ቂርቆስ | 200 | 9 | |
| አራዳ | 20 | - | |
| አቃቂ ቃሊቲ | 2 | - | |

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ ከተማ | 46 | - |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 117 | - |
| ቦሌ | 14 | - |
| የካ | 16 | - |
| ጉለሌ | 17 | 3 |
| **ድምር** | **963** | **183** |

*ምንጭ*: Lideta sub city housing transfer office, 2009

**ስለመልሶ ማልማት ፕሮግራሙ፣**

- ከ91 የግል ቤት ባለቤቶች 81 ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዋል
- በ8 ሄክታር መሬት ላይ 10 ባለ ሰባት ፎቅ ህንጻዎች፣ 41 ባለ 4 ፎቅ ህንጻዎች እና በጠቅላላው 51 ህንጻዎች ተገንብተዋል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ
- 351-------- ስቱዲዮዎች
- 755-------- ባለ 1 መኝታ ቤቶች
- 434-------- ባለ ሁለት መኝታ ቤቶች
- 319-------- ባለ ሶስት መኝታ ቤቶች፣ በጠቅላላው 1859 ቤቶች ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ ተደርገዋል፡፡

**በተጨማሪም፣**

- ከለማው 26 ሄክታር መሬት ውስጥ 5 ሄክታር በሊዝ እንዲሸጥ የታሰበ ሲሆን 23,540 ሜትር ካሬ ደግሞ ለኢንቨስተርስ ተሰጥቷል፣
- እያንዳንዳቸው 6,500 ሜትር ካሬ የሆኑ ሁለት አረንጓዴ ሜዳዎች እንዲለሙ ተደርጓል፣
- በ67 ማህበራት ለተደራጁ 3,564 ሰዎች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፣
- በተጨማሪም ርዝመቱ 5,580 የሆነ የተለያየ ስፋት ያላቸው መንገዶች በተለያዩ ማቴሪያሎች እንዲሰሩ ተደርጓል (1,308 ሜትር የሚሆነው በኮብል ስቶን የተሰራ መንገድ ሲሆን ስፋቱም 15 ሜትር ነው)፡፡
- 8 ኪሎሜትር ትልልቅ ቧንቧዎች 8.4 ኪሎ ሜትር መካከለኛ መጠን ያላቸው ቧንቧዎችና 4.7 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ተዘርግተዋል፡፡

### ለመልሶ ማልማት ፕሮግራሙ የወጣ ወጭ

- ለካሳና መልሶ ለማስፈር-----------------ብር 119,415,910.11
- ለኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት---------ብር 19,289,304.24
- ጠቅላላ ወጭ---------ብር 138,702,219.35

የዕቅድ ሕጉ እንደሚለውም አሁን በከተማዋ እየተካሄደ ካለው ሁኔታ እንደሚታየው የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶችን ኃሳብ የማፍለቅ፣ የማዘጋጀት እና የማስፈጸም ሥራዎች የተከናወኑት በመንግሥት በኩል ሲሆን ልማቱ ያተኮረው በአብዛኛው የከተማዋን ገጽታ ከመገንባት እና መሬቱን ለግል አልሚዎች በመሸጥ በሚገኘው ገንዘብ ላይ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ኗሪዎች መፈናቀላቸው ሊያስከትል የሚችለው ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ሳይጠኑ በከተማዋ የተለያዩ ክፍሎች እንዲዛወሩ ተደርገዋል፡፡

### በአዲስ አበባ የመልሶ ማልማት ፕሮግራሞች ላይ የህዝብ አስተያየት

በከተማዋ እየተካሄደ ያለውን መጠነ ሰፊ የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች በተለይም በቅርቡ በመስተዳድሩ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ የህብረተሰቡን አስተያየት ለመሰብሰብ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በዚህ የዳሰሳ ጥናት 297 መላሾች የተሳተፉ ሲሆን ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 8፣ በከተማ መልሶ ማልማት ዓላማ ላይ የህዝብ አስተያየት

| | በጣም አበረታች ነው | ጥሩ ነው | አልደግፈውም | ኃሳብ የለኝም | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 218 | 69 | 4 | 6 | 297 |
| በፐርሰንት | 73 | 23 | 1 | 2 | 100 |

ምንጭ: Abebe, et al 2013

በዚህም መሠረት ከ297 መላሾች 218ቱ (73 ፐርሰንት) የመልሶ ማልማት ሥራዎቹ አበረታች ውጤት እያመጡ በመሆናቸው በጣም የሚደግፉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 1 ፐርሰንት መላሾች የሚካሄደውን የመልሶ ማልማት ፕሮግራም እንደማይደግፉ ሲገልጹ ቀሪዎቹ 6ቱ ወይም 2 ፐርሰንቶቹ ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር እንደሌላቸው

ገልጸዋል፡፡ አብዛኛውን ማህበረሰብ ይወክላሉ ተብለው የሚታሰቡትና ፕሮግራሙን የሚደግፉት መላሾች ለመደገፋቸው የሚከተሉትን ምክንያቶች ሰጥተዋል፡፡

**የሚካሄደውን የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ዓላማዎች የደገፉባቸው ምክንያቶች፣**

- ከተማዋን በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቷን እንድትጠብቅ ያደርጋታል
- የከተማዋን ገጽታ ያሻሽላል
- የአህጉሯ መዲና መሆኗን ያጎላል
- ያረጁ አካባቢዎችን ይለውጣል፣ መሠረተ ልማትን ያሻሽላል
- የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ያሻሽላል
- የከተማዋን የልማት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል
- በአጠቃላይ የዜጎችን የህይወት ዘይቤ ያሻሽላል

በህዝቡ የተገኘው ተቀባይነት የሚያመለክተው የፕሮግራሙ ዓላማዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር በተያያዘ የህዝብን እምነት ያለ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ከእምነት በተጨማሪም ህዝቡ በከተማዋ መውደቅና ማርጀት የተሰላቸ መሆኑን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 9፣ በመልሶ ማልማት ሂደት ላይ በህዝብ ዘንድ ያለው አጠቃላይ አስተያየት

| የተግባር አይነት | መጠን | የግምገማ ደረጃዎች | | | | | መልስ ያልሰጡ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | ጥሩ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | | |
| ጥናትና አካባቢ መረጣ | ብዛት | 115 | 80 | 66 | 28 | 8 | 0 | 297 |
| | % | 39 | 27 | 22 | 9 | 3 | 0 | 100 |
| የተፈናቀዮች ተሳትፎ | ብዛት | 50 | 74 | 92 | 44 | 21 | 16 | 297 |
| | % | 17 | 25 | 31 | 15 | 7 | 5 | 100 |
| የተተኪ መሬት አሰጣጥ | ብዛት | 27 | 60 | 84 | 71 | 36 | 19 | 297 |
| | % | 9 | 20 | 28 | 24 | 12 | 6 | 100 |
| የተተኪ ቤት አሰጣጥ | ብዛት | 34 | 59 | 95 | 60 | 29 | 20 | 297 |
| | % | 11 | 20 | 32 | 20 | 10 | 7 | 100 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የካሳ መጠን | ብዛት | 17 | 32 | 82 | 90 | 48 | 28 | 297 |
| | % | 6 | 11 | 28 | 30 | 16 | 9 | 100 |
| መልሶ ማስፈሩ የተቀመጠው ጊዜ | ብዛት | 26 | 79 | 71 | 68 | 36 | 17 | 297 |
| | % | 9 | 27 | 24 | 23 | 12 | 6 | 100 |
| ለተፈናቃዮች የተደረገ ዕገዛ | ብዛትy | 19 | 51 | 88 | 71 | 41 | 27 | 297 |
| | % | 6 | 17 | 30 | 24 | 14 | 9 | 100 |

ምንጭ: Abebe, Demeke & Mathewos A., (2012)

ከሠንጠረዡ እንደሚታየው በአዲስ አበባ ከተማ በሚካሄደው የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ላይ በተሰጠው የህዝብ አስተያየት መሠረት መልስ ከሰጡት 297 መላሾች ውስጥ፡-

- 39 ፐርሰንቱ የቦታ መረጣው በጣም ጥሩ የነበረ መሆኑን የገለጹ ሲሆን 3 ፐርሰንት ብቻ ናቸው ጥሩ ያልነበረ መሆኑን የገለጹት፣
- የተፈናቃዮችን ተሳትፎ በተመለከተ 17 ፐርሰንት የሚሆኑት ጥሩ እንደነበር ሲገልጹ 31 ፐርሰንቱ የነበረውን ሂደት መካከለኛ እንደነበር ሲያስቀምጡ 7 ፐርሰንቱ ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፣
- ተተኪ መሬት ከመስጠት ጋር ተያይዞ ደግሞ 9 ፐርሰንት ብቻ ናቸው በጣም ጥሩ ነው ብለው የመዘኑት፣ 28 ፐርሰንቱ መካከለኛና 12 ፐርሰንቱ ዝቅተኛ በማለት ገልጸዋል፣
- ተተኪ ቤት መስጠትን በተመለከተ 11 ፐርሰንቱ በጣም ጥሩ እንደነበር፣ 32 ፐርሰንቱ መካከለኛና ቀሪዎቹ 10 ፐርሰንቶች ደግሞ ዝቅተኛ ብለውታል፣
- የተከፈለውን የካሳ መጠንና የተሰጡ ተተኪ ቤቶችን በተመለከተ 6 ፐርሰንቱ በጣም ጥሩ እንደነበር፣ 28 ፐርሰንቱ መካከለኛና 16 ፐርሰንቱ ዝቅተኛ እንደነበር ገልጸዋል፣
- ለመልሶ ማስፈሩ የተሰጠውን ጊዜ በተመለከተ 9 ፐርሰንት መላሾች ብቻ በጣም ጥሩ ብለው ሲመልሱ፣ 24 ፐርሰንቱ መካከለኛና 12 ፐርሰንቱ ዝቅተኛ በማለት መዝነውታል፣
- ለተፈናቃዮች የተሰጠውን ድጋፍ ስንመለከት 6 ፐርሰንት መላሾች በጣም ጥሩ እንደሆነ ሲገልጹ፣ 30 ፐርሰንቱ መካከለኛና 14 ፐርሰንቱ ዝቅተኛ በማለት መዝነውታል፡፡

**ስለመልሶ ማልማቱ ፕሮግራም በመሳሾች የተነሱ ችግሮች፣**

*መሳሾቹ ከመልሶ ማልማት ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ የነበሩትን ችግሮችም ገልጸዋል፡፡ ከተጠቀሱት ችግሮች ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡*

- *መልሶ ማልማቱ የሚመለከታቸውን ኗሪዎች ሙሉ እምነት ያለማግኘቱ፣*
- *ለተፈናቃዮች በቂና አግባብ ያለው ዝግጅትና ቅድመ ሁኔታዎች አለመከናወናቸው፣*
- *ተፈናቃዮች ሙሉ ለሙሉ ሳይነሱ ቤቶችን ማፍረስ መጀመሩ፣*
- *ለቀድሞ ቤቶች የተሰጠው ምትክ ካሳ በቂ አለመሆኑ፣*
- *ተፈናቃዮች በነበሩበት ቦታ ሳይሆን በከተማዋ ማስፋፊያ ቦታዎች ላይ ማስፈር፣*
- *ከተፈናቃዮች ይልቅ ለአልሚዎች ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣*
- *በሂደቱ የሙስና ሥራ መኖሩ፣*
- *የግሉ ሴክተር ሰፊ ተሳትፎ ያለማድረግ፣*
- *የቅንጅት ማነስ፣ ለአረጋውያን የትራንስፖርት አገልግሎት ያለመኖር፣*

*በከተማ መስተዳደሩ የተካሄደውን የመልሶ ማልማት ሂደት በተመለከተ የተሰጡ ዋና ዋና አስተያየቶች ናቸው፡፡*

## 5. ወደፊት መከናወን የሚገባቸው ሥራዎች

### *5.1 የቁልፍ የባለድርሻ አካላት ሚናዎች*

**የከተማዋ አስተዳደር፣**

- *ምንም እንኳን ሁኔታው በቅርቡ በነበረው ምዝገባ ላይ የተሻሻለ ቢሆንም ለኮንዶሚኒየም ቤት የሚደረገው ምዝገባ የራሳቸው ቤት ያላቸውን በሚለይ መልኩ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መካሄድ ይኖርበታል፣*
- *የከተማው አስተዳደር በምዝገባው ሂደት የሚነገሩ አሉባልታዎችን በማስቀረት ከአድልኦ ነጻ የሆነና ውጤታማ የሆነ ድልድልን መሠረት በማድረግ ያለውን የቤት እግር ለመፍታት እንዲቻል ቴክኖሎጂን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ እንዲሳተፍ ማድረግ፣*
- *የከተማዋ መስተዳድር ብዙ የቤተሰብ አባላት ስላሏቸው ለቤት ለመቆጠብ ችግር ላለባቸው ሰዎች ትኩረት በመስጠት በጣም ባልተወደዱ የግንባታ ቁሳቁሶች አግባብ ባለው አካባቢና የአካባቢው*

ጥራት ሳይዛባ ቤቶችን በመገንባት በኪራይ የሚያገኙበትን ሁኔታ ቢያመቻች፣

- የከተማው መስተዳድር በተለይ ምንም አማራጭ የሌላቸውንና ለኮንዶሚኒየም ቤት ተቀማጭ ለመክፈል የማይችሉትን የኪራይ ቤቶችን እንደአንድ አማራጭ በመውሰድ ቢሰራ፣
- መንግስት በጣም ዝቅተኛ የሆነውን 10/90 እንኳን ለመክፈል አቅም የሌላቸውን የማህበረሰብ ክፍል በተመለከተ ኃላፊነቱን ቢወስድ፣
- ለሴት አመልካቾች 30 ፐርሰንት ዕድል እንደሚሰጠው ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ኮንዶሚኒየም ለሚፈልጉ አካል ጉዳተኞች ተመሳሳይ ዕድል ቢሰጥ፣
- በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የከተማዋ ኗሪዎች አቅምን ያገናዘቡና ሳቢ የሆኑ አፓርትመንቶችን ለመስራት እንዲችሉ የከተማዋ አስተዳደር ትክክለኛና ዕውነተኛ የሆኑ የሪል እስቴት አልሚዎችን ቢያበረታታ፣
- የከተማዋን ማህበረሰብ የቤት ችግር ለማቃለል የተለያዩ የቤቶች አማራጭ ፕሮፖዛሎች የቀረቡ ቢሆንም መንግስት ብቻውን ይህን ከባድ ኃላፊነት መሸከም አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ አሁን 3 ሚሊዮን የሆነው የከተማዋ የህዝብ ብዛት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ሁለት እጥፍ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፤ ለዚህም ከገጠር ወደ ከተማ ስደት ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ ይህም በቤቶች ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ ስለሚኖረው የቤቶችም ፍላጎት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የከተማ አስተዳደሩ የሚመለከታቸውን ማሳተፍ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት፣ እነዚህም የግል ገንቢዎች፣ የቤት ማህበራት፣ ሪል እስቴቶች፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (የድሃ ድሃ የሆኑ ሰዎችን በማሰብ) ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሁሉም የሚጠቅም ተስማሚ የሆነ ማበረታቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ቀስ በቀስም መንግስት ከቤቶች ልማት ራሱን በማውጣት የማመቻቸት ሥራ መስራት አለበት። ማመቻቸቱም በቀላሉ መሬትን ለማግኘት፣ ለብድር፣ እንደሁኔታው የሚያገለግል አግባብ ያለው ፖሊሲ፣ ህጎች፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች ማውጣት፣ አነስተኛ ወጭ የሚያስወጡ የግንባታ ቁሳቁሶችን ማምረትና ማቅረብ እና ሌሎች ቴክኒካዊ ዕገዛዎችን መስጠት ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ በቂና ለብዙዎቹ ቤት ፈላጊ የማህበረሰቡ ክፍሎች ተደራሽ የሆነ ቤት ለማቅረብ ያስችላል፡፡
- መንግስት የቤት እጥረትን ለማቃለልና የቤቶችን ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በመሬት አሰጣጥና አስተዳደር፣ በመንግስትና በኮንዶሚኒየም ቤቶች ሂደት ላይ የሚታዩት ስር የሰደደው የሙስናና ቢሮክራሲያዊ ችግሮች ካልተቀረፉ እየተከናወኑ

*ያሉ ጥረቶችን እንደሚጎትቱ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የከተማዋ አስተዳደር ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የችግሩን ምክንያት ከሥረ መሠረቱ በማጥናት ለሌሎችም ትምህርት በሚሆን መልኩ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡*

**ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት**

- *ችግር ፈቺ በሆኑ ጥናቶች ላይ በመሳተፍ አቅምን ያገናዘቡ የግንባታ ቁሳቁሶችን ከማምረትና በዝቅተኛ ዋጋ ሃገራዊ በሆኑ ቁሳቁሶች ሊሰሩ የሚችሉ ቤቶችን እንዲሰሩ ማገዝ፡፡ የዚህ ዋና አላማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የከተማዋ ኗሪዎች ቤትን ለማቅረብ ነው፡፡*

**የከተማ ልማት ኮንስትራክሽንና ቤቶች ሚኒስቴር**

- *ሁሉን አቀፍ የሆነ አቅጣጫ ለማስቀመጥ፣ የቤቶች ሥራን ለማፋጠንና ያሉትን የቤቶች ችግሮች ለመቅረፍ እንዲቻል የቤቶች ፖሊሲ ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን፡-*
- *የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፖሊሲውን አፈጻጸም በየጊዜው መከታተልና መገምገምና ፖሊሲው ያስቀመጠውን ዓላማ ማሳካቱን በየጊዜው መለካት ይኖርበታል፡፡*
- *በተገኘው የግምገማ ውጤት ከማህበረሰቡ በተሰጡ ተጨማሪ አስተያየቶች መሠረት በፖሊሲው ላይ ማስተካከያዎችን ማድረግ፡፤ ይህም የቤቶች ልማት ሥራዎችን ወደኋላ የሚጎትቱ ችግሮችን በሁሉም ተዋናዮች ማለትም የግሉን ሴክተር (የግል ቤቶ፣ ማህበራት፣ እሪል ስቴት)፣ በህዝብ እና በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ጨምሮ እንዲቀረፉ ያስችላል፡፡*

**የከተማዋ ቤት ፈላጊ ማህበረሰብ**

- *ተመሳሳይ የሆነ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለዚሁ ሲባል ለሚቆጥቡና በውጭ ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው የገንዘብ እገዛ ለሚያገኙ የመንግስት ሠራተኞች ተደራሽ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ የሚያስፈልገውን ተቀማጭ መክፈል እንዲችል በየወሩ የመቆጠብ ወኔና ልምድ ሊያዳብር ይገባል፡፡*

## 5.2 *ከቤቶች ልማት ጋር የተያያዙ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች*

- ያለው የ500,000 ቤቶች እጥረት ያረጁ ቤቶችን ጨምሮ መሟላት አለበት
- አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዓመት 50,000 ቤቶች መገንባት ይኖርባቸዋል
- መንግስት ብቻ በዓመት 20,000 ቤቶችን መስራት ይጠበቅበታል
- እንደ አንዳንድ ጥናቶች በዓመት ከ500 ሄክታር በላይ ለመስጠት የተለዩ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ
- አዳዲስ ቤቶችን ለመገንባት የሚያስፈለገው ወጭ በጣም ብዙ ነው
- በሁሉም ሴክተሮች ያለው ተቋማዊ አቅም አነስተኛ መሆኑ
- ደካማ የግንባታ ቁሳቁሶች አቅርቦት
- የግንባታ ቁሳቁሶች ዝቅተኛ የሆነ ቴክኖሎጂ መጠቀም
- የኮንዶሚኒየም ቤቶች ዝውውር ሂደት ጊዜን የሚወስድና ውጣ ውረድ የበዛበት መሆን
- የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ የወጣላቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለዕድሎች ተቀማጩን ለማስቀመጥ ያለመቻልና በዚህም ምክንያት ወደሌሎች በማስተላለፋቸው የታሰበለትን ዓላማ ማሳካት ያለመቻል
- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የተዛወሩበትን አካባቢ ኑሮ ሊለምዱ ባለመቻላቸውና በሌሎች ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የተነሳ ወደቀድሞ ሰፈራቸው መመለስ
- ለኮንዶሚኒየም ቤቶች ልማት ቦታ ሲመረጥ የመሠረተልማት ጉዳይ መዘንጋቱ

## 5.3 *የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊትና በኋላ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች*

- የመልሶ ማልማቱ ፕሮግራሙ የሚመለከታቸው አካላት በቅድሚያና በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፉ ማድረግ
- ወደሌላ ቦታ የሚሰፍሩ ተፈናቃዮችን አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች እና መሠረተ ልማቶች እንዲሁም ሥራና የመሳሰሉት ባሉበት አካባቢ ቢሆን
- በሚፈናቀሉ ሰዎች ቦታ ምርጫ መሠረት ምትክ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ቢሰጡ
- ለሚፈናቀሉ አረጋውያን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ
- የተጠናቀቁ ኮንዶሚኒየሞችን መስጠት

- ተፈናቃዮች ሲፈልጉ ለመግዛት ወይም ሌላ ቤት ለመገንባት የሚያስችል ካሳ መስጠት
- ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ ተፈናቃዮች ተደራሽ በሆነ አካባቢ በቂ መሬት እንዲያገኙ ማድረግ
- የመሬት ልማት ፕሮጀክቱ ያሰበውና በተግባር እየተከናወነ ባለው መካከል ያለውን ልዩነት እንዲጣጣም ማድረግ፣
- የአካባቢውን ልዩ ባህሪ መሠረት ያደረገና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የመሬት ልማት ፕሮጀክት ማዘጋጀት
- የመሬት ልማት ፕሮጀክት ዝግጅቱ የከተማ ዲዛይን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ ቢሆን
- የግል ሴክተሩን ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ሳይተው ለማህበረሰቡ ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት
- በተለይ በዝቅተኛ ገቢ ላይ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ገቢ የሚያስገኙ አዳዲስ የሰፈራ ፕሮግራሞችን መቅረጽ
- በቅድሚያ በሚደረገው ጥናት መሠረት የሚፈናቀሉ ኗሪዎችን ፍላጎት ማሟላት
- ለአረንጓዴ ሜዳዎችና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች በቂ መሬት መስጠትና በጊዜው እንዲጠናቀቁ መከታተል
- በመልሶ ማልማቱ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት ያላቸውን ሚና መለየትና ማጠናከር
- በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ብቻ በተበታተነ መልኩ የሚደረገውን የመልሶ ማልማት ስራ በመቀነስ በከተማ ደረጃ የሚከናወን ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ባለብዙ ፎቅ ህንጻዎች መገንባት ላይ ብቻ ሳይሆን ደረጃውን የጠበቁ መሰረተ ልማቶች እንዲዘረጉ ትኩረት መስጠት
- በመልሶ ማልማቱ ሂደት የሚከሰቱ ክፍተቶችን ለማቃለል ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መገንባት
- በመጨረሻም ለመልሶ ማልማቱ ስራ መጠነ ሰፊ ፋይናንስ ያስፈልጋል

## ዋቢ መጻሕፍት

AAHDPO (2012), "a paper (Amharic version) presented for discussion related to Addis Ababa's 125th anniversary

Abebe Zeliul, Demeke Haile & Mathewos Asfaw, 2012: Housing Development and Urban Renewal in Addis Ababa, A paper presented on a conference organized in connection with the 125th Anniversary of Addis Ababa City. (Power Point Presentation)

Addis Ababa's Health Bureau website, Accessed on 12, 2, 2013: http://www.moh.gov.et/English/Information/Pages/AddisAbabaHealth Bureaus.aspx.

Bahru Zewde (1991) *A History of Modern Ethiopia Addis Ababa*, Addis Ababa University Press and Publications Office, 1991).

Babar M. 2001: *Why Cities Need Slums*:, Reader in Housing Studies at the DPU-reproduced from *Habitat Debate*, UNCHS, Vol. 7, No. 3,

Berhanu Adane & Mesfin T/Giorgis, 2012: Cost Effective Condominium Construction Project in Addis Ababa, a Thesis Submitted in Partial Fulfillment of Bachelor of Science Degree in Construction, Technology and Management-Addis Ababa University Department of Construction Technology and Management

Dominique Couret and Daniel Solomon, 2003: A Presentation on Addis-Ababa's urban dynamics environmental approach - Ethio-French research program, Addis-Ababa, the 1st of April 2003

Delivering Affordable Housing, Communities and Local Government, 2006: Department for Communities and Local Government, London

Demeke Haile, 2008: Urban Housing Provision & Management- Unpublished Lecture Hand-out, for Urban Planning Department, BSc Program at ECSU, Addis Ababa, Ethiopia

Ellen Geurts, Aug 2013: a presentation for TMT Ethiopia, based on World Bank Institute's document intitled "Adaptive Approaches to Urban Slums"

Elias Yitbarek, Yonas Alemayehu et al (2011) "Performance Evaluation Development Plan of Addis Ababa 2003 – 2010, Housing Component"

Ezana Haddis, 2011: Factors Influencing Affected Group Participation in Urban Redevelopment in Addis Ababa: The Case of Senga Tera-Fird Bet I Project

FEACC and Transparency Ethiopia, 2009: Land Administration and Corruption in cities (focusing on Addis Ababa and the surrounding towns), a paper presented on a panel discussion organized by collaboration of Federal Ethics and Anti-Corruption Commission and Transparency Ethiopia

Marja C. Hoek-Smit,2009: “Subsidizing Housing Finance for the Poor,” Wharton School, University of Pennsylvania- Paper prepared for Development Initiatives Group

Peter Malpass and Alan Murie, 1990: Housing Policy and Practice

Tadesse G.Giorgis (2000) “The Urban Housing Situation in Ethiopia: Problems and Prospects”: A Paper discussed at Symposium on "Reviewing Ethiopia's Socioeconomic Performance 1991-99", Organized by Inter Africa Group, 26 – 29, April 2000, Addis Ababa

MWUD, (Year not specified)“*Housing in Addis Ababa*”

Trynos Gumbo, 2010:Microfinance institutions and urban housing in Addis Ababa: Challenges and prospects for sustainable poverty alleviation

UN-HABITAT (1996), “Global Report on Human Settlements” released in March 1996, cited in the un-published course handout of Housing Development by Demeke Haile, 2008, to Urban planning, Urban Engineering and Urban Management Departments, IUDS, ECSU, Addis Ababa, Ethiopia.

UN-HABITAT (2011) “Condominium Housing in Ethiopia, the Integrated Housing Development Programme”

UN-HABITAT, 2008: "Shelter for All: The Potential of Housing Policy in the Implementation of the Habitat Agenda,”

UN-HABITAT, 2008: Addis Ababa Urban Profile

UN-HABITAT, 2007: Situation Analysis of Informal Settlements in Addis Ababa, Citles Without Slums-Sub -Regional Program for Eastern and Southern Africa, Addis Ababa Slum Upgrading Programme, Nairobi, Kenya

Wikipedia, the free encyclopedia: *http://en.wikipedia.org/wiki/Condominium, accessed on Dec 12, 2013.*

World Bank Business Anti corruption portal,*http://www.business-anti corruption.com/country-profiles/sub-saharan-africa/ethiopia/corruption-levels/land-administration/. (Accessed on Dec 23, 2013)*

James M. **Miller**, 1959: New Life for Cities around the World; international handbook on urban renewal..;

Demeke, 2012: *Housing Development in Addis Ababa* (*Pre and post 1991*), a study paper prepared for public forum, on the occasion of the 125th anniversary of Addis Ababa City

MUDHC, 2012: Housing Policy paper issued by the Federal Ministry of Urban Development Construction and Housing

UNHSP, 2003: *The challenge of slums: global report on human settlements,*

Corrected, and "Geurts,2013" is put in the first place

Elias Yitbarek 2008, *Revisiting «Slums», Revealing Responses Urban upgrading in tenantdominated inner-city settlements, in Addis Ababa, Ethiopia*, NTNU.

Juppenlatz, Morris. 1970.: *Cities in Transformation: The Urban Squatter Problem of the Developing World*. St. Lucia: University of Queensland Press.

David Drakakis-Smith, 1981: Urbanisation, housing and the development process.

CSA, 1999: The Population and Housing Census of Ethiopia: Results at Country Level. Volume I. Statistical Report. June 1999.

Lishan Seyoum, 2010: *Socio-Economic Impacts of Relocation in Addis Ababa: The Case of Relocatees From Sheraton Hotel and Economic Commission for Africa (ECA) Areas*,

Masters of Arts edn, Addis Ababa Univerisity, Addis Ababa.

Mesay Tefera, 2008: Land Development and Allocation in Addis Ababa: The Case of Meri-Luke and Cassanchis Housing Development Areas, Masters of Arts edn, Addis Ababa Univerisity, Addis Ababa.

Gebre Yntiso, June 2008: Urban Development and Displacement in Addis Ababa: The Impact of Resettlement Projects on Low-Income Households; From: Eastern Africa Social Science Research Review

Oakley, P. 1991: *Projects with people; the practice of participation in rural development,* International Labour Office, Geneva.

Imparato, I. & Ruster, J. 2003, *Slum upgrading and participation: lessons from Latin America,*World Bank, Washington, D.C.

## Acronyms

**AAHDPO**…………… Addis Ababa Housing Development Project Office
**AAHDA**……………………… Addis Ababa Housing development Agency
**MWUD**…………………….. Ministry of Works and Urban Development
**MUDCH** (*instead of* ***MoHUDC***)……… Ministry of Urban Development Construction and Housing
**FEACC**…………………….. Federal Ethics and Anti Corruption Commission

# የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች የአገልግሎት ችግሮች

*ፈቃዱ ጉርሜሣ*

## 1. መግቢያ

በትራንስፖርት ዘርፍ ዕውቅ የሆኑት ተመራማሪዎች በጽሑፋቸዉ ሰዎች ስለ ትራንስፖርት ያጎለበቱትን አመለካከት በተመለከተ በተለይም ብሪያን ሆዬል እና ሪቻርድ ኖውለስ (1998) የተባሉት ምሁራን መስኩን አስመልክተዉ በደረሱት መጽሐፋቸው ያሰፈሩትን በመግቢያነት መጥቀስ እፈልጋለሁ። እነርሱ እንዳሉት፣

> *የትራንስፖርት አጠቃላይ ጠቄሜታና አስፈላጊነት የማያጠራጥር ነዉ፣ ነገር ግን ዕለት ተዕለትነቱ ብቻ፤ ነገሮች ሲበላሹ ካልሆነ በቀር፣ ሁሌ ያለና የተለየ ትኩረት የሚስብ የጥናት ዓይነት አይደለም የሚል ግምት እንዲንሰራፋ አድርጓል። የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት፣ የትራንስፖርት አድማዎች አገልግሎቱን ሲገቱ፣ወይም ደግሞ በትራንስፖርት ዘርፍ በሕዝብ ዘንድ ግርምትን ፈጥረዉ ልብን የሚሰቅሉ አስደናቂ ግኝቶች ወይም ዉዝግብ የሚፈጥሩ ግኝቶች ሲከስቱ ትራንስፖርት የሚዲያ ትኩረት ነዉ።* (Hoyle & Knowles, 1998)

በእኔ ግምት የሆዬልና የኖዉለስ አስተዉሎት የትራንስፖርት ዘርፍን በተመለከተ በኢትዮጵያችን ካሳለፍነዉና አሁንም ስላለንበት ሁኔታ ዓይነተኛ ገላጭ ነዉ። ምናልባትም በሴክተር መሥሪያ ቤቱ ካልሆነ በቀር ከዚህ ግባ የሚባል ሚዲያዉንም ጨምሮ የሁሉንም ሕብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ሳይስብ ቆይቷል። በመግቢያዉ የጠቅስኳቸዉ ምሁራን እንዳመለከቱት የተፈጥሮ አደጋ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ሲከሰቱ ለተጠቁት ወገኖች ዕርዳታ ለማቀበል የትራንስፖርት ችግር ሁነኛ እንቅፋት እንደነበር በሚዲያዎቹ ተዘግቧል። የኢትዮጵያ ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተከትሎ በአዲስ አበባ የሕዝብ ትራንስፖርት በታክሲዉ ዘርፍ የተከሰተዉ የሥራ ማቆም አድማ ሚዲያዉንም ጨምሮ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ስቦ እንደነበር ከሁላችን የተሰወረ አይደለም። ምሁራኑ እንዳመለከቱት ነገሮች ሲበላሹ ብቻ

ለትራንስፖርት ትኩረት መስጠት የተለመደ ተግባራችን መሆኑ የሚካድ አይመስለኝም፡፡ "ነገሮች ሲበላሹ ብቻ" (When things go wrong)፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ፣ የትራንስፖርት ጉዳይ እንደ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ የዘርፉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ በጥቂቱም ቢሆን የምሁራን ተመራማሪዎችን፣የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችንና የሚዲያ አካላትን ቀልብ ገዝቷል፡፡ ዛሬ ምሽት በዚህ ተሰብስብን በአዲስ አበባ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ጉዳይ ላይ ባለ ድርሻ አካላት ተግኝተዉ እንዲመክሩ የForum for Social studies መድረኩን የማመቻቸቱ ሁኔታ የዚሁ የትኩረት ትኩሳት ነፀብራቅ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ በአብዛኛዉ የትራንስፖርት ጉዳይ ትኩረት የሚቸረዉ ""ነገሮች ሲበላሹ ብቻ" ነዉ፤ የሚለዉን የሆዬልንና የኖዉለስን ግንዛቤ የምንጋራ ከሆነ ምን ነገር ተበላሽቶ ነዉ የትራንስፖርት ጉዳይ በተለይም በአዲስ አበባ የትኩረት ትኩሳት እየሆነ የመጣዉ?

በአዲስ አበባ የመንገድ ትራንስፖርት የሕዝብ አገልግሎት ዙሪያ የተበላሸ ወይም ልክ ያልሆነ ነገር ነቅሶ ለማዉጣት መጀመሪያ በዛም አነሰ ልክ ይሠራል ሊባልለት የሚችል የከተማ የመንገድ ትራንስፖርት ምን ባሕሪያት እንዳሉት መገንዘቡ ይጠቅማል፡፡

## 2. የከተማ የመንገድ ትራንስፖርት የሕዝብ አገልግሎት ስርዓት ጤነኛ ባሕሪያት

- ❖ የትራንስፖርት ሪሶርሶችን ወጪ ቆጣቢ
    - ❍ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት
    - ❍ መሬት
    - ❍ ተሽከርካሪ
    - ❍ ነዳጅ
    - ❍ የሰው ኃይል ቆጣቢ
    - ❍ የተጠቃሚዉን ጊዜና ወጪ ቆጣቢ
- ከጥግግት (Congestion) ነፃ መሆን
- አስተማማኝ፣ በተፈለገበት ጊዜና ቦታ የመገኘት

❖ **ፍትሃዊና ተደራሽ መሆን**

የትራንስፖርት የፍትሃዊነት ጉዳይ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሁሉም ተደራሽ የመሆን ነው፡፡

- የተለየ ፍላጐት ያላቸውን
- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን
- መኪና የሌላቸውን
- አረጋውያንና ልጆችን/ለመንዳት ዕድሜ ያልደረሱ
- አካል ጉዳተኞችን
- በልማት ወደኋላ የቀሩ የከተማ ክፍሎችን

ታሳቢ አድርጎ የተቃኘ አገልግሎት የሚሰጥ የከተማ መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ነዉ፡፡

❖ **የደህንነት ደረጃውን የጠበቀ**

- ከአደጋ ነፃ የሆነ ወይም የአደጋ መጠኑ ያልተጋነነ
- ሕይወት የማይቀጥፍ
- ቀጣይነት (Sustainable) ያለው
- በሰውነት አቋሙ ዝውውር ማድረግ ቢችል፣ ባይችል፤ የገቢ መጠኑ ከፍ አለ ዝቅ፣ የማኀበራዊ ሕይወቱ ማንነት ከግምት ሳይገባ፣ የመሥሪያ ሆነ የመኖሪያ ቦታ ሳያግደው የግለሰብን የዝውውር ነፃነት የሚያረጋግጥ፡፡

❖ **አስተማማኝ**

- ከደጅ ደጅ የሚያደርስ
- ምቹ
- የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ

❖ **በመሠረተ ልማት አቅርቦት (Infrastructure)**

- ለሁሉም ሞዶች ፕላን፣ ፋይናንስ፣ ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ኦፕሬሽንና ጥገና ብቁ የሆነ
- የከተማ ልማቱ ከትራፊክ ፍሰቱ ጋር የተቀናጀ
- የከተማ ልማቱ በቁጥጥር የሚመራ (Development Control)

- የተለያዩ ሞዶች እርስ በእርስ በተመሳሰርና በመመጋገብ የተቀናጀ መሆን ይገባዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸዉ የከተማ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጤነኛ ባሕሪያት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ከብዙ በጥቅቱ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከእነኝህ ባሕሪያት አኳያ ሲገመገም እጅግ የወረደ እንደሆነ አንዳንድ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

የምናደርገዉ ዉይይት ፈር እንዲይዝና ድባቡም የተመቻቸ እንዲሆን በርዕሱ ለተመለከቱት ቃላት ወይም አባባሎች ትርጓሜ መስጠቱ የጋራ መግባቢያ ይፈጥራል ብዬ አምናለሁ፡፡

በርዕሱ ከተመለከቱት ገለጻ የሚያሻቸዉ አንኳር ነገሮች፤

1) ትራንስፖርት
2) የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች
3) የአዲስ አበባ ከተማና ትራንስፖርቷ

**1) ትራንስፖርት፡-**

**3. የትራንስፖርት ጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ**

የትራንስፖርት ጽንሰ ሐሳብ የሰዎች፣ የሸቀጦች (የጓዝ)፣ የሐሳብ (ideas) በሞተር ሆነ በሞተር አልባ የመጓጓዣ ዘዴዎች (modes) በመጠቀም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በተለይም ከአንድ መነሻ ወደ ሌላ መድረሻ መጓዝን ያመለክታል (Mekete Belachew, 2009)::

ለምሳሌ ብዙ ሰዎች ትራንስፖርትን ከመኖሪያ ቤታቸዉ ወደ ሥራቸዉ ቦታ፣ እንዲሁም ጓዛቸዉን (ሸቀጣቸዉን፣ ጭነታቸዉን) ከአንድ ከነበረበት ሥፍራ ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ትራንስፖርትን ይፈልጋሉ፡፡ ሰዎች ጤና፣ ትምህርት፣ የመሳሰሉትን፤በአብዛኛዉ በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የሚሰጡትን አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን የግድ እነዚህ አገልግሎቶች ወደሚሰጡባቸዉ ቦታዎች መሄድ ይኖርባቸዋል፤ ትራንስፖርት በምርትና በፍጆታ ቦታዎች መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ጥንታዉያን ማህበረሰዎች ትራንስፖርትን የመሠረታዊ ፍላጎቶቻቸዉ ማለትም የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያ ፍላጎቶቻቸዉን ለሟሟላት ይጠቀሙ ነበር፡፡ ነገር ግን ዛሬ ያደጉ ማህበረሰቦች ትራንስፖርትን ለመሠረታዊ ፍላጎት ሟሚያ ብቻ

ሳይሆን የማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶቻቸዉን ለሚሟላት ይጠቀማሉ፡፡

ዘመነኛዉ ማህበረሰብ ያለ ትራንስፖርት መሠረታዊ ፍላጎቶቹን እንኳ ሚሟላት አይችልም፡፡ መሠረታዊዉ የትራንስፖርት ተግባር ምርትን ከገበያ፣ ሰዎችን ከመኖሪያቸዉ ወደ አገልግሎት መስጫና ከመሥሪያ ቦታዎቻቸዉ እንዲደርሱና እንዲመለሱ ማድረግ ነዉ፡፡ በዚህም ትራንስፖርት ግለሰቦች ሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች በአቅራቢያቸዉ የማያገኙትን ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን በአቅራቢቻያዉ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

የትራንስፖርት ውጤት አገልግሎት ነዉ፡፡ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ ውጤት የለውም፡፡ ይሁን እንጂ የትራንስፖርት አገልግሎትን መግዛት ልክ ሌሎች የፍጆታ ሸቀጦችን አማርጠንና አንዱን ከሌላኛዉ ጋር አወዳድረን እንደ መገበያየት ዓይነት ትንሽም ቢሆን የመጋራት ባሕሪይ አለዉ፡፡ ይህም ባህሪይው የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡ ማመላለሻ ዘዴዎች አካላት የተሠሩባቸው የጥራት መጠን፣ የሚያስከፍሉት የትራንስፖርት ዋጋ፣ ሊሰጡ የሚችሉት ምቾት፣ፍጥነታቸዉ፣አስተማማኝነታቸዉና ደኅንነታቸዉ አንዱን የትራንስፖርት አገልግሎት ከሌላዉ ጋር እንደ ማነጻጸሪያና ማበላለጫ መሥፈርት ሊታዩ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ትራንስፖርት ከኢኮኖሚ ጠቀሜታ ገጽታዉ ባለፈ ማህበረሰብን ለብቁና ምሉዕ ማህበረሰብነት የሚያበቃ (social enabler) ነዉ፡፡ ስለዚህ ከትራንስፖርት ትንታኔ ውስጥ የማህበራዊ ጉዳይን ችላ ብሎ ማለፍ ፈጽሞ አይቻልም፤ በተለያዩ ደረጃዎች የሌሎች ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ተፈጥሮአዊ ጉዳዮችን ምንነትና ክንዋኔን፣ እንቅስቃሴና የተግባራት አሰረጫጨትን፤ በእነዚህም መካከል የሚኖረውን ውስብስብ ትስስር የሚሳይ ዓይነተኛ መገለጫ ነዉ፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላኛዉ ቦታ መንቀሳቀስ (መጓጓዝ) የዕለት ተዕለት የሰው ልጅ ተግባር፣ ፍላጎትና መሠረታዊ ክንዋኔ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት በእጅጉ እንዳይሟላ የተለያዩ የሰዉ ሰራሽና (ማህበራዊና) ተፈጥሮአዊ ችግሮች ተጋርጦበታል፡፡ ዋነኛው ጋሬጣ ከአንድ መነሻ ቦታና ከሌላኛው የመድረሻ ቦታ መካከል ሊኖር የሚችለው ‹ርቀት› (distance) የሚባለዉ እኩይ ክስተት ነው፡፡ ይህም ‹ርቀት›፣ ለመጓጓዝ

በሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን፣ ርቀቱ በሚፈጀው ጊዜና እንዲሁም በሚያስከተለው ድካም ሊገመትና ሊሰላ ወይም ሊገለፅ ይችላል፡፡

3.1 *የትራንስፖርት ዓላማ፡-* ቀለል ባለ መልኩ የከተማ መንገድና ትራንስፖርት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማ፣

- የአገልግሎቱ መስጫ ቦታዎችን ከአገልግሎት ፈላጊው ጋር መገናኘት፣

ለምሳሌ ፡- የታመመውን ወደ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማድረስ፣

- ተማሪ፣ አስተማሪው በጊዜ ት/ቤት ተገኝቶ በሥራ ገበታው እንዲገኝ ማድረግ
- የፋብሪካው ሠራተኛ በምርት ሥራው ላይ በተመደበበት ጊዜ እንዲገኝ ማድረግ
- የመገበያያ፣ የመዝናኛ ቦታዎችን ተደራሽ ማድረግ
- የማምረቻ ሥፍራዎችን ከገበያ ጋር ማስተሣሠር
- የከተማው ኗሪ የዕለት ተዕለት የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የተቀላጠፈ እንዲሆን መርዳት… ወዘተ

በሌላ በኩል ደግሞ የትራንስፖርት ዓላማ ወይም ግብ ሰዉ ሰራሽና ተፍጥሮአዊ ጋሬጣዎችን (constraints) እንደ ርቀት፣ ጊዜ፣ አስተዳደራዊ ድንበሮችን፣ አስቸጋሪ የሚባሉ መልከዓ ምድራዊ ጋሬጣዎችን አሸንፎ የሰዉ ልጅ ሆነ የሚንንዘዉ ነገር ከታሰበበት ቦታ እንዲደርስ ማገዝ ነዉ፡፡ እነዚህ ጋሬጣዎች በጥቅሉ ‹የርቀት ፍትጊያ› (Friction of Distance) በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሰው ልጅ ባሳለፈዉ የታሪክ ዘመናት የቦታ ርቀትን አስቸጋሪነት ለማስወገድ ያልተቋረጠ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፤ እንዲሁም ዘመናዊዉ ሰው በተራቀቀ ቴክኖሎጂው በመታገዝ ይህንን ተግዳሮት ለማስወገድ ባለው በሌሌው አቅሙ ታግሏል፡፡ በዚህም ትግሉ የጊዜንና የቦታ ከቦታ ርቀትን (በትራንስፖርትና በኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ) ተግዳሮት በአስደናቂ ሁኔታ ከቁጥጥር ሥር ለማዋል ችሏል ለማለት ከሚያስደፍር ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ከዚህም የተነሣ ነው ‘ ዓለም እንደ አንድ መንደር ሆናለች’ የሚል አባባል ሠርክ የምንሰማው፡፡ በኢኮኖሚ የበለፀጉት አገሮች የትራንስፖርትና የኮሚዩኒኬሽን መሠረተ ልማቶቻቸው በእጅጉ ያደገ በመሆኑ ከአፅናፍ አፅናፍ፣ ከቦታ ቦታ፣ ከከተማ ገጠር፣ በከተማቸውም ውስጥ የመንንዝ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡

የሰዉ ልጅ የመጓጓዣና የመገናኛ ጋሬጣዎችን ገርስሶ በቀበረዉ መቃብር ተንተርሶ የተንሰራፋዉ ግሎባላይዘሽን የተባለዉ የዘመናችን ክስተት ለበለፀጉት አገሮች ዓለማችን እንደ አንድ መንደር የሆነችበትና ለታዳጊ አገሮች ግን የቀድሞ መንደራቸዉ እንኳ ተራርቆባቸዉ ሰፊ ዓለም የሆነበት ሁናቴ ላይ እንገኛለን፡፡ በአዲስ አበባችን እንኳ ቀድሞ ከለገሀር ተነሥተን ቢሾፍቱ መድረስ እንችል በነበረበት ጊዜ ዉስጥ ከለገሀር ተነሥተን ቃሊቲ መድረስ የማንችልበት ሁኔታ ተፍጥሯል፡፡

ባለንበት የግሎባላይዘሽን ዘመን የሰዉ ልጆች ከቦታ ቦታ የመዘዋወር/የመጓጓዝ ፍላጎት ባደጉትም ሆነ በታዳጊ አገሮች ተገትቶ ይገኛል፡፡ ይህም መገታት እንደየአገራቱ የኢኮኖሚ አቅምና ዕድገት ደረጃ ጊዜያዊ፣ወይም ለረጅም ጊዜ ወይም ዘላቂ ሊሆን ይችላል፡፡ አብዛኞቹ ችግሮች የሚመነጩት ከኢኮኖሚ አቅም በተለይም የትራንስፖርት ወጪ ከመሸፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ በርካታ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ለማድረግ ለሚሹት ጉዞ የመጓጓዣ ወጪ መሸፈን አይችሉም፡፡ በአደጉት አገሮች እንኳ ሁኔታዉ እንደ ታዳጊ አገሮቹ የከፋ ባይሆንም የመጓጓዝ ክፍተት ይታያል፡፡

ዞሮ ዞሮ የትራንስፖርት ዓላማና ግብ መልክዓ ምድራዊ ነዉ፣ማለትም በሁለት በተለያዩ ሥፍራዎች ባሉት ቦታዎች መካከል ያለዉን ጉዞ ማመቻቸት፣ ቦታዎቹን ማቀራረብ፣ የርቀት አድካሚነትን መቀነስ ወዘተ ናቸዉ፡፡ በዚህም ባህሪይዉ ትራንስፖርት ሥፍራዎችን ያዋቅራል (structure) ያደራጃል (organize) አንዳንድ ሥፍራዎችን ከሌሎች መሰል ሥፍራዎች በዋጋ በማበላለጥ አንዳንዶቹን ሥፍራዎች ለመኖሪያነት፣ አንዳንዶቹን ደግሞ ለመሥሪያቤትነት እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ዋነኛዉ መንስዔና ምክንያት የአንድ ቦታ ከሌላኛዉ ቦታ የመቅረብና የመራቅ ጉዳይ ሲሆን ይህም የትራንስፖርት ወጪ ልዩነትን በማስከተል አንድን ቦታ ከሌላኛዉ ሥፍራ ተመራጭ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 3.2. *የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ጽንሰ ሐሳብ*

የ"ሕዝብ ትራንስፖርት" የሚለዉ ሐረግ አሻሚ ትርጉሞች ስላሉት ለመግባባት ሲባል ትንሽ ማየት የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ በአንድ በኩል፣ የአገልግሎቱን ዋጋ መክፈል እስከ ቻለ ድረስ መጓጓዣዉ የማን ይሁን የማን ማንም ሰዉ የሚሣፈርበት ማለት ነዉ(White, 2002)፡፡ በአማርኛ ሆነ በእንግሊዘኛ

ትርጉሙ "የሕዝብ" ወይም "public" የሚለዉ ቃል "የመንግሥት" ወይም "የጋሪዮሽ፣ የማንም" ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ለምሳሌ፣ Anbessa bus is a public transport owned by Public Agency በሚለዉ አረፍተ ነገር ዉስጥ ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡ በትራንስፖርት ቋንቋ ሌላም ቃል አለ፣ በእንግሊዘኛ "Passengers Transport" ይባላል፡፡ ይህ አባባል "የሕዝብ ትራንስፖርት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ነገር ግን "public transport" ከሚለው ትንሽ ሰፋ ይላል፡፡ ምክንያቱም "Passengers Transport" የከተማ መንገድና ትራንስፖርትን የሚጠቀሙ ሌሎች የግል ተሸከርካሪዎችንና (የጓዝ የጭነት መኪኖችን በስተቀር) ሌሎች የከተማ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን ስለሚጨምር፡፡ ስለዚህም ነዉ በአርዕስቱ እንደተመለከተዉ "ሕዝብ" ከሚለዉ ይልቅ "Passengers Transport" "የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች" ያልኩት፡፡ እናም በዚህ ፅሑፍ ዉስጥ ለእኔ "የሕዝብ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚ" ማለት ነዉ፡፡

## 4. የከተማ መንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ችግርን የመገንዘቢያ አቅጣጫ

- የከተማ ጉዞንና ትራንስፖርትን ችግር ከሲስተም አቅጣጫ ማየት
- ሲስተም ምንድን ነው?
    - ሲስተም ተደጋጋፊና ተዛማጅ ከሆኑ የተለያዩ አካላት(Components) የተቀናጀ ወጥ ውቅር ነው
- የሲስተም ዓላማ
    - በአካላቱ መካከል በሚደረግ መስተጋብር የታለመለትን ዓላማ መተግበር፣
    - የመንገድና ትራንስፖርት የሕዝብ አገልግሎት መሳለጥ/ አለመሳለጥ የአንድ አካል ውጤት አይደለም፣
    - የትራንስርፖት ችግርን መንስዔ ለመረዳት የሲስተም አተገባበርን መፈተሽ ያሻል፡፡
- የከተማ ውስጥ ዝውውርና ትራንስፖርት አገልግሎት ሲስተም አካላት
    - የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና አወቃቀራቸው
    - የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ

- የከተማ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች
- የከተማ ትራንስፖርት ሞዶችና ሞዳዊ የእርስ በርስ ትስስሮች (Intermodal connections) ናቸው፡፡

ሜዬሪና ሚለር የተባሉት እዉቅ የትራንስፖርት ምሁራን የከተማ ዉስጥ ዝዉዉርንና ትራንስፖርትን ችግር በአግባቡ ለመረዳት የከተማ ጉዞንና ትራንስፖርትን ባሕሪያት ከሲስተም አቅጣጫ (System perspective) ማየት ተገቢ ነዉ ይላሉ (Meyer & Miller, 2001)፡፡ ለዚህም በመጀመሪያ የሲስተም ትርጓሜ ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-

> *A system is a group of interdependent and interrelated components that form a complex and unified whole intended to serve some purpose through the performance of its interacting parts.* (Meyer & Miller, 2001)

ከዚህ ከላይ የተመለከተዉን የሲስተም ትርጓሜ ከሰጡ በኋላ ትርጓሜዉ ለትርንስፖርት ግንዛቤ ምቹ መሣሪያ ነዉ ይላሉ፡፡ የዚህም ትርጓሜ ጠቅለል ባለ መልኩ "ሲስተም በአካላቱ መካከል በሚከሰት መስተጋብር የታለመለትን ዓላማ ለመተግበር ተደጋጋፊና ተዛማጅ ከሆኑ የተለያዩ አካላት ረቂቅና የተቀናጀ ዉቅር ነዉ"፡፡ ይህም ማለት የከተማ የመንገድ ዝዉዉር መሳለጥ የአንድ የስስተም አካል ዉጤት ሳይሆን ተደጋጋፊና ተዛማጅ የሲሰተሙ አካላት ረቂቅና የተቀናጀ መስተጋብር ዉጤት ነዉ፡፡ አንድ ሲስተም ከታለመለት ዓላማ አኳያ ተቀባይነት ያለዉና ተፈላጊ ዉጤት ካልሰጠ ለችግሩ መንስዔ የሲስተሙን ጠቅላላ አካላት አተገባበር (across the components of the system) መፈተሽ ያሻል ማለት ነዉ፡፡

የትራንስፖርት ችግርን በአግባቡ ለመረዳትና የመፍትሔ ሀሳብ ለመስጠት የሲሰተም አቀራረብ ጠቀሜታን የሚያሰምሩበት ሌሎች የዘርፉ ምሁራን ብሪያንና ኖዉለስ ናቸዉ፡፡ ከሞድ አቅጣጫ ማለትም መንገድን፣ ባቡርን፣ የትራፊክ ፊስትን፣ ታክሲን፣ የአዉቶቢስ አገልግሎትን፣ የግል ይዞታ አቶሞቢሎችን/ ሞተራይዘሽን፣ እግረኛን ወዘተ በተናጠል ችግራቸዉን የሚያጠና ትዉፊታዊ አቀራረብ ምንም እንኳ ለአንዳንድ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን (Specific issues) ከቅርበት ለማጥናት ካልሆነ በቀር የትራንስፖርት አገልግሎት ሞዶችን የርሰ በርስ ትስስርና ተደጋጋፊ አገልገሎት ከግምት ማስገባት ያቅተዋል ይላሉ (Brian & Knowles, 1998) ፡፡

ሌላኛዉ በጣም የተለመደ አቅጣጫ የፋክተር አቀራረብ/ Factors Approach ማለትም የትራንስፖርትን የመንገድ መረብ ለመዘርጋትና የትራንስፖርትን ፍላጎት ለማሟላት እንቅፋት የሚሆኑ የተፈጥሮ ጉዳዮችን፣ የኢኮኖሚ አቅምንና የመሳሰሉትን በተናጠል ማጥናት ማለት ነዉ፡፡ የትራንስፖርት ስስተምን አቅምና ዉስንነትን በማስገንዘብ አኳያ ጠቃሚ ቢሆንም ለአንድ ለተለየ ፋክተር/Specific Factor ትኩረት መቸር እነኝህ ፋክተሮች በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተደጋጋፊ ጫና እንደሚያሳድሩ አበክረን እንዳንገነዘብ ዕይታችንን ያደበዝዛሉ በማለት ይህንን ትዉፊታዊ አቀራረብ ይኰንናሉ፡፡

በርግጥ የትራንስፖርት ሲስተም ከተሞች ከተማ እንዲሰኙ ወይም ለከተማነት ከሚያበቋቸዉ ለምሳሌ፡-

- የከተማ መሬት አጠቃቀም፣
- የዉኃ አቅርቦትና ስርጨት፣
- የኤሌክትሪክ ኃይል መስመር፣
- የጽዳትና የቆሻሻ ማስወገጃዎች፣
- የትምህርት ድርጅቶች፣
- የቴሌኮሚዩኒኬሽን መሰረተ ልማት እና ከመሳሰሉት ከበርካታ ሌሎች የከተማ ሲስተሞች መካከል አንዱ ሲስተም መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የከተማ መንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ሲስተም ከእነኝህ እህት ሲስተሞች ጋር ጤናማ መስተጋብር እንዲኖረው ግድ ይላል፡፡ ለጤናማ ከተማ ሕይወት አንዱ ሲስተም ከሌላኛው ጋር መጣረስ የለበትም፡፡


ሚለርና ሜዬር የከተማ ውስጥ ዝውውርና ትራንስፖርት አገልግሎት ሲስተም አካላት ናቸው ያሏቸዉን፣

- የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና አወቃቀራቸው፣
- የትራንስፖርት መሠረተልማትና የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ፣
- የከተማ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች፣
- የከተማ ትራንስፖርት ሞዶችና ሞዳዊ የእርስ በርስ ትስሰሮች (Intermodal connections) በማለት ዘርዝሯቸዋል፡፡

## 5. አዲስ አበባና ትራንስፖርቷ

በ1879 ዓ.ም ተወልዳ በ1884/5 ዓ.ም (Bahru Zewde, 1991) ለኢትዮጵያ ዋና ከተማነት የታጨችዉ አዲሰ አበባ 125ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሏ አከባበር በርካታ ተግባራት በከተማዉ እየተከናወኑ ባሉበት በአሁኑ ወቅት፣ የዕድገቷን ታሪክ እያወሳን በትራንስፖርቱ ዘርፍ ያስመዘገበችዉን እመርታና በዚሁ ዘርፍ እየገጠማት ያለዉን ተግዳሮት ለመዳሰስና ለመወያየት በኤፍ.ኤስ.ኤስ መታደማችን እጅግ በጣም ጥሩ አጋጣምሚ ነዉ።

ካርታ 1:- በምሥረታዋ የመጀመሪያ አምስት ዓመታት የአዲስ አበባ መንገዶች ገጽታ (According to Yirgalem,2008)





አዲስ አበባ በምስረታዋ ማግስት የዘመናዊቱ ኢትዮጵያ መዲና ከመሆን ባሻገር በመላዉ ዓለም ዝናዋ ናኝቶ በእጅጉ እንድትታወቅና የነጮቹንም ሆነ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ቀልብ እንዲትስብ የሚያደርግ ታሪካዊ የ1888 ዓ.ም የአድዋ ጦርነት ተከሰተ። ጦርነቱ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቀቀ። ይህም

ለመጀመሪያ ጊዜ ነጮች በጥቁሮች እጅ ድል የሆኑበት በመሆኑ ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከማሳወቁም በላይ፣ ኢትዮጵያ ለወዳጅነት የምትፈለግ አገር እንጂ ለጠላትነት የማትመች መሆኗን የተረዱት ምዕራባዉያን ቅኝ ገዢዎችና ሌሎችም አዲስ አበባን በዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖቻቸው ማጥለቅለቅ ጀመሩ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ነፃነት አፍቃሪ የኢትዮጵያ ሕዝብና መሪዎቿ በቅኝ ግዛት ይማቀቁ ለነበሩ አፍሪካዉያን ወንድሞቻቸዉ ያሳዩት የወገናዊነት ትግል ሰምሮ እ.ኤ.አ. በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት የአዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናነት ታሪክ እዉን መሆን ጀመረ፡፡ በዚህ ሚናዋ የሚቀኑ አንዳንድ ኃይሎች አልጠፉም፡፡ ነገር ግን በልጆቿ አይበገሬነት የአፍሪካ መዲናነቷ ይህ ፅሑፍ እስከቀረበበት ጊዜ እርግጥ ሆኗል፡፡ በዚህ አጋጣሚ በሕልፈተ ሕይወት የተለዩን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የአዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናነት ሚና ሳይደበዝዝ እንዲቀጥል በአፍሪካ ስብሰባዎች የተፋለሙትን ፍልሚያ ማስተወስ ግድ ይላል፡፡

ዛሬ፣ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ትልቁ ሜትሮፖሊስና ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ ኦፊሴላዊ ዲፕሎማቲክ መዲና እንዲሁም የአፍሪካ ሕብረት ዋና መሥሪያ ቤትና ብዙ የተለያዩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ በመሆኗ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ይኖሩባቸዋል ከሚባሉት የዓለም ከተሞች በአራተኛነት ተርታ ላይ ትገኛለች (Peng Mo, et.al, 2008) ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አመሠራረትና እድገትን ሁኔታ ካርታ-1-ንና ካርታ -2-ን በማስተያየት የበለጠ ማጤን ይቻላል፡፡


ካርታ 2:- የሐርትሾርን የከተማ መንገዶችና የከተማ አራዳዎች (Nodes) አፈጣጠርና ዕድገት ሞደል (Meyer & Miller, 1998)




የአፄ ምንሊክን ግቢ ማዕከል አድርገን፣ አራዳ ጊዮርጊስን፣ ራስ ብሩ ሠፈርን፣ራስ ተሰማ ሠፈርን፣ፊታዉራሪ ኃብተ ጊዮርጊስን ሠፈር፣ ዘበኛ ሠፈርንና ዉኃ ስንቁን ሠፈር አካታ (Bahru Zewde, 1991) የተመሠረተችዉ አዲስ አበባ በመቶ ሃያ አምስት ዓመቷ አድጋና ሰፍታ 540 ኪሎ ሜትር ካሬ ሆናለች፡፡ ይሁን እንጂ በሐርትሾርን ሞዴል በተመለከተዉ ሂደት የከተማ መንገዶቿና አራዶዎቿ አልተፈጠሩም፡፡ ይህ ጥናት በተደረገበት አመት የቆዳ ስፋቷ የተለያየ መጠንና የሕዝብ ብዛት ባላቸዉ 10 ክፍለ ከተሞች እና 116 ወረዳዎች ተከፋፍሏል (የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ቢሮ፡ 2005)፡፡ በአፄ ምንሊክ የመጨረሻ ዘመን አካባቢ 80000 (ሰማኒያ ሺ) (Yirgalem, 2008) ገደማ የነበረዉ የሕዝብ ብዛቷ ከሶስት ሚሊዮን በላይ ሆኗል፡፡ የከተማው ህዝብ ቁጥር ከ1953 እስከ 1976 ዓ.ም በሶስት ዕጥፍ ያደገ ሲሆን ከ1976 እስከ 2000 ዓ.ም በዕጥፍ አድጓል፡፡ የከተማው ህዝብ በ2.9 በመቶ

እያደገ ያለ ሲሆን በ2012 ዓ.ም ወደ 5 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። በ150 ታዳጊ አገሮች የተደረገዉ ጥናት እንደሚያሳየው ለእያንዳንዱ 1000 የሰው ብዛት ጭማሪው በየቀኑ ከ350 እስከ 400።

ካርታ 3፡- እ.አ.አ ከ1886-2003 የአዲስ አበባ ከተማ የቆዳ ስፋት አጨማመር (According to Yirgalem, 2008)




የሚደርስ የህዝብ ትራንስፖርት ጉዞን ሊያስከትል እንደሚችል፤ በሌላም በኩል ደግሞ በከተማ የቆዳ ስፋት ላይ የእያንዳንዱ የአንድ ኪሎ ሜትር ካሬ ጭማሬ የ500 ያህል የህዝብ ትራንስፖርት ጉዞን ሊያስከትል እንደሚችል ያሳያል (Transport Research Laboratory, (2002))።

በ1894 ዓ.ም ግድም በዘመናቸዉ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ መጠን አዲስ አሠራር ነዉ በሚባል መልኩ ከቤተ መንግስት እንጦጦ፣ ከቤተ መንግሥት አዲስ አለም ከተዘረጉት ሁለት መንገዶችና(የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ሚያዚያ 2004) ከነበሩት ሠፈሮች ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወስዱ የተወሰነ መረብ የነበራቸዉ የሠፈር የእግር መንገዶች ለሰዉና ለጓዝ ማመላለሻ በቅሎ (ካርታ 1 ይመልከቱ)፣ ፈረስና አህያ ማስተናገጃ የነበሩት

መንገዶች ሲዘረጉ ከነበራቸዉ ዓላማ ዉጭ በቴክኖሎጂና በመጠን አድገዉ ዛሬ 1758 ኪ.ሜ የአስፓልት መንገድ፣1687 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ፣ 530 ኪ.ሜ የእግር መንገድ በጥቅሉ 3512 ኪ.ሜ ደርሷል፡፡(ፍኖተ አዲስ፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን መስከረም 2004 ቁ. 6) ይህም የመንገድ ሽፋን 13.7% መሆኑ ነዉ፡፡ በአፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት ማብቂያ ግድም በ1899 ዓ.ም አዲስ አበባ የገቡት ሁለት መኪናዎች በቁጥር በዝተዉ 116,297 ሆኗል (የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽንቢሮ፡2005)፡፡

አዲስ አበባ ሞቅ ያለች፣ ታዳጊና በፍጥነት እየተለወጠች ያለች ሜትሮፖሊታዊ ከተማ ናት፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከተማዋና በዳርቻቿ እየተከናወኑ የሚገኙት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የገቢ መጠናቸዉ መኪና መግዛት የሚያስችላቸዉን የመካከለኛ ገቢ ያላቸዉ ጥቂት የሕብረተሰብ ክፍል መፍጠር በማስቻሉ የግል ይዞታ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ የጎዳናዋን የመንገድ መረብ እያጣበበዉ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የሞተራይዘሽን ወይም የነፍስ ወከፍ የግል መኪና ይዞታ መጠን እጅግ አነስተኛ ነዉ፡፡ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የፋይናንስና የንግድ ተቋማት የሚገኙባት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማዕከልና 85% የሚሆነዉ የአገሪቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ባለቤት ናት፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ በታሪካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዋ አንፃር የአፍሪካ መዲና ብሎም የዓለም አራተኛ ዲፕሎማሲያዊ ማዕከልም ናት፡፡ እ.ኤ.አ በ2007 በተደረገዉ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መሠረት 2,738,248 ከነበረዉ የነዋሪዋ ቁጥር አብዛኞቹ 75% በ15 እና በ64 መካከል ባለዉ የዕድሜ ክልል የነበሩ የወጣት ጎልማሶች ከተማ ናት፡፡ ከአጠቃላይ የከተማዉ ሕዝብ 24% ከ15 ዓመት ዕድሜ ክልል በታች የሚገኝ ሆኖ ቀሪዉ 3% የ65 ዓመት ወይም በላይ የሆናቸዉ አረጋዉያን ነበሩ፡፡

አብዛኛዉ የአዲስ አበባ ሕዝብ በጣም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ደሃ ነዉ፡፡ 48.4% ያህሉ ቤተሰብ ከድህነት ወለል በታች 23% ደግሞ እጅግ የነጡ ከፍጹም የድህነት ወለል በታች የሚገኙ ነበሩ (Mitiku, 2011)፡፡ እንደ ምትኩ አስማረ ገለጻ ከኗሪዉ አማካይ የወር ገቢያቸዉ ከ4000 ብር የሚዘለዉ 0.6% የሚሆን ቤተሰብ ብቻ ነዉ፡፡ ከዚህም የተነሣ 10% የሚሆኑ ቤተሰቦች ብቻ መኪና ሲኖራቸው ከ9% የማያንስ የቤተሰብ ገቢ በትራንስፖርት ይጠፋል፡፡

በአገሪቷ ከተመዘገቡት ተሽከርካሪዎች 80% የሚገኙባት አዲስ አበባ ባሏት ጎዳናዎቿ በቀን 4 (አራት) ሚሊዮን ያህል የመንገድ ተጠቃሚዎችን ታስተናግዳለች (Berhanu, et. Al., 2011)፡፡ በአማካይ ዕለታዊ ሁኔታ ሲሰላ ለትምህርትና ለሥራ ጉዳይ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ከፍተኛዉን ከቦታ ቦታ ዝዉዉር ድርሻ ይጋራሉ፡፡ ከከተማዋ የዝቅተኛ የመንገድ መረብ ሽፋን፣ከዝቅተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት ተደራሽነትና ከዝቅተኛ ገቢ የተነሣ ከ60-70% የሚሆነዉ የከተማዉ ኗሪ በከተማዉ ጎዳናዎች ከቦታ ቦታ ለየጉዳዩ የሚንቀሳቀሰዉ በእግሩ ነዉ ((የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽንቢሮ፡ 2005፣ Mitiku, 2011; AAUTS 2004/2005፣Transport Research Laboratory,(2002))::

የአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብ በከተማዋ የዕለት ተዕለት ኑሮዉን ለማሸነፍ የሚያደርገዉ ከቦታ ቦታ ዝዉዉር በእጅጉ የተገታና ቢያደርግም ለጤናው፣ ለሞራሉ፣ለኢኮኖሚዉ አሉታዊ የሆኑ እጅግ አስከፊ ዉጣ ዉረዶችን መጋፈጥ ይጠበቅበታል፡፡ ኗሪዉ እስከመቼ? እያለ ማጉረምረም ከጀመረ ዉሎ አድሯል፡፡ የከተማዋ የመንግሥትም ሆነ የግል ሚዲያዎች በቂ ሽፋን በመስጠት የከተማዋን ትራንስፖርት መሽመድመድና ለሞት ማጣጣር ዘግበዋል፡፡ አስገራሚው ነገር ደግሞ የከተማዋ ትራንስፖርት አለመመቸት መኪና ላለውም ሌላውም የመንገድ ተጠቃሚ የመሆኑ ጉዳይ ነዉ፡፡ ግራ የሚያጋባ ነገር ቢኖር ደግሞ ይህ ሁሉ ችግር የሚከሰተዉ መንግሥት ጉዳዩን አጢኖ መፍትሔ ለመስጠት እጅጉን እየተጋ ባለበት ሁኔታ መሆኑ ነዉ፡፡

ችግሩ ምኑ ላይ ነው? ይህንን ከመመልከታችን በፊት ችግሮቹን ነቅሰን ለማዉጣት እንሞክር፡፡

## 6. የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ችግሮች

አዲስ አበባ እንደማንኛቸዉም የታዳጊ አገሮች ከተማ የግል መኪና የነፍስ ወከፍ ይዞታ ዝቅተኛ፤ ለትራንስፖርት መሠረተልማት ግንባታ፣ጥገናና አስተዳደር የፋይናንስ ዕጥረት ያለባት ከተማ ነች፡፡ በተጨማሪም የትራንስፖርትና የከተማ መሬት አጠቃቀም  ቅንጅትና አፈጻጸም፣ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ድክመት በስፋት ይስተዋልባታል፡፡ በከተማዋ ጎዳናዎች የተጠቃሚዎች ዝዉዉር እ.አ.አ በ2001-2010 በነበረዉ የ13 ዓመታት ጊዜ ዉስጥ ብቻ በ250% በመቶ ጭማሬ አሳይቷል፡፡

ከህዝብ ትራንስፖርት አሰጣጥ አኳያ (እ.አ.አ በ1984) 12 በመቶ የነበረዉ የአንበሳ አዉቶበስ ድርሻ እ.አ.አ በ2010 ወደ 16 በመቶ ሲያድግ በተመለከተዉ ዘመን የታክሲ ድርሻ ከ10 በመቶ ወደ 24 በመቶ እድገት አሳይቷል። የግል መኪናዎች ድርሻ ከ 8 ወደ 5 በመቶ ቀንሷል።

እ.አ.አ በ1982 የአንበሳ አዉቶቡስ በ126 አዉቶቡሶች በመታገዝ በ42 መሥመሮች፣ 4500 ተራ ታክሲዎችና ዉይይት ታክሲዎች አገልግሎት ይሰጡ እንደነበርና የግል ተሽከርካሪ መኪናዎች 33000 ሆነዉ የከተማዉ ኗሪ የተሽከርካሪ መኪና ጥመርታ 1:40 እንደነበር ተዘግቧል(Cesen-Ansaldo Finmeccanica, 1986)። ሴሴን አልሳንዶ በጥናቱ እንዳመለከተዉ የአዲስ አበባ ከተማ በጥናቱ ዘመን (እ.አ.አ 1982) ከነበረባት ብሎም በአዲሱ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አሥር ዓመት ከተማዋ ከሚኖርባት የሕዝብ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ችግር ትንሽ ፋታ ለማግኘት 50 የከፍተኛ ፍጥነት ባቡሮች፣250 ጃምቦ ትራሞች፣ 700 አዉቶቡሶች፣400 ትሮሊ ባሶች፤1500 አነስተኛ ማመላለሻ መኪኖች ያስፈልጓታል ሲል ገልፆ ነበር።

ዛሬ 30 ዓመታት ከሴሴን አልሳንዶ ጥናት በኋላ በአዲስ አበባ 93972 የቤት መኪናዎች፣ የአንበሳ አዉቶቡስ 645 (158 በጥገና ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ ያሉ)፣ሚኒ ባስ፣ ውይይትና ሀይገር (ሚዲ ባስ) በድምር 9750፣ እና 6795 የሳሎን ታክሲዎች ይገኛሉ (የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ቢሮ፡ 2005)።

ከዚህ መረጃ የከተማይቷ ጎዳና ዕለት ተዕለት የምትጨናነቀው አነስተኛ የወንበር ቁጥር ባላቸው ከጠቅላላው በከተማዋ ከሚገኙ ተሽከርካሪዎች 80.8 ከመቶ በሚያህሉ 93972 የቤት መኪኖች መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 1:- እ.አ.አ የአዲስ አበባ የሞዶች ድርሻ (1984)፣ (2005)፣ (2010) (According to Brehanu et.al, 2011) በ*የተመለከተው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኪሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፣ (2005 ዓ.ም.) የተወሰደ ነው፡፡

| የሞዱ ዓይነት | የሞድ ድርሻ ከመቶኛ ሲሰላ (እ. አ. አ) | | | |
|---|---|---|---|---|
| | (1984) | (2005) | (2010) | (2012)* |
| እግረኛ | 70 | 60 | 55 | 60.5 |
| አዉቶቢስ | 12 | 11 | 16 | 11 |
| ታክሲ | 10 | 21 | 24 | 20.6 |
| መኪናና ሌሎች | 8 | 8 | 5 | 3 |

በ2002 ዓ.ም የአዲስ አበባን ከተማ ትራንስፖርት ፖሊሲ አስመልክቶ ለባለ ድርሻ አካላት ለውይይት የቀረበ ረቂቅ የከተማውን ትራንስፖርት ችግር አስመልክቶ አንዳንድ ነጥቦችን አስፍሯል፡፡

- ✓ በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት የሥራ፣ የትምህርት፣ የጤናና የሌሎች ተደራሽነት አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ✓ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዕጥረት መኖር፤ ከዋና ዋና መንገዶች ዉጪ ያሉ ነባር የመኖሪያ ሠፈሮችና አዳዲስ መንደሮች በአብዛኛዉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ ያለመሆን፤
- ✓ የመጓጓዣ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመርና በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ላለው ሕብረተሰብ የኢኮኖሚ ጫና ማሳደሩ፣
- ✓ ሞተር አልባ የሆኑ መጓጓዣ ዘዴዎች (ለብስክሌትና እግር ጉዞ) የማይመች መሆኑ፣
- ✓ በከተማዉ መስፋት ምክንያት የሥራና የመኖሪያ ቦታ መራራቅ፣
- ✓ የትራፊክ አደጋ ከፍተኛ መሆን፣
- ✓ የአየርና የድምፅ ብክለት መጨመሩ፣
- ✓ የመንገድ ላይ ፓርኪንግ መበራከትና በትራፊክ ፍሰቱ ላይ ጫና ማሳደሩ፣

- ✓ ከመንገድ ውጭ የፓርኪንግ ቦታዎች አለመኖራቸዉና የመናኸሪያዎች ማነስ ወይም ምቹ አለመሆንና ያፈጻጸም ችግሮች፤ የሚሉትን አስፍሯል፡፡
- ✓ የመንገድ መጥበብ (በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፣ 2002)


ሌሎች ምንጮች ደግሞ:-

- ➢ የከተማዋ የመንገድ ርዝመት መጠን፣ እያደገ ከመጣዉ የከተማዋ የሕዝብና የተሽከርካሪ ቁጥር ጋር አለመመጣጠን፣
- ➢ በከተማዋ ጎዳናዎች ላይ በፍጥነት እያደገ ያለዉ የተሽከርካሪዎች ከቦታ ቦታ ዝዉዉር፣
- ➢ የከተማዋ የቆዳ ስፋት ያለ አግባብ መለጠጥ፣
- ➢ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅና በቂ ያልሆነ የከተማ ትራንስፖርት ሲስተም ዕቅድና

የመሳሰሉትን ችግሮች ጠቅሰዉ ሌሎች ማለትም በፈጣን የከተማዋ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት፣ የዘርፉ ዝቅተኛ የጊዜ፣ የገንዘብ፣ የጉልበት ቆጣቢነት አቅም፣ የአስተማማኝነት፣ የደኅንነት ደረጃ፣ደንብ የማስከበርና የፋይናንስ ዉስንነት ችግሮች የተጠቀሱትን ችግሮች እንዳባባሱ ያመለክታሉ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የአዲስ አበባ የመንገድ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ችግሮች ከሲስተሙ ጤናማ ያልሆነ አተገባበር የመነጨ ተቀባይነት የሌላቸውና አላስፈላጊ ውጤቶች ናቸው፡፡ ለችግሮቹ መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው መንስዔያቸዉን በሲስተሙ አካላት/ የእርስ በርስ መስተጋብርና የዚሁ ሲስተም አካላት ከሌሎች የከተማው ሲስተም አካላት ጋር ከሚያደርጉት መስተጋብር ሂደት ዉስጥ መፈለግን ያሻል፡፡

ካርታ 4:- ኢ.ኢ.አ በ1954 በአበርኩሩምቢ ተነድፎ ተሻሽሎ የቀረበ የአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን የመንገድ መረብን፣ የቀለበት መንገድን ጭምር እንዴት እንዳስቀመጠ ማስተዋል ይበጃል (According to Yirgalem, 2008)




ለአብነት ያክል ለማንሳት፣ የከተማ መሬት አጠቃቀም ሥርዓት ከትራንስፖርት አገልግሎት አተገባበር ጋር የተቆራኘ ግንኙነት አለዉ። የከተማ መሬት አጠቃቀም ሥርዓት የከተማዉን ተግባራት ጂኦግራፊያዊ ስርጭትን የሚወስን ሥርዓት ነዉ፤ የመኖሪያ ቦታዎች፣ የኢንዱስትሪ ዞን፣የከተማ አስተዳደር ቢሮ፣ የንግድ ማዕከላት፣ የጤና ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት፣ የባህልና ማህበራዊ ማዕከላት፣መንገዶችና የትራንስፖርት ሲስተሞች፣ የሥራ ቦታ፣የመዝናኛ

ሥፍራዎች በከተማዉ የቆዳ ሽፋን የት የት ማረፍ እንደሚገባቸዉ የሚወስን ሲሆን የትራንስፖርት ዋነኛ ተግባር የአገልግሎት ደረጃዉን ጠብቆ አግባብ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ የተጠቃሚዎችን ምቾትና ደኅንነት ጠብቆ አግባብነት ባለዉ ዋጋ ተጠቃሚዎችን ከነኝህ የተግባራት ማዕከላት ጋር ማገናኘት ነዉ፣ ወይም እነኝህን ማዕከላት ተደራሽ ማድረግ ነዉ፡፡ የአንድ ከተማ ምርታማነት የከተማዋ የትራንስፖርት ሲስተም የከተማዉን ሠራተኛ፣ የተለያዩ የከተማዋ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን፣ ጓዝን ከመነሻቸዉ ወደ መደረሻቸዉ ለማጓጓዝ ባለዉ ብቃት ደረጃ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሲስተሞች ቀስ በቀስ መክሰማቸዉ አይቀሬ ነዉ፡፡ ለዚህም የከተማ መሬት አጠቃቀምን የሚወስኑ ተቋማት (land use planners) ከከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ፐላን ተቋማት (urban transport planners) ጋር ተናበው መሥራት ይጠበቅባቸዎል፡፡

## 7. የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫዎች

የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ከሲስተሙ አካላት አተገባበር የተነሣ የከፋ ችግር እንዳለባቸዉ ገሃድ እዉነት ነዉ፡፡ ይህንን እዉነት አስመልክቶ በህዳር 2005 ይፋ በሆነዉ የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የዳሰሳ ጥናት መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ ጥናቱ በመግቢያዉ፣

> *ይሁንና ከተማችን ለተያያዘችዉ ፈጣን ለዉጥና እድገት ጉዞ ተግዳሮት እየሆኑ ከሚፈታተኗትና የነዋሪዎቿ የነጋ ጠባ እሮሮ በሆኑ የተለያዩ ችግሮች ዉስጥ የምትገኝ መሆኗ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ፡፡ ከነዚህ ወቅታዊና ጊዜያዊ ችግሮች መካከልም በሥራ መግቢያና መዉጫ ሰአታት እየታየ ያለዉ የህዝብ የመንገድ ትራንስፖርት ችግር በቀዳሚነት እየተጠቀሰ ይገኛል (*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ (2005ዓ.ም)*) ይላል፡፡*

ጥናቱ "በሥራ መግቢያና መዉጫ ሰዓታት" ይበል እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ችግሮች ከሥራ መግቢያና መዉጫ ሰዓታት ዉጪም ተለጥጦ ቀኑን ሙሉ የመሆን አዝማሚያ እየያዘ ለመሆኑ

ፍንጮች እየታዩ ነዉ። ይህም ሊሆን የሚችልበትም ምክንያት በአዲስ አበባ የአገልግሎት ዘርፍና የአነስተኛና ጥቃቅን እንዱስትሪ የሥራ መስኮች እያደጉ በመምጣታቸዉ በዚያ ተቀጥረዉ የሚሠሩ ሠራተኞች እንደ ተማሪና እንደመደበኛዉ የመንግሥት ሠራተኛ የተወሰነ የሥራ መግቢያና መዉጫ ጠብቀዉ የሚንቀሳቀሱ ሳይሆን የሥራ ባሕሪይዉ በሚጠይቀዉ በማናቸዉም ሰዓት መንቀሳቀስ ስለሚኖርባቸዉ ነዉ።

“የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ከድጡ ወደ ማጡ” (ሪፖርተር፡- ቅፅ 16 ቁጥር 26/1132 እሑድ የካቲት 27 ቀን 2003) የተባለለት የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ችግሮች የመፍትሄ ሁኔታን ስናሰላስል የዘመናዊ ትራንስፖርት ጂኦግራፊ ምሁራን ብሪያን ሆዬልና ሪቻርድ ኖዉሌስ (1998) ያሰፈሩትን ጭብጥ ማጤን ተገቢ ይመስለኛል። ይህም ጭብጥ፣

> “*ሁሉም የትራንስፖርት ስስተሞች ሊሻሻሉ ይችላሉ፤ከቆዳ ስፋት ሽፋን አኳያ፣ ከተደራሽነት አኳያ፣ ፈጣን አገልግሎት ከመስጠት አኳያ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በጣም ጊዜ፣ ገንዘብንና የኃይል ፊጆታ ቆጣቢ አገልግሎት እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፤ይህ፣ ሁሌም የሚፈለግ ሆኖ ግን ትራንስፖርት የከባቢን ሁኔታ እንዳያዛባና የበለጠ ቀጣይነት ያለዉ እንዲሆን ያሻል። የማንኛቸዉም የትራንስፖርት አገልግሎት በጣም ጊዜ፣ ገንዘብንና የኃይል ፊጆታ ቆጣቢና የከባቢ ሁኔታዎችን ሳያዛባ በተሸለ ሁኔታ ቀጣይ ሆኖ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ወደሚያረካ ደረጃ እንዲደርስ የማድረጉ ጉዳይ በመሠረቱ የፖለቲካ ጉዳይ ነዉ፣ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ከሌሎች የኢኮኖሚ አዉታሮች አንጻር መንግሥት ሪሶርሱን ለትራንስፖርት በሚመድብበትና በሚደለድልበት መጠን ላይ፤ እንዲሁም ደግሞ የግል ባለሀብቱ በትራንስፖርት እንቨስት እንዲያደርግ በሚፈቅድበትና በሚያበረታታበት መጠን ላይ የተመሠረተ ነዉ። ስለዚህ የትራንስፖርት ዉሳኔዎች፣ሁሉም ሊባል በሚችልበት ደረጃ፣ የትራንስፖርት ነክ ዉሳኔ የመንግሥት ጉዳይ ነዉ*” (Hoyle & Knowles, 1998) ይላሉ።

በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን የፖለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለዉጦች አንፃር የኒዎ-ሊበራሊዝም የኢኮኖሚክ ፖሊሲ እሴቶች በተለይም ገበያ-መር የአግልግሎት አቅርቦት ፖሊሲ እየተሸረሸረ መጥቶ መንግሥት ቁልፍ በሆኑት የአገልግሎት አቅርቦት ዘርፎች ጣልቃ የመግባት አስፈላጊነት እምነት በምዕራብም ዓለም ቢሆን እየጎላ መጥቷል። ኢያን ዶቸሪ፣ጆን ሻዉና ማቲያስ ጋዘር የተባሉት ተመራማሪዎች በትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የኒዎ-ሊበራሊዝም የገበያ-መር የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ፅንሰ-ሐሳብን ወደ

ኋላ በመተዉ መንግሥታት ለዜጎቻቸዉ አገልግሎቱን በማቅረብ ረገድ ማበርከት ስለጀመሩበት ሁኔታ ያትታሉ (Docherty,et.al.,2004) በተጨማሪም የገበያ-መር የትራንስፖርት ፖሊሲ አቅመ-ደካሞች፣ችግረኞች፣ሥራ አጥ፣ አረጋውያን፣ ሕፃናት የህብረተሰብ ክፍሎችን የመድረስ የአገልግሎት ፍትሃዊነት ስለሚጎድለዉ የመንግሥት ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ነዉ፤ይላሉ።

በበርካታ የሕዝብ አገልግሎቶች አሰጣጥ በተለይም የደኃዉ የሕብረተሰብ ክፍል በሚበዛበት ሁኔታ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እጅግ ወሰኝ ነዉ። ከዚህም በተጨማሪ በድህነት ቅነሳ ትግል ወሳኝ በሆኑ የትራንስፖርት አገልግሎት በመሳሰሉት የሕዝብ አገልግሎቶች የመንግሥት እጅ እጅጉን አስፈላጊ ነዉ። የሚደረገዉም የትራንስፖርት የፐብሊክ ሴክተር ኢንቨስትመንት ደኃዉንና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸዉን የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር መቃኘት ይኖርበታል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የመንግሥት አስፈጻሚ ክንፍ የሚባለዉ የመንግሥት አካል ጉዳይ መነሳት ያለበት ይመስለኛል። የመንግሥት አስፈጻሚ ክንፍ ከሁለት አካላት የተዋቀረ ነዉ፤ አንደኛዉ political executive የሚባለዉ፣ በአብዛኛዉ የፖሊቲካ ተሿሚ ሆኖ የወቅቱን የፖሊቲካ ትኩሳት ተከትሎ በየጊዜዉ ሊቀያየር የሚችል ሲሆን፤ ሁለተኛዉ በሙያዉ ብቃት በሰለጠነበት መስክ በተቀጠረበት ዘርፍ እዉቀቱን ሽጦ ለመኖር ለረጅም ጊዜ በአንድ የሥራ መስክ በአንድ በተወሰነ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሊቆይ የሚችል Permanent executive የሚባለዉ አካል ነዉ። የመጀመሪያው የፖሊቲካ ዉሳኔ መስጠት፣ ፖሊሲዎችን መቀየስ ከሚጠበቅበት ተግባራት ጥቂቶቹ ናቸዉ። ሁለተኛዉ ሲቪል ሰርቪሱን፣ቢሮክራሲዉን ብሎም ቴክኖክራቱን ያቀፈ ነዉ። ቴክኖክራቱ አስፈላጊዉን ሙያዊ ጥናትና ምርምር አድርጎ የድርጊት መርሃ ግብሩ በሚፈቅደው መሠረት ዕቅዶችን አዘጋጅቶ ለዉሳኔ ለፖለቲካ ሹመኛው ማቅረብና ማማከር ከተግባራቱ አንዱ ነዉ። ከዚህም የተነሣ መንግሥት አንድን ነገር ለማከናወን የቱንም ያህል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ቢኖረዉም ቴክኖክራቱ/ ኤክስፐርቱ የሚያቀርበዉ ዕቅድ አግባብነትና ጥራት የሕብረተሰቡን ኑሮ የማቅለልና የማክበድ አንድምታ ይኖረዋል። በተጨማሪም የአገር ዉስጥ ሆነ የዓለም አቀፍ የየዘርፉ አማካሪ ቡድኖች ከየራሳቸዉ የወደፊት ጥቅም /vested interest/ አንፃር የመምከር አዝማሚያ ስላላቸዉ ለመንግሥት በሚያቀርቡት

ዕቅድ የሕብረተሰቡን ሕይወት የመጥፎም ሆነ የበጎ፣የተሻለ ሆነ የከፋ አቅጣጫ በማስያዙ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም፡፡

እዚህ ላይ ጥያቄዉ የከተማ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ፣ የከተማ መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት ዕቅድና ከእነኝህ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ተቋማት ቴክኖክራትና ኤክስፐርቶች ክህሎት፣ የሙያ ብቃትና ተዓማኒነት ነዉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ ጃን ጃኮብስ (Jacobs Jane, 1996) የተባለ ሰዉ ስለ ፕላንና ዕቅድ ባለሙያዎች እንዲህ ሲል አስፍሯል፣ "በርካታ ቁጥር ያላቸዉ የፕላንና የዲዛይን ባለሙዎች የትራፊክን ችግር ብቻ መፍታት ቢችሉ የከተሞችን ዋነኛ ችግር መፍታት እንደቻሉ ይቆጥራሉ፡፡ ከተማ፣ ከኦቶሞቢል ትራፊክ የዘለለ ውስብስብ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ችግሮች አሉት፡፡ ከተማ እንዴት እንደተዋቀረ፣ እንዴት እንደሚሰራ፣ የትራፊክ ሁኔታዉ እንዲሻሻል ምን ምን እንደሚፈልግ ካላወቅህ የትራፊኩን ሁኔታ ለማሻሻል ምን ማድረግ እንደሚገባ እንዴት ታውቃለህ?" ሲል በጥያቄ አስቀምጦታል፡፡

የትራፊክ ችግር የማሻሻያ ሆነ የከተማ ትራንስፖርት ችግር ለመፍታት የምንከተለዉ ፍልስፍናም ሊፈተሽ የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡ እንግሊዞች ሲከተሉት ከነበረዉ መርሆ "Predict and Provide" (Walton, 2003) ከሚለዉ መርሆ "Predict and Prevent" ወደሚለው መለወጥ ግድ ብሏቸዋል፡፡ ይህም ማለት "Predict and Provide" ለምሳሌ፣ "ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ትሠለፋለች በዚያን ጊዜ ዜጎች በቂ ገንዘብ ስለሚኖራቸው የነፍስ ወከፍ መኪና ሊገዙ ስለሚችሉ በርካታ መኪኖች በጎዳና ላይ ስለሚወጡ ለእነዚህ መኪኖች የሚበቃ መንገድ ማዘጋጀት አለብን ብሎ ወደ ፊት ማቀድና በርከታ መኪኖችን ለማስተናገድ መሞከር እንደ ማለት ነዉ"፡፡ ሁለተኛው "Predict and Prevent" የሚለው መርሆ ሃሳብ ደግሞ "ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ስትሆን ዜጎች በቂ ገንዘብ ስለሚኖራቸዉ የነፍስ ወከፍ መኪና ሊገዙ ስለሚችሉ በርካታ መኪኖች ጎዳና ወጥተው መንገዱን እንዳያጨናንቁ መንገድን እናስፋ ከሚለዉ መርሆ ሌላ ምን ዘዴ ተጠቅመን ያሉን ጎዳናዎች ለወደፊት ሊኖር ለሚችለዉ የትራፊክ ፍሰት በቂ እንዲሆኑ ለማድረግ እንችላለን ብሎ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መተለም" እንደ ማለት ነዉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከዚህ በፊት በታሪኳ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መንግሥት ከፍተኛ የሆነ የመንገድ ማስፋፋት ወይም የአዳዲስ መንገድ ዝርጋታ አድርጓል፣ እያደረገም ይገኛል፡፡ በብዙዎች ዘንድ ይህ አስደናቂ የሆነ የመንገድ ማስፋፋትና ዝርጋታ አብዮት በአዲስ አበባ ለሚታየዉ የትራፊክ ፍሰት ጭንቅንቅ ፍቱን መድኃኒት መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ነገር ግን የመንገድ ማስፋፋትና ዝርጋታ ብቻውን መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል የበለፀጉ አገሮች ልምድ ጉልህ ማሳያ ነዉ፡፡ የመስኩ ተመራማሪዎች ተሸከርካሪ መኪኖች፣ ሥፍራ ባገኙ መጠን ቦታ የመዉረር (የመሙላት) (Parkinson's Law) ባህሪይ አላቸዉ ይላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በአዲስ አበባ የተስፋፉትና፣ የቀለበት መንገዱን ጨምሮ አዳዲስ የተዘረጉት መንገዶች በከተሟ የተከሰተዉን የትራፊክ መጨናነቅ በእጅጉ ይቀንሳሉ የሚል እምነት ተጥሎባቸዉ ነበር፡፡ ይሁንም እንጂ እዉነታዉ ከዚህ የራቀ ነዉ፡፡ ተሸከርካሪ መኪኖች መንገዶቹ በሰፉትና በተዘረጉት መጠን በዝተዉ መንገዶቹ በተመረቁበት ማግሥት የትራፊክ መጨናነቅ ከወትሮው በልጦ ይታያል፡፡ እዚህ ላይ አንድ በመስኩ በአዲስ አበባ ላይ ጥናት ያደረገ ሰዉ በጥናቱ ያሰፈረዉን እንዳለ ቃል በቃል በእንግሊዘኛ ያሰፈረዉን ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፡፡ ይህን በተመለከተ ጥሩ አድርጎ እንደሚከተለዉ አስፍሮታል፣

> *Despite the great effort and success stories of the city of Addis Ababa in recent years, including an aggressive expansion of transportation network capacity, the demand for a safe and efficient transportation service keeps growing and the congestion level and delays in traffic seems unabated.* (Mitiku, 2011)

ይህ ሊሆን የቻለዉ በአንድ በኩል፣ከመንገድ ማስፋፋትና አዳዲስ መንገዶች ከመዘርጋት ጎን ለጎን ለብዙኃን የሕዝብ ማመላለሻ ልንሰጥ የሚገባንን ትኩረት አለመቸራችን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በጎዳናዎቻችን የሚጠቀሙ በተለይም አነስተኛ የመጫን አቅም ላላቸዉ ተሸከርካሪዎች ያለን ፖሊሲ ነዉ፡፡ ይህም በግለሰብ ሆነ በቤተሰብ ደረጃ የነፍስ ወከፍ የመኪና ይዞታ ተበራክቶ “ሞተራይዘሽን” የሚባለውን ክስተት ለመግታት የሚያስችል ፖሊሲ አለመንደፍ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ጎዳናዎች ይሽከረከራሉ ከሚባሉት 116297 ተሽከርካሪዎች መካከል 93972 የአንበሳውን ድርሻ በሚይዙ (80.8 በመቶ) በአማካይ አንድ ወይም ሁለት ሰዉ ብቻ በሚፈናጠጥባቸዉ የቤት መኪኖች ጎዳናዎቹ የሚጨናነቁ መሆናቸውን መገንዘብ ልንከተለዉ የሚገባንን ለምሳሌ

የትራፊክ ማኔጅመንት የመሳሰሉ የትራንስፖርት ፖሊሲ አቅጣጫ በመቀየስ ረገድ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በአሁኑ ወቅት መንግሥት የአዲስ አበባ የመንገድና ትራንስፖርት ተጠቃሚዎችን ችግር ሊቀርፍ ይችላል በሚል ግምት እያስፋፋዉ ያለው የቀላል ባቡር ግንባታም ቢሆን ከላይ የተጠቀሱት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ካልተገበሩ በስተቀር ዉጤታማ ሊሆን እንደማይችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ሌላኛዉ ጉዳይ ደግሞ የሚመለከታቸዉ ባለ ድርሻ አካላት እንዲሁም ተቋማት በቅንጅትና በመተባበር (Integration and Coordination) ሊሠሩ ይገባል፡፡ በከተማ መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ተቋማዊ አወቃቀር ሕብረተሰብን መሠረት ያደረጉ ቡድኖች (CBOs)፣ የሕዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች ማሕበር፣ የመልካም አስተዳደር ቡድኖች፣ የንግዱ ሕብረተሰብ ድርጅቶች፣ ምናልባትም በመስኩ የተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎችም ሊታቀፉ ይገባል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት

Bahru Zewde. (1991) *A History of Modern Ethiopia 1855-1974*. Addis Ababa University Press, Addis Ababa.

Berhanu Woldetensae, Yichilal Fanta and Asgedome Haile. (2011) *Evaluation of the Addis Ababa Structure Plan 2003 to 2010.* Transport Sector. EIABC-Addis Ababa University.

Docherty, I. Shaw, J. and Gather M. (2004) State Intervention in Contemporary Transport. *Journal of Transport Geography*, www.elsevier.com/ locate/jtrangeo

ERA. (2005) Addis Ababa Transport Study/ UTS

Fenmeccanica, Cesen A. (1986) An energy efficient public transport system for Addis Ababa in Diamantani, C and Patassini, D (1996) (eds.) *Urban Ethiopia, Evidenses of the 1980's*. Istituto Univesitario di Architecttura, Venezia

Hoyle, B. and Knowles, R. (1998) *Modern Trnasport Geography* (2nd ed.). Wiley, England

Jacobs, J. (1996) "The Death and Life of Great American Cities" in *Readings in Planning Theory* by Campbell & Fainstein). Blackwell, G.B

Mekete Belachew (2009) *Transport Modes and Their Impacts on Development in the Developing World: With Emphasis on Ethioipia*. Addis Ababa

Meyer, D. and Miller, J. (2001) *Urban Transportation Planning* (2nd ed.), Mckgrow-Hill, New York

Mitiku Asmare (2011) *The Role of Bajaj Transport Provision in Addis Ababa.* Ethipian Civil Sevices College, M.A Thesis in Urban Management. Addis Ababa.

Transport Research Laboratory (2002) *Sub-Saharan Africa Transport Study: Scoping Study:*

*Urban Mobility in Three Cities, Addis Ababa, Dar es Selam, Nairobi*. The World Bank

Walton, W.,(2003) Applying the new approach to transport policy at local level. *Journal of Transport Geography 11 1-12* www.elswevier.com/ locate/ jtrangeo

White, (2002) *Public Transport: Its planning, Management and Operation*. London.

Yirgalem Mahiteme (2008) *The Growth and Management of Addis Ababa*.NTNU.

*ሪፖርተር ጋዜጣ፡-* ቅፅ 16 ቁጥር 26/1132 እሑድ የካቲት 27 ቀን 2003 አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ *ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትራንስፖርትና መገናኛ* ሚኒስቴር (2002) *የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ፖሊሲ (ለባለ ድርሻ አካላት ዉይይት የቀረበ ረቂቅ)*፡፡ አዲስ አበባ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ *መንገዶች* ባለሥልጣን (2004) *ፍኖተ አዲሱ*-የአዲስ አበባ ከተማ *መንገዶች* ባለሥልጣን በየሩብ *ዓመት* የሚታተም *መ*ስከረም 2004 ቁጥር 6

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ (2005) *የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ የመንገድ ትራንስፖርት አሰጣጥ ያለበት ሁኔታንና የቀጣይ የትኩረት አቅጣቻን የሚያሳይ የዳሰሳ ጥናት*፡፡ አዲስ አበባ

# የሕዝብ መናፈሻና አርንጓዴ አካባቢ ልማት በአዲስ አበባ

*ቁምላቸው የሺጥላ*

## 1. የከተማ አርንጓዴ ምንነትና ጠቀሜታ

### 1.1 *የከተማ አርንጓዴ ቦታዎች*

አርንጓዴ ቦታ በአስፋልት፣ በኮንክሪት፣ ወይም በድንጋይ ያልተሸፈነ፤ ውሀ ወደ መሬት ውስጥ ማስገባት የሚችል፣በኋላም ይህን ውሃ ወደ አየር ሊለቅ የሚችል በአፈር ወይም በዕፅዋት የተሸፈነ ቦታ ነው።

አርንጓዴ መሠረተ ልማት ማንኛቸውም በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ የተገኙ በከተማ ውስጥ እና በከተማ ዙርያ ያሉ የተያያዙ አርንጓዴ ቦታዎችን የሚያካትቱ ሥነ ምህዳራዊ መዋቅር ናቸው። የአርንጓዴ ቦታዎች ጥምረት የአርንጓዴ መሠረተ ልማትን ይፈጥራሉ (Benedict & McMahon, 2000).አርንጓዴ መሠረተ ልማት ለአካባቢያዊ፣ ማህበራዊእና ኢኮኖሚያዊ ቀጣይነት ዋና የሥነምህዳር ማዕቀፍ ነው። በመሆኑም የከተማ አርንጓዴ መሠረተ ልማት ለከተሞች ዘላቂ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። እንደ አርንጓዴ ቦታዎች ከሚያካትቱአቸው ውስጥ የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ ዳር ዛፎች፣ ወንዞችና ሌሎች ውሃ ነክ ሥርዓተ ምህዳሮች፣ የዘላቂ ማረፊያ ቦታዎች፣ የከተማ ውስጥ እርሻ፣ ረግረጋማ ቦታዎች፣ ደኖችና ሌሎች በዕጽዋት የተሸፈኑ ቦታዎችን ይገኙባቸዋል።

### 1.2 *የከተማ አርንጓዴ ቦታዎች ጥቅሞች*

የከተማ አርንጓዴ ቦታዎች ለህዝቦች የተለያዩ አካባቢያዊ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይሰጣሉ። እነዚህ ጠቀሜታዎች በአርንጓዴ ቦታዎች ብዛት፤ ጥራትና ተደራሽነት ይወሰናሉ።

የአርንጓዴ ቦታዎች ብዛት ከከተማ ስፋትእና ከህዝብ ቁጥር ጋር አንፃር የሚታይ ሲሆን የአርንጓዴ ቦታዎች ጥራት በውስጣቸው ከያዙአቸው የብዝሃ ህይወት ስብጥር እና ውበት አንፃር የሚለካነው። የአርንጓዴ ቦታዎች ተደራሽነት ማለት የመኖሪያና የሥራ ቦታዎች ከአርንጓዴ ቦታዎች አንፃር ያላቸው ርቀት የሚለካበት ነው። በበቂ ሁኔታ የተሰራጩ የከተማ አርንጓዴ ቦታዎች የነዋሪዎችን የአኗኗር ደረጃን ከሚወስኑ ነገሮች ውስጥ ይካተታሉ። በተለይ የአየር ንብረት ለውጥ ባለበት ሁኔታ ከአርንጓዴ ቦታዎች የሚገኙት ጥቅሞች እየጨመሩ የሚሄዱ ናቸው።አርንጓዴ መሠረተ ልማት በአግባቡ

ከታቀደ እና ከለማ ለኢኮኖሚ እድገትና ለተፈጥሮ ጥበቃ ማዕቀፍ በመሆን የከተማ ልማትን አቅጣጫ ሊያሳይ የሚችል ነው፡፡

### 1.2.1 የከተማ አርንጓዴ ቦታዎች አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች

1. **የብዝሃ ህይወት ጥበቃ፥** አርንጓዴ ቦታዎች በራሳቸው የመኖርያ አካባቢ ስለሆኑ ለተለያዩ ዕጽዋቶች፣ እንስሳቶችና ደቂቅ ዘአካላት መኖርያነት በማገልገልለ ብዝሃ ህይወት ጠበቃ የራሳቸው አስተዋጽዖ አላቸው (Kong et al. 2010).
2. **የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ፥** አርንጓዴ ቦታዎች ውስጥ ያሉ ዕጽዋቶች ከአየር ላይ ካርቦን ዳይኦክሳይድን በመውሰድ ምግብ ስለሚያዘጋጁ በአየር ውስጥ ያለውን ካርቦን በመቀነስ ረገድ አስተዋጽዖ አላቸው፡፡
3. **የአካባቢን አየር ንብረት ለማስተካከል፥** በከተሞች ውስጥ ያሉ አስፋልት እና ኮንክሪት ሙቀትን በቀን ጊዜ በመውሰድ የአየር ሙቀትን ሲያስከትሉ፤ በምሽትም በቀን የወሰዱትን ሙቀት በመልቀቅ የከተማን መሬት በምሽት ጊዜ እንዲሞቅ ያደርጋሉ (Kuttler, 2008):: የአርንጓዴ ቦታዎች በእጽዋት የተሸፈኑ በመሆናቸው የአካባቢን የአየር ሙቀት በመቀነስ እና የእርጥበት መጠን እንዲስተካከል ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በቱርክ አንካራ ከተማ በተደረገ ጥናት አርንጓዴ ቦታዎች በአካቢያቸው ካሉ የመኖርያ ቦታዎች ይልቅ እስከ 5.2°C የቀነሰ የሙቀት መጠን ይኖራቸዋል (Baris et al., 2009)፡፡
4. **የአየርና የድምፅ ብክለትን ለመቀነስ፥** አርንጓዴ ቦታዎች በአየር ውስጥ የሚገኙ አቧራ እና ብናኝ ነገሮችን በመውሰድ የአየር ብክለትን ስለሚቀንሱ የከተሞች ሳንባ በመባል ይታወቃሉ፡፡በተጨማሪም አርንጓዴቦታዎች የድምፅ ብክለትን ከመቀነስ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው፡፡
5. **ጎርፍን ለመከላከል፥** በከተማ ውስጥ የሚገኙ ረግረጋማ ቦታዎችና ሌሎች አርንጓዴ ቦታዎች ከከፍተኛ ቦታ የሚመጣን ጎርፍንና በውስጡ የሚገኙ አፈርንወደ ውስጥ በማስረግ በዝቅተኛ የከተማ ቦታዎች ሊደርስ የሚችልን የጎርፍ አደጋን እና የወንዝን በአፈር መበከልን ለመከላከል ይረዳሉ (Boyer & Polasky,2004)፡፡
6. **የውሃ ተፋሰስን በመጠበቅ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ፥** አርንጓዴ ቦታዎች የወንዞችን ተፋሰስ በመጠበቅ የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር ውሃን በማበልጸግ ቀጣይነት ያለው ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ይረዳሉ፡፡

4. **የፍሳሽ ቆሻሻን ለማጣራት፥** በረግረጋማ ቦታዎች የሚያድጉ ዕጽዋትና እንስሳትበፍሳሽ ቆሻሻ ውስጥ ያሉ ንጥረነገሮችንበመውሰድ ቆሻሻ ውሃውን በማጣራት ለመልሶ መጠቀም አገልግሎት እንዲውል ይረዳሉ፡፡

### 1.2.2 የአርንጓዴ ቦታዎች ማህበራዊና ባህላዊ ጠቀሜታዎች

1. የአርንጓዴ ቦታዎች በመኖርያ አካባቢ መኖር ለህብረተሰብ መልካም ግንኙነት፤ የሥነልቦና መቀራረብና ማህበራዊ መስተጋብር እንዲኖራቸው ይጠቅማል (Kuo, 2003; Maas et al., 2009)፡፡

2. የአርንጓዴ ቦታዎች መኖር ለወንጀል መቀነስ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡የለሙ አርንጓዴ ቦታዎች በአንድ አካባቢ መኖር የህብረተሰብን መደራጀት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ብዙ ጊዜ ሰዎች በአካባቢያቸው እንዲያሳልፉ ስለሚያደርጉ ወንጀለኞች በዚያ አካባቢ እንዳያተኩሩ ሊያደርጉ ይችላሉ (Kuo & Sullivan 2001፤ Kuo 2003))፡፡

3. አርንጓዴ ቦታዎች ተማሪዎችንና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማስተማር ይጠቅማሉ፡፡አርንጓዴ ቦታዎች በውስጣቸው የተለያዩ የዕጽዋት አይነቶችን የያዙ በመሆኑ ስለ ሥነ አካባቢ እና ብዝሀ ህይወት ጠቀሜታ ለማስተማሪያ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

### 1.2.3 የአርንጓዴ ቦታዎች ከህዝብ ጤና ጥበቃ አንጻርያላቸው ጠቀሜታ

የተለያዩ ጥናቶች የሰዎች ደህንነትና ጤናማነት ከአርንጓዴ ቦታዎች በብዛትና በጥራት መኖር ጋር የተያያዙ መሆናቸውን አሳይተዋል (Mitchell & Popham፣ 2008)፡፡ አርንጓዴ ቦታዎችን ማየት፤ መጎብኘትና፤ መንከባከብ ለግለሰቦች የስነልቦና እና የፊዚካል ጤና አስተዋፅዖ ያደርጋል (Ellaway et al., 2005)፡፡ ለአርንጓዴ ቦታዎች ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከራቁት አንፃር ጤናማ የመሆን እድላቸው ከፍተኛ ነው (Kaplan, 2001)፡፡ አርንጓዴ ቦታዎች በህክምና ተቋማት ውስጥና አካባቢ መኖር በሽተኞች በፍጠነት ከህመማቸው (ከቀዶ ህክምና) እንዲያገግሙ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ (Ulrich,1984)፡፡ በተጨማሪም አርንጓዴ ቦታዎች ከሙቀት ጋር ተያይዞ ለሚመጡ ህመሞች መጋልጥን ይቀንሳሉ፡፡

በአውሮፓ የተካሄደ ጥናት እንደሚያሳየው በአርንጓዴ ቦታዎች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በሦስት እጅ የተሻለ በአካል ብቃት እና አርባ ከመቶ ከአላስፈላጊ ክብደት እና ውፍረት ነፃ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ የተለያዩ ጥናቶች አርንጓዴ ቦታዎች መልካም ስሜትንና መዝናናትን በመፍጠር እንዲሁም ጭንቀትን በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርጉ አሳይተዋል (Ulric+h, 1984)፡፡

### 1.2.4 የአርንጓዴ ቦታዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች

የአርንጓዴቦታዎች ክፍል የሆነው የከተማ ግብርና ለከተማ ነዋሪዎች የምግብ ሰብል እና አትክልትና ፍራፍሬ በማቅረብ በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ ለሚተዳደሩ ስዎች የገቢ ምንጭ ከመሆኑም በላይ ለከተማ ህዝብ ትኩስ የአትክልትና ፍራፊሬ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የአርንጓዴ ቦታዎች የማገዶ እንጨትና የከብቶች መኖ አቅርቦት ያገለግላሉ፡፡ የከተማ ደኖች ለማገዶ እና ለግንባታ ሊያገለግሉ የሚችሉ የእንጨት ምርቶችን በመስጠት ለአልሚው የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ የሳር መሬቶችም ለከብቶች መኖ የሚሆኑ የሳርና ሌሎች ዕጽዋቶችን ያበቅላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአርንጓዴ ቦታዎች ልማት በማህበር ለታደራጁ እና ለግለሰብ ሠራተኞች የሥራ ዕድልን በመፍጠር አለታዊም ሆነ ወራዊ ገቢ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

አርንጓዴ ቦታዎች የመንግስትን የመሠረተ ልማት ጥበቃና አገልግሎት ወጪ ይቀንሳሉ፡፡ ማዘጋጃ ቤቶች አርንጓዴ ቦታዎችን በማልማት የወንዝ ተፋሰሶችን መጠበቅ ቢችሉ ለጎርፍ መከላከል፣ ለፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገድና ለንጹህ ውሃ አቅርቦት የሚያወጡትን መዋዕለ ንዋይ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የኒዎርክ ከተማ በ1990ዎቹ ለውሃ ማጣራትና ማከም ስራዎች ልታወጣ የነበረውን ከ6-8 ቢሊዮን ዶላር ካትስኪል የተባለውን ተፋሰስ በ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ብቻ በማልማት ከፍተኛ ገንዘብ ለመቆጠብ ችላለች፡፡ በመኖሪያ እናበንግድ ቤቶች ግቢ ውስጥ እና አካባቢ የአርንጓዴ ቦታዎች መኖር፤ ቤቶቹ በአንፃራዊ ሁኔታ የተሻለ የኪራይ እና የሽያጭ ዋጋ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

አርንጓዴ ቦታዎች እና ዕጽዋቶች ለህንፃዎች ጥላ በመሆን የውስጥ ሙቀታቸውን በመቀነስ፤ ለአየር ማቀዝቀዥያ የሚወጣውን ወጪ እንዲቀንስ ይረዳሉ (McPherson and Simpson 2003) ፡፡ በሞቃት ጊዜ በእግረኛ መንገድ ላይ የጥላ ዛፎች ካሉ ለእግረኞች ጥላ በመሆን እግረኞች ከአጭር እስከ መካከለኛ ርቀት በእግር በመጓዝ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ከማስቻሉም በላ የትራንስፖርት ወጪንም በመቀነስ አስተዋጽዖ ደርጋሉ፡፡

የአርንጓዴ ቦታዎች አስፈላጊነት ከሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የሚባሉት የሰው ልጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሥርዓተ ምህዳር ሥራዎች (Ecosystem function) የሚያገኛቸው ጥቅሞች ናቸው፡፡የሥርዓተ ምህዳር ሥራዎች (Ecosystem function) በሥርዓተ ምህዳር ውስጥ የሚካሄዱ የፊዚካል፣ የኬሚካል፣ እና የባዮሎጂካል ሂደቶች ሲሆኑ እነዚህም የሚከሰቱት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከአካባቢያቸው ጋር እና እርስ በርስ በሚያደርጉት ግንኙነት ነው፡፡የአርንጓዴ

ቦታዎች በብዛት፤ በጥራትና በበቂ ተደራሽነት መኖር ከሥርዓተ ምህዳር የሚገኙ አገልግሎቶችን ማስፋት ነው። የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች በአራት ይከፈላሉ። እነሱም፡-

1. የአቅርቦትአገልግሎቶች (Provisioning services) (ምግብ፤ማገዶእንጨት፤ ባህላዊመድሀኒት)፤ 2. የማስተካከልአገልግሎቶች (Regulating services) (የአየርንብረትማስተካከል፤ ውሃማጣራት፤ የአፈርመከላትንመከላከል)፤3. የባህላዊአገልግሎቶች (Cultural services)፤ መዝናኛ፤ትምህርታዊ፤መንፈሳዊ፤ሥነውበት)፤ 4. ድጋፍሰጪአገልግሎቶች (Supporting services) በመባል ይታወቃሉ።

## 2. የከተማ አርንጓዴ ቦታ ይዞታ በአዲስ አበባ ምን ይመስላል?

### 2.1 *የአርንጓዴቦታዎች ዓይነት*

የአዲስ አበባ ከተማ አርንጓዴ ቦታዎች በአብዛኛው ተነጣጥለው የሚገኙ እና ተያያዥነት የሌላቸው ናቸው። እነዚህ አርንጓዴ ቦታዎች በ7 ዓይነቶች ሊከፈሉ ይችላሉ። እነዚህም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

የከተማ ግብርና ቦታዎች (Urban Agriculture)፤ 2. የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች (Public Recreational Parks)፤ 3. በወንዝ ዳር የሚገኙ ዕፅዋቶች (Riverine vegetation)፤ 4. የተተከሉ ደኖች (Plantation Forest)


5. የመንገድ ላይ ዛፎች (Street Plantation)፤ 6. የአገር በቀልና መጤ ዛፎች ቅልቅልደን (Mixed Forest)፤ 7. የሳር መሬት (Grassland)

#### 2.1.1 የከተማ ግብርና ቦታዎች (Urban Agriculture)

የከተማ ግብርና ቦታዎች በከተማ ክልል ውስጥ እና በከተማ ዳርቻ አካባቢ የምግብ ሰብል፤ አትክልትና ፍራፍሬ እና ለምግብነት የሚውሉ እንስሳት የሚለሙበት ቦታ ናቸው። እነዚህ ቦታዎች በአዲስ አበባ ለሁለት ይከፈላሉ፡ 1ኛ) የሰብል ልማት ግብርና 2ኛ)የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ግብርና ናቸው። በሰብል ልማት ግብርና ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚለሙት ውስጥ ጤፍ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ሽምብራ፣ ምስርና፣ ባቄላ የገኙበታል። በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ውስጥ ካሮት፣ የተለያዩ ዓይነት ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ቃርያ፣ ቀይሥር እና ዱባ ሲገኙባቸው የፍራፍሬ እና የአበባ ልማት በስፋት ያልተያዘ ግን ሰፊ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ዘርፍ ነው።በ1992 ዓ.ም. የወጣው የአዲስ አበባ የማስተር ፕላን ክለሳ ሰነድ እንደሚያሳየው በአዲስ ውስጥ 51000 ቤተሰቦች ኑሮአቸውን በግብርና ስራ የመሰረቱ ናቸው። የከተማ

ግብርና አርንጓዴ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለድህነት ቅነሳ እና ለከተማ ህዝብ የምግብ እህል እና ትኩስ የሆኑአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ በወንዝ ዳር ላይ የሚተከሉ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ሌሎች ዕጽዋቶች የዝናም ውሃን በመውሰድ እና ወደ መሬት በማስረግ የጎርፍ አደጋን ሊከላከሉ የሚችሉ ናቸው፡፡

ስዕል 1:- የከተማ ግብርና ቦታዎች ሀ) የምግብ ሰብል እርሻ ቦታ ለ) የአትክልት እርሻ ቦታ




### 2.1.2 **የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች (Public Recreational Parks)**

የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች በከተማዋ ውበት፣መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳድር ኤጀንሲ እና በሌሎች መስተዳድሩ መ/ቤቶች ስር የሚተዳድሩ ለህዝብ መዝናኛ እና ለሰርግ አገልግሎት የሚውሉ አርንጓዴቦታዎች ናቸው፡፡ ከኤጀንሲው በተገኘ መረጃ መሠረት በከተማዋ ውስጥ በኤጀንሲው ስር የሚተዳደሩ 10 የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ብሄረጽጌ ፓርክ፣ ሐምሌ 19 ፓርክ፣ ኢትዮ ኮርያ ውዳጅነት (አፍንጮ በር) ፓርክ፣ አምባሳደር፣ አፍሪ ካፓርክ፣ ፈረንሳይ ፓርክ፣ ተክለሀይማኖት ፓርክ፣ ጎላ ፓርክ፣ ኢትዮ ኩባ ፓርክ እና የካ ፓርክ ናቸው፡፡ ማዕከላዊ ፓርክ እና አንበሳ ግቢ በከተማዋ ከንቲባ ጽ/ቤት የሚተዳደሩ ሲሆኑ ሸገር ፓርክ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የሚተዳደር ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመኖርያ እና በንግድ ቤቶች አካባቢ እየለሙ ያሉ መናፈሻ ቦታዎች ለህዝብ መናፈሻ እና ማህበራዊ አገልግሎትየ ሚውሉ በመሆናቸው በህዝብ መናፈሻ ፓርኮች ምድብ ውስጥ የሚመደቡ ሲሆኑ ልማታቸውም ወጥ በሆነ መንገድ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ስዕል 2 :- የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች ሀ) ኢትዮ ኩባ የወዳጅነት ፓርክ ለ) የመኖርያ አካባቢ ፓርክ (ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 7)




### 2.1.3 **በወንዝ ዳር የሚገኙ ዕፅዋቶች (Riverine vegetation)**

በወንዝ ዳር የሚገኙ ዕፅዋቶች በከተማዋ በሚገኙ ወንዞች ዳር የሚገኙ እንጨታማ እና እንጨታማ ያልሆኑ ዕፅዋቶችን የሚያካትት ነው፡፡ ሆኖም አብዛኛው የከተማዋ ወንዞች ዳር በመኖርያ ቤቶች የተሸፈኑ በመሆናቸው ለደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ እየዋሉ በመሆኑዕፅዋቶች በበቂ ሁኔታ በቅለው አይታዩም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ወንዞች ተገቢውን የሥርአት ምህዳር አገልግሎት እየሰጡ አይደሉም፡፡


ስዕል 3:- የጀሊሳ ወንዝ ጉርድ ሾላ አካባቢ (የመልሶ ማልማት ከተካሄደበት በኂላ)



## 2.1.4 የተተከሉ ደኖች (Plantation Forest)

አዲስ አበባ በተራሮች የተከበበች ከተማ ናት። አብዛኞቹ እነዚህ ተራሮች በባህር ዛፍ የተሸፈኑ ሲሆኑ አልፎ አልፎ የፈረንጅ ጽድ ተተክለው ይገኛሉ። በእንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኘውን የባህር ዛፍ ተከላ በማስወገድ በአገር በቀል ዛፎች ለመተካት በተካሄደው እንቅስቃሴ በአሁኑ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ የኮሶ እና የሐበሻ ጽድ ዛፎች በውስን ደረጃ በቅለው ይታያሉ።

ስዕል 4:- የተተከሉ ደኖች ሀ) የባህርዛፍ ደን በእንጦጦ ተራራ ለ) የአገር በቀል ዛፎች ልማት በእንጦጦ ተራራ




## 2.1.5 የመንገድ ላይ ዛፎች (Street Plantation)

የመንገድ ላይ ዛፎች በከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች ዳር፤ በመንገድ አካፋይ፤ በመንገድ ኮሪደር እና በመንገድ አደባባይ ላይ የሚገኙ ዛፎችንና ሌሎች ዕጽዋቶችን የሚካትት ነው።አብዛኞቹ በመንገድ አካፋይ እና በእግረኛ ማንገድ ላይ የተተከሉ ዛፎች መጤ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥም ዘንባባ፣ ሸውሸዌ፣ ግሬቪላ፣ ጃካራንዳ፣ እና ስፓቶድያ ይገኙበታል። በመንገድ አደባባይ ላይ የተተከሉት ደግሞ ሳር፣ አበባ እና ቁመታቸው አነስተኛ የሆኑ ቁጥቋጦዎችናቸው።

ስዕል 5:- የመንገድ ላይ ዛፎች ሀ) በመንገድ አካፋይ ላይ የተተከሉ ዛፎች ለ) የመንገድ አደባባይ ዕጽዋቶች (ጦር ሀይሎች)




### 2.1.6 **የአገር በቀልና መጤ ዛፎች ቅልቅል ደን (Mixed Forest)**

ይሄ የደን ዓይነት በከተማዋ በሚገኙ እና ቀደም ያለ ይዞታ ባላቸው የመንግስታዊ እና የዲፕሎማቲክ ተቋማት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በመንግስታዊና በሌሎች ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ደኖችን ሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ ደኖች በአብዛኛው አገር በቀል እና መጤ ዛፎች (በተለይ ባህርዛፍ) ተቀላቅለው የሚገኙበት ሲሆንለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፣ ለካርቦን ልቀት እና ለአየር ብክለት መቆጣጠርያ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፡፡ በሃይማኖት ተቋማት ይዞታ ውስጥ የአገር በቀል ዛፎች በብዛትየሚገኙ ሲሆን አገልግሎታቸውም ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፤ለካርቦን ልቀት እና ለአየር ብክለት መቆጣጠርያ እና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ነው፡፡ እነዚህ ደኖች ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ከመሆናቸውም የአዲስ የከተማዋ ሳንባ በመባል ይታወቃሉ፡፡


ስዕል 6:- በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ዛፎች (አራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን)



### 2.1.7 **የሳር መሬት (Grassland)**

የሳር መሬት የሚባሉት በዝናም ወቅት ለከብቶች ግጦሽ አገልግሎት የሚውሉ ሳሮችን የሚያበቅሉ ሲሆን በደረቅ ወቅት ሳር ስለማያበቅሉ ባዶ መሬት ሆነው ይታያሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ መኖርያ ሰፈሮች አካባቢ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የመናፈሻ ቦታዎች በሳር የተሸፈኑ ናቸው፡፡

ስዕል 7 የሳር *መሬት ሀ*) በዝናም ወቅት ለ) በደረቅ ወቅት




## 2.2 *የአዲስ አበባ ከተማ አርንጓዴ ቦታዎች ስፋት*

የአዲስ አበባን የአርንጓዴ ቦታዎች ዓይነት፣ ስርጭት እና ስፋት ለማወቅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ የአርኪቴክቸር ህንጻ ግንባታና ከተማ

ልማት ኢንስቲቲዩት በተደረገው ጥናት መሠረት በ1998 ዓ.ም.እና በ2003 ዓ.ም.ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

ሠንጠረዥ 2:- የአዲስ አበባ አርንጓዴ ቦታዎች ስፋትና የመቶኛ ድርሻ

| | አርንጓዴ ቦታ | በ1998 ስፋት | | በ2003 ስፋት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በሄክታር | የመቶኛ ድርሻ | በሄክታር | የመቶኛ ድርሻ |
| 1 | የሰብል እርሻ | 19209.4 | 70.6% | 14578.3 | 64.5% |
| 2 | የአትክልት እርሻ | 583.12 | 2.1% | 341.1 | 1.5% |
| 3 | የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች | 50.2 | 0.18% | 69.3 | 0.3% |
| 4 | በወንዝ ዳር የሚገኙ ዕፅዋቶች | 1596.2 | 5.9% | 1803.8 | 8% |
| 5 | በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች (ተራሮች) ላይ የሚገኙ ደኖች | 3903.7 | 14.4% | 3373.6 | 14.9% |
| 6 | በሃይማኖት፣መንግስታዊ እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ደኖች | 1353.1 | 5% | 1598.8 | 7.1% |
| 7 | የሳርመሬት | 507.6 | 1.9% | 830.7 | 3.7 |
| | ጠቅላላ የአአ አርንጓዴ ቦታ ስፋት | | 27,203.3 | | 22,595.6 |

በሠንጠረዥ 2 እንደሚታየው የሰብል እና የአትክልት እርሻ ቦታዎች ከ1998 ዓ.ም.ይልቅ በ2003 ዓ.ም. በ24.1 ከመቶ እና በ41.5 ከመቶ ሲቀንሱ በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ደኖች በ13.6 ከመቶ ቀንሰዋል፡፡የሰብል እና የአትክልት እርሻ ቦታዎች በስፋት የቀነሱት በሰሜን ምስራቅ እና በምዕራብ አዲስ አበባ አካባቢዎች ነው፡፡ እነዚህ ቦታዎች በአሁኑ ጊዜ ለተቋማትና ለመኖርያ ቤት ግንባታ እየዋሉ ናቸው፡፡

የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች፣በወንዝ ዳር የሚገኙ ዕፅዋቶች፣በተቋማት ውስጥ የሚገኙ ደኖች እና የሳር መሬቶች ከ1998 ዓ.ም.ከነበረው ይዞታቸውአንጻር በ2003 ዓ.ም.በቅደም ተከተል በ27.1 ከመቶ፣ በ11.5 ከመቶ፣በ15.4 ከመቶ እናበ38.9 ከመቶ ጨምረዋል፡፡ በጥቅሉ የአዲስ አበባ አርንጓዴ ቦታዎች በ1998 ዓ.ም.በስፋት 27,203.3 ሄክታር የሚሸፍኑ የነበሩ ሲሆን በ2003 ዓ.ም.ሽፋኑ ወደ 22,595.6 ሄክታር ቀንሷል፡፡ ይህም በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የከተማዋ አርንጓዴ ቦታዎች ስፋት በ16.9 ከመቶ መቀነሱን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በቋሚ ዕጽዋት የተሸፈኑ አርንጓዴ ቦታዎች ሽፋን በ1998 ዓ.ም.ከነበረው 6903.2 ሄክታር በ2003 ዓ.ም. ወደ 6845.5 ሄክታር ብቻ የወረደ ሲሆን ይህም

የ0.84 ከመቶ ቅናሽ ነው፡፡ በርግጥ የአየር ንብረት ለውጥን ከመቋቋም እና ሌሎች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን ከማስፋት አንጻር ከሚጠበቀው የአርንጓዴ ቦታዎች መስፋፋትና የተደራሽነት መጨመር አንጻር የታየው የአርንጓዴ ቦታዎች ስፋት መቀነስ አሳሳቢ በመሆኑ የከተማው አስተዳደር ትኩረት መጨመር እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ ነው፡፡

### 2.4 *የአዲስ አበባ የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታድርሻ*

ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው የሚያቀርቡትን የአርንጓዴ ቦታ ስፋት ከነዋሪዎች ቁጥር አንጻር ማሰቀመጥ የተለመደ አሰራር ሲሆን ይህም የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታ ድርሻ ተብሎ ይታወቃል፡፡ የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታ ድርሻ ስሌት የሚገኘው በከተማ ውስጥ የሚገኙ ለህዝብ ተደራሽነት ያላቸውን የአርንጓዴ ቦታዎችን ስፋት ከከተማው ህዝብ ቁጥር በማካፈል የሚገኝ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በአዲስ አበባ ህዝብ በመደበኛነት የሚጎበኛቸው አርንጓዴ ቦታዎች የህዝብ መናፈሻ ፓርኮችና የመንገድ ዳር ዛፎችና ኮሪደሮችን በማካተትናቸው የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታ ድርሻ 0.29ካ.ሜነው፡፡ ይህም የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት ካስቀመጠው ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታ ድርሻ 9 ካ.ሜ. በሰው በእጅጉ ያነሰ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በከተማዋ ያሉትን አርንጓዴ ቦታዎች ለህዝብ ተደራሽ ብናደርጋቸው የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታን ወደ 20.4 ካ.ሜ ከፍ ልናደርግ እንችላለን፡፡

## 3. በአዲስ አበባ ከተማ አርንጓዴ ቦታዎችን ለማልማትና ለመጠበቅ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፍ

በአዲስ አበባ ከተማ አርንጓዴ ቦታዎችን ለማልማትና ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አሉ፡፡

### 3.1 *የኢፌዴሪ ህገ መንግስት*

የኢትዮጵያ ፌደራሊዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 43 እና 44 ዜጎች በንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መሰረታዊ መብቶች እንዳሏቸዉ ይደነግጋል:: በተጨማሪም አንቀጽ 92 መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረዉና አካባቢን የመንከባከብና የመጠበቅ ሀላፊነትና ግዴታ እንዳለበት፣ ዜጎችም አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታና የአካባቢን ደህንነት በተመለከተ በሚወጡ ፖሊሲና ፕሮግራሞች ተሳትፍ እንዲያደርጉ እንዲሁም ማንኛዉም የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ደህንነትን የማያናጉ መሆን እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡

### 3.2 *የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ*

በ1989 በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀ ሲሆን በአፈር ጥበቃና ዘለቄታዊ እርሻ፣ በደን ልማትና ጥበቃ፣ ብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ በዉሀ ሀብት ልማትና ጥበቃ፣ በኢነርጂና ማዕድን ሀብት ልማት፣ በህዝቦች አሰፋፈር፣ ከተማ ልማትና አካባቢያዊ ጤና ቁጥጥር፣ የአካባቢና የአየርብክለት ማስወገድና ቁጥጥር፣ የአየር ንብረት ለዉጥ፤ ባህላዊና ተፈጥሯዊ የተለያዩ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያስቀመጠ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም ፖሊሲ ዉስነ-ህዝብ የህብረተሰብና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ መሬትና መሬት ነክ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የመሬት አጠቃቀም፣ ስርዓተፆታ፣ የአካባቢ ኢኮኖሚክስ፣ መረጃ ስርዓትና ምርምር ከኣካባቢ ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ ፖሊሲያዊ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡

### 3.3 *የኢፌዴሪ የከተማ ልማት ፖሊሲ*

በ1998 ዓ.ም የወጣው የከተማ ልማት ፖለሲ በከተሞች የአካባቢጥበቃና የውበት ጉዳዮችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በፖሊሲዉ የመዝናኛ ቦታዎች እጥረትና ለአረንጓድ ልማት የተከለለ ቦታ አለመኖር የታማት ፖሊሲ ቀይሶ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በተያያዥም ፖሊሲዉ የከተማ አስተዳደሮች አረንጓዴ ቦታዎችን በከተማ ፕላን ደረጃ መከለል፣ በየተቋማቱ፣ በመኖሪያቤቶች፣ በየመንገድና በከተማዉ መናፈሻዎችና ተፋሰሶች ዕጽዋት የመትከልና የመንከባከብ ሥራ እንዲካሄድ ያስቀምጣል ፡፡

### 3.4 *የኢፌዴሪ የከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ፖሊሲ፣*

በ2003 ዓ.ም. የወጣው የኢፌዴሪ የከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ፖሊሲከተሞች በመሬት አጠቃቀም ኘላናቸው ማዕቀፍ ውስጥ አረንጓዴ፣ የተዋበ፣ የተክል እና እጽዋት ከተማን (Garden City) መርህን በተከተለ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ እንደ ፖሊሲ አቅጣጫ ያስቀበጠ ሲሆን ይህንንም ለመተግበር የከተሞችን የአረንጓዴ ሽፋን ልማት እና ውበት ጥበቃን የሚያረጋግጥ ጠንካራ የአሰራር እና አደረጃጀት ስርዓት መዘርጋት፣ በከተሞች የአረንጓዴ ቦታዎች ልማት እና የማስዋብ ተግባር ላይ ባለሀብቱ ፣ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን አግባብ በማመቻቸት ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ የማድረግ መሰረታዊ የአፈፃጸም ስልቶች በስራ ላይ እንዲውሉ ይደነግጋል፡፡

### 3.5 *የቆሻሻ አያያዝና አወጋገዴ የአረንጓዳ ሌማትና ውበት ስትራቴጂ*

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተዘጋጀው የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፤ የአረንጓዴ ልማትና ውበት ስትራቴጂ የአረንጓዴነት መሰረተ

ልማቶች ህብረተሰቡን ባሳተፈና የሥራ እድል ሊፈጥርና ከተሞችን ዉበት ሊያብስ በሚችል መልኩ መልማት እንደሚገባቸዉ አስቀምጧል፡፡

## 4. የአርንጓዴ ቦታዎች ፕላን በአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን

አሁን የመተግበሪያው ጊዜ ያለፈው የአዲስ አበባ ከተማማስተር ፕላን የከተማዋን የአርንጓዴ ቦታ ሽፋን ወደ 22,000 ሄክታር (ከአጠቃላይ የከተማዋ ስፋት 41 ከመቶ የሚሆን) ለማድረስ የሚያስችሉ ወደ 17 የሚደርሱ የአርንጓዴ ቦታዎች ልማት እቅድ ተነድፈው ነበር እነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡

1. የጉለሌ ዕጽዋት ማዕከል መመስረት
2. በአዲስ አበባ ከፍተኛ ቦታዎች የደን ልማት ማካሄድ
3. የባህርዛፍ ተከላን ከእንጦጦ ተራራ አስወግዶ በአገር በቀል ዛፍ መተካት
4. የእንስሳት ማቆያ በማዕከላዊ ፓርክ መመስረት
5. የነባር ፓርኮችን ደረጃ ማሻሻልና የዘላቂ ማረፊያ ቦታዎችን ከመናፈሻ አገልግሎት ጋር ማጣመር
6. በቀለበት እና ዋና ዋና መንገዶች ዳርቻ ዛፎችን መትከል
7. ከቦሌ አየር ማረፊያ በስተደቡብ ምስራቅ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል የደን ልማት ማልማት
8. የወንዝ ዳር ቦታዎች በዕጽዋት እንዲሸፈኑ ማድረግ
9. ገርጂ አካባቢ አዲስ የከተማ ፓርክ ማልማት
10. የቡልቡላ ወንዝን ተከትሎ ከእስጢፋኖስ ቤተክርስትያን እስከ ኢትዮ-ኩባ ወዳጅነት ሀውልት መናፈሻ መመስረት
11. አንድ ዛፍ በአንድ መኖርያ ቤት እንዲተከል ማድረግ

ከእነዚህ እቅዶች ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የተተገበረው የጉለሌ መካነ ዕጽዋት ማዕከል ማቋቋም ብቻ ነው፡፡ ከተራ ቁጥር 2-6 ያሉት እቅዶች በተለያዩ ደረጃ በመተግበር ላይ ያሉ ሲሆን፤ ከተራ ቁጥር 7-11 ያሉት እቅዶች ሙሉ ለሙሉ ያልተተገበሩ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ የአርንጓዴ ልማት የተያዙ ቦታዎች ለሌሎች አገልግሎቶች የተለወጡበት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡

## 5. የአርንጓዴ ቦታዎችን ልማትና ጥበቃ ለማስፈጸም በአዲስ አበባ ያለው ተቋማዊ አደረጃጀትና ብቃት

የአዲስ አበባን የአርንጓዴ ቦታዎችንለማልማትና ለማስጠበቅ ሦስት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ተቋቋመዋል፡፡ እነዚህም፥

1ኛ) የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፥ ይህ መ/ቤት በአመዛኙ የከተማዋን አካባቢ ነክ ጉዳዮችን የሚቆጣጠር ሲሆን በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ የደን ቦታዎችን የማልማትና የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ዋናው ሠራ ቁጥጥር (ሬጉላቶሪ) ቢሆንም የኦፐሬሽን ሥራም እየሰራ ይገኛል፡፡

2ኛ) የውበት፣ መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጄንሲ፥ ይህ መ/ቤት የከተማዋን የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች፣ የበአል ማክበርያ ስፍራዎች፣ ከሃይማኖት ተቋማት ውጭ ያሉ የዘላቂ ማረፍያ ቦታዎችን፣ የመንገድ ዳር ዛፎችን እና የወንዝ ዳር ዕጽዋቶችን የማልማትና ማስተዳደር ሀላፊነት አለበት፡፡

3ኛ) የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን ዋና የሥራ ሂደት፥ ይህ መ/ቤት በከተማዋ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ስር የሚተዳደር ሲሆን በዋናነት በከተማዋ የሚካሄዱ የሰብል፤ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳት ልማት ስራን ደጋፍ የሚደርግ ነው፡

## 6. የከተማ አርንጓዴ መሠረተ ልማት ከማስፋፋት አንፃር በአዲስ አበባ ያሉ ችግሮች

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙትን አርንጓዴ መሠረተ ልማት ከማስፋፋት አንፃር እየታዩ ያሉትን ችግሮችና ተግዳሮቶች በከተማው ከሚገኙ የተለያዩ የአርንጓዴ ቦታዎች አንጻር ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.1 *በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች ካሉ ደኖች ጋር የተያያዙ ችግሮች*

በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች ካሉ ደኖች ጋር የተያያዙ ችግሮች በዋነኛነት ከመሬት አጠቃቀም ለውጥ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በከተማዋ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ የደን ቦታዎች ይዞታ ባለመካለል እና በዚሁ መልኩ እንዲጠበቁ ባለመደረጉ የህገወጥ መሬት ወረራ በማካሄድ የደን ቦታዎቹን ለመኖርያ ቤት መስሪያ እና ለ እርሻ ሥራ አገልግሎት በመዋል ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በአንቆርጫ ተራራ ላይ የሚገኘው ቦታ ነው፡፡ በፊሊዶሮ የሚገኘውም ቦታ በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት ለደን ልማት  የተያዘ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ለመኖርያ ቤት መስሪያ ውሏል፡፡ በመሬት አጠቃቀም

መርህ መሠረት በከፍተኛ ደረጃ ተዳፋትማ የሆኑ ቦታዎች ለደን ልማት አገልግሎት መዋል ሲገባቸው የየካ ተራራ ለሃብታም ሰዎች የመኖርያ ቤት መስርያ በመዋል ላይ ይገኛል፡፡

እዮብ ጠንክር በ2002 ዓ.ም. ያወጣው ጥናታዊ ጽሁፍ እንደሚያሳየው በኮተቤ፣ በአንቆርጫ፣ በእንጦጦ እና በሳንሱሲ ከፍተኛ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሄደ ሲሆን በተለይ በ1998 በአንቆርጫ 12486፣ በኮተቤ 16519፣ በእንጦጦ 8981 እና በሳንሱሲ 2470 ሰዎች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

ስዕል 8:- የዘመናዊ ቤቶች ግንባታ በየካ ተራራ



### *6.2 ከህዝብ መናፈሻ ቦታዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች*

ከህዝብ መናፈሻ ቦታዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች በሶስት ደረጃ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም 1ኛ) የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች በበቂ መጠን አለመኖር 2ኛ)የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች ለሌሎች አገልግሎት ማዋል፣ 3ኛ)የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች በበቂ ተደራሽነት አለመኖር ናቸው፡፡

ከላይ በምዕራፍ 2 እንደተገለጸው የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች እና የመንገድ ዳር ዛፎችን በመመርኮዝ የከተማዋ የነፍስ ወከፍ የአርንጓዴ ቦታ ድርሻ 0.29ካ.ሜ በሰው ነው፡፡ ይህም በማንኛውም መስፈሪያ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የከተማው መስተዳድር ተጨማሪ የመናፈሻ ቦታዎችን እና የመንገድ ዳር ዛፎችን በተለያዩ አካባቢዎች ማልማት ይጠበቅበታል፡፡

አንዳንድ በከተማው ውስጥ ያሉ የመናፈሻ ቦታዎች ከተመሠረቱበት ዓላማ ውጭ ለንግድ አገልግሎት በማዋላቸው አብዛኛው የከተማው ህዝብ ሊጠቀምባቸው አልቻሉም፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የአምባሳደር መናፈሻ ነው፡፡ ይህ መናፈሻ ለተወሰኑ ዓመታት ለግለሰብ ነጋዴ በኮንትራት መልክ

ተሰጥቶ ለምግብ እና ለመጠጥ ቤት አገልግሎት በመዋሉ በዚህ መናፈሻ ውስጥ መጠቀም የሚችሉት ከፍለው ምግብ መብላትና መጠጥ መጠጣት የሚችሉ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም መናፈሻው ሊሰጣቸው የሚችሉትን የሥርዓተ ምሕዳር አገልግሎቶች ህዝብ በነጻ ወይም በተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘት አልቻለም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ የንግድ አገልግሎት በመቅረት ላይ ይገኛል፡፡

ስዕል 9:- የአምባሳደር መናፈሻ (የፊት ለፊቱ አጥር ለተለያዩ የንግድ ሱቆች የዋለ ነው)



በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ አርንጓዴ ቦታዎች ተመጣጣኝ ስርጭት በከተማው ውስጥ የሌላቸው እና ለአብዛኛው የከተማው ህዝብ በበቂ ርቀት ተደራሽነት ያለቸው ባለመሆናቸው ነዋሪዎች ሲጎበኙአቸው አይታዩም፡፡ ለምሳሌ በእንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኘው ደን በከተማዋ የሰሜን ዳርቻ ላይ የሚገኝ በመሆኑ መኪና ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ካልሆነ በስተቀር ለአብዛኛው ህዝብ በቀላሉ ሊደረስበትና ሊጎበኝ የሚችል አይደለም፡፡

በመኖርያ ሰፈሮች አካባቢ ያሉ አብዛኞች የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የሌላቸው በመሆኑ ነዋሪዎች ሊያለሙአቸውና ሊጠቀሙባቸው አልቻሉም፡፡ በዚህም ሁኔታ የተነሳ በአንዳንድ ቦታዎች እነዚህን የመናፈሻ ቦታዎች ለመኖርያ ቤት እና ለመጋዘን መስሪያ እና ለንግድ ሥራዎች አገልግሎት ሲውሉ ይታያሉ፡፡

### 5.3 ከወንዝ ዳር ቦታዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች

የወንዝ ዳር ቦታዎች በአግባቡ በታቀደ መልኩ በዕጽዋት ከለሙ የከተማን የአርንጓዴ መሠረተ ልማት ከማስፋፋት እና የሥነ ምህዳር አገልግሎችን ከመስጠት አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል፡፡ የወንዝ ዳር የዕጽዋቶች ቦታዎች በተለይ ለዱር እንስሳት መኖርያ እና መተላለፊያ ሊያገለግሉ የሚችሉ የአርንጓዴ መሠረተ ልማት አካል ናቸው፡፡ ስለአዲስ አበባ የወንዝ ዳር ቦታዎች ስናስብ በቅድሚያ ወደ ነዋሪዎች ህሊና የሚመጣው በደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ መበከላቸው እና ለሰዎች መኖርያነት ብቁ ባልሆኑ የመኖሪያ ቤት ግንባታ መያዛቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የወንዝ ዳር ቦታዎች በአሁኑ ይዞታቸው ለህዝብ መናፈሻ አገልግሎት ሊውሉ የማይችሉ ናቸው፡፡ የአዲስ አበባ ወንዞች ከሰሜን አቅጣጫ ተነስተው ወደ መሃል የከተማዋ ክፍል እስከሚደርሱ ጥልቀት ባለው ሸለቆ ውስጥ የሚጓዙ በመሆናቸው በእነዚህ ቦታዎች ለወንዝ ዳር ግብርና አገልግሎት ሊውሉ አይችሉም፡፡ ወንዞቹ ወደ መሃል እና ደቡብ የከተማዋ ክፍል ሲደርሱ ከሸለቆ ወጥተው ወደ ላይኛው የመሬት ክፍል ስለሚወጡ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ይውላሉ፡፡ ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው ወንዞቹ ከመኖር ቤቶች፣ ከህክምና ተቋማት እና ከማምረቻ ድርጅቶች በሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ የተበከሉ በመሆናቸው፤ በእነዚህ ወንዞች በመጠቀም የሚለሙ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ለሰዎች ጤና ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ ኝጥረ ነገሮች የያዙ እንደሆኑ የተለያዩጥናቶች አሳይተዋል፡፡

ስዕል10:- የወንዝ ዳር ቦታ በመኖርያ ቤቶች የተያዘ (ጎላ ሰፈር)



የአዲስ አበባ ወንዞች በሙሉ ከሰሜን የከተማዋ ክፍል ተነስተው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ስለሚፈሱ በክረምት ወራት ሞልተው በመፍሰስ በተወሰኑ የንፋስ ስልክ ላፍቶ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ቦታዎች በንብረት እና

በእንስሳት ህይወት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ለምሳሌ ነሐሴ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ በጣለው ዝናም ምክንያት በተከሰተ የጎርፍ አደጋ የአቃቂ ብረታብረት ፋብሪካ፣ አቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሠራተኞች መኖርያ ቤቶች፣ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የችግኝ ማፍያ ጣብያ፣ የከተማ ግብርና የሚካሄድባቸው ቦታዎች እና ሌሎች ቦታዎች በከፍተኛ ውሃ በመጥለቅላቸው በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡

### *5.4 ከከተማ ግብርና ቦታ ጋር የተያያዙ ችግሮች*

በመሬት አጠቃቀም ለውጥ ምክንያት በአዲስ አበባ የከተማ ግብርና ቦታዎችን ወደ ግንባታ ሥፍራዎች እየተለወጡ በመሄዳቸው እነዚህ አካባቢዎች በተፈጥሮ ሊሰጡ የሚችሉትን የሥራዓተ ምህዳር አገልግሎቶች በመቀነስ ወይም በማስቀረት የከተማ ህዝብ ኑሮ ላይ ጫና ሊያስከትሉ የሚችሉበት ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ ከሚችሉ ችግሮች የጎርፍ አደጋ፣ የምግብ ሰብል እና የአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት መቀነስ እና የሥራ እድል ማጣት ይገኙበታል፡፡

### *5.5 ከመንገድ ዳር ዛፎች አተካከል ጋር የተያያዙ ችግሮች*

በአዲስ አበባ ከተማ ከመንገድ ዳር ዛፎች አተካከል ጋር የተያያዙ በሦስት መደቦች ሊከፈሉ የሚችሉ ችግሮች ይታያሉ፡ እነዚህም 1ኛ) የዛፍ ዓይነቱ አመራረጥ፣ 2ኛ) የችግኝ መትከያ ቦታ አመራረጥና ዝግጅት፣ እና 3ኛ) ከችግኝ ተከላ በኋላ የሚያስፈልግ እንክብካቤ ናቸው፡፡

**1ኛ) የዛፍ ዓይነቱ አመራረጥ፥**በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ዳር ተተክለው ከሚገኙ ዛፎች በብዛትበውስን የመጤ ዛፍ ዓይነቴዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎም በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች (ለምሳሌ እሾክ ያላቸው) በመንገድ ዳር ላይ ተተክለው ይታያሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው እሾካማ የግራር ዛፍ ከኡራኤል ወደ ቦሌ መድሃኔዓለም በሚወስደው መንገድ ላይ መተከላቸው ነው (Eyob Tenkir, 2010)፡፡ ኢትዮጵያ በዕጽዋት ዓይነቴዎች ስብጥር የምትታወቅ ሀገር ነች፡፡ በቁጥር ወደ 1000 የሚደርሱ ሀገር በቀል የእንጨታማ ዕጽዋት ዓይነቴዎች እንደሚገኙባትም ይታወቃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አነስተኛ ሊባሉ የማይችሉት ለመንገድ ዳር ተከላ ሊውሉ እንደሚችሉ ይገመታሉ፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ዛፎች ስራቸውን ቁልቁል ወደታች ከማሳደግ ይልቅ ወደ ጎን ስለሚያሳድጉ የመንገድን መዋቅር በማበላሸት የመንገዱን የአገልግሎት ጊዜ ያሳጥራሉ፡፡

**2ኛ) የችግኝ መትከያ ቦታ አመራረጥና ዝግጅት፥** በአግረኛ መንገድ ላይ የተተከሉ ዛፎች በአብዛኛው በተጠቀጠቀ መሬት ላይ የተተከሉ በመሆናቸው የዛፎቹ ሥሮች በቂ አየርና ውሃ ስለማያገኙ እንዲሁም ለዛፎቹ እድገት በቂ

*የሆነ ቦታ ስለማይተውላቸው ዛፎቹ እንዳያድጉ ወይም እድገታቸው እንዳይፋጠን ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የከተማዋ መንገዶች ዳር የተተከሉ ዛፎች ከመንገድ ዳር በቂ ርቀት ጠብቀው ባለመተከላቸው ለትራፊክ እና ለእግረኞች እንቅስቃሴ ችግር ሲፈጥሩ ይስተዋላል፡፡*

3ኛ) **ከችግኝ ተከላ በኋላ የሚያስፈልግ እንክብካቤ፥** *በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ዳር በተተከሉ ዛፎች ከሚታዩት ችግሮች ውስጥ ከተከላ በኋላ በቂ እና ተከታታይ እንክብካቤ አለማድረግ ይገኝበታል፡፡ችግኞች በቂ ውሃ ባለማግኘት፣በሰው እና በእንስሳት በመጎዳት እድገታቸው በአጭሩ ሲቀጭ ይታያል፡፡የመሠሰረተልማት ማስፋፊያ ሥራዎችም* (*ለምሳሌ የውሃ፣ የስልክ፣ የመብራት*) *በአደጉ ዛፎች ላይ ጉዳት ሲያደርሱም ላደረሱት ጉዳት ምንም ዓይነት የማካካሻ ተከላ ስለማያደርጉ በከተማዋ የመንገድ ዳር ዛፎችን ከማልማት አንጻር የራሳቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርጋሉ፡፡*

ስዕል11:- *የአያያዝ ጉድለት ያጋጠማቸው የመንገድ ዳር ዛፎች ሀ*) *የሞተ የዘንባባ ዛፍ ለ*) *በተጠቀጠቀ የእግረኛ መሄጃ መሬት ላይ የተተከለ የዘንባባ ዛፍ*




*አብዛኞቹ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች ሊከሰቱ የቻሉት በመስኩ በቂ እውቀት ባለመኖሩ ሲሆን ችግሮቹን በዘላቂነት ለመፍታት በቂ ጥናትና ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በጥናትና ምርምር ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትና ባለሙያዎች ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡*

## 7. በአዲስ አበባእና በኦሮሚያ ዙሪያ የአርንጓዴ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ የወደፊት አቅጣጫ

*በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የሚገኙ ከተሞች የመሪ ፕላን እየተዘጋጀ ሲሆን በዚህ መሪ ፕላን የአርንጓዴ ቦታዎች*

ልማትና ጥበቃ አንዱ የፕላን አካልነው፡፡ የአርንጓዴ መሠረተ ልማት ጥበቃና ልማት የተፈጥሮ አካባቢን በማስጠበቅ የከተሞችን ማህበራዊ እናኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን ያስችላል በሚል መርህ ላይ በመመስረት ይህንንም ለማሳካት የአርንጓዴ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ በሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ላይ እንዲመሰረት ማድረግና በከተሞቹ ያሉትን ወደፊት የሚለሙትን አርንጓዴ ቦታዎች በማስተሳሰር የአርንጓዴ መሠረተ ልማት በከተሞቹ እንዲመጣታሳቢ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የአርንጓዴ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ ከዚህ የሚከተሉትን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች እንዲሰጡ ታሳበ ማድረግ በመታቀድ ላይ ነው፡፡

- የአየርንብረትለውጥማጣጣሚያእናመከላከያ
- የከተማሙቀትንመቀነስ
- የካርቦንልቀትንመቀነስ
- የአየርብክለትንመቀነስ
- ዘለቄታዊለሆነየጎርፍውሃአያያዝ
- የንጹህየመጠጥውሃአቅርቦት
- የምግብሰብልአቅርቦት
- የማገዶእናየግንባታእንጨትአቅርቦት
- የመዝናኛአገልግሎት
- የትምህርታዊአገልግሎት
- የከተማውበትን መጠበቅ

ከላይ የተዘረዘሩትን የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ታሳቢ በማድረግ፤ የከተሞችን የመሬት አቀማመ ጥሁኔታ፤ የመሬት አጠቃቀም እናሽፋን መነሻ በማድረግ በክልላዊ ፕላን ደረጃ እና በመዋቅራዊ ፕላን ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ 6 ታሳቢ የአርንጓዴ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ ዕቅዶች ተነድፈዋል፡፡

## 8. የአርንጓዴ መሠረተ ልማትን ለማልማት የባለድርሻ አካላት ሚና

የአርንጓዴ መሠረተ ልማት ስራ ከፍተኛ ገንዘብ፣ ዕውቀት እና ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የመንግስትንና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡

1ኛ) **የመንግስት ድርሻ**

- የፖለቲካ ፈቃደኝነት መኖር
- አመች የህግ ማዕቀፍ ማውጣትና ማስፈጸም (ምሳሌ፡ የአርንጓዴ መሠረተ ልማት ፖሊሲ)
- የአስፈጻሚ ተቋም ጥንካሬን ማረጋገጥ (ምሳሌ፡ በቂ በጀት መመደብ፣ ተገቢ ባለሙያዎችን መመደብ
- የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ከእቅድ ማውጣት እስከ አፈጻጸም ድረስ በማስተባበር የአርንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ
- የግንዛቤ ማሳደግያ ሥራ በስፋትና በተከታታይነት መስራት

2ኛ) **የህብረተሰብ ድርሻ**

- በመኖርያ ቤቶች ግቢ ውስጥ የዕጽዋት ተክላ ማካሄድ
- በመኖርያ ቤቶች አካባቢ አርንጓዴ ቦታዎችን በጋራ ማልማትና መጠበቅ

3ኛ) **የባለሀብቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድርሻ**

- በአርንጓዴ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ ሰፊ የገንዘብ እና የቁሳቁስ አስተዋጽዖ ማድረግ

4ኛ) **የትምህርትና የምርምር ተቋማት ድርሻ**

- ስለከተማ አርንጓዴ ቦታዎች ሥነ ምህዳርና ፕላኒንግ በሥርአተ ትምህርት ውስጥ አካትቶ ማስተማር
- ከአርንጓዴ መሠረተልማት አንጻር ያሉ የእውቀት ክፍተቶችን በመለየትና ምርምር በማድረግ ለልማት ሥራው እውቀትን፣ መረጃንና ቴክኖሎጂን ማስገኘት
- ለአርንጓዴ ቦታዎች ልማት ምን ዓይነት ፖሊሲዎች፣ የትምህርት መርሀግብር፣ እና የእድገት ስትራቴጂዎች እንደሚያስፈልጉ በማሳወቅ ረገድ ተመራማሪዎች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

## 9. ዋቢ መጻህፍት


Benedict, M. A. and McMahon, E. T. (2000).Green Infrastructure.Sprawl Watch Clearing House Monograph Series, 36pp.

Boyer, T.and Polasky, S. (2004).Valuing urban wetlands: A review of non-market valuation studies. Wetlands, 24, 744–755.

Ellaway, A., Macintyre, S. and Bonnefoy, X. (2005). Graffiti, greenery, and obesity in adults: secondary analysis of European cross sectional survey. *British Medical Journal***331**(7517), 611-612.

Eyob Tenkir (2010).Assessment of challenges, problems and interventions made to develop urban forest in Addis Ababa. Heinrich Böll Foundation.

Kaplan, R. (2001). The nature view from home: Psychological benefits. *Environment & Behavior* 33, 507-542.

Kong, F., Yin, H., Nakagoshi, N. and Zong, Y.(2010). Urban green space network development for biodiversity conservation: Identification based on graph theory and gravity modeling. Landscape and Urban Planning 95 (2010) 16–27

Kuo, F.E. (2003). The role of arboriculture in a healthy social ecology. J. Arboricult. 29, 148–155.

Kuo, F.E., andSullivan, W.C. (2001). Environment and crime in the inner city – does vegetation reduce crime? Environment and Behavior 33, 343–367.

Kuttler, W. (2008).The urban climate – basic and applied aspects. In: Urban Ecology– An International Perspective on the Interaction between Humans and Nature. Springer, New York, pp. 233–248.

Maas, J., Verheij, R. A., Groenewegen, P. P., de Vries, S., and Spreeuwenberg, P. (2006). Green space, urbanity, and health: How strong is the relation? Journal of Epidemiology and Community Health, 60(7), 587–592.

Mcpherson, E. G. and Simpson, J. R. (2003). Potential energy savings in buildings by an urban tree planting programme in California. *Urban Forestry & Urban Greening* **2**(2), 73-86.

Mitchell, R., and Popham, F. (2008). Effect of exposure to natural environment on health inequalities: An observational population study. The Lancet, 372(9650), 1655–1660.

Ulrich, R. S. (1984). View through a window may influence recovery from surgery. *Science* (224), 420-421.

# የደረቅና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ በሀዋሳ ከተማ:
# የሃዋሳ ሀይቅን ለመጠበቅ አፋጣኝ የተቀናጀ ሥራ አስፈላጊነት

*ግርማ ጥላሁን*

## 1. መግቢያ

*የሀዋሳ ከተማ የታላቁ የምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ አካል በሆነው የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ መሀል ላይ ትገኛለች:: ከተማዋ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለች ፣ በረካታ የመሠረተ ልማት ግንባታ የሚካሄድባት፣ ፈጣን የሕዝብ ዕድገትና የፋብሪካዎች መበራከት የሚታይባት ናት:: ሀዋሳ የብዙዎችን ቀልብ እንድትስብ ያደረጋት ለውበቷና ለስያሜዋ መነሻ የሆናት የሀዋሳ ሀይቅ ሲሆን ይህም ሁኔታ ሀዋሳን ከሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች የተለየች ያደርጋታል::*

*ሀዋሳ አዲስ ከተማ ናት፤ የተቆረቆረችው በ1958 ዓ.ም. ነበር፤ ስትቆረቆርም ፕላን ተነድፎ፣ ገና ከመጀመሪያው የዘመናዊ ከተማ ባህርይ ይዛ እንድታድግ ተደርጓል፤ በዚያን ጊዜ በነበረበው የመንግስት ፖሊሲ መሰረት፣ አሀዱ ተብላ የተመሰረተች ከተማ ስትሆን ሌሎቹ እህቶቿ ባህር ዳርና አርባ ምንጭ ናቸው። በወቅቱ በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ለሚባለው ክልል ዋና ከተማ ስትደረግ ህዝቧም 3600 ነበር። ባጭር ጊዜ ውስጥ እየሰፋች ስለሄደች የህዝቡ ቁጥርም እንዲሁ በማደግ 1986 ዓ.ም. ሰባ ሺህ ሲደርስ በ1992 ወደ 94010 አድጓል። ከዚያ በኋላ፣ በአስር አመት ብቻ፣ የከተማዋ የህዝብ ብዛት ወደ 200396 ሲመነደግ፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የኤኮኖሚ ተቋማት (በተለይ በአገልግሎት ክፍለ ኤኮኖሚው) ተከፍተዋል። የከተማዋ የቆዳ ስፋትም በዚሁ ዓይነት በጣም እየሰፋ ሄዷል።*

*በአሁኑ ወቅት ሀዋሳ ከአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ አንዷ ስትሆን በማስመዝገብ ላይ ላለችው እጅግ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚና የህዝብ እድገት የሀዋሳ ሀይቅ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ እንዳለ ይታወቃል።*

*የሀዋሳ ሀይቅ በምሥራቅ አፍሪቃ የስደተኛና የነዋሪ ወፎች ማረፊያና መጠለያ ነው :: ሀይቁ የባህልንና የተፈጥሮ መስህብ አይነተኛ መገለጫ ከመሆኑ ባሻገር ለጀልባ ሽርሽር ለሠርግና ለሀይቅ ዳር መዝናኛ ወደር የለውም ፤ከዚህም የተነሳ የፍቅር ሀይቅ በመባል ይታወቃል:: ሆኖም ይህ ሀይቅ ሰው ሰራሽ የሆነ የብክለትና የደለል አደጋ ተጋርጦበት ይገኛል::*

ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው በሀዋሳ ከተማ ስለደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና ከዚህም በሚነሳ የብክለት ጦስ በሀዋሳ ሀይቅ ብዛ ህይወት ላይ እደደረስ ስለአለው አደጋ ነው:: ጽሑፉ ያለውን አደጋ የሚያሳዩ በአብዛኛው ካለፉት 10 አመታት ወዲህ በተለያዩ ተመራማሪዎች የተገኙትን የምርምር ውጤቶች ያቀርባል:: የጽሑፍ አላማ ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በምርምር በተገኘ መረጃ አስደግፎ አደጋውን በማሳየት በአፋጣኝ ከወዲሁ መወሰድ ስላለበት የተቀናጀ እርምጃ ለማመላከት ነው:: በተጨማሪም ጽሑፉ ለማህበረሰብ ውይይትና መነሳሳት የሚረዳ የመንደርደሪያና የማጣቀሻ ሀሳብ ለማበርከትም ይረዳል:: ይህ ጽሑፍ ሶስት ክፍሎች አሉት:: እነዚህም አመላካች የምርምር ግኝቶች፣ ብክለት አደጋ በሀዋሳ ሀይቅ ብዛ ህይወት ላይ የደቀነው አደጋ፣ የሀዋሳ ሀይቅን ለመጠበቅና ለመታደግ በአፋጣኝ መካሄድ ያለበት የተቀናጀ ሥራ ናቸው:: በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱት አመታት በሙሉ እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር የቀረቡ ናቸው:: ለአቀራረብ በመመቸቱ በጽሑፉ ውስጥ ያሉት ማጣቀሻዎች በሙሉ በእንግሊዘኛ ጽሑፍ ቀርበዋል ::

## 2. ዋና ዋና የምርምር ግኝቶች

በሀዋሳ ከተማ ከደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ጋር በተያያዘ የተሠሩና በውል የታወቁ የምርምር ሥራዎች ያተኮሩት በሚከተሉት ዙሪያ ነው:: 1/ የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ 2/የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ኢንቬንተሪ 3/ የሆስፒታል ፈሳሽ ቆሻሻ 4/ የኢንዱስትሪዎች ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ናቸው ::

### *2.1 የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ*

የሀዋሳ ከተማ የዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ከሁለት አሥርት አመታት ብዙም የዘለለ አይደለም:: ሆኖም ከተማዋ ከአሥር አመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት ያደገች ስትሆን ከዕድገቷ ጋር የሚመጣጠንና ደረጃውን የጠበቀ የቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስልት ሊፈጠር አልቻለም:: ከቤት ለቤት ለሚካሄድ የቆሻሻ አሰባሰብ ማህበረሰቡ የሚያሳየው ትብብር ከፍተኛ ነው:: ለሚሰጠውም ግልጋሎት ለመክፈል ፈቃደኛ ነው :: ሆኖም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ወይም የግል ድርጅቶች ግልጋሎቱን በአጥጋቢ ሁኔታ መስጠት አልቻሉም::

በሀዋሳ ከተማ የደረቅና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ላይ በተለይ ከሆቴሎች፣ ከገራዦች፣ ከንግድና ከህክምና መስጫ ማዕከሎች፣ ... ወዘተ በሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝ ላይ የተሠሩ ሥራዎች የሉም ቢባል ይቀላል :: ከደረቅና ቆሻሻ አያያዝ አንፃር በውል የተጠናና የተገኘው መረጃ በተመረጡ ሁለት የሃዋሳ ቀበሌዎች ላይ

የተካሄደው ጥናት (Derje , 2009) ሲሆን ተፈላጊው መረጃ በገበታ 1 ከሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ጋር በንጽጽር ቀርቧል ::

ሰንጠረዥ 1:- በአራት የኢትዮጵያ ከተሞች የየመኖሪያ ቤቱ የደረቅ ቆሻሻ በሚወጣበት ፍጥነትና መጠን በንጽጽር የቀረበ (ማጣቀሻ ጽሑፍ በቁጥርና በቅንፍ የተመለከተው ነው)

| የተለካው የደረቅ ቆሻሻ | ሀዋሳ (1) | አዳማ (2) | ጂማ (3) | አዲስ አበባ (4) |
|---|---|---|---|---|
| ከየመኖሪያ ቤቱ የሚወጣበት ፍጥነት (ኪ.ግ በነፍስ ወከፍ በቀን) | 0.20 | 0.15 | 0.16 | 0.25 |
| አጠቃላይ መጠን (በቶን በቀን ) | 39.7 | 35.2 | 25.8 | 85.1 |

*ምንጭ:-* 1= Dereje (2009); 2= Lemma (2007); Melaku (2008); Nigatu *et al.* (2011)

ሰንጠረዥ 1 እንደተመለከተው የሀዋሳ ከተማ ከአዳማና ከጂማ ከተማዎች የበለጠ የደረቅ ቆሻሻ የመፍጠር ፍጥነትና መጠን አላት :: በጥናቱም እንደቀረበው የደረቅ ቆሻሻው ምንጭ በአብዛኛው (59.7%) የተክሎችና የእንስሳት ተዋፅኦ ተረፈ ምርትና የምግብ ብስባሽ ሲሆኑ በመቀጠል የአመድና ደቃቅ ጥራጊዎች የ 31.3% አስተዋጽኦ አላቸው:: የብረታ ብረትና የጎማ ውዳቂዎች እንዲሁም የጠርሙስ ስብርባሪዎች እያንዳንዳቸው ከ 0.5% ያልበለጠ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ::

በአጠቃላይ ሲታይ የሀዋሳ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ አጥጋቢና ደረጃውን የጠበቀ አይደለም :: ከቤት ለቤት የሚሰበሰበው ደረቅ ቆሻሻ የሚጓጓዘው በግለሰቦች በሚመሩ የአህያ ጋሪዎች ሲሆን አሠራሩ ብዙ ችግር አለበት :: ሥራው የሚካሄደው የዕለት ገቢ ለማግኘት ብቻ ሲሉ በሚሠሩ ዜጎች ለጤና አደጋ ባለው መንገድ በትንንሽ ህፃናት ሳይቀር ነው:: ቆሻሻውም ብዙ ጊዜ ከመድረሻው ሳይደርስ መንገድ ላይ የሚነጠባጠብና አንዳንዴም አሳቻ ቦታ ላይ የሚደፋ ነው:: በተለያዩ ቦታዎች የተቀመጡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች በከተማው አንዳንድ ቦታዎች ቢኖሩም ቆሻሻው ወደነዚህ ገንዳዎች ተሰብስቦ የመሚመጣበት ፣የሚጠራቀምበትና በመጨረሻም በመዘጋጃ ቤት መኪናዎች ተጓጉዙ የሚወሰድበት አሠራር በጣም ደካማ ነው ::

## 2.2 *የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝ*

በአሁን ጊዜ መርዛማ ኬሚካሎች በውስጣቸው የያዙ የመድሀኒት (pharmaceuticals ) ፣የመዋቢያ (cosmotics) ና የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች (e- wastes) በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮችና ከተማዎች ላይ እያንገዘበቡ ያሉ ችግሮች ናቸው :: እነዚህ ችግሮች ለህብረተሰቡ ለጊዜው በግልጽ በማይታይ መንገድ እያደጉና ሰውንና ሌሎች ፍጡራንን ውስጥ ለውስጥ እያጠቁ ናቸው:: የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች ከኤሌክትሮኒክ መገልገያዎች (ምሳሌ ኮምፒውተሮች ፣ሞባይሎች ፣ ቴሌቪዥኖች፣ ሪፍሪጀሬተሮች … ወዘተ) አርጅተው ሲወገዱና ተበላሽተው ሲጠገኑ የሚመነጩ ናቸው ፤በአግባቡ ካልተያዙና ካልተወገዱ አካባቢውን የሚበክሉበት ዕድል ይፈጠራል:: ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች ቁጥራቸውና አይነታቸው የበዛ በርካታ መርዛማ ኬሚካሎች በውስጣቸው የያዙ በመሆናቸው በግዴለሽነት ከተጣሉ ይህ ነው የሞባይል ጉዳት በአካባቢና በሰው ጤና ላይ ያደርሳሉ::

የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎችን በተመለከተ በተወሰኑ የኢትዮጵያ ከተሞች ላይ የተደረገው ጥናት (PAN-Ethiopia, 2011) እንዳመላከተው ችግሩ አሳሳቢና በሚመለከታቸው አካላትና በህብረተሰቡ በትኩረት መታየት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ነው :: በጥናቱ ከተካተቱት የኤሌክተሮኒክስ በለንብረቶች ውስጥ የግል መኖሪያ ቤቶች ፣የትምህርትና የምርምር ተቋማት፣ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች ፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የጅምላ ንግድና አከፋፋዮች፣ የኤሌክትሮኒክስ ጥገና ሱቆች ይገኙበታል ::

የተጠኑት የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች ምንጫቸው አራት ሲሆን እነዚህም ኮምፒውተሮች ፣ ሞባይሎች ፣ ቴሌቪዥኖችና ሪፍሪጀሬተሮች ናቸው ::

ሰንጠረዥ 2፡- በሶስት የኢትዮጵያ ከተሞች ላይ በተደረገ ዝርዝር ጥናት የተመዘገበ ጥቅል የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች ምንጭ በቁጥር ክምችት በ 2011 እና ከ 2011 እስከ 2020

| ከተማ | በ 2011 | ከ 2011 እስከ 2020 ተሻጋሪ ግምት | የጭማሪ መጠን (እጥፍ) |
|---|---|---|---|
| ባህር ዳር | 6,368 | 68,799 | 10.8 |
| ድሬዳዋ | 11,645 | 121,548 | 10.4 |
| ሀዋሳ | 3,955 | 47,508 | 12 |

*ምንጭ፡-* PAN-Ethiopia, 2011

በሰንጠረዥ 2 እንደሚታየው የሀዋሳ ከተማ የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ ጥቅል ክምችት መጠን ከባህር ዳር ና ከድሬዳዋ ጋር ሲነፃር ከ 2 እስከ ሶስት እጅ በላይ ያነስ ነው:: ሆኖም በራሱ ሲታይ የ2010 የኤሌክትሮኒክስ ክምችት እስክ 2020 ክምችት ጋር ሲነፃር የ12 እጅ እጥፍ ጭማሪ ማሳየቱና ይህም ከሁለቱም ከተሞች የሚበልጥ መሆኑ እጅግ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው:: ስለዚህ በሀዋሳ በመጪዎቹ አመታት ከኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች በጥገና ወቅትና በየቦታው ከሚጣሉ የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎች የሚወጡ መርዛማ ኬሚካሎች መጠን ከወዲሁ መቆጣጠር የግድ ይላል:: ይህ ካልሆነ ግን መርዛማ ኬሚካሎቹ በአካባቢው ባሉት ውሃ አዘል መሬቶች፣ የመሰኖና የወራጅ ውሃ አካላትና በመጨረሻም በሀዋሳ ሀይቅ በመድረስ በብዛ ህይወት ላይና በከባቢው ነዋሪ ላይ የሚያደርሱት ጠንቅ የከፋ ነው የሚሆነው ::

## *2.3 የሆስፒታል ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ*

ከህክምና ቦታዎች የሚወጣ ፈሳሽ ቆሻሻ በአብዛኛው ከመድሀኒትና ከኬሚካል መጋዘኖች፣ ከዕዳት ሥራዎች ከህክምና መገልገያ መሳሪያዎች…ወዘተ ይመነጫል:: ይህም ቆሻሻ በውስጡ ለሰው ልጅ ጤና ጠንቅ የሆኑ ተውሳኮች፣ መርዞች ፣ፀረ ህይወት ኬሚካሎችና ሬዲዮ አክቲቭ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ያዘለ ነው ::

በሃዋሳ ከተማ በአለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ የህክምና ግልጋሎትና መገልገያዎች በከፍተኛ መጠን እያደጉና እየተስፋፉ መጥተዋል:: ሆኖም ከህክምና ተቋሞች የሚወጣውን ቆሻሻ ይዘትና መጠን በመ\ዛጥናት የተካሄደና የተመዘገበ መረጃ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ::ከዚህ አንፃር በውል የተጠናውና ለህትመት የበቃው ሥራ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ሪፈራልና የመማሪያ ሆስፒታል ላይ በተለያዩ ተመራማሪዎች (Simachew, 2008 ; Hunachew and Getachew, 2011) የተሠራው ነው:: የኋልኞቹ ሁለት ተመራማሪዎች የሪፈራል ሆስፒታሉ አምስት የተያያዙ ማጣሪያዎች የማጣራት ብቃታቸውን በገመገሙበት ጥናት የሚከተሉትን እውነታዎች አሳይተዋል::

1) ማጣሪያዎቹ በፍሳሽ ውስጥ የተቀላቀሉትን አልሚ ንጥረ ነገሮች የማጣራት ብቃታቸው ለናይትሬትና ጥቅል ናይትሮጅን ($NO_3$ & Total Nitrogen) በቅደም ተከተል 69% እና 55% ሲሆን ይህም ዝቅተኛ የሚባል ነው:: ይበልጥ ዝቅተኛ የማጣራት ብቃት የተመዘገበው ለፎስፌትና ጥቅል ፎስፈረስ ($PO_4$ & Total Phosphorus ) ሲሆን ይህም በቅደም ተከተል 2% እና 9% ብቻ ነው:: ይህም የሚያሳየው በመጨረሻ ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚለቀቀው የሆስፒታሉ

ፍሳሽ በአልሚ ንጥረ ነገሮች የበለፀገና የማይፈለግ የአልጌና የሀይቅ ዳር ተክሎች ማደግና መስፋፋት (Eutrophication) የሚያስከትል እንደሆነ ነው ::

2) ምንም እንኳን ማጣሪያዎቹ ጎጂ ባክቴሪያዎችን (total coliform and fecal coliform bacteria) የማጣራት መጠን በቅደም ተከተል 99.7% እና 99.4% ቢሆንም በመጨረሻ ወደ ሀይቁ በሚለቀቀው ፍሳሽ ውስጥ የነዚህ ሁለት ጎጂ ባክቴሪያዎች ቁጥር በቅደም ተከተል 1.95 X $10^5$ እና 7.49X$10^3$ በ 1oo ሚሊ ሊትር ነው:: ይህም ቁጥር መብለጥ የለበትም ከሚባላው 1000 ኮሊፎርም በ100 ሚሊ ሊትር የዘለለ ከመሆኑም በላይ ለሀይቁ ጠንቅ የሚያሰከትልና ለመስኖም ሆነ ለአሣ ማራቢያ ጨርሶ የማይውል ነው ::

3) የሆስፒታሉ ፍሳሽ የተሸከመውን ኦርጋኒክ ማተር በኦክሲጅን የማብላላት (oxidation) ብቃት ከፍተኛ ሲሆን በመቶኛ ሲገለጽ ለBOD እና COD በቅደም ተከተል 94% እና 87% ነው:: ይህም መጠኑን በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ለBOD እና COD ፍሳሹ ከ 632 ሚሊ.ግ በሊትር ወደ 37 ሚሊ.ግ በሊትርና ከ 1389ሚሊ.ግ በሊትር ወደ 187 ሚሊ.ግ በሊትር ያወርደዋል:: ይህ በጣም ከፍተኛ የማብላላት ብቃት ቢሆንም ወደ ማጣሪያው የሚገባው የ ኦርጋኒክ ማተር ጫና 678.7 ኪ.ግ በሄክታር በቀን ነው:: ይህ አሃዝ እንዲኖር ከሚፈቀደውም 22- 67 ኪ.ግ በሄክታር በቀን ጋር ሲነፃፀር ከ10 እስከ 30 እጅ የሚበልጥና በማጣሪያው ላይ እጅግ ከፍተኛ ጫና እንዳለ አመልካች ነው::

መርዛማ የሆኑ ሄቪ ሜታልስን በመሸከም ረገድ ወደ ማጣሪያው ገብቶ በመጨረሻ ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚለቀቀውን ፍሳሽ ይዘት በማጥናት (Hunachew and Getachew, 2011) በ2009 እና በ2010 ዓም ያለውን ጭማሪ የሚያሳየው መረጃ በገበታ 3 ቀርቧል ::

ሰንጠረዥ 3:- ወደ ሀዋሳ ሀይቅ ከሚለቀቀው ከመጨረሻ ፍሳሽ በ 2009 እና 2010 ዓም ከተወሰደ ናሙና የተገኘ የሄቪ ሜታሎች አማካይ መጠን (ሚ.ግ በሊትር) በንጽጽር የቀረበ

| ሄቪ ሜታሎች | መጠን (2009) | መጠን (2010) | ጭማሪ (እጥፍ) |
|---|---:|---:|---:|
| ካድሚየም (Cd) | 0.63 | 8.3 | 13.1 |
| ክሮሚየም (Cr) | 13.9 | 40.2 | 2.9 |
| ኮባልት (Co) | 3.3 | 14.7 | 4.5 |
| አይረ ን (Fe) | 0.31 | 2.51 | 8.11 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኒኬል (Ni) | ከሚለካው በታች (እጅግ በጣም ትንሽ) | 0.35 | - |
| ሊድ (Pb) | 3.7 | 22.8 | 6.2 |
| ዚንክ (Zn) | 0.03 | 5.62 | 204.2 |

*ምንጭ፡-* Munachew and Getachew, 2011

በገበታ 3 እንደሚታየው የሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል ፍሳሽ በማጣሪያዎቹ ገንዳዎች ካለፈ በኋላ ወደ ሃዋሳ ሀይቅ የሚገባው የሄቪ ሜታሎች መጠን በ2010 ዓም ከ3 እስከ 13 እጅ ጨምሯል:: በተለይ ዚንክ 204 እጥፍ መጨመሩና የኒኬልም መጠን በጣም ማደጉ በሀይቁ ላይ የተጋረጠውን አደጋ ያሳያል (ገበታ 6ን በቀጣይ ይመልከቱ)::

## *2.4 የኢንደስትሪ ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ*

በሀዋሳ ከተማ ያሉት ፋብሪካዎች ያሉት በከተማው ምሥራቃዊ ክፍል የኢንድስትሪ ዞን ተበሎ በተከከለው ቦታ ጎን ለጎን ተደረደረው ነው:: የእነዚህ ፋብሪካዎች ፈሳሽ ቆሻሻ በትንሹ ወይንም ጨርሶ ሳይጣራ በቀጥታ ከፋብሪካዎቹ ጀርባ ወደአለው የሻሎ ውሃ አዘል መሬት እየተለቀቀ በጥቁር ውሃ በኩል በመጨረሻ ወደ ሀዋሳ ሀይቅ ይገባል:: በኢንዱስትሪ ዞኑ በቅርብ ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች መሀል የቢራና የለስላሳ ሁለት ፋብሪካዎች ሲሆኑ ከነዚህ ፋብሪካዎች የሚወጣው ፍሳሽ በአብዛኛው የኦርጋኒክ ማተር ሊሸከም የሚችል መሆኑ ቢገመትም የፍሳሹ መጠንና ይዘት እንዲሁም በፋብሪካዎቹ ስለሚካሄደው የማጣራት ሥራ አልተጠናም:: ከተቋቋመ ብዙ አመታት ያስቆጠረውና በተለያዩ ተመራማሪዎች በተለያየ ጊዜ ከፋብሪካው የሚወጣው ፍሳሽ የተጠናው የሃዋሳ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ነው:: ፋብሪካው የሰላሳ አመታት ዕድሜ ያለውና ከፍተኛ የኬሚካልና የውሃ መጠን የሚጠቀም ነው:: ከፋብሪካው በሚወጣው ፍሳሽ ውስጥ የሚገኙ ሄቪ ሜታሎችና አልሚ ንጥረ ነገሮች አይነትና መጠን እንዲሁም በፍጡራን ላይ ፤በተለይ በሀዋሳ ሀይቅ ብዛ ህይወት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ተመራማሪዎች (Zerihun,1997; Zinabu & Zerihun, 2002; Girma 2005 ; Birnesh ,2007 ; Girma & Tigist, 2011) አሳይተዋል:: ምንም እንኳን የሀዋሳ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ፍሳሽ የያዛቸው ኬሚካሎች ፍሳሹ በሻሎ ረግረግ መሬት አልፎ ወደ ጥቁር ውሃ ሲወርድ መጠናቸው እንደሚቀንስ የሚያሳይ ጥናት ቢኖርም (Birnesh, 2007) በመጨረሻ በሃዋሳ ሀይቅ ዳርቻ በሚገኙ ዕፅዋትና የሀይቁ ሴዲሜንት እየተከማቸ እንዳለ ተረጋግጧል (Girma & Tigist, 2011) ::

ከሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሚወጣው ፍሳሽ ወደ ሻሎ ረግረግ መሬት ከመለቀቁ በፊት በማጣሪያ ኩሬዎች (biological lagoons) አልፎ የሚሄድ ቢሆንም ወደ ማጣሪያው የሚገባው ፍሳሽ ከያዛቸው ሄቪ ሜታሎችና አልሚ ንጥረ ነገሮች በበለጠ መጠን ከማጠሪያው በመጨረሻ የሚወጣው ፍሳሽ ውስጥ እንደሚገኝ በጥናት ተደርሶበታል ፤ ይህም መረጃ በገበታ 4 ቀርቧል :: ግኝቱ የሚያሳየው ፍሳሹ በማጣሪያ ኩሬዎች ሲቆይ በሚካሄደው ከፍተኛ ትነት የኬሚካሎቹን መጠን ማበራከቱ ነው ::

ሰንጠረዥ 4:- ከሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የሚወጣው ፍሳሽ በማጣሪያ ኩሬዎች (biological lagoons) ከመግባቱ በፊትና ወደ ሻሎ ረግረግ መሬት ከመለቀቁ በፊት በተወሰደ ናሙና ውስጥ የተለካ የሄቪ ሜታሎች መጠን (ማይክሮ ግራም በሊትር) ና የአልሚ ንጥረ ነገሮች መጠን (ሚሊ ግራም በሊትር)

| ሄቪ ሜታሎች[1] /አልሚ ንጥረ ነገሮች [2] | ከመግባቱ በፊት | የሚለቀቀው | ጭማሪ (እጥፍ) |
|---|---|---|---|
| አርሴኒክ (As) | 9.98 | 43.19 | 4.3 |
| ክሮሚየም (Cr) | 19.84 | 42.58 | 2.1 |
| ሜርኩሪ (Hg) | 3.77 | 5.10 | 1.6 |
| ሊድ (Pb) | 1.39 | 7.53 | 5.4 |
| ናይትሬት ($NO_3$) | 8.4 | 34.8 | 4.1 |
| ፎስፌት ($PO_4$) | 3.9 | 12.1 | 3.1 |
| ሲሊኬት ($SiO_2$) | 73.1 | 88.0 | 1.2 |
| ሰልፌት ($SO_4$) | 27.6 | 49.6 | 1.8 |

*ምንጭ*: 1 = Zinabu & Zerihun, 2002; 2 = Girma, 2005

## 3. የብክለት አደጋ በሃዋሳ ሀይቅ ብዛ ህይወት ላይ

የሃዋሳ ሀይቅ ከባህር ወለል በላይ በ1680 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል:: በሀይቁ ዙሪያው ያለው ተፋሳስ በሙሉ ከዚህ ከፍ ያለ በመሆኑ ሀይቁ በሁሉም አቅጣጫ የቆሻሻ ፍሳሽ ተቀባይ (Septic Tank) ያደርገዋል:: በቅርብ የተደረገ ጥናት (Girma & Tigist, 2011) የሀዋሳ ሀይቅ ምን ያህል በየአቅጣጫው የብክለት አደጋ እንደተጋረጠበት ያሳያል (ሰንጠረዥ 5 )::

ሰንጠረዥ 5:- በሃዋሳ ሀይቅ ዳርቻ በሴዲሜንት ተከማችቶ ያለ የሄቪ ሜታሎች መጠን (ሚሊ ግራም ሄቪ ሜታል በኪሎ ግራም ሴዲሜንት )

| ቦታው | ፍሳሹ | ሜርኩሪ (Hg) | ክሮሚየም (Cr) | ዚንክ (Zn) | ካድሚየም (Cd) | ሊድ (Pb) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንዶ ጢቃ | የእርሻ | 0.0052 | 2.05 | 32.13 | 0.027 | 0.72 |
| ጥቁር ውሃ | የፋብሪካ | 0.0068 | 9. 69 | 61.60 | 0.068 | 0.75 |
| ዩኒክ ፓርክ | የከተማ | 0.0066 | 5.69 | 58.89 | 0.021 | 1.44 |
| አሞራ ገደል | የከተማ | 0.0017 | 8.10 | 107.50 | 0.095 | 1.73 |
| ሎቄ | የእርሻ | 0.0054 | 6.86 | 71.95 | 0.018 | 1.32 |
| የማነፃፀሪያ ቦታ (Reference site) | … | **0.0011** | **1.56** | **11.40** | **0.010** | **0.59** |

*ምንጭ፡-* Girma and Tigist, 2011

ምንም እንኳን በሃዋሳ ሀይቅ ውሃ ውስጥ ያላው የሄቪ ሜታሎች መጠን በአሁን ጊዜ በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም ይህ መጠን በሀይቁ ዳርቻ ባለ ሴዲሜነት እንዲሁም በዕፅዋትና በአሣ ሰውነት ውስጥ በመከማቸት (Bioaccumlation) በምግብ ሰንሰለት ሊጎላ (Biomagnification) ይችላል:: በመጨረሻም አሣን በሚመገቡ ሰዎች ዘንድ ሲደርሱ ሄቪ ሜታሎቹ ለ ጤና ጠንቅ ሊሆኑ በሚችሉበት መጠን ሊደርሱ ይችላሉ :: ከዚህ አንፃር የተለያዩ ተመራማሪዎች (Abayneh et al., 2003, Aweke and Tadesse, 2004; Zerihun *et al*. 2007; Zenebe, 2011; Larissa *et al.* , 2012 ) በሃዋሳ ሀይቅ ባሉ አሣዎች ሰውነት ውስጥ ( ምሳሌ ስንጥብ ጡንቻና ጉበት) የሚገኙትን ሄቪ ሜታሎች (ምሳሌ:- ካድሚየም ፣ሜርኩሪ፣ ሊድ፣ ክሮሚየምና ዚንክ) ውሃ ውስጥ ካለው መጠንና ና በተለያዩ የአሣ ዝርያዎች አካል የተከማቸውን መጠን በማወዳደር ለማሰየት ሞክረዋል:: ለአብነትም ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት ተመራመሪዎች ግኝት የሚከተለውን በማቅረብ እያንዣበበ ያለውን ችግር ማሳየት ይቻላል::

1/ በትልቁ ብልጫ (large barbus) ና በትንሹ ብልጫ (small barbus) በሰው በሚበላው ጡንቻ (ፊሌት) ውስጥ የተገኘው የሜርኩሪ መጠን (በቅደም ተከተል 0.36 ና 0.27 ሚ.ግራም ሜርኩሪ በኪሎ ግራም የአሣው እርጥብ ክብደት)

በሰው ምግብ ውስጥ ሊኖር ከሚገባው የዘለለ እንደሆነ ተመዝግቧል (Zerihun *et al*, 2007) ::

2/ በቅርብ በተካሄዱት ጥናቶች (Zenebe, 2011; Larissa *et al.* , 2012) በሃይቁ ውሃና በአሣዎቹ አካል የተመዘገበው የሄቪ ሜታሎች መጠን ቀጥታ ተዛምዶ እንዳለው ለማሳየት ተችሏል:: ብክለቱ በጠነከረበት የሀይቁ ዳርቻና ውሃው ውስጥ ከፍ ብሎ የተገኘው የሄቪ ሜታል በአለበት ቦታ ያሉ አሣዎች እነዚሁ ሄቪ ሜታሎች በሰውነታቸው ውስጥ በዝተው ተገኝቷል:: በ ገበታ 6 እንደተመለከተው በጥቁር ውሃና ከአሞራ ገደል እስከ ሪፈራል ባለው የሀይቁ አካል በተወሰዱት የፍሳሽ የሴዲሜንትና የአሣ ሰውነት ናሙናዎች ውስጥ የተገኙት የተወሰኑ ሄቪ ሜታሎች መጠን (ምሳሌ ሊድና ዚንክ) ይህንን እውነታ ያንፀባርቃሉ (ገበታ 6 ን ከገበታ 3 እና 5 ጋር በማዛመድ ይመልከቱ ) ::

ሰንጠረዥ 6:- በሃዋሳ ሀይቅ ባለ የቆሮሶ (Tilapia) አሣ ጡንቻ ውስጥ የተገኙ የተወሰኑ ሄቪ ሜታሎች ክምችት


| ናሙና የተወሰደበት / የተፈቀደው መጠን | መጠን ማይክሮ ግራም በግራም የአሣው ደረቅ ክብደት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ኮፐር (Cu) | ሊድ (Pb) | ኒኬል (Ni) | ዚንክ (Zn) |
| ጥቁር ውሃ | 2.62 | 2.15 | 0.41 | 25.38 |
| ዶሬ ባፈና | 3.52 | BDL | 0.48 | 25.95 |
| ሪፈራል ሆስፒታል | 3.17 | BDL | 0.43 | 29.93 |
| የተፈቀደው ከፍተኛው መጠን | 30[a], 10[b] | 0.5[a],0.1[b] | 70-80[c] | 40[a] |

ምንጭ:- Zenebe, 2011 a= FAO/WHO (1989), b= EU (2001), c = USFDA(1993), BDL = Below detection limit

በሰንጠረዥ 6 ከተመለከተው በመነሳት ብዙዎቹ ሄቪ ሜታሎች መጠናቸው ጤናን የማይጎዳ ቢሆንም የሊድ መጠን በጥቁር ውሃ መጠኑ የዘለለ መሆኑና ዚንክ በሁሉም ቦታ ወደ ማይፈለገው መጠን እየቀረበ መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ገዳዩ የቅርብ ክትትልና (close monitoring) ተጨማሪ የማረጋገጫ ምርምር የሚያስፈልገው ነው::


**በውሃ ብዛ ህይወት ላይ ብክለት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት  በላቦረቶሪ መሪ ገንዳ** (aquarium ) **ና በምስለ ኩሬ** (experimental pond) **አስቀድሞ ማሳየት ይቻላል**:: **ይህንን ታሳቢ በማድረግ የሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፍሳሽ በሃዋሳ ሀይቅ ብዛ ህይወት** (fish fries, phytoplankton and Zooplankton) **ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለማሳየት የተለያዩ ተመራማሪዎች ሞክረዋል** (ግራፍ 1 እና 2 ፣ገበታ 7 ን ይመልከቱ)::

**ምስል**:-1 **ከሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ለተወሰደ የተለያየ የፍሳሽ መጠን** ( % dilution) **የተጋለጡ የቆረሶ ጫጩቶች የሞት መጠን** (% of mortality) (BLW = **ፈሳሽ ያልተጨመረበት** 100 % **የሃወሳ ሀይቅ ውሃ**)




ምንጭ:- Yosef, 2012 በምስል 1 እንደተመለከተው የቆረሶ ጫጩቶች የሞት መጠን ከተጋለጡበት የፋብሪካው የፍሳሽ መጠን መጨመር ጋር እንደሚጨምር ከማሳየቱም በተጨማሪ  በ 20% የፍሳሽ መጠን ከ90% በላይ የሞት መጠን ይታያል::

**ምስል:-2. ከሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ለተወሰደ የተለያየ የፍሳሽ መጠን** (% dilution) **ከ4 እስከ 5 ቀናት የተጋለጡ አልጌዎች** (phytoplankton) **የመጠነ አካል** (biomass) **ለውጥ** (BLW = **ፈሳሽ ያልተጨመረበት** 100 % **የሃዋሳ ሀይቅ ውሃ** ) -




***ምንጭ:-*** Girma 2005

**በምስል 2 እንደሚታየው በ10% የፍሳሽ መጠን የአልጌዎቹ ዕድገት ከመጀመሪያው ቀን** (Initial day) **ጋር ሲተያይ በእጅጉ መጨመሩ ይታያል:: በ20% የፍሳሽ መጠን ይህ ዕድገት በንጽጽር ቀንሷል:: ይባስ ብሎ በ30% የፍሳሽ መጠን የተመዘገበው መጠነ አካል ከመጀመሪያው ቀን ያነሰ ነው ::ይህ የሚያሳየው የሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ፍሳሽ አልሚ ንጥረ ነገሮች ስላሉት የአልጌውን መጠነ አካል በአነስተኛ የፍሳሽ መጠን** (% dilution) **ሊጨምረው ይችላል፤ ሆኖም የፍሳሹ መጠን በጨመረ ቁጥር አብረው ያሉት መርዛማ ኬሚካሎች ስለሚጨምሩ የአልጌዎቹ ዕድገት ይሰናከላል::**

ሰንጠረዥ 7:- ለሞት የሚያበቃ(ገዳይ) የመርዛማነት መጠን ጥናት (Acute toxicity test) ፣ ከሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ለተወሰደ ፍሳሽ የተጋለጡ የ"ውሃ ቁንጫ " ( "Water flea" - Daphnia bioassay ) — አማካይ የሞት መጠን/ፐርሰንት እና በቅንፍ የተመለከተ 95 % confidence interval

| የፍሳሽ ናሙና | በ24 ሰዓት 50% ሞት የተመዘገበበት የፍሳሽ መጠን | በ48 ሰዓት 50% ሞት የተመዘገበበት የፍሳሽ መጠን |
|---|---|---|
| ማቅለሚያ ሳይጨመረበት በፊት | 26. 5<br>(19.7 — 34.5) | 16.0<br>( 11.64 — 20.61) |
| ማቅለሚያ ከተጨመረበት በኋላ | 3.9<br>(1.74 — 5.96) | 1.6<br>(0.14 — 3.49) |

ምንጭ- በጸሀፊው እጅ የሚገኝ ያልታተመ ጥናት

በሰንጠረዥ 7 እንደተመለከተው ማቅለሚያ የተጨመረበት ፈሳሽ (መርዛማ ንጥረ ነገሮች በብዛትና በአይነት የያዘ ፍሳሽ) ግማሾቹን ዳፍኒያዎች በ24 ሰአት ውስጥ በ96 እጅ ንጹህ ውሃ ከመቶ በ48 ሰአት ውስጥ ደግሞ በ99.4 እጅ ንጹህ ውሃ ከመቶ ቢበረዝ እንኳን ገድሏቸዋል:: የዚህ ጥናት ትልቅ ቀም ነገር ወደ ውሃ አካል የሚገባ መርዝ ምን ያህል ለህይወት አደገኛ እንደሆነና በመበረዝ አደጋው ይጠፋል ብለው መርዝ ወደ ውሃ ለሚደፉ ትልቅ ማሳያና ማስጠንቀቂያ መሆኑ ነው::

ወደ ሀዋሳ ሀይቅ ከየአቅጣጫው የሚገባው ፍሳሽ የያዛቸው ሄቪ ሜታሎች በሀይቁ ዳርቻ ባሉ ዕፅዋት ሥርና ቅጠል ውስጥ እንደሚከማቹ የተጠና ሲሆን (Girma & Tigist, 2011) በአልሚ ንጥረ ነገሮች ወደ ሀይቁ መጨመር የተነሳ ዕፅዋቱ ወደ ራቀው የሀይቁ ክፍል እየገሰገሱና በስፋት እየተንሰራፉ መሄዳቸው በአይን የሚታይ እውነት ነው:: ይህ የዕፅዋቱ መንሰራፋትና መጠን ያለፈ ዕድገት (Eutrophication) ተደራራቢ ችግር ያመጣል:: ከዚህም ውስጥ የሀይቁን ውሃ በማትነን ዳርቻውን ማድረቅ ፣ ዕፅዋቱ በሚበሰብሱ ጊዜ የውሃውን የኦክሲጅን መጠን መሚጠጥና በሀይቁ ዳርቻ የሚራቡትንና የሚያድጉትን አሣዎች ለሞት መዳረግ ዋነኞቹ ጉዳቶች ናቸው::

## 4. ለሀዋሳ ሀይቅ የተለየ ትኩረት የመስጠትና በተቀናጀ አሠራር የመጠበቅ አስፈላጊነት

በፈጣን ዕድገት ላይ ባሉ ከተሞች አጠገብ ያሉ ወራጅ ወይንም ቋሚ የውሃ አካላት በተለያየ አቅጣጫና ተነስተው በሚመጡ የቆሻሻ አይነቶች ማራገፊያ በመሆን ይጠቃሉ:: የሀዋሳ ሀይቅ በዚህ መልክ ሰው ሠራሽ የሆነ የብክለት አደጋ በእጅጉ የተጋረጠበት ነው:: ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የዚህ ጽሑፍ አካል የአደጋውን መጠን በሳይንሳዊ ጥናት ከተገኙ መረጃዎች ማሳየት ተሞክሯል:: እነዚህ መረጃዎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡና ጉዳዩ ለነገ ይደር ከተባለ ጥፋቱ ሊቀለበስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ በአጭር ጊዜ እንደሚደረስ ያመለክታሉ ::

በኢትዮጵያ ጠንከር ያለ ግዳጅና ቅጣት የሚጥሉ የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ አዋጆች፣ ህጎችና ደንቦች በመንግሥት በተለያየ ጊዜ ወጥተዋል:: ከዋና ዋናዎቹ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር የወጣው የ1997ቱ የከባቢ ፖሊሲ፣ የ1998ቱ የውሃ ሀብት አያያዝ ፖሊሲ፣ የ2002ቱ የከባቢ ብክለትን የመቆጣጠርና የከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ፣ የ2007ቱ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ መጥቀስ ይቻላል:: ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የተሰማማችባቸውና የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ገዴታዎችም አሉ:: ከነዚህም ውስጥ የብዘሀ ህይወት ስምምነት (convention on Biological Diversity, CBD)፣በተባበሩት መንግሥታት የበረሃ መስፋፋትን ለመዋጋት ስምምነት (convention to combat Desertificatio, CCD)፣ በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳትና ዕፅዋት አለማቀፋዊ ንግድ (International Trade in Endangered species of fauna and flora) እና ሌሎችም የበካይና ለህይወት አደገኛ የሆኑ መርዛማ ኬሚካሎች ድንበር ዘለል ዝውውር መቆጣጠርን ለመቀበልና ለመተግበር የተካሄዱ ስምምነቶች ናቸው::

የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ አዋጆች ህጎችና ደንቦች ከመውጣት በሻገር አስፈፃሚ አካላትን ባልተማከለ አቀራረብ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ፈጥሯል:: ይህንን ታሳቢ በማድረግ የከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን (EPA) በፌዴራል ደረጃ፣ የመሬት አስተዳዳር አጠቃቀምና የከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን (LAUEPA) ደግሞ በክልል ደረጃ በአዋጅ የተቋቋሙ ሲሆን እነዚህ መ/ቤቶች ባለጉዳይ አካላትንና የከባቢ ጥበቃ ሥራ የሚመለከታቸውን ሌሎች የሴክተር መ/ቤቶች የማስተባብርና የማቀናጀት ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል::

በእርግጥ አካባቢን የመጠበቅ ሥራ አሽጋሪና ውስብስብ ቢሆንም ሁሉም ሰው መኖር ስለሚፈልግ ለህልውና ሲባላ መደረግ አለበት:: በዚህም ሂደት ከዳር ቆሞ የሚያይ መኖር ስለሌለበት ሀብትን፣ ጉልበትና ችሎታን አቀናጅቶ ከመሥራት

ውጪ ሌላ የተሻለ አማራጭ የለም:: ከዚህ አንፃር  በሀዋሳ ከተማና በሀዋሳ ሀይቅ ዙሪያ እያደገ በመሄድ  ላይ ያለው የብክለት አደጋና  በተፋሰሱ ላይ የሚታየው መጎሳቆል ጊዜ ሊሰጠው አይገባም:: የከተማው የደረቅና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና ቁጥጥር በጣም ተጠናክሮ ካልተካሄደ የከፋ ጉዳት ለማየት ብዙ የሚያስጠብቅ አይሆንም:: ይህ እንዳይሆን ደግሞ ሁሉን አቀፍ፣ ማህበረሰብ አሳታፊ የሆነና የተቀናጀ ሥራ ማካሄድ ይጠይቃል::  የሚካሄደውም እንቅስቃሴ የሀዋሳ ሀይቅንና የዙሪያውን ተፋሰስ ያማከለ መሆን ይኖርበታል፤ ምክንያቱም የሀዋሳ ከተማ ህልውናንና ውበትን  ከሀዋሳ ሀይቅና ከዙረያው ተፋሰስ ነጥሎ ማየት ባለመቻሉ ነው::

በሀዋሳ ከተማ የሚካሄደው የቆሻሻ  አያያዝና የአካባቢ ጥበቃ ከከተማዋ ፈጣን እድገት ጋር ተመጣጣኝና እጅግ ዘመናዊ መሆን አለበት:: ስኬታማ ሥራ ለመሥራት ህብረተሰቡን በስፋትና በማይቋረጥ መንገድ ማስተማርና ማነሳሳት ያስፈልጋል:: በተለያየ ጊዜ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የወጡትን  የብክለት፣ የቆሻሻ አያያዝና የሌሎች የአካባቢ ጥበቃ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን በስፋት ማስተዋወቅና መተግበር ያስፈልጋል:: አካባቢን በካዮች በአጠፉት መጠን  በህግ መቅጣት ያስፈልጋል:: በተቃራኒው ለአካባቢያቸው ጥበቃ ተጨማሪ ወጪና ጉልበት ለሚያፈሱ ግለ ሰቦች፣ አምራችና ሰርቪስ ሰጪ ድርጅቶች  የተለየ ዕውቅና፣ ሽልማትና ማበረታች ሊሰጣቸው ይገባል::

በአጠቃላይ በሀዋሳ ከተማና በሀዋሳ ሀይቅ ዙሪያ እያደገ በመሄድ ላይ ያለው የብክለት አደጋና በተፋሰሱ ላይ የሚታየውን መጎሳቆል በዘላቂነት ለመፍታት ከንግግርና ከውይይት ባሻገር መሬት ላይ የሚታይ ሥራ መሰራት አለበት:: ይህንንም በአስተማማኝ መንገድ ከዳር ለማድረስ ክኮሚቴና ከግብረ ሀይል የአንድ ሰሞን ሥራ በዘለለ ተከታታይና ዘላቂ የብክለትና ቁጥጥርና የተፋሰስ ልማት የሚሠራ ነፃ አካል (Independent body ) መፈጠር አለበት::

## ዋቢ መጻህፍት

Abayneh Ataro, Tadesse Wondimu ., & Chandravanshi, B. S. (2003). Trace metals in selected fish species from lakes Awassa and Ziway, Ethiopia. SINET: Ethiopian Journal of Science,26, 103–14.

Aweke Kebede , & Tadesse Wondimu (2004). Distribution of trace elements in muscle and organs of Tilapia, Oreochromis niloticus, from lakes Awassa and Ziway, Ethiopia. Bulletin of the Chemical Society of Ethiopia, 18, 119–130.

Derje Diriba(2009) . Household solid waste generation rate, composition and content analysis for disposal and resource recovery in two selected kebles of Hawassa town. MSc Thesis. Addis Ababa University. 82 pp

EU (European Union),(2001). Commission Regulation as regards heavy metals, Directive, 2001/22/EC, No: 466FAO/WHO, (1989). Evaluation of certain food additives and the contaminants mercury, lead and cadmium, WHO Technical Report, Series No. 505

Girma Tilahun (2005). Effect of textile effluent on the different phytoplankton class size of Lake Hawassa: The case of Hawassa Textile Factory. A paper presented on international conference on applied phycology – Kunming (China). July 2005.

Girma Tilahun and Tigist Amare (2011). Heavy metals accumulation by aquatic macrophytes from Lake Hawassa, Ethiopia: Phytoremediation for water quality improvement. A paper presented on international conference on ecosystem conservation and sustainable development. Ambo University. Feb. 2011

Hunachew Beyene and Getachew Redaie (2011). Assessement of waste stabilization ponds for the treatment of hospital waste water. The case of Hawassa University Hospital. World Applied Sciences Journal 15(1): 142 – 150

Larissa, D.; Mesfin Mengesha; Elias Dadebo; Carlos E.V.; and Seven S. ( 2012). Assessement of heavy metals in water samples and itissues of edible fish species from Awassa and Koka rift valley lakes , Ethiopia. Environ. Monit. Assess. Published on line. 22 July 2012. Springer.

Lemma Asfaw (2007). Household solid waste generation rate and composition analysis in two selected Kebeles of Adama . MSc Thesis. Addis Ababa University. 63 pp

Melakamu Tegegn (2008). Household solid waste generation rate and physical composition analysis in Jimma town, Ethiopia. MSc Thesis. Addis Ababa University. 43 pp

Nigatu Regassa, Rajan. D.S., and Bizunesh Bogale ( 2011). Challenges and opportunities in municipal waste management : The case of Addis Ababa City, Central Ethiopia. J.Hum,Ecol.33(3): 179 – 190.

Pan Action Nexus Association ( PAN – Ethiopia) (2011). E – waste inventory in four cities of Ethiopia: Bahir Dar, Dire Dawa, Hawassa and Addis Ababa. 260 pp

Simachew Dires (2008) . Characterization of waste water composition from hospital effluent and evaluation of the treatment performace of the five series of oxidation ponds in Hawassa Referral Hospital. MSc Thesis. Addis Ababa University. 68 pp

USFDA, (1993). Food and Drug Administration. Guidance Document for Nickel in Shellfish. DHHS/PHS/FDA/CFSAN/Office of Seafood, Washington, D.C.

Yosef Tekele Giorgis (2012). Effect of factories effluent on the biota of Lake Hawassa. A paper presented on Regional conference organized by Hawassa City Council .

Zenebe Yirgu (2011) Accumaltion of certain heavy metals in Nile Tilapia (*Oreochromis niloticus)* fish species relative to heavy metal concentrations in the water of Lake Hawassa. MSc Thesis. Addis Ababa University. 63pp.

Zerihun Desta (1997). Industrial Environmental management: The case of Awassa Textile Factory, Ethiopia. MSc. Thesis. Wegningen Agricultural University (WAU), the Netherlands.

Zerihun Desta, Borgstro.R, Roseseland .B.O. and Elias Dadebo (2007) Lower than expected Mercury concentration in Piscivorous African sharptooth Cat fish *Clarias gariepinus* ( Burchell) from Lake Awassa , Ethiopia. Sci. Total.Environ. 376(1-3): 134 – 142.

Zinabu Gebre – Mariam and Zerihun Desta (2002). The chemical composition of the effluent from Awassa Textile factory and its effect on aquatic biota. SINET: Ethiop. J. Sc., 25(2): 263 – 274.

# ሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በፌደራልና በአዲስ አበባ ደረጃ

*አትክልት አሰፋ*

## 1. *መግቢያ*

*የህዝብ አገልግሎት የመንግሥት የማስፈፀሚያ አካል ሲሆን በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ትንተና የማድረግ፣ መከናወን ስለሚገባቸው ጉዳዮች ሃሳብ የመስጠት እና የማስፈፀም ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በዚህም ማዕከላዊ ሚና ምክንያት ብዙ ሁኔታዎች ማለትም ታሪክ፣ ፖለቲካ እና ፍልስፍና/ እምነት እና ሌሎች ጉዳዮች የሕዝብ አገልግሎት ተግባራትንና አደረጃጀቱን ይወስናሉ፡፡*

*በኢትዮጵያ የደርግ መንግስት በግንቦት* 1991 *መውደቅ የሁሉም ቀውሶች ማብቂያ የተበሰረበት ወቅት ነበር፡፡ ከሐምሌ* 1991 *እስከ ነሐሴ* 1995 *ድረስ የሽግግር መንግስቱ በኋላም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሀገሪቷን ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ከተዘፈቀችበት የማህበራዊ ችግሮች ለማላቀቅ ጥረት አድርገዋል፡፡*

*ውጤታማ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ባለፉት ሃያ ሁለት ዓመታቶች ውስጥ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል፣ ሀ) ዲሞክራሲያዊ የሆነ የመንግስት ቅርፅ ማስተዋወቅ፣ ለ) በፌደራል የአደረጃጀት መስመር መንግስትን እንደገና ማደራጀትና ሥልጣንን ለክልሎች ማከፋፈል፣ ሐ) ከዕዝ ኢኮኖሚ ወደ ገበያ መር ኢኮኖሚ መሸጋገር፣ እና መ) ሁሉን አቀፍ የህዝብ አገልግሎት ሪፎርምና የፍትህ አካላት ሪፎርም፣ የሚሉ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ለውጦች የዲሞክራሲ ሂደቱንና መልካም አስተዳደሩን ለማጠናከር ግልፅነት፣ ስነ-ምግባርና ተጠያቂነትን አስመልክቶ መሠረታዊ መሻሻልን ይጠይቃሉ፡፡*

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

*ወደ ገበያ ተኮር ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግር የህዝብ አገልግሎቱን መሠረታዊ ሚና በዘላቂነት የሚቀይር ነው፡፡ ስለሆነም በመንግስት ስትራቴጂ መሠረት የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሪፎርሞች የሚከተሉትን ያካትታል፤ ሀ) የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ሥልጣን ወደታችኛው እርከን የማስተላለፍ፣ ለ) የሕገ-መንግስት ሪፎርም፣ ሐ) የኢኮኖሚ ሪፎርም እና መ) የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ባለሀብቶች ማስተላለፍ*

ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የህዝብ አገልግሎት ዘርፉን ለማዘመን በ14 ጉዳዮች ላይ የብሔራዊ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ቀርጾ እንቅስቃሴ መጀመሩ ቁርጠኝነቱን ያመለክታል፡፡ ስለፕሮግራሞቹ ወደፊት ባሉት አንቀጾች ይብራራል፡፡
አሁን ካለው አጠቃላይ የሪፎርም ተሞክሮዎች እንደሚስተዋለው ውጤታማ፣ ብቃት ያለውና ዝግጁ የሆነ የተቋማት አሰራርን/ አደረጃጀትን ለማስረፅ/ለማስተዋወቅ ሰፊ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ይህ ፍላጎት ከፌደራል መንግስቱ አስፈፃሚ አካል አልፎ ሁሉንም የመንግስት አካላት- አስፈፃሚ፣ ህግ አውጪና ህግ ተርጓሚ እንዲሁም የክልልና የወረዳ ተቋሞችና የምጣኔ ሀብት ወይም የማህበራዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የተደራጁትን የሲቪል ማህበረሰብ አደረጃጀቶችን ይጨምራል፡፡

የሕዝብ አገልግሎት ሪፎርም ጉዳይ ከክፍያ ሪፎርምና አደረጃጀቶችን ከማሻሻል ጋር ከተያያዙ ፍላጎቶች ላቅ ያለ ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ጉዳዮች በህዝብ አገልግሎት ሪፎርም ውስጥ የሚነሱ ጉዳዮች ቢሆኑም፣ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ አይደሉም፡፡ ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት የመንግስትን መዋቅሮች የማስተካከል፣ የህዝብ አገልግሎቱን በተገቢው መጠን የማስቀመጥና የደመወዝ ማሻሻያዎችን አስመልክቶ ስራዎች ቢከናወኑም፣ የመልካም አስተዳደሩን ለማጠናከር ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል ከከፍተኛ ተሳትፎ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማለትም ግልፅነትና ተጠያቂነት በውሳኔ አሰጣጥ እስካሁን ድረስ እልባት ያላገኙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሪፎርሞች ዋና ዓላማ መንግስት በአስተዋይነት አገልግሎቱን እንዲወጣና ተግባርና ኃላፊነቱን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲያከናውንና በየጊዜው እየተወሳሰበና እየተደበላለቀ የሚታየውን የህገሪቷ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችል ስርዓት ለመገንባት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ዋናው ጉዳይ የመንግስትን አቅም በማሳደግ ወደ ገበያ ኢኮኖሚና ዲሞክራሲያዊ መልካም አስተዳደር መሸጋገር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት

የጥናቱ አስፈላጊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በከተማ የህዝብ አገልግሎት የሚስተዋለውን ሥነምግባርና ተጠያቂነት እንዲሁም የሪፎርም እንቅስቃሴዎች ውጤታማነትን አስመልክቶ ግንዛቤው ይጨምራል፣
- አሁን ባለው አሠራር ላይ መሻሻል ስለሚገባቸው የፖሊሲ ጉዳዮች ተገቢውን ግብዓት ይሰጣል፣

- በከተማ የህዝብ አገልግሎት የተገኙ ተሞክሮዎችን ለግሉ ዘርፍና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በትምህርት መልክ ያስተላልፋል፣

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

"የስነ-ምግባርና ተጠያቂነት በከተማ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ" በሚል የቀረበው ርዕስ እንደ አንድ የአቅም ግንባታ ሂደት አካል ተገቢና ጥናት ሊካሄድበት የሚችል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ በሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት ዙሪያ ያሉ መሠረታዊ ጉዳዮችን ለመመርመርና በተግባራዊው ዓለም ያሉትን ጉዳዮች ለመዳሰስ ነው፡፡

የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፖሊሲ፣ የሕግና የተቋማት አቅም ክፍተትን ለመለየት፣
- ውጤታማና ብቃት ያለው የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ያሉ የሥነ-ምግባርና የተጠያቂነት ጉዳዮችን ለመዳሰስ፣
- የልማት አቅምን ለመገንባት በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍና በሲቪል ማህበረሰብ መካከል የሚኖረውን ሁሉን አቀፍ ትብብር ለማጠናከር፣

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት አሁን ያለውን የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በተለይም በአዲስ አበባ-የፌደራል መንግስቱ ዋና ከተማ፣ ላይ በማተኮር ሚዛናዊ ዳሰሳ በማካሄድ፤ የስነ-ምግባርና የተጠያቂነት ጉዳዮችን ይበልጥ ትኩረት በመስጠት የህዝብ አገልግሎትን ማዕከል በማድረግ የሚስተዋሉ የሙስና አደጋዎች ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ /ስልት

በጥናቱ ዙሪያ የተዳሰሱ ጉዳዮችን ለማካተት እንዲቻል የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የመረጃዎቹን በቂነትና ተአማኒነት በተመለከተ፣ በቅርብ ጊዜ የተሰሩ የጥናት ውጤቶችን በማጠናቀር እንዲሁም ጥናቱን በአግባቡ ለማሟላት በማሰብ ተገቢ የሆኑ ፅሁፎችን ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

### 1.6 የጥናቱ ውስንነት

የጥናቱ ዋና ውስንነት ሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት በሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ ለማድረግና መጠይቆችን ለመበተን ወይም የተወሰኑ ሰዎችን ለማወያየት ባለው የጊዜ እጥረት ምክንያት ማከናወን አልተቻለም፡፡ ጉዳዩን አስመልክቶ ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማከናወን አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በቅርብ ጊዜ በተሰሩ ጥናቶች ላይ የቀረቡ ግኝቶች ላይ ሲሆን የዚህም ምክንያቱ የሥነ-ምግባርና የተጠያቂነት ልምዶች ሁላችንንም የሚመለከቱና የሚሰሙን በመሆኑ ነው፡፡

### 1.7 የጥናቱ አቀራረብ

የጥናቱ የመጀመሪያ ክፍል መግቢያውን ጨምሮ ዳራ፣ አስፈላጊነቱ፣ ዓላማ፣ ወሰኑ፣ ስልት እና የጥናቱ ውስንነት በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ጥናቱ ይዞት ስለተነሳው ችግር የሚያብራራ ነው፡፡ በሶስተኛው ክፍል የስነ-ምግባር ንድፈ ሀሳቦች እና ፅንሰ ሀሳቦች ማለት የስነ-ምግባር ትርጉም፣ ተጠያቂነት፣ የህዝብ አገልግሎት እና በአብዛኛው ተቀባይነት ያለው የተጠያቂነት መንገዶች የተገለፁበት ነው፡፡ ስለ ህዝብ አገልግሎት በተለይም ስለሪፎርምና ስለተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች ከክፍል አራት እስከ አስራ አንድ ባሉት ውስጥ እንዲመለከት ተደርጓል፡፡ የሙስና ስጋት በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በክፍል አስራ ሁለት የተመለከተ ሲሆን በክፍል አስራ ሶስት ደግሞ የሰው ሃብት ሥራ አመራር ስትራቴጂ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በክፍል አስራ አራት ደግሞ በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በተጨባጭ የታዩ ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆኑ ልምዶች ተመልክተዋል፡፡ በክፍል አስራ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያና መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ተመልክቷል፡፡

## 2. ጥናቱ የሚያነሳው ችግር

ሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት አሳሳቢ ጉዳይ የሆነው መንግስት የሕዝብ አገልግሎቱን ከላይ በተጠቀሱት እርምጃዎች ዘመናዊ ለማድረግ ካለው ቁርጠኝነት ስለሚነሳ ነው፡፡ ይህንንም ይበልጥ የሚያጠናክረው መንግሥት የሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት ጉዳዮችን ምላሽ ለመስጠት ጉዳዩን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም አንዱ አካል በማድረግ ብቃት ያለው፣ ታማኝና የህዝብ አገልጋይነትን የተላበሰ የህዝብ አገልግሎት ለመፍጠር በማሰቡ ነው፡፡

ሆኖም የስነ-ምግባር ጉዳዮች አከራካሪ ናቸው፡፡ በየሚዲያው ዋና ርዕስ ሆነው የሚቀርቡት ጉዳዮች ትላልቅ መረዎችን የሚያሳፍርና ህዝቡንም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ክርክሮች ይሰነዘራሉ፡፡ በአንድ በኩል ሥነ-ምግባራዊ ያልሆኑ ተግባራት ምንጭ የአቅም ችግሮች ናቸው የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቅጡ ያልወጡ የህግ ወይም የፖሊሲ መሳሪያዎች እና የተቋማት ደካማነት በምክንያትነት ይቀርባሉ፡፡

ሆኖም የሥነ-ምግባርና የተጠያቂነት ጉዳዮች በሕዝብ አገልግሎት ዋናው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ሥነ-ምግባራዊ ያልሆኑ ተግባራትና የተጠያቂነት መላላት በሀገሪቱ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የባህል ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ስለዚህ ለጉዳዩ በአግባቡ ምላሽ ለመስጠት በተናጠል የተወሰኑ ጉዳዮችን ለይቶ እርምጃ ከመውሰድ ባሻገር ሥነ-ምግባርን ባልተከተሉ መሠረታዊ ተግባራት ለምሳሌ፣ ጉቦ፣ በዘመድ መስራት፣ ሕግና ደንብን መጣስ፣ በጎሳ/በብሔር ላይ የተመሠረተ አድሎኝነት፣ የመንግስት የስራ ጊዜን ለሌላ ጉዳይ ማዋል፣ ግለኝነት ወይም ሙስና ላይ በአጠቃላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ስለሆነም ለእነዚህና ተያያዥ ጉዳዮች ትልቅ ትኩረት መስጠት የወቅቱ አጀንዳ ከመሆኑም በላይ የአቅም ማጎልበቱን ሥራ ለማጠናከር ይረዳል፡፡

## 3. የሥነ-ምግባር ንድፈ-ሃሳቦች፣ ጽንሰ-ሃሳቦችና የተጠያቂነት መሣሪያዎች ሥነ-ምግባር

ዌብስተር መዝገበ ቃላት የግሪክ ቃል የሆነውን Ethics (በአማርኛ ሥነ ምግባር ብለን ያቀረብነውን) ሥነ-ምግባር በሚከተለው መልኩ ይገልፀዋል፡፡ "ሥነ-ምግባር የጥናት ዘርፍ ሆኖ የሚያጠናውም ጥሩ እና መጥፎ የሆነውን እንዲሁም የሞራል ግዴታና ኃላፊነትን፣ የሞራል መርሆዎች ወይም እሴቶች፣ የንድፈ ሃሳብ ወይም የሞራል እሴቶች ስርዓት፣ አንድን ግለሰብ ወይም ቡድንን ለማስተዳደር ልንጠቀምባቸው የሚገቡ የአሰራር መርሆዎችን ነው፡፡"

በሌላ በኩል ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ ሥነ-ምግባርን በሚከተለው መልኩ ገልፆታል፡፡ "ሥነ-ምግባር እሴቶችን፣ ሀሳቦችን ማለትም ጥሩ፣ ይገባል፣ ትክክለኛ፣ ስህተት፣ ወ.ዘ.ተ… እና ለማናቸውም ሁኔታዎችና ጉዳዮች ተግባራዊ ልናደርጋቸው የሚገቡ አጠቃላይ መርሆዎችን ስርዓት ባለው ሁኔታ የማጥናት ነው፡፡"

በቻንድለርና ፕላኖ የህዝብ አስተዳደር መዝገበ ቃላት (1982) መሠረት ሥነ-ምግባር ማለት የአንድ መስሪያ ቤት ወይም የሥራ አመራር ሙያ ባልደረቦች የሞራል አሰራራቸውን አስመልክቶ የሚተዳደሩበት ሕጎች ወይም መለኪያዎች ናቸው፡፡ በሞራል ፍልስፍና ውስጥ ሥነ-ምግባር ‹‹የፍልስፍና አካል ሆኖ የሰው ልጅ ስለሚፈፅማቸው ድርጊቶች ትክክለኛነት ወይም ስህተት፤ ድርጊቶችን ለመፈፀም የሚያነሳሳው ምክንያት ጥሩነት ወይም መጥፎነት እና የድርጊቶቹ የመጨረሻ ግቦችን በተመለከተ ያሉ እሴቶችን ይዳስሳል፡፡

ሥነ-ምግባር ሲገለጽ ስለአንድ ጉዳይ መታየት ያለበት ባህሪይ ወይም ደንብ ሆኖ ጥሩ ወይም መጥፎ፣ ትክክል ወይም ስህተት የሚለውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሥነ-ምግባር አንድን ሥራ ለመስራት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ለራሳቸው ያስቀመጧቸው የሞራል መለኪያዎች ሆነው አንድን ባህሪ ትክክል ወይም ስህተት ብለው የሚገልፁባቸው ናቸው፡፡

አራቱ የሥነ-ምግባር ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው፣

ሀ) **አሻሚነት** (Relativism)

- ሞራልን የምንመዝንበት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው መለኪያ የለም፣
- ለአንድ ማህበረሰብ ትክክል የሆነው ለሌላው ስህተት ሊሆን ይችላል፣
- ሥነ-ምግባርና ሞራል አሻሚዎች ናቸው፣

ለ) **የአሻሚነት ችግሮች**

- ፍፁማዊ የሆኑ ነገሮች የሉም፤ ባንድ የታሪክ ወቅት ግድያ፣ ባርነት፣ ማሰቃየት፣ አስገድዶ መድፈር ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ማህበረሰብ ወይም ከማህበረሰብ በታች ስንል ምን ማለታችን ነው?
- የእያንዳንዱ ሰው አስተያየት ትክክል ነው ወደሚል የማጠቃለያ ነጥብ ያመራል፡፡
- ማንም ሰው የሚሰራው ስራ በሞራል ደረጃ ስህተት ነው ማለት አይቻልም፡፡

ሐ) **ራስ ወዳድነት** /Egoism/

- ማንም ሰው የራሱን (የራሷን) ፍላጎት መሠረት አድርጎ ያከናውናል፣
- የራስን የግል ፍላጎት የሚያሟላ ማናቸውም ድርጊት እንደ ሥነ-ምግባር ባህሪይ ይቆጠራል፣
- ይህ ሃሳብ ህጎችን ማክበር የለብህም አይልም፡፡ ሆኖም ማናቸውም ድርጊቶች የሚፈፀሙት የራስን የግል ፍላጎት ሲያሟሉ ብቻ ነው፡፡

## መ) የራስ ወዳድነት ችግሮች

- ከማናቸውም የግል ድርጊቶች ጋር በተያያዘ አንዱ የፈፀመው ድርጊት በሌላው ላይ የሚያሳድረው ጥቅም ወይም ጉዳት ሳይታይ ትክክል ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ፣ እስካልተያዙ ድረስ ጉቦኛ ሆኖ መቀጠል፣

## ሐ) እስከጠቀመ ጊዜ ድረስ መሥራት (Utilitarianism)

- የአንድ ድርጊት የሞራል ሁኔታ የሚወሰነው በውጤቱ ነው፣
- አንድ ድርጊት ሥነምግባራዊ የሚሆነው ለአብዛኛው ማህበረሰብ የሚጠቅም ሥራ ሲሆን ነው፣
- ጥቅሙና ጉዳቱን መመዘን፣

## ሠ) እስከጠቀመ ጊዜ ድረስ የመሥራት ችግሮች

- ጥቅምና ጉዳቶችን በምን መልኩ ቆጥረህ ዋጋ ትሰጣቸዋለህ?
- ፍትሃዊ ወዳልሆነ ውጤት ሊያመራ ይችላል
- የአነስተኛውን ማህበረስብ ፍላጎት ለማሟላት የብዙሃኑን ፍላጎት መገደብ እስከጠቀመ ጊዜ ድረስ የመሥራት ሃሳብ አይደለም

## ረ) ለሁሉ የሚሆን (Universal)

- ግለሰቦች የወዷያውኑን ውጤት ዋጋ ሳይሰጡ የተወሰኑ እሴቶችን ለምሳሌ፣ ታማኝነት አጠናክረው ሊይዙ ይገባል፣
- አስፈላጊ እሴቶች የሚባሉት ማህበረሰቡ መደበኛ ተግባሩን እንዲያከናውን የሚረዱት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ሰዎች ሁልጊዜ ታማኝ መሆን አለባቸው፡፡ ያለበለዚያ ግን ግንኙነቱ ይበላሻል፡፡

**ቀ) ለሁሉ የሚሆን የሚለው አስተሳሰብ ችግሮች**

- ሁሉም የማህበረሰቡ አባሎች ታማኝ ናቸው ወይ? አስፈላጊ የሆኑት እሴቶች የትኞቹ እንደሆኑ ይረዱታል?
- ሌሎቹ የሥነ-ምግባር ሃሳቦች ይህንን ይቃረኑታል፣

***የሥነ-ምግባር ሙከራዎች/ ፈተናዎች***

*ማናቸውም አስቸጋሪ/ ምስቅልቅል ጉዳዮች በሚከተሉት የሥነ-ምግባር ሙከራዎች/ ፈተናዎች ላይ ያጠነጥናሉ፡፡*

- ***ይህ ሥነ-ምግባራዊ /ሕጋዊ ሙከራ/ፈተና ነው?፣***
  *ሀ) ሥነ-ምግባራዊና ሕጋዊነት፣ ለ) ሥነ-ምግባራዊና ሕገ-ወጥነት*
  *ሐ) ኢ-ሥነ-ምግባራዊና ሕጋዊነት መ) ኢ-ሥነ-ምግባራዊና ሕገወጥነት*
- ***የጥቅምና ጉዳት ሙከራ/ፈተና***
  *ጥቅሙ ጉዳቱ አንፃር ለማንም ቢሆን ይበልጣል?*

- ***‹ካቶጎሪካል ኢምፔሬቲቭ›***
  *ሁሉም ሰዎች የታሰበውን ድርጊት እንዲፈፅሙ ፈቃደኛ ነህ? ወይም ልዩ ጉዳይ እንዲሆን ትፈልጋለህ?*

- ***የቀን ብርሃን* (Light of Day) *ሙከራ/ፈተና***
  *ድርጊቱ ለህዝብ ምርምራ ክፍት ቢሆን ኖሮ ምላሽህ ምን ሊሆን ይችል ነበር?*

- ***በሌሎች ላይ የምትሰራውን በራስህ ላይ አድርግ / በአንተ ላይ እንዲሰራብህ የማትፈልገውን በሌሎች ላይ አትስራ፣ ወርቃማው ህግ***
  *ሌሎች በአንተ ላይ ተመሳሳይ ነገር እንዲፈፅሙ ትፈቅዳለህ ወይ? ይህ ሙከራውን/ፈተናን ያልፋል*

- ***‹የቬንትሌሽን› ሙከራ/ፈተና***

የሌሎችን አስተያየት/ሀሳብ መሻት፤ ከላይ የተመለከቱትን አምስት ሙከራዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ተወያይ፤ ሌሎቹ ጥሩ ስሜት ከተሰማቸው ሙከራውን/ፈተናውን አለፍክ ማለት ነው፡፡

### የሥነ-ምግባር ባህሪይ /ድርጊት

በመንግሥት ዘርፍ አሠራርና የድርጅት ዓላማ ላይ የበለጠ ተፅዕኖ የሚኖረው የሥነ-ምግባር ባህሪይ/ድርጊት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሥነ-ምግባርና የመልካም አስተዳደር አስፈላጊነት እየጎላ በመምጣቱ፤ የድርጅት ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ከግምት ውስጥ የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ይህ በቀጥታ ትክክለኛ ከመሆን ወይም ካለመሆን ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ አንድ ድርጅት/ተቋም ኢ-ሥነምግባራዊ የሆኑ ውሳኔዎችን በመስጠት ስሙ የታወቀ/የገነነ ከሆነ ድርጅቱ ትልቅ አደጋ እንደተጋረጠበት ተቋም ከመታየቱም በላይ የተቋሙ ሠራተኞችም ሆኑ አበዳሪዎች፣ አቅራቢዎችና ሸሪኮች በድርጅቱ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

ድርጅቶችን የተመለከቱ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች በሦስት ደረጃ ይገኛሉ፣

- **በብሔራዊ ደረጃ፣** በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ የድርጅቱ ሚና እና ይህም ትኩረቱ የተለያዩ የፖለቲካ/የማህበራዊ ሥርዓቶችን አንፃራዊ ጥቅም የመዳሰስ፣ ለምሳሌ፣ በማዕከላዊ ዕቅድ የሚመሩ የምጣኔ ሃብቶችና የገበያ ተኮር ድርጅቶች፣
- **በተቋም ደረጃ፣** እያንዳንዱ ድርጅት ስትራቴጂውን ሲቀርፅና ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያጋጥመው የሥነ-ምግባር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፣
- **በግለሰብ ደረጃ፣** በድርጅት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የሚያሳዩት ባህሪና ድርጊቶችን ይመለከታል፣

### የሥነ-ምግባር አስቸጋሪ ሁኔታ

የሥነ-ምግባር አስቸጋሪ ሁኔታ የሚከሰተው አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ የሞራል ችግር ሲገጥመውና ትክክለኛ ወይም ስህተት የሚለውን ለመለየት

ሲቸገር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚከተሉት ምሳሌዎች የድርጅት መሪዎች የሚገጥማቸውን ችግሮች ያሳያሉ፣

- ❖ አንድ ሰው በሞራል ደረጃ ትክክለኛ ነው ብሎ ያሰበውን የማህበራዊ ሥነ-ምግባር ሲያከብር ከሕጎች ጋር መጋጨቱ፣
- ❖ አድሎአዊነት ወይም አሳፋሪ ድርጊቶች በብዝሃነት ሥራ አመራር ጉዳዮች፣
- ❖ ልጆችን ወይም እርጉዝ ሴቶችን መቅጠር፣
- ❖ በቀላል ሁኔታ የአካባቢ ህግን ለመፈፀም መዘጋጀት ወይም ከሚጠበቀው በላይ መስራት፣
- ❖ ሰዎች ጉቦ ሲሰጣቸው ምን ሊያደርጉ ይገባል?
- ❖ ሰዎችን ከስራ መቀነስ ሲያስፈልግ እና አንዳንድ ሰዎች እንዲቀነሱ ሲደረግ፣
- ❖ ስለ አገልግሎት ደህንነት ወይም ስለሠራተኞች የተሳሳተ መረጃ መስጠት፣

### የሥነ-ምግባር አቋሞች

ጆን ስኮልስና ዊቲንግቶን የሥነ-ምግባር አቋሞችን በሚከተለው መልኩ ይገልፁታል፡፡ ‹‹ድርጅቱ ለባለድርሻ አካላት ከዝቅተኛው ግዴታ በላይ እስከምን ድረስ ሊሄድ ይችላል››፡፡ አራት የሥነ-ምግባር አቋሞች አሉ፣

❖ **የአጭር ጊዜ የባለድርሻ አካላት/መንግስት ፍላጎት**
በበጀት ዓመቱ ጥቅሞችን በተቻለ መጠን ከፍ ለማድረግ ማለም፣

❖ **የረጅም ጊዜ የባለድርሻ አካላት /መንግስት ፍላጎት፣**
ወደፊት ለሚገኘው ከፍተኛ ትርፍ አሁን ተጨማሪ ወጪዎችን ማውጣት፣

❖ **የብዙ ባለድርሻ አካላት ግዴታ**
የሁሉንም የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

❖ **የማህበረሰብ ቀራጭ** /Shaper of Society/

ከድርጅቱ ዓላማ አንፃር የገንዘብና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ፍላጎት በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ መሆኑ፣

### ሥነ-ምግባርን የተከተለ ድርጅት ጥቅሞች

ሥነ-ምግባርን የተከተለ ድርጅት ከመሆን ባሻገር፣ ትክክለኛ የሆነ ሞራልን መከተል በቁጥር ሊገለፁ የሚችሉ ጥቅሞች አሉት፣

- ዝቅተኛ የሆነ አደጋና የተረጋጋ ወይም ታማኝ የሆነ ሁኔታን መፍጠርና የገንዘብ /የበጀት መኖር፣
- ለደንበኞች ወይም ለባለድርሻ አካላት ተመራጭ መሆን፣
- ለወደፊት ተቀጣሪ ሠራተኞች ተመራጭ መሆን፣
- ለወደፊት ተባባሪዎችና አጋሮች ተመራጭ መሆን፣
- በተቆጣጣሪ ድርጅቶች በሚካሄደው ምርመራ የሚጠፋው ጊዜና ገንዘብ ማነስ፣
- ለጉዳቶችና ለመቀጮ የሚወጣው ገንዘብ ማነስ፣

### የተቋም ማህበራዊ ኃላፊነት

የተቋም ማህበራዊ ኃላፊነት አንድ ድርጅት ለባለድርሻ አካላት በደንቡና በተቋሙ መልካም አስተዳደር በተመለከተው መሠረት ከገባው ዝቅተኛ ግዴታ በበለጠ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስቀምጣቸውን መንገዶች/አቅጣጫዎችን ይመለከታል፡፡

ምንም እንኳን የትኛው ድርጊት ሥነ-ምግባራዊ ወይም ኢ-ሥነ-ምግባራዊ የሚለው ላይ ልዩነት ቢኖርም፣ አንዳንድ ሰዎች እንደሚከራከሩት የድርጅት ስነ-ምግባር ለምሳሌ ታማኝነት፣ በበጎ ፈቃድ የሚከናወን ነው፡፡ ሆኖም የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነትን በተመለከተ በግልጽ የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ የተለያዩ አመለካከቶች ይስተዋላሉ፡፡

### የባለሀብቶች አመለካከት (ለትርፍ ለተቋቋሙ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች አግባብነት አለው)

ሚልተን ፍሬድማን እንደሚከራከረው ‹የቢዝነስ ማህበራዊ ኃላፊነት ትርፍ ማግኘት ነው›› ይላል፡፡ ለዚህ ነጥብ የሚያነሳቸው መከራከሪያ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ትርፍ ማግኘት ቅጥርን ይጨምራል፣ የምጣኔ ሀብት እድገትን ያመጣል፣ ፈጠራን ያበረታታል፣ የታክስ ገቢን ይጨምራል፣

በአጠቃላይ የመኖር ደረጃን ያሻሽላል፡፡ ስለዚህ ትርፍ በራሱ የሕዝብ ንብረት ነው፡፡ ለንግድ ሥራም በቂ የሆነ ዓላማ ነው፡፡

- ዳይሬክተሮች የባለአክሲዮኖች/የመንግስት ወኪል በመሆን ተግባራቸውን መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ማለት ዳይሬክተሮች በሌሎች ሰዎች ገንዘብ ላይ ቸር የሚሆኑበት ነው፡፡
- የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ትርፍ/የትርፍ ድርሻ ክፍፍል እንደፈለጋቸው መጠቀም ስለሚችሉ ከፈለጉ ለተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ሊያውሉት ይችላሉ፣
- የንግድ ድርጅት የሞራልና የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን ለመወሰን አቅም የለውም፣

## የረጅም ጊዜ የራስ ፍላጎት አመለካከት

ፒተር ድራከር እንደሚከራከረው የድርጅቱን የረጅም ጊዜ የምጣኔ ሀብት ፍላጎቱን ለማሟላት ኃላፊነቱን በጠበቀና ምክንያታዊ በሆነ አካሄድ ድርጊቱን መፈፀሙ ተገቢ ነው፡፡

- ይህንን በአግባቡ አለማከናወን የሕግ ለውጥን ሊያስከትል ይችላል፣
- ይህንን በአግባቡ አለመስራት ድርጅቱን እንዲሁም የሥራ ዘርፉን ሊያዳክም/ጉዳት ሊያደርስበት ይችላል፣
- ተቋሙ ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣቱ የሚገኝ የሕዝብ ግንኙነት እንዲሁም ዕውቅናና ሙገሳ በረጅም ጊዜ ሂደት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ስለዚህ የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት የረጅም ጊዜ ጥቅሞችን ለማግኘት የሚከፈል ወጪ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## የባለድርሻ አካላት አመለካከት

ይህ አመለካከት ከብዙ የባለድርሻ አካላት መካከል ባለአክሲዮኖች/ መንግስት አንዱ በመሆኑ ፍላጎታቸው ሁልጊዜ ላቅ ያለ/ በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የባለአክሲዮኖች/ የመንግስት ፍላጎት በሌሎች የባለድርሻ አካላት ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል፡፡

የትኛው የባለድርሻ አካል የተሻለ ድጋፍ ሊያገኝ እንደሚገባ ውሳኔ የሚሰጥበት የአወሳሰን ሁኔታ ግልጽ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ አደጋ የሚሆነው ተጠቃሚ የሚሆነው የባለድርሻ አካል በአብዛኛው ኃይል ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የባለድርሻ አካላትን ላይጨምር ይችላል፡፡

ድርጅቶች የሚሳተፉባቸው የተለመዱ የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ጉዳዮች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፣

- የሥራ ዕድልን የመፍጠርና የሥልጠና ፕሮግራሞች፣.
- የሥዕልና የስፖርት ፕሮግራሞችን መደገፍ፣
- የሠራተኞች የደህንነት ፕሮግራም፣
- ለትምህርት ተቋማት ድጋፍ ማድረግና ከድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣
- የውጭ እርዳታ መስጠት፣
- የአካባቢ ፕሮግራሞች

አርቼ ካሮል አራት የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ሞዴሎችን ያዘጋጀ ሲሆን እነሱም፣ የምጣኔ ሀብት፣ ሕጋዊ፣ ሥነ ምግባር እና የበጎ አድራጎት ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ በመነሳት ካሮል የሚከተለውን የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ትርጉም አስቀምጧል፡፡ ‹የተቋም የማህበራዊ ኃላፊነት ማህበረሰቡ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ከተቋሙ የሚጠብቃቸው የምጣኔ ሀብት፣ የሕግ፣ የሥነ-ምግባርና የበጎ ፈቃደኝነት ጉዳዮችን የሚያካትት ነው፡፡›

- **የምጣኔ ሀብት ኃላፊነት፣** የባለአክሲዮኖች/መንግሥት ያልተጋነነ ትርፍ፡ ለሠራተኞች ደህንነትና ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የደንበኞችን የጥራት ፍላጎት ማሟላት፣
- **የሕግ ኃላፊነት፣** በማህበረሰቡ ውስጥ ሥራን ለማከናወን ሕጉ አንድ የመነሻ ነጥብ ነው፡፡ ለድርጅቱ ሥራዎች ተቀባይነት ያገኘ የሕግ መፅሐፍ ነው፡፡
- **የሥነ ምግባር ኃላፊነት፣** ትክክለኛ፣ ልክና ተገቢ የሆነ ሥራ መስራት፣ ከምጣኔ ሀብትና ከሕጋዊ ኃላፊነት በተጨማሪ ማህበራዊ ተቀባይነትን እንደገና ማረጋገጥ፣

- **የበጎ አድራጎት/የነፃነት ኃላፊነት፣** የሰዎችን ኑሮ ለማሻሻል የነፃነት ባህሪይ፣ የበጎ አድራጎት ስጦታዎች፣ የመዝናኛ ቦታዎችን፣ የሥዕልና የስፖርት በዓላትን ወጪ መሸፈን፣

የማህበራዊ አገልጋይነት ከድርጅቱ አቅም ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ለማህበራዊ ግፊቶች ምላሽ ለመስጠት ካሮል የሚከተሉትን አራት ስትራቴጂዎች አቅርቧል፣

- **ጉዳዩ ሲመጣ ምላሽ መስጠት** (Reaction)፣ ለማህበራዊ ጉዳዮች ያለንን ኃላፊነት መካድ፣
- **መከላከል** (Defense)፣ ኃላፊነትን መቀበል ግን ጉዳዩን በተቻለ መጠን መዋጋት፣
- **መቀበል** (Accommodation)፣ ኃላፊነትን መቀበልና በሚጠይቀው መሠረት መፈጸም፣
- **ቀድሞ መሄድ (Pro-action)**፣ ከሕዝብ አገልግሎት አሠራሮች ወጣ ብሎ መሥራት፣

ስለዚህ በመልካም የተቋም አስተዳደር ላይ የባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ በተለይም የማህበራዊ ኃላፊነት ፍላጎት እንዲጨምርና በተቋሙ እንዲኖር ለማድረግ፣

- **የሥነ ምግባር ተጠያቂነት፣** የውስጥ የሥራ አመራር ሥርዓቶችንና የአሠራር ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- **የአካባቢ ተጠያቂነት፣** በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያለው ተፅዕኖ፣
- **የማህበራዊ ተጠያቂነት፣** የሠራተኞች ሁኔታ፣ የጤና እና የደህንነት፣ እኩል ዕድሎች፣
- **የቀጣይነት ተጠያቂነት፣** ሦስቱንም ጉዳዮች ማለትም ሕዝብ፣ መሬትና ትርፍን ከአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ጋር ማዛመድ፣

**የተቋም የሕዝብ መንፈስ (Corporate Citizenship)**

የተቋም የሕዝብ መንፈስ ሰፋ ያለ የተቋም ሚናን የሚገልፅ ሲሆን በቀጥታ ከሚኖረው የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ወጣ ባለ ሁኔታ ማየትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ከተቋም ተጠያቂነት ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም ማለት

ተቋሙ ለሚፈጽማቸው ማናቸውም ተግባራት ከባለድርሻ አካላት ጋር ካለው ግንኙነት ውጪ ተጠያቂ የሚሆንበት ነው፡፡

ኮርፖሬሽኖች/ድርጅቶች የበለጠ ተጠያቂ እንዲሆኑ ፍላጎቶቹ የመጡትና አዲሱን ሚና እንደማናቸውም የማህበረሰብ አባላት እንዲቀበሉት የሚያስገድዱት ሁኔታዎች የተከሰቱት ከሁለት ምንጮች ነው፡፡

❖ *የመንግስት አለመቻል*

ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ የሆኑ አደጋዎች፣ በፖለቲካ በጎፈቃድ ላይ የኤሌክትሮኒክስ ተፅዕኖ፣ ከችግሩ ጋር የተያያዙ አደጋዎች፣ ያለውን የሕይወት ስልት መቀየር አለመቻል፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች፣ ለምሳሌ፣ የግሪንፒስ እንቅስቃሴ በፖለቲካ በጎ ፈቃድ የሚያስከትለው ስጋት፣

❖ *የተቋም ሥልጣን*

በገበያ የሚመራ ስርዓት፣ የመንግስት ድርጅቶችን ለግል ባለሀብቶች መሸጥ፣ የሥራ ዕድል እጦት (ሥራ አጥነት)፣ በተቋም ተግባራት እና የገንዘብ ድጋፍ የመንግሥት ተሳትፎ አለመኖር፣ ውስብስብ ድንበር ተሻጋሪ የሕግ ስምምነቶች፣

የድርጅት ሥነምግባርን በማስተዳደር ሂደት ውስጥ የሥነምግባር ድርጊቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች፣

- የበላይ ኃላፊዎች ባህሪይ፣
- የአንድ ኢንዱስትሪ/ዘርፍ ወይም ሙያ የሥነ ምግባር ልምዶች/ተግባራት፣
- በድርጅት ውስጥ ያለ የጓደኝነት ባህሪይ፣
- የድርጅት ፖሊሲ ወይም የፖሊሲ አለመኖር፣
- የግለሰብ የገንዘብ ፍላጎት፣

የሥነ -ምግባር ጉዳዮችን በተመለከተ ምላሽ የሚሰጥባቸው ደረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታል፣

- ❖ **በግለሰብ ደረጃ፣** በግል ህይወት ውስጥ ያጋጠሙ ሁኔታዎች/ጉዳዮች፣
- ❖ **በድርጅት ደረጃ፣** የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች የሚያጋጥሟቸው የሥራ ቦታ ሁኔታዎች፣

- **በኢንዱስትሪ/በዘርፍ ደረጃ፣ በሙያ ደረጃ ያጋጠሙ ሁኔታዎች/ጉዳዮች፣**
- **በማህበረሰብ እና በአለም አቀፍ ደረጃ፣** ከአካባቢ እስከ አለምአቀፍ ደረጃ ያጋጠሙ ሁኔታዎች፣

**ሰንጠረዥ 1: የኮልበርግ የማሰብ የሞራል ዕድገት ደረጃዎች (Kohlberg Levels of Cognitive Moral Development)**

| የማሰብ የሞራል ዕድገት ደረጃዎች | ማብራሪያዎች | ምሳሌዎች በድርጅት/በሕዝብ አገልግሎት |
|---|---|---|
| 1.1. ቅድመ መደበኛ<br>❖ መታዘዝና ቅጣት | በሥልጣን ላይ ባሉ አካላት ትክክለኛ ወይም ስህተት የሚለው ከተጓዳኙ ሽልማት እና/ወይም ቅጣት ጋር ተገልጿል:: | ኢሥነምግባራዊ ውሳኔዎች ይወሰዳሉ፣ ምክንያቱም ሠራተኞቹ ይሸለማሉ ወይም ድርጅቱ ላይቀጣቸው ይችላል ብለው ያስባሉ:: |
| 1.2. ቅድመ መደበኛ<br>❖ የዓላማዎች መሳሪያነትና ልውውጥ | ትክክለኛ የተባለው የተገለፀው በልውውጥ ሂደት ውስጥ ተገቢ አካሄድ አለ ተብሎ በማሰብ ነው:: ስለዚህ ግለሰቦች የራሳቸውን የግል የቅርብ ፍላጎቶች ላይ ያተኩራሉ:: | አንድ ሠራተኛ ለቀረው ጓደኛ ይሸፍንለታል:: ይህም የሚሆነው እሱ በሚቀርበት ሰዓት ጓደኛው እንደአስፈላጊነቱ ስለሚሸፍንለት ነው:: ስለዚህ ሠራተኞቹ ሥራቸውን የሚያከናውኑት ጥቅም ስለሚሰጣቸው ብቻ ነው:: |
| 2.1. መደበኛ<br>❖ የግለሰቦች ስምምነትና ስርዓቱን መከተል | ድርጊቶች የሚገለፁት የቅርብ የሥራ ባልደረቦች ወይም ጓደኛሞች ከሚጠብቁት አንፃር ነው:: | አንድ ሠራተኛ ለግሉ በድርጅቱ ስልክ እና ኢንተርኔት ሲጠቀም የሚያቀርበው ምክንያት ሁሉም ሠራተኞች ይህንን ስለሚያደርጉ ነው ይላል:: |
| 2.2.መደበኛ<br>❖ የማህበራዊ ስምምነት እና ስርዓትን መጠበቅ | ድርጊቶች የሚገለፁት በማህበራዊ ስርዓት እንጂ በቅርብ የሥራ ባልደረቦች አይደለም | አንድ የሥራ ኃላፊ የሥራ ሁኔታዎችን ከዝቅተኛው ወደ ሌላው ደረጃ የሚያሸጋግረው የቅርብ የሥራ ባልደረቦች፣ ደንበኞችና ሌሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ቡድኖች ከሚጠብቁት አንፃር ነው:: |
| 3.1. ድህረ መደበኛ<br>❖ ውልና የግለሰብ መብቶች | ትክክል እና ስህተት የሚወሰኑት ከመሠረታዊ መብቶች፣ እሴቶችና በማህበረሰቡ ወስጥ ባሉ ውሎች ነው:: | አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ በምርቱ ውስጥ ያሉትን ተፈላጊ አካላት በይፋ ያስቀምጣል፣ ምንም እንኳን በህግ የተቀመጠ መስፈርት ሳይኖር እና ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ቡድኖች የዚህ ዓይነት መረጃ ሳይጠይቁ ነው:: |
| 3.2. ድህረ መደበኛ<br>❖ ዓለም አቀፋዊ የሥነ ምግባር መርሆዎች | ግለሰቦች ውሳኔ የሚሰጡት ራሳቸው በመረጧቸው ሁሉም ሰዎች ሊከተሏቸው ይገባቸዋል ብለው በሚገምቱት የሥነምግባር መርሆዎች ነው:: | የግዢ ሥራ አስኪያጁ በእንስሳት ላይ የተሞከረ ምርቶችን ላይገዛ ይችላል:: ምክንያቱም ሙከራው እንስሳት ከጉዳት ነፃ የመሆን መብት የማያስከብር በመሆኑ ነው:: |

**ምንጭ፡** ACCA-Professional Accountant, pp. 281-283

## ተጠያቂነት

በዴል ኦሉዎ (1993) መሠረት ተጠያቂነት ማለት የሕዝብን እምነት የተቀበሉ መሪዎች/ባለስልጣኖች ለዜጎች ወይም ለተወካዮቻቸው ስለተጠቀሙበት እምነት ምላሽ የሚሰጡበት አሰራር ነው፡፡ ተጠያቂነት የሕዝብ ፍላጎት ከግል ፍላጎቶች የበላይ መሆኑን እንደሚያሳይና ይህም በማናቸውም እንቅስቃሴ እንዲሁም በመንግስት ባለስልጣን አሠራር ላይ የሕዝብ ፍላጎት የበላይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው፡፡

በአስተዳደር ሁኔታ ተጠያቂነት የሚያያዘው የሥርዓቱን ተያያዥ ሕጎችና ደንቦች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ነው፡፡ ይህም በአመራር ቦታዎች ላይ የሚገኙ ማህበረሰቡ የሚያስቀምጣቸውን ሥነ ምግባር፣ ጥሩ፣ ተገቢ ወይም የሞራል እሴቶች የሥራቸው አካል እንዲያደርጉት ይጠይቃል። በሌላ በኩል የሕዝብ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኞችና ሥራ አስኪያጆች አንዱ ተፈላጊ ጉዳይ ለሠሩት ሥራ ተጠያቂ የመሆን ነው፡፡ ይህ ሃሳብ በብዙ ምሑራንና የተግባር ሰዎች የሚሰበክ ነው፡፡

## ተጠያቂነትና አስፈላጊነቱ

የሕዝብ አገልግሎት የመንግስትን የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የአስተዳደር ፖሊሲዎች የማስፈፀም ከፍተኛ ሥልጣን አለው፡፡ ይህ ተግባራዊ የሚሆነው የሚመለከታቸው የመንግሥት ኃላፊዎች ሥልጣናቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉት ነው፡፡ ስለሆነም ፖሊሲዎችን በተገቢው መንገድ መተርጎማቸውንና መተግበራቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥርዓቶችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

መንግስት ለመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ ካልሆነ፣ ሥራውን በግልፅ፣ በታወቀና በተጠያቂነት መንገድ ማከናወን አይችልም፡፡ መንግስት አንዴ ተጠያቂ ካልሆነ፣ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ልምዶች ማለትም የጥቅም ግጭት፣ ጉቦ የመቀበልና የመስጠት፣ የመንግስትን ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል፣ የመንግስትን ንብረት ያለአግባብ መጠቀም፣ የምግብና ሌሎች እርዳታዎችን ለተገቢው ተጠቃሚዎች ሳይሆን ለሌሎች መስጠት፣ ጉዳይ ያለባቸውን ፋይሎች ማጥፋትና የፍትህ ሂደቱን ማበላሸት/ማሰናከል፣ ሥልጣን ያአግባብ መጠቀም፣ ያለመስራት፣ ሥራን ችላ ማለት፣ ሕግና ደንበኞችን ከቁብ አለመቁጠርና ወ.ዘ.ተ… ይስፋፋሉ፡፡ ሥነ ምግባርና ተጠያቂነት የሚደጋገፉ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ሥነ-ምግባር ለተጠያቂነት መሠረት የሚሰጥ ሲሆን፣ የተጠያቂነት ፅንሰ ሃሳብና ተግባር የመንግስት ኃላፊዎች ለወሰዷቸውና ላልወሰዷቸው እርምጃዎች ኃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ ነው፡፡ ሥነ-ምግባር የመንግሥትን ግልፅነት የሚጨምር፣ የመንግስትን ተደራሽነትና

አገልጋይነት ከፍ የሚያደርግና ሕጋዊ ዕውቅና የሚሰጥና የፖሊሲ አፈፃፀምን የሚያሻሽል ነው፡፡

ሆኖም በአጠቃላይ የመንግሥት ዘርፍ (የመንግስት መስሪያ ቤቶች) ኃላፊዎች እና ሥራ አስኪያጆች ለሕዝቡ ተጠያቂነታቸው የደከመ/ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠያቂ ለመሆን ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ ተቋማት (Watchdog) ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም ተቋማት ተጠያቂነትን ለማስፈን ሰፊ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የተቋማቱ አሰራር የተለያየ ሲሆን ይህም በሦስት ይከፈላል፣ የውስጥ ቁጥጥር፣ የውጪ ቁጥጥር እና መደበኛ ያልሆነ የግል ቁጥጥር ናቸው፡፡ በተመሳሳይም የተጠያቂነት ዓይነቱ ከፖለቲካዊ፣ ከሕጋዊ፣ ከገንዘብና ከሞራል አንፃር ሊታይ ይቻላል፡፡ ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ ተቋማት ምሳሌዎች በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፣ ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ ተቋማት በዲሞክራሲያዊ ሀገራት**

| የውስጥ ቁጥጥር | ሕግ አውጪውን መሠረት ያደረገ | አስፈፃሚውን መሠረት ያደረገ | የፍትሕ አካላትን መሠረት ያደረገ | ልዩ ልዩ |
|---|---|---|---|---|
| 1. የሲቪል ሰርቪስ ህጎች/ደንቦች(የፋይናንስ ትዕዛዞችን ይጨምራል) | 1. የሕግ ሰነዶችን ማመንጨትና ማፅደቅ | 1.የሚኒስቴር መ/ቤት ቁጥጥር | 1.ፍርድ ቤቶች | 1.የመገናኛ ብዙሃን |
| 2.ሥልጠና(መደበኛና መደበኛ ያልሆነ፣ ውጤታማ ቁጥጥርን ይጨምራል) | 2.በጀት የመገምገምና የማፅደቅ | 2.በጀት (ማዘጋጀት፣ መተግበርና መከታተል) | 2.ክፊል የፍትህ አካላት ለምሳሌ፣ የምርመራ ኮሚሽን፣ የአስተዳደር ፍ/ቤቶችና ሌሎች ልዩ ተቋማት ለምሳሌ የሕዝብ/የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 2.ተፅዕኖ ፈጣሪ /የፍላጎት ቡድኖች |
| 3.የዲሲፕሊን/የግምገማ ስርዓት | 3.በሕዝብ የሂሳብ ኮሚቴ ኦዲት ማካሄድ | 3.ለከፍተኛ ቦታዎች መታጨትና ግምገማ | 3.የሥነ-ምግባር ደንብ እና የማስፈፀሚያ ተቋማት | 3.የፖለቲካ ፓርቲዎች |
| 4.ተቆጣጣሪዎች/ኢንስፔክተሮች | 4.የከፍተኛ ቦታዎችን ምደባ ማጽደቅ<br>5.ያለአግባብ የመንግስት ሥልጣን መጠቀምን መመርመር የመንግስት ባለሥልጣንን በሕግ መሠረት ማባረር | - | - | 4. ምርጫ |

**ምንጭ፣** Ethics and Accountability in African Public Services, Page 224

የተለያዩ የተጠያቂነት አሠራሮች ስንገመግም፣ ከውስጥ ተቋማት መካከል የሲቪል ሰርቪስ ህጎች ደንቦች፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ሥልጠናዎች፣ የዲሲፕሊን መመሪያዎችና ተቆጣጣሪዎች ይገኙበታል፡፡

**ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ ተቋማት (Watchdog Institutions)**

በእኛ ሀገር ሥነ-ምግባርንና ተጠያቂነትን የሚከታተሉ የውጪ ተቋማት የሚከተሉትን ይጨምራል፣

- ሕግ አውጪውና በስሩ ያሉ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፣
- የሕዝብ የሂሳብ ኮሚቴ፣
- የፌደራል የዋናው ኦዲተር መ/ቤት፣
- የፌደራል የሥነ ምግባና የፀረ ሙስና ኮሚሽን፣
- የፌደራል ዕምባ ጠባቂ ተቋም፣
- የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣
- ፍርድ ቤቶች፣
- የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች፣
- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣
- የመገናኛ ብዙሃን፣
- ተፅዕኖ ፈጣሪ ቡድኖች፣
- የፖለቲካ ድርጅቶች፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣

አንዳንዶቹ መሥሪያ ቤቶች ከሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ውጪ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ከሕዝብ አገልግሎት ውጪ የሆኑ ለምሳሌ፣ መገናኛ ብዙሃንና ተፅዕኖ ፈጣሪ ቡድኖች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ይይዛል፡፡ በተቻለ መጠን ውጤታማ ለመሆን ሁለቱ መንገዶች እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ ሥራቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡

## 4. የሕዝብ አገልግሎት አጭር ዕይታ

የሕዝብ አገልግሎት በኢትዮጵያ ከዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በአፄ ኃይለስላሴና በደርግ ሥርዓት የቀጠለ ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡

አሁን ያለው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 691/2010 ሲሆን ይህም ሁለት መ/ቤቶችን ማለትም የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር እና የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲን በማዋሃድ የተዋቀረ ነው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋና ዓላማ የሜሪት ስርዓትን መሠረት ያደረገ ብቃት ያለው፣ ውጤታማ የሆነና ዘላቂነት ያለው ሲቪል ሰርቪስ እንዲኖር ማድረግ ሲሆን በሲቪል ሰርቪስ የተካተቱ መሠረታዊ ሕጎቹና ደንቦቹ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

- የመንግስት ሠራተኞች ደንብ ቁጥር 1/1961፣
- የመንግስት ሠራተኞች የሥራ ምደባና የደመወዝ ደረጃ ደንብ ቁጥር 2/1972፣
- የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 264/2002፣
- የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/2007፣

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባላሰለሰ የረጅም ጊዜ ትግል የሚከተሉትን ዋና ዋና ሥራዎች አከናውኗል፡፡

- ሁሉም የሲቪል ሰርቪስ የሥራ መደቦች ምደባ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ደመወዞችና አበሎች በማዕከል እንዲወሰኑ ተደርጓል፡፡
- ለሁሉም የተመደቡ የሥራ መደቦች ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ ተቀምጧል፡፡
- የምልመላ፣ የዕድገትና የደመወዝ ጭማሪ ጉዳዮችን በአብዛኛው የሜሪት ሥርዓትን ተከትሎ ተፈፅሟል፡፡
- ትምህርት፣ የሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀም ለደረጃ ዕድገትና ለደመወዝ ጭማሪ ዋና መስፈርቶች ናቸው፡፡
- በሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች አንድ ወጥ የሆነ የዲሲፕሊን መመሪያ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የመንግስት ሠራተኛው ለማዕከላዊ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ የማለት መብቱ የታወቀ ነው፡፡
- በማዕከላዊ ደረጃ የፐርሶኔል ውሳኔዎችን ከሲቪል ሰርቪስ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አንፃር መፈፀማቸውን ለመከታተል ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፡፡
- የመንግሥት ሠራተኞችንና ሥራ አስኪያጆችን አቅምና ችሎታ/ክህሎት ለማዳበርና ለማሻሻል ሥልጠና ይካሄዳል፣

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የዘመናዊ አስተዳደር ዋና ወኪልና ተምሳሌት በመሆን ተመሳሳይ የሆነ ዘመናዊ አሰራሮች መተግበራቸውን ለማረጋገጥ

ሰፊ ሥራ መስራት ይኖርበታል፡፡ ከተለምዶአዊ ወደ ዘመናዊ አስተዳደር የሚደረገው ሽግግር በተቃውሞና በአለመግባባቶች የተወጠረ ነው፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ሃላፊነቶች ጨምረዋል፡፡ ዛሬ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አንድ ወጥ በሆኑ ሕጎች የሚመራ ብቸኛ የፌደራል መንግሥት ተቋም ሲሆን ከጊዜ ወደጊዜ ብዙ መስሪያ ቤቶች በሕግና በደንቦች መሠረት ለመስራት በስሩ እየተካተቱ ይገኛሉ፡፡

## 4.1 አሁን ያለው የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሁኔታ

### የሰው ኃብት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ሠራተኞች ማለት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ በኮሚሽኖች፣ በሕዝብ አገልግሎት ባለስልጣኖች፣ በመንግስት ኤጀንሲዎች፣ በኢንስቲትዩቶችና በማዕከሎች እና በሌሎች የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም የክልል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ ሠራተኞችን ያጠቃልላል፡፡ ሆኖም ከመንግስት ሠራተኛ ክልል ውጭ ከሆኑት መካከል የጦር ሠራዊትና የፖሊስ አባላት፣ በሕግ በተወሰነው መሠረት ዳኞች፣ የፓርላማ አባላት፣ ከዳይሬክተር/ከመምሪያ ኃላፊ ወይም ተመሳሳይ ደረጃ በላይ ያሉ የመንግስት ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሠራተኞች፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች፣ ጊዜያዊ፣ ወቅታዊና የኮንትራት ሠራተኞች ይገኙበታል፡፡

### ዋና ተግባራት

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የኮሚሽን፣ የመንግስት ባለሥልጣኖች፣ ኤጀንሲዎች፣ ኢንስቲቲዩቶች እና ሌሎች የመንግሥት አካላት የሚያከናውኗቸው ዋና እና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- የፌደራል መንግስቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
- የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል፣ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣

- ለክልል አስፈፃሚ አካላት እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፣

- ሚኒስትሮችን ያማክራል፣ ፖሊሲዎች ሲዘጋጁ ወይም ውሳኔዎች ሲሰጡ ምክር ይሰጣል፣ የአስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል፣ የአስተዳደር ሥርዓቱን ይመራል፣

## 5. የሕዝብ አገልግሎት ሪፎርም ፕሮግራም

በሀገሪቱ የለውጥ ማዕቀፍ ውስጥ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም ጀምሯል፡፡ እነሱም፣ 1) የፋይናንስ ወጪና ሥራ አመራር፣ 2) የሰው ኃብት ሥራ አመራር፣ 3) የአገልግሎት አሰጣጥ፣ 4) የበላይ ሥራ አመራር ሥርዓት እና 5) ሥነ-ምግባር፣ ናቸው፡፡

በኋላም ሁሉን አቀፍ የሆነ ብሔራዊ የሕዝብ አገልግሎት አቅም ግንባታ ሪፎርም ፕሮግራም የሚከተሉትን 14 አካባቢዎችን የያዘ ነው፡፡

1) የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም፣
2) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና - የግብርና ፕሮግራም፣
3) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና - ግብርና ነክ ያልሆኑ ፕሮግራም፣
4) የከፍተኛ ትምህርት ሪፎርም ፕሮግራም፣
5) የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም፣
6) የፍትህ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራም፣
7) የወረዳ ያልተማከለ አስተዳደር ፕሮግራም፣
8) የሕብረት ሥራ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣
9) የጨርቃ ጨርቅና ልብስ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣
10) የታክስ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራም፣
11) የከተማ ሥራ አመራርና ልማት አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣
12) የሲቪል ማህበረሰብ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣
13) የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ልማት ፕሮግራም፣
14) የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም በሀገሪቱ የሚካሄዱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የአስተዳደር ሪፎርም ፕሮግራሞች አካል ሲሆን እነዚህም ፕሮግራሞች የሀገሪቱን አቅም ለመገንባትና የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ የልማት ግቦች እና ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲሁም ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ያለሙ ናቸው፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም መተግበር የጀመረው በ1996 ነበር፡፡ የሲቪል ሰርቪሱን ብቃትና ውጤታማነት የሚገድቡ ጉዳዮችን አስመልክቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት ህዳር 1994 በተቋቋመ የሲቪል ሰርቪስ ጥናት ግብረሃይል አማካኝነት ጥናት ተካሂዶ ሪፖርት መቅረቡ ይታወሳል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም የቅርብ ጊዜ ዓላማ በግብረ-ሃይሉ የቀረቡ የሲቪል ሰርቪስ ሥራ አመራር ችግሮችና ደካማ ጎኖች ላይ ምላሽ መስጠት ነበር፡፡ በመሆኑም ግብረ-ሃይሉ አምስት ቁልፍ አካባቢዎችን ለይቷል፡፡ በዚህ ረገድ የተገኙ ልምዶችን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

**የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም**

1. የበላይ ሥራ አመራር ሥርዓት
2. የወጭ አስተዳደርና የቁጥጥር ማሻሻያ
3. የሰው ኃይል አስተዳደር
4. የአገልግሎት አሰጣጥ እና
5. የሥነ-ምግባር ማሻሻያ

**ቀጣይነት ላለው የሪፎርም ፕሮግራም በዋናነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች**

የኢትዮጵያ ልምድ እንደሚያሳየው የሚከተሉት ዋና ጉዳዮች የሪፎርም ፕሮግራሙ ቀጣይነት እንዲኖረው አስችለዋል፡፡

**ሀገር በቀል ሪፎርም፣** መንግስት አጀንዳውን በማስቀመጥ በፌደራል እና በክልል ደረጃ ያሉ የመንግስት ሠራተኞች ተሳትፎ ያደረጉበትና ችግሮቹን ለመለየትና ምላሽ ለማስቀመጥ ቁርጠኝነት አሳይተውበታል፡፡

**ቁርጠኝነት፣** በትልቅ ደረጃ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳየታቸው እንዲሁም የሽግግር መንግሥቱና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሲቪል ሰርቪሱን ሪፎርም ተግባራዊ ለማድረግ የሰጠው ትልቅ ድጋፍ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነበር፡፡

**ራዕይ፣** የኢትዮጵያ መንግስት ሀገሪቷ የምትፈልገውን ሲቪል ሰርቪስ ቀድሞ ከነበረው የተለየ መሆኑን በማስረገጥ የወደፊቱን ራዕይ አስቀምጧል፡፡ በዚህም የመንግስት አዲሱ ሚናን፣ መወሰድ ስለሚገባቸው ዝርዝር

እርምጃዎች በተለይም ምን መለወጥ እንዳለበትና እንዴት የሚሉትን የሚያካትት ነበር፡፡

**በሪፎርሞቹ መካከል ያለው ትስስር**፣ የሕዝብ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል መንግሥት መሠረታዊ ለውጦችን እና የፖሊሲ መሳሪያዎችን ቀርፆ ተግባራዊ ማድረጉን እና እነዚህም ለውጦች ከሕገ-መንግስት ሪፎርም፣ ያልተማከለ አስተዳደር፣ የኢኮኖሚውን ሁኔታ ለማረጋጋት የተካሄደ የምጣኔ ሀብት ሪፎርም እንዲሁም የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል የማዛወር እርምጃዎች ትስስሩን የበለጠ ማድረጋቸው፣

**ዝቅተኛ የሠራተኛ ክፍያ**፣ ዝቅተኛ የሠራተኛ ደመወዝ መጠንን ለመወሰን እጅግ በጣም ልዩ ጉዳይ መሆኑንና የክፍያ ጥያቄውም በሚገኘው የገንዘብ መጠን እና በመንግሥት የመክፈል አቅም የሚወሰኑ ናቸው፡፡ የቀድሞው የደመወዝ ስኬል በተለያዩ ጊዜያቶች የተሻሻለ ቢሆንም የደመወዝ ጥናት ዳሰሳ የማካሄድና ያለውን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ስርዓት መገምገም ዋነኛ ተግባር ይሆናል፡፡

**የአገልግሎት አሰጣጥን መለማመድ**፣ በውጤት ተኮር የሥራ አመራር ላይ በማተኮር "የሲቪል ሰርቪስ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ" በ2001 መውጣቱ ይታወሳል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም የሕዝብ አገልግሎት ተቋማት እንደ አንድ የትራንስፎርሜሽን መሳሪያ የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ አካሂደዋል፡፡

**ሥነ-ምግባር፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት**፣ የኢትዮጵያ መንግስት ጠንካራ የሆነ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም ቁርጠኝነቱን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በሕዝብ አገልግሎት የሚታዩትን ሙስናዎች ለመግታት ልዩ ልዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

**የለጋሽ አገራት ድጋፍ**፣ የሕዝብ አገልግሎት ዘርፍ አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ተገቢ የሆነ፣ የተቀናጀ ወቅታዊ ድጋፍ በዓለም ባንክ የተደረገ ሲሆን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም ደግሞ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም አማካኝነት ይደገፍ ነበር፡፡ ሌሎች የባይላተራልና መልቲላተራል ለጋሾች ለሪፎርም ፕሮግራሞች ውጤታማነትና ቀጣይነት ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል፡፡

እስከ 2001 ድረስ ትኩረት የተሰጠው የተለያዩ ስልቶችን/መንገዶችን በመጠቀም ወቅታዊ፣ ብቃት ያለው፣ ውጤታማ፣ ሙያዊ፣ ውጤት ተኮር የሆነና በሞራል የታነፀው የሕዝብ አገልግሎት ለመገንባት ነበር፡፡ እነዚህም፣ 1) ተገቢ የሆነ ሕግና የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና መተግበር፣ 2) የተቋም የአሰራር ማሻሻያ ማካሄድ፣ 3) የሰው ሀብት ሥራ አመራርን ዘመናዊ ማድረግ እና 4) የተሻሻሉ የሥራ አመራር ሥርዓቶችንና ጥሩ ተሞክሮዎችን

ተግባራዊ ማድረግን ያካተቱ ነበር፡፡ ሆኖም ሥልቶቹን ለመምራትና ለመተግበር ያለው ልምድ ውስን በመሆኑ በሪፎርም ሥራዎቹ የተገኙ ፍሬዎች የተጋነኑ አልነበረም፡፡

ስለሆነም መንግሥት የሕዝብ አገልግሎትን ሥር ነቀል በሆነ ሁኔታ ለመቀየር ተንቀሳቅሷል፡፡ የሕዝብ አገልግሎቱን ደንበኛ ተኮር ለማድረግ፣ መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲን ለማስፈን፣ ውጤት ተኮር የሆነ የሥራ አፈፃፀም ሥርዓትን ለመገንባት የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ እንደ አንድ የዘላቂ የለውጥ መሣሪያ ተመርጦ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ መተግበር የተጀመረው በ2002 ሲሆን ብዙ የፌደራል መሥመራዊ የሚኒስቴር መ/ቤቶችና ኤጀንሲዎች የሥራ አፈፃፀምና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በመፈተሽ የሥራ ሂደቱን በአዲስ የሥራ ሂደት በመተካት ተጨባጭ የሆነ ለውጥ/ዕድገት አሳይተዋል፡፡ ሆኖም የሕዝብ አገልግሎት በዘላቂነት ተለውጦ ለማየት ረጅም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ስለዚህ ከዚህ አንፃር አንዱ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ የሕዝብ አገልግሎት የሰው ሃብት ሥራ አመራርን አቅም መገንባት ነው፡፡ ይህም ሥራ የሕዝብ አገልግሎትን የሥራ አፈፃፀምና የአገልግሎት አሰጣጥ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለማሻሻል የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ የመንግሥትን የአስፈፃሚ አካል በማሻሻል የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በሕዝብ አገልግሎት ያለውን የሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት በተመለከተ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ሚና ይህን ያህል ከፍተኛ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ የሥራ ዘርፍ በብዙ መሥሪያ ቤቶች በአስተዳደርና ፋይናንስ ሥር ከመምሪያ በታች ሆኖ እንደ ንብረት አስተዳደር /ሥራ አመራር ተቆጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም አሁን የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ሂደት እንቅስቃሴ ይህን ሁኔታ በመቀየር የሰው ኃብት ሥራ አመራር ራሱን ችሎ እንዲዋቀር አድርጓል፡፡ ሆኖም የሰው ኃብት ሥራ አመራር ለመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ሂደት ያበረከተው አስተዋፅኦ አነስተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ለድርጅት የለውጥ ሂደት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች ጥቂቶች በመሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሥራ ዘርፉ በሰው አስተዳደር ተግባራት የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ይህም ማለት የሰው ኃብት ሥራ አመራር ወደፊት በመሄድ በለውጥ ሥራ አመራር፣ በማማከርና በማገዝ ሥራ ላይ በማተኮር የድርጅቱን ፍላጎቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል ብዙ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግባራዊ በማድረግ ረጅም ርቀት ሄደዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ወደሚቀጥለው ደረጃ ማለትም ሚዛናዊ ስኮር ካርድን መሠረት ያደረገ ሁሉን አቀፍ የሥራ አፈፃፀም ሥርዓት በመዘርጋት ላይ ናቸው፡፡ በመሠረታዊ የአሰራር ለውጥና በሚዛናዊ ስኮር ካርድ መሳሪያነት፣ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች መሪዎች ለተቋማቸው ሥራ አፈፃፀም እና በተለይም ለደንበኞች የሚሰጡትን አገልግሎት በተመለከተ ተጠያቂ እየሆኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለምጣኔ ኃብት ዕድገት፣ ድህነትን ለማቃለል እና የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን በብዛትና በዓይነት ለማስፋፋት ያልተቋረጠ ትኩረትን ይጠይቃል፡፡ ይህንን ሥራ ለማከናወን በመንግሥት ተቋማት በመካሄድ ላይ ያለው ትራንስፎርሜሽን ሊቀጥልና ሊጎለብት ይገባል፡፡ ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት እስከአሁን ድረስ ትኩረት የተሰጠው ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት ሲሆን ይህንንም ወደዘላቂ ለውጥ በመውሰድ ቀድሞ የመንግስት ተቋማት ወደውስጥ የሚመለከቱበትን ሥርዓት በመቀየር ደንበኞችን ማገልገልን እንደዋነኛ ዓላማ ሊይዙ ይገባል፡፡

## 6. ሥነ-ምግባርና ተጠያቂነት በሕዝብ አገልግሎት ሪፎርም ፕሮግራም

ሥነ-ምግባር ለረጅም ጊዜ መተግበር ከጀመረው የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም አንዱ አካል ነው፡፡ መንግስት የሕዝብ አገልግሎት ዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን የሚከታተልበትና ተገቢውን እርምጃ የሚወስድበት የሥነ-ምግባር መሠረተ ልማት የሌለው መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸው፡፡

- ሙሉና ሥርዓት ያለው የሕግ ማዕቀፍና ጠንካራ ተቋም አለመኖር፣
- በጉዳዩ ክብደትና ውስብስብነት የማህበረሰቡ/የሕዝቡ የንቃተ ህሊና ደረጃ በቂ አለመሆን፣
- የሙስናና ተያያዥ ጉዳዮችን ለመከላከል፣ ለመለየት፣ ምላሽ ለመስጠት፣ ለመመርመር፣ ክስ ለማቅረብና የመሳሰሉትን ተግባራትን ለማከናወን የአቅም ክፍተት መኖሩ፣
- የመገናኛ ብዙሃን የምርመራ ሪፖርቶችን ገለልተኛ በሆነና በተገቢ መንገድ ለማቅረብ ድክመት መኖሩ፣

ከላይ በተጠቀሱት ድክመቶች ምክንያት፣ በፕሮግራም የታቀደው ፕሮጀክት የሚከተሉትን ይዟል፡፡

- የሙስናን ጉዳዮችንና የሚመለከታቸውን አካላት የሚያስተባብር ራሱን የቻለ ማዕከላዊ መንግሥታዊ አካል በሥነ-ምግባር ረገድ ማቋቋም፣
- የሕዝብ አገልግሎት ዋና እሴቶችንና መለኪያዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥነ ምግባር ደንብ ማዘጋጀት፣
- የፖሊስን፣ የፍትህ አካላትን እና የዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤቶችን አቅም ማጎልበት፣
- የሕዝቡን የሥነ- ምግባር ግንዛቤና ትምህርት ከፍ ማድረግ፣
- በምርመራ ጋዜጠኝነት አቅምን መገንባት፣ እና
- በሀገሪቱ ያለውን ወሳኝ የሙስና ወሰን አስመልክቶ በየጊዜው የሕዝብ አመለካከት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣

**ውጤቶች**

እስከአሁን ድረስ የተገኙ ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታል፣

- **በሥነ-ምግባር ረገድ ራሱን የቻለ ማዕከላዊ አካል መቋቋሙ፣**
  - የሙስናን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 235/2001 የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽንን በግንቦት 2001 አቋቁሟል፡፡
- **የተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 433/2005፣**
  - ይህ አዋጅ ዋና አላማው በመከላከል ላይ ያተኮረ እርምጃዎች ላይ ሆኖ የሥነ-ምግባር ትምህርትን ማስፋፋት፣ የሙስና ክሶችን የመመርመር ሥልጣን እና አሁን ባለው ልምድና አሰራር ላይ ጥናት ማካሄድ፣
- **የሥነ-ምግባር መሠረተ ልማት**
  - በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥነ-ምግባር አገናኝ መኮንን ማቋቋም፣
- **የሙስና ምርመራ፣**
  - የፌደራል ሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ራሱ መርምሮ ጉዳዩን ለፍርድ ቤቶች ለክስ ማቅረብ፣
- **ምርምርና ጥናቶች፣**
  - ኮሚሽኑ በየዓመቱ በተመረጡ ርዕሶች ላይ ጥናቶችን ማካሄዱ፣
- **የሲቪል ማህበረሰቡን በፀረ-ሙስና ትግሉ እንዲቀላቀል ማድረግ፣**

- *መንግሥት የሲቪል ማህበረሰቡ የፀረ ሙስና ትግሉን እንዲቀላቀሉ ዝግጁነትን መግለፁና ኮሚሽኑም ይህንን ዓላማውን ዕውን ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን መስራቱ፣*

❖ ***የሥነ-ምግባር ደንብ ማዘጋጀት፣***
- *የሲቪል ሰርቪስ የሥነ-ምግባር ደንብ መዘጋጀቱና በሁሉም የሲቪል ሰርቪስ መሥሪያ ቤቶች መተግበሩ፣*

❖ ***የመገናኛ ብዙሃንን አቅም መገንባት፣***
- *ኮሚሽኑ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃንን አቅም ለመገንባት በተለያዩ ጊዜያት የአሠልጣኞች ሥልጠና ማካሄዱ፣*

❖ ***በሙስና ወሰን ላይ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣***
- *በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አማካኝነት በ2001 በሙስና ደረጃ ላይ የዳሰሳ ጥናት ሲካሄድ ከ10 ዓመት በኃላም በ2011 ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም የዓለም ባንክ፣ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል እና ክሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ጥናቶች አካሂደዋል፡፡*

## 7. የአገልግሎት አሰጣጥ በመንግስት መ/ቤቶች (በሕዝብ አገልግሎት)

*በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሕዝብ አገልግሎት የተስተዋለው ዝቅተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ በተለያዩ ችግሮች ሊከሰት እንደሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩል የመንግሥት አስተዳደር ለዜጎችን መብትና ለሕዝብ አገልግሎት ደንበኞች በአግባቡ ምላሽ አይሰጥም፡፡ ከሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ለኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራት ዕድል የሚሰጡ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታዎችን ማየት ይቻላል፡፡*

- ❖ *ለሕዝብ አገልግሎት ያለው ቀና አመለካከት በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉን፣*
- ❖ *ዜጎች ከመንግሥት አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው በቂ ግንዛቤ አለመያዙ፣*
- ❖ *በሕዝብ አገልግሎት ዘርፍ የሚጠበቀውን የሥራ አፈፃፀም ያላሟላ ሰው ተጠያቂ አለመሆን፣*
- ❖ *በብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጡ ረጅምና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ፣ እጅግ በጣም ረጅም የእዝ ሰንሰለትና ያረጀ የሥራ አመራር ልምድ ላይ ያተኮረ መሆኑ፣*

- *በአብዛኛው የሚሰጠው አገልግሎት ሥራውን ለሚያከናውኑ ባሙያዎች የአስተዳደር ቅለት እንጂ የተገልጋዮችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ፣*
- *የሕዝብ አገልግሎት ተቋማት በአብዛኛው የሚያተኩሩት በግብዓቶችና በዝርዝር ሥራዎች እንጂ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በመተግበርና አገልግሎቱን በማሻሻል በተጨባጭ በሚገኝ ውጤት ላይ አለመሆኑ፣*
- *አብዛኛውን ጊዜ የሕዝብ አገልግሎት ስለ አገልግሎት አሰጣጡ ሁኔታና አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች በግልፅና በቂ የሆነ መረጃ እንደማይሰጥ፣*
- *ለአንዳንድ አገልግሎቶች የሕዝብ አገልግሎት ተቋማት ብቸኛ አገልግሎት ሰጪ መሆናቸው፣*
- *ብዙዎቹ ተቋማት መደበኛ የሆነ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት እንደሌላቸው፣*
- *የአገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን በተመለከተ ያላቸውን ፍላጎት በአብዛኛው እንደማይጠየቅ፣*
- *በብዙ የመንግሥት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ በዕቅድ ሂደት ውስጥ በቂ ቦታና ትኩረት እንደማይሰጠው፣*
- *አገልግሎቶችን ለማሻሻል የተነሳሽነትና የቁርጠኝነት ደረጃ በአብዛኛው ሁኔታዎች ከሚፈለገው በታች መሆን፣*
- *አገልግሎቶችን በሚፈለገው ደረጃ ለማሻሻል የኃብት እጥረት መኖር፣*
- *ተያያዥ አገልግሎቶችን በሚሰጡ ተቋማት ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥ አለመሆናቸው እና በተለያዩ ተቀራራቢ /ተያያዥ መሥሪያ ቤቶችም ሆነ በአንድ ድርጅት ውስጥ ባሉ መምሪያዎች መካከል ያለው መደጋገፍና መተባበር ዝቅተኛ መሆኑ የአገልግሎት አሰጣጡ ብቃት ያለው እንዳይሆን ማድረጉ፣*
- *በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለው የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሥርዓቱና የአሠራር ሁኔታ ሠራተኞችን ለማነቃቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያበረታታ አለመሆን፣*
- *የአገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን አስመልክቶ ስላላቸው መብትና ግዴታ ምንም የሚያውቁ አለመሆኑ እና አንዳንድ ጊዜም አገልግሎቱን ለማግኘት ወዳልተፈለገ አካሄድ የመሄድ፣* (Service Delivery Policy in the Civil Service, 2001)

መሥሪያ ቤቶችን በምን መልኩ መደራጀት እንዳለባቸውና ውጤታማ፣ ብቃት ያለውና ጥራት ያለው አገልግሎት በተመጠነ ወጪ ሊሰጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ የሚያሳይ ብሔራዊ ፖሊሲ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ሥራ አመራሩ ትኩረቱ በአዋጅ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ በመሆኑና ይህም የአገልግሎት አሰጣጥ መመዘኛዎችን የሚገልፅ አይደለም፡፡

በእነዚህና ሌሎች ችግሮችና ተግዳሮቶች የመንግሥት የአገልግሎት ዘርፍ የመንግሥትን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አገልግሎቶች ሊሰጡ አልቻሉም ነበር፡፡

ስለሆነም ይህ ሁኔታ በፌደራል መሥመራዊ ተቋማትና በከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በጀት ተመድቦላቸው በሚሰሩ ሌሎች የፌደራል መንግሥት ኤጀንሲዎች ተግባራዊ የሚደረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲና መሠረታዊ ማሻሻያን የሚጠይቅ ነው፡፡

የፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ የተጠቃሚዎችን እርካታ ማረጋገጥ ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- ብቃትና ውጤታማነት፣
- በመንግሥት አገልግሎቶች ፍትሃዊ የሆነ ተደራሽነት እና
- የተሻለ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣

የፖሊሲው መሣሪያዎች (አቅጣጫዎች) የሚከተሉትን ይጨምራል፣

- የመሥሪያ ቤቱን ተልዕኮ ማስቀመጥ፣
- ለሕዝብ አገልግሎት ጥሩ አመለካከትን ማዳበር፣
- አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መለየት፣
- ቀላል የሆኑ ተደራሽነትን መቀየስ፣
- ተቀራራቢ አገልግሎቶችን ማስተባበር፣
- የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓትን ማደራጀት፣
- በቂ መረጃ መስጠት፣
- ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ጋር መመካከር፣
- የአገልግሎት መለኪያዎችን ማስቀመጥ፣
- ወጪ ቆጣቢ የሆነ አገልግሎት መስጠት እና
- ግልፀኝነትን ማዳበር

(Service Delivery Policy in the Civil Service, 2001)

የአተገባበር ሥልቶች ደግሞ የሚከተሉትን ያካትታል፣

- ራሱን የቻለ አስፈጻሚ አካል ማደራጀት፣
- ስለጉዳዩ ግንዛቤ መፍጠር፣

- ❖ አቅም ግንባታ፣
- ❖ የሠራተኞችን ተሳትፎ ማበረታታት፣
- ❖ በምርምርና በዕቅድ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያን ማስተዳደር፣
- ❖ አገርአቀፍ የሽልማት ሥርዓት መመሥረት፣
- ❖ ተምሳሌት የሆኑ ፈፃሚዎችን መሸለም እና፣
- ❖ ከህዝብ ጋር በትብብር መስራት፣

(Service Delivery Policy in the Civil Service, 2001)

## 8. *መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ እንደዘላቂ የለውጥ መሣሪያ በሕዝብ አገልግሎት*


*የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ማለት የሥራ ሂደትን ሥር-ነቀል በሆነ አኳኋን በመለወጥ ወሳኝ በሆኑ የሥራ አፈፃፀም መለኪያዎች ማለትም በወጪ፣ በጥራት፣ በፍጥነትና በአገልግሎት አሰጣጥ አስደናቂ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሠረታዊ የአሠራር ማሻሻያ እንቅስቃሴ ነው* (Hammer and Champy, 1993)፡፡

### *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ውጤቶች፣ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎች*

*የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ እንደ አንድ ዘላቂ የለውጥ መሣሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ይህም ሞዴል ለአገልግሎት አሰጣጥ ከተቀመጠው የተቋም የዘላቂ ለውጥ ሞዴል ጋር የሚስማማ ነው፡፡*

**የቢዝነስ ስርዓት አልማዝ**

**ስትራቴጂክ ፕላን እና መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ሂደት**



## ውጤቶች

በጥሩ ሁኔታ የተተገበረ የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝቷል፡፡

- **የሥራ ሂደቶችን እንደገና ማዋቀር፣** የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በተካሄደባቸው ተቋማት፣ ደንበኞችን ለማገልገል የተቀመጠ የሥራ ሂደት ደንበኞችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደገና ተዋቅሯል፡፡
- **ብቃትን ያሻሽላል፣** ብዙ አገልግሎቶች በተሻለ ብቃት ይሰጣሉ፡፡ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ሂደት ምክንያት አገልግሎቶች በትንሽ ጊዜና ገንዘብ ይሰጣሉ፡፡
- **የዝርግ አደረጃጀት ውጤት፣** የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ዋና ትኩረቱ በሥራ ሂደት ላይ በመሆኑ ረጅም የዕዝ ሰንሰለቱን በመቀነስ ቅልጥፍናንና የሥልጣን ውክልናን ያረጋግጣል፣ አገልግሎት አሰጣጡንም በትንሽ ክትትልና ቁጥጥር ማቀላጠፍ ያስችላል፡፡
- **የሥራ አፈፃፀምን ለመለካትና የክፍያ ሥርዓትን ለማመቻቸት የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት መቻሉ፣** የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በተካሄደበት ተቋም፣ የሥራ አፈፃፀም የሚለካው በተጨማሪ በተፈጠረው እሴት ብቻ ነው፡፡ የክፍያ ሥርዓቱ ዕውቅናና ሽልማት የሚሰጠው አዳዲስ ለተፈጠሩት እሴቶች ነው፡፡
- **የሰው ኃብት ሥራ አመራርን ያሻሽላል፣** ውጤትን መሠረት ያደረገ ድርጅታዊ መዋቅር የተፈጠረ ሲሆን የሰው ኃብቱ አቅጣጫም እሴትን በማግኘትና በመጨመር ላይ ያተኩራል፡፡ ችሎታዎች ተሻሽለዋል፡፡ የተለያዩ ሥራዎች አንድ ላይ የተዋቀሩ ስለሆነ ብዙ ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች ይስተዋላሉ፡፡ የሠራተኛው አመለካከት እየተለወጠና እየተሻሻለ ሄዷል፡፡
- **የደንበኞች እርካታ፣** በሲቪል ሰርቪሱ የደንበኞች እርካታ ጨምሯል፡፡ ደንበኞችና ዜጎች ከመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በኋላ በሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት ተደሳች ሆነዋል፡፡
- **ውጤታማነት በየጊዜው መሻሻሉ፣** ውጤታማነት የሚገለፀው "ትክክለኛ የሆነውን ሥራ መሥራት" በሚል ነው፡፡ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ምክንያት የቡድን ቻርተር ተዘጋጅቶ የየቡድኖቹን ተልዕኮና ያላቸውን ሥልጣን በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይህም ቡድኖች የተሰጣቸውን ግቦችና ኃላፊነቶች ለመወጣት ያስችላቸዋል፡፡

- **የተለወጠ አመለካከት፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ የመንግሥት ሠራተኞችን አመለካከት በመቀየር በደንበኞች ፍላጎት ላይ እንዲያተኩሩ አድርጓል፡፡ ደንበኞች በግንባር ቀደም ቦታ እንዲቀመጡ አግዟል፡፡ ይህም የቢሮክራሲ ሂደትን በመቀነስ የአገልግሎት አሰጣጥ ዑደትን በማፋጠንና ቅልጥፍና እንዲሰፍን አድርጓል፡፡ "ደንበኛ ንጉስ ነው" የሚለው የግሉ ዘርፍ መፈክር በሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ሠራተኞች አዕምሮ ውስጥ ይገኛል፡፡*
- **የሠለጠነ ሠራተኛ፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ የመንግሥት ሠራተኞችን ችሎታ ወደላቀ ደረጃ አሳድጎታል፡፡ ሰዎች በቡድን ውስጥ ብዙ የተለያዩ ሥራዎችን እንዲያከናወኑ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ሁሉንም ችሎታዎች የያዘ የመንግስት ሠራተኛ በመፈጠር ላይ ነው፡፡*
- **የቡድን ሥራ፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ የመንግሥት ሠራተኞችን በቡድን በማደራጀት የታወቁ አገልግሎቶችን ለመስጠት ሠራተኞቹ በአንድ ክፍት በሆነ ቢሮ ውስጥ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ተቀምጠው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡ የቡድን መንፈስ አሁን ዳብሯል፡፡ በተጨማሪም ውጤትን ለማጎልበት የተባበረ ጥረት ይደረጋል፡፡*
- **በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎቶች ማግኘት፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎቶች የማግኘት ዕድል ፈጥሯል፡፡ ቀድሞ ደንበኞች አንድን አገልግሎት የሚያገኙት በተለያዩ ቦታዎች ነበር፡፡ አሁን ግን ሁሉንም አገልግሎቶችን በአንድ መስኮት ማግኘት ይችላሉ፡፡*
- **የደንበኞች እንክብካቤና የደንበኞች ግንኙነት፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት የደንበኞች እንክብካቤ እንዲሻሻል አድርጓል፡፡ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ስትራቴጂካዊ ዕይታ መሠረት አሰልቺ የሥራ ሂደቶች መወገዳቸው፣ የመንግሥት ሠራተኛው አገልግሎት ለመስጠት የተነቃቃ መሆኑና ለአገልግሎት አሰጣጥ የተሻለ አመለካከት መኖሩ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡*
- **የሥራ አመራር ችሎታ መሻሻል፣** *የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ትግበራ የሚጀምረው በጠንካራ የስትራቴጂክ ሥራ አመራር እና አስተሳሰብ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተቋም ተልዕኮውን፣ ራዕዩንና ዓላማውን በአግባቡ ይገመግማል፡፡ ይህ የስትራቴጂክ አስተሳሰብ ሂደት በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለውን የሥራ አመራር ችሎታ*

አሻሽሎታል፡፡ በተቋማት የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ጥናት እንዲያከናውኑ ኃላፊነት የተሰጣቸው የሥራ አመራር ቡድኖች የተለያዩ ሥልጠናዎችን ወስደዋል፡፡ እነሱም፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ፣ የለውጥ ሥራ አመራር እና አመራር ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ሥልጠናዎች የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በጥሩ ሁኔታ እንዲተገበር አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

## ተግዳሮቶች

- **የአቅም ማነስ**፣ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ትግበራ ትልቁ ተግዳሮት የአቅምና የችሎታ ማነስ ነው፡፡ ይህም የሚመነጨው ስለመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ያለው አስተሳሰብ ዝቅተኛ መሆኑ፣ የሠራተኛው ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ እና ቴክኒካዊና ተግባራዊ የሆኑ ፅንሰሃሳቦችን ለምሳሌ፣ ደንበኛ፣ ሂደት፣ ግብዓት፣ ውጤት (output) ለመረዳትና በአግባቡ ለመገንዘብ ዝቅተኛ ችሎታ መኖር፣
- **ለለውጥ ዝግጁ አለመሆን**፣ እንደማናቸውም የድርጅት የለውጥ ሁኔታ፣ ሠራተኞች የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥን ለመቀበል ዝግጁነታቸው አነስተኛ ነበር፡፡ የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በመሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሲጀመር ሠራተኞቹ የተቀበሉት በተደበላለቀ ስሜቶች ነበር፡፡ ዋናው የተሳሳተ ስሜት የመጣው የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ የመጣው ሠራተኛ ለመቀነስ ነው የሚል ነው፡፡ ሌሎች ሠራተኞች ደግሞ የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ የመንግስት ፕሮግራም በመሆኑ ፖለቲካዊ ነው የሚል ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ የውጭ ሃገር መሳሪያ በመሆኑ በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ሊደረግ አይችልም የሚል ነው፡፡
- **እርስ በእርስ የሚጋጩ ሕጎችና አዋጆች**፣ አሁን በሥራ ላይ ያሉ አንዳንድ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ከመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ አስተሳሰብ ጋር አብረው አይሄዱም፡፡ በመሆኑም አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞች እነዚህን ሕጎች የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ሂደትን እያደናቀፉት እንደሚገኙ ያስባሉ፡፡
- **ተገቢ የሆነ ዕቅድ አለመኖርና የስትራቴጂክ ትግበራ ማነስ/እጥረት**፣ አንዳንድ ተቋማት የመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ

ትግበራ የጀመሩት በመንግሥት ግፊት በመሆኑ በዕቅዳቸው ውስጥ ቀድሞውኑ ተካቶ የሚሰራ አይደለም፡፡

*መፍትሔዎች*

- ❖ *ዕውቀትን ለማስተላለፍና የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ቡድኖችን ቁርጠኝነት ለመጨመር በመሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ማካሄድ፣*
- ❖ *ስለ መሠረታዊ የአሰራር ለውጥ፣ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ዕቅዶች፣ ፕሮጀክቶች፣ ውጤቶች እና ስለታሰበው ለውጦች ግልፅ ግንኙነት መመስረት፣*
- ❖ *አዲስ ውጤት ለማስመዝገብና አገልግሎት ተኮር የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ አካሄድን ለመከተል አሁን በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎችና ደንቦች መገምገም፣*
- ❖ *የትግበራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ይህም በግልፅ ሊሰሩ የሚገባቸው ተግባራት እንዲሁም የክትትልና የግምገማ ዕቅድን እንዲያካትት ማድረግ፣*

## 9. ለሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሚዛናዊ ስኮር ካርድ እንደ አፈፃፀም ሥራ አመራር መሣሪያነት

*ሚዛናዊ ስኮር ካርድ አዲስ የመለኪያ ማዕቀፍ ሲሆን ከድርጅቱ ስትራቴጂ በመነሳት የፋይናንስና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ መለኪያዎችን የሚያጣምር ነው* (Kaplan & Norton, 1996)፡፡

### *የሚዛናዊ ሰኮር ካርድ ውጤቶች፣ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎች*

### *የተሠሩ ሥራዎች*

- ❖ *በሚዛናዊ ስኮር ካርድ ሥልጠና ተሰጥቷል፣*
- ❖ *የሚዛናዊ ስኮር ካርድ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፣*
- ❖ *ሚዛናዊ ስኮር ካርድ ተግባራዊ ሆኗል፣*
- ❖ *የሠራተኞች የሥራ ድርርቦሽ በግልፅ ተከስቷል፣*

***ተግዳሮቶች***

*በመንግሥት ሠራተኞች ከተገለፁት የአቅም ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፣*

- *በሠራተኞች ውስጥ ስለ ሚዛናዊ ስኮር ካርድ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ፣*
- *የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣*
- *በሚዛናዊ ስኮር ካርድና በውጤት መካከል ያለው መደናገር፣*
- *የመረጃ መሰብሰብ እና የሥራ አፈፃፀም መለኪያ፣*
- *አፈፃፀምን ለማረጋገጥ ማስቸገሩ፣*
- *በሠራተኛ ደረጃ ተልዕኮን ለማስቀመጥ ማስቸገሩ፣*
- *የስትራቴጂክ ዕቅድና የሥራ አመራር ዝግጅትና የሥራ አመራር ልምድ በተገቢው ሁኔታ አለመጓዙ፣*

***መፍትሔዎች***

- *ሥራ አፈፃፀምን ማስተዳደር፣ ሥራ አፈፃፀም ከፋይናንስ ሥራ አመራር ስርዓት ጋር ሊያያዝ ይገባል፣ ይህም የሚጠቅመው ከግብ ጋር ተገቢውን ቁርኝት ለማድረግ ነው፡፡*
- *የተሻለ የተቋም አቅም እና የሰው ኃብት ሥራ አመራር ባለሙያዎችን ሥራ አፈፃፀምን ማስተዳደር እንዲችሉ ማብቃት፣*
- *የሚዛናዊ ስኮር ካርድን ሂደት ለመምራትና ለመተግበር በጉዳዩ ላይ የተመሰከረላቸውን /የበቁ/ ባለሙያዎችን ማበራከት፣*
- *የክትትልና የግምገማ መመሪያዎች ማዘጋጀትና መተግበር፣*
- *የአሠልጣኞች ሥልጠናን ማካሄድ፣*
- *ከሥራ የሚለቁ ሰዎችን ለመግታት በሠልጣኙና በድርጅቱ መካከል ስምምነት ማድረግ፣*
- *በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን መ/ቤቶች ልምድ መውሰድ፣*

## 10. የሕዝብ አገልግሎት የሥነ ምግባር መርሆዎች

### *የመንግሥት ሠራተኞች የሥነምግባር ግዴታዎች*

*በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር* 515/2007 *መሠረት የመንግሥት ሠራተኞች ግዴታ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ማናቸውም የመንግሥት ሠራተኛ*

- *ለሕዝቡና ለሕገ መንግስቱ ታማኝ መሆን፣*
- *መላ ጉልበቱንና ችሎታውን ለሕዝቡ አገልግሎት ማዋል፣*

- በሥራ ዝርዝሩ መሰረት የሚሰጡትን የሥራ ዕቅዶችና ሌሎች በሕጋዊ መንገድ የሚሰጡትን ትዕዛዞች መፈፀም፣
- የመንግሥትን ሥራ የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማክበር፣
- የመንግስትን ፖሊሲ በብቃት መፈፀም፣

የሕዝብ አገልግሎት የሥነምግባር መርሆዎች ደግሞ፣

- ሐቀኝነት
- ታማኝነት
- ግልጽነት
- ምስጢር መጠበቅ
- ቅንነት
- ተጠያቂነት
- ለሕዝብ ጥቅም መስራት
- ሕጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል
- አድሎዎ አለመፈፀም
- ሕግን ማክበር
- ሕዝብ አገልጋይነት
- አመራር ሰጪነት

በሌላ በኩል በሕዝብ አገልግሎት አሁን ያለውን የመልካም አስተዳደር እና የሥነ ምግባር ሁኔታ በሚመለከት የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥነምግባርና ተጠያቂነትን ለማጠናከር፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቅርቡ መሠረታዊ የሥራ መርሆዎችን የሚያመለክት የለውጥ ሠራዊት ሰነድ (January, 2013) ሥራ ላይ አውሏል፡፡ እነዚህ መርሆዎች በሕዝብ አገልግሎት ተቋማት ተግባራዊ የሚደረጉና ዋና ዋናዎቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ገለልተኛነት
- ተሳትፎ
- መግባባት
- ግልጽነትና ተጠያቂነት
- ለሕዝብ ጥቅም መስራት
- የሕግ የበላይነት እና
- ብቃትና ውጤታማነት

# 11. በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ የሥነ ምግባርና የተጠያቂነት ችግሮች

በከተማ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ የታዩ ዋና ዋና የሥነ ምግባርና የተጠያቂነት ችግሮች፣ የችግሮቹ ምንጮችንና መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ለመለየት የተለያዩ የቀድሞ ጥናቶች ተፈትሸዋል፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ የሕዝብ አገልግሎት ያለው የሥነ-ምግባርና የተጠያቂነት ችግሮች ከሰሃራ በታች ካሉ ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም የሥነ-ምግባርና የተጠያቂነት ጉዳዮች እያደጉ የመጡ ችግሮች መሆናቸውን ብዙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአጠቃላይ የተጠያቂነት መጥፋት፣ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ባህሪያት እና የሙስና ተግባራት እየተስፋፉ ከመምጣታቸውም በላይ በሕዝብ አገልግሎት የተለመዱና እንደ ተቋም ተግባራት እየተቆጠሩ መጥተዋል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከዚህ በታች ባሉት አንቀፆች በሕዝብ አገልግሎት ላይ የሚስተዋሉ የሥነ ምግባርና ተጠያቂነት ዋና ዋና ችግሮች ላይ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

## 11.1 *አጠቃላይ ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራትና የተጠያቂነት ክፍተቶች*

በአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ ሥነምግባርና ተጠያቂነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በኢትዮጵያ የሕዝብ አገልግሎት ተቋማት ከመንግሥት ፖሊሲዎች አንፃር እንደገና የተደራጁት ከ20 ዓመታት በፊት ነው፡፡ የመንግሥት ሠራተኛው ቁጥር ከተቋማት ለውጥ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆንና በተለያዩ ጊዜያትም የደመወዝ ማሻሻያ መደረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም የአገልግሎት ጥራት ማነስ፣ ሙያዊ አለመሆን፣ ኢ-ሥነምግባራዊ ልምዶች/ተግባራት/ እና የተጠያቂነት ክፍተቶች በሕዝብ አገልግሎት አሁንም የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

በዓለም ባንክ ጥናት መሠረት በአጠቃላይ አነጋገር ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሃገሮች የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም በኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራቶች ምክንያት እየተገታ ነው፡፡ ከኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራት መካከል፣

- ሥልጣን ለግል ጥቅም ማዋል፣ የዘመድ አዝማድ ሥራ፣ ሙስና፣ የፖለቲካ ሥልጣንን ለግል ጉዳይ የማዋል፣ የፖለቲካና የዘር ቁርኘት መኖር፣

- ❖ ምልመላ፣ ዕድገትና የኬሪየር ልማት ከሜሪት ይልቅ በግል ግንኙነትና ለፖለቲካ ሥርዓቱም ሆነ ለግለሰቦች ታማኝ በመሆን እንደሚፈጸም፣
- ❖ የሥራ አመራሩ ባህል በተለያዩ ዓይነት ሙስናዎች ማለትም ሥራ በመስጠት፣ ኮንትራት በመስጠት፣ ወ.ዘ.ተ… የታጠረ መሆኑ፣
- ❖ የቁርጠኝነት፣ የግልፅነትና የተጠያቂነት አለመኖር እና
- ❖ ደካማ የዲሲፕሊን ጉዳዮች ሥራ አመራር፣ ፍትህን በማስተዳደር ረገድ ረጅም ጊዜ መፍጀቱና ብቃት ማነስ፣ የፍትህ አካላት ነፃነት ላይ ተፅዕኖ መኖሩ፣

ከላይ የተመለከቱት ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራት ሕጎችን፣ ደንቦችንና የተቋማት አደረጃጀቶችን የሚያጠፉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሙስና ትክክለኛ ውሳኔ እንዳይሰጥ ከማስደረጉም በላይ የምጣኔ ሀብትን ከአምራቹ ክፍል ወስዶ የሕዝብ አገልግሎት ባህልን ውጤታማ እንዳይሆንና እንዲበላሽ፣ በመጨረሻም በሙስና የተጨማለቁ ተቋማት እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል በዓለም ባንክ ሪፖርት መሠረት በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ የሥነ ምግባርና ተጠያቂነት ጉድለቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ❖ ሕጎችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ ቁርጠኝነት ማጣት፣
- ❖ የሲቪል ሰርቪስ የሥልጠናና ልማት ፖሊሲ አለመኖር፣
- ❖ ሙያዊ የሥራ አፈፃፀም መለኪያን ተግባራዊ አለማድረግ፣
- ❖ የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና የሜሪት ሥርዓት የባሕል ችግሮች፣
- ❖ የሲቪል ሰርቪስ ክፍያ ዝቅተኛ መሆን እና የማነቃቂያ ልምዱ ዝቅተኛ መሆን፣
- ❖ የሥራ አደረጃጀቶችና መመሪያዎቹ ሥርዓትን የጠበቀ አለመሆን፣

እነዚህ እና የተቋም አቅም ድክመቶች የሕዝብ አገልግሎትን የሥራ አመራርና የአስተዳደር ኃላፊነትን እጅግ በጣም አዳክመውታል፡፡ ስለዚህ የሥነ ምግባርና የተጠያቂነት ጉዳዮች ሳይጎለብቱ እንዲሁም ቁርጠኛ የሆነ የፖለቲካ አመራር ሳይኖር ንፁህ የሆነ የሕዝብ አገልግሎት አስተዳደርና መልካም አስተዳደር የሚታሰቡ አይደለም፡፡

## 12. የሙስና አደጋዎች በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ

በሕዝብ አገልግሎት ተገቢ የሆነ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ዋነኛ ችግር ሙስና ነው፡፡ ሆኖም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሙስናን ለመቀነስ

ቁርጠኛ በመሆን ጠንካራ የሥነ ምግባርና ፀረሙስና ተቋም በማቋቋም ለሚከተሉት ጉዳዮች ምላሽ ሰጥቷል፡፡ እነሱም፣ የሕዝብ አገልግሎትንና የፍትህ አካላትን እንደገና ማዋቀርና ሪፎርም ማካሄድ እንዲሁም በሙስና በተዘፈቁ ኃላፊዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ናቸው፡፡ የሕዝብ አስተያየት እንደሚያመለክተው በሀገሪቷ ውስጥ ሙስና ዋነኛ ችግር እየሆነ ነው፡፡

ሙስና በሁሉም ቦታ ያለ ከመሆኑም በላይ ጥንታዊ ነው፡፡ የፀረሙስና ሕጎች የጀመሩት "የአስርቱ ትዕዛዝ" ከመውጣት ጀምሮ ሲሆን በዚህም ውስጥ "አትስረቅ" የሚለውን አንዱ ትዕዛዝ እግዚአብሔር ለህዝቡ ተናግሯል፡፡ ሆኖም አሁን ያለው የፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ሁኔታ ሙስና በፊት እምብዛም በማይታይበት በሰለጠነው ዓለም የቢዝነስ ሰዎችና ፖሊሲ አውጪዎች በሙስና መዘፈቃቸው የሚያመለክተው ሙስና የደሃ ሃገሮች በሽታ ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡

ሙስና የተለያዩ ዓይነቶች ሲሆኑ ከትንሽ እስከ ከፍተኛው ሊያመራ ይችላል፡፡ በጣም የሚታወቁት የሙስና ድርጊቶች በሕዝብ አገልግሎት የሚከተሉት ናቸው፡፡ ጉቦ፣ ግፊት ማሳደር፣ የመንግስትን ሃብት ለግል ጥቅም በሕገወጥ መንገድ መጠቀም፣ በሥራ ላይ ለማይገኙ ሠራተኞች ክፍያ መፈፀም፣ ላልቀረቡ ዕቃዎች ወይም ላልተሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ መፈጸም፣ ኮሚሽን መውሰድ፣ ማጭበርበር፣ የመንግሥትን ገንዘብ ማጉደል፣ ያለአግባብ ገንዘብ መጠቀም፣ ያለፈቃድ በትርፍ ሰዓት መሥራት፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለዘመድ ወይም ለጓደኛ በማናቸውም ሁኔታ ቅድሚያ መስጠት፣ በምርጫ ውድድር ድጋፍ ለሰጡ አካላት ሥራ፣ እድገት፣ ሹመት ወ.ዘ.ተ… መስጠት፣ ግለኝነት፣ ችሎታው ሳይታይ ጓደኛን ለሥልጣን ማጨት፣ አንድን ጉዳይ ለማስፈጸም የግብረስጋ ግንኙነት መጠየቅ በዋናነት የሚጠቀሱ የሙስና ዓይነቶች ናቸው (Atkilt, 1996)፡፡

ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ ተቋማት የሙስና ድርጊቶች በጣም የተጋነኑ ናቸው፡፡ ትራንፓረንሲ ኢንተርናሽናል (1995) በሙስና ላይ ያካጣጠረ ጥምረት ሲሆን በዋነኛነት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ተቋማትን እንደሚከተለው አስቀምጧል፡፡

- የመንግስት ግብር፣
- ጉምሩክ፣
- ታክስ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት፣
- ፖሊሲ /በተለይም ትራፊክ ፖሊስ/፣
- ኢሚግሬሽን፣

- የንግድና የሥራ ፈቃድ የመንጃ ፈቃድን ጨምሮ፣
- በመንግሥት በሞኖፖል በተያዙ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣
- የኮንስትራክሽን ፈቃድና መሬትን ማካለል፣ እና
- የመንግሥት ሹመት

በሌላ በኩል በመንግሥት ተለይተው የተቀመጡ የኪራይ ሰብሳቢነት በብዛት የሚስተዋልባቸው አካባቢዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመሬት አስተዳደርና አሰጣጥ፣
- ታክስና ሌሎች ክፍያዎች፣
- የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ እና
- ትላልቅ የመንግሥት ግዢዎችና ሥራዎች (Ethics, Magazine, Vol.12, No.3, March 2013)

ስለሆነም የሕዝብ አገልግሎት መስሪያ ቤቶችና የሥራ እንቅስቃሴ ከላይ ከተመለከቱት ጉዳዮች አንፃር በማየት በቀላሉ ለሙስና የተጋለጡ መስሪያ ቤቶችን መለየት ይቻላል፡፡ ሆኖም ለዚህ ፅሁፍ ዓላማ ሲባል ለውይይት ተትቷል፡፡

## 12.1 *የሙስና በሽታ*

የሙስና በሽታ በሁለት ጫፎች ማለትም ቀላል ሙስና በአንድ በኩል ከባድ ሙስና በሌላ በኩል በማለት መግለፅ ይቻላል፡፡

በአብዛኛው ቀላል ሙስና ዜጎች በየቀኑ የሚያጋጥሟቸው ሲሆን በዝቅተኛ ደረጃ የሕዝብ አገልግሎት ላይ ይስተዋላል፡፡ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ሠራተኛ ክፍያው በቂ ስላልሆነ ከሕዝቡ ኪራይ በየጊዜው ይሰበስባል፡፡

ከባድ ሙስና የሚስተዋለው በከፍተኛ ደረጃ ባሉ የመንግሥት አካላት ላይ ነው፡፡ ይህ በሽታ በሙስና አቀንቃኞች በሚከተለው መልኩ ይገለጻል፡፡

- በግለሰብ ጉዳዮች ሙስና የአስተዳደር ሂደትን ለማፍጠን እንደ ዘይት ማገልገሉ፣
- ግትር እና ቅልጥፍና ያጣን አስተዳደር ሙስና እንደሚያስተካክለው፣
- ሙስና የሕይወት መጥፎ እውነታ ነው የሚለው ከልምድ ጋር ይያያዛል፣ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ጥሩ ክፍያ

ለማያገኙት የመንግሥት ሠራተኛ እንደማነቃቂያ ተደርጎ ይወሰዳል፣

- ❖ በጣም አደገኛ ሙሰኞች ሙስናን ብቃት እንደሚጨምር ይናገራሉ፣ የውሳኔ አሰጣጥን በግለሰቦች እጅ በማድረግ ሙስና ደካማውን/ብቃት የሌለውን የመንግሥት መዋቅር ያሽንፋል፣
- ❖ ራስን የማታለል ወይም ለዚህ ክስተት "አይንን መሸፈን" ከሥነ ምግባር አኳያ ተገቢ አይደለም፡፡ በተጨማሪም መሥሪያ ቤቶችን ወይም ግለሰቦችን በሙስና ተግባር ሲጨማለቁ ዝም ብሎ ማየቱም ተገቢ አይደለም፡፡

## 12.2 የሙስና ምክንያቶች

የሙስና ምንጮች ከብዙ ነገሮች ጋር ማለትም ከኢኮኖሚና ከፖለቲካው ሁኔታ፣ ከማህበራዊና የባህል ሁኔታና ከተቋማት ደካማነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሙስና ወሰኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ተፅዕኖ ይደርስበታል፡፡

- ❖ ድህነት፣
- ❖ የመንግስት ሠራተኞች እጅግ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ፣
- ❖ ለፖለቲከኞችና ለመንግሥት ሠራተኞች የሚያገለግል የአሰራር ደንብ አለመኖር፣
- ❖ የኦዲት ሥርዓትን በአግባቡ እንዲተገበር አለማድረግ፣
- ❖ በማዕከላዊ የዕቅድ ስርዓት የምጣኔ ሀብት ሥልጣንን በመንግስት ኤጀንሲዎች መያዙ፣
- ❖ የሠራተኛ ቅነሳን የሚያበረታቱ የመንግሥት ፖሊሲዎች የሥራ ዋስትናን ማሳጣታቸው፣
- ❖ የመንግስት ቁልፍ ውሳኔ ሰጪዎች ስላላቸው ንብረትና ዕዳ በተመለከተ በየጊዜው ክትትል የሚደረግበት ፖሊሲ አለመኖር፣
- ❖ በፖለቲካውና በአስተዳደሩ መሣሪያ ሙስናን ለማጋለጥ ያለው ዕድል አነስተኛ መሆኑ፣ እና
- ❖ እጅግ ደካማ የፍትህ ሥርዓትና ደካማ ቅጣቶች፣

## 12.3 *የሙስና ተፅዕኖ*

*ሙስና በፖለቲካ፣ በልማት፣ በምጣኔ ሀብት ዕድገትና በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ምሕረት የለሽ አደጋ ያደርሳል፡፡ በአጠቃላይ ሙስና የሚያደርሰው ተፅዕኖ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡*

- *ሙስና ነፃና ገለልተኛ ምርጫን ያግዳል፣ የሕግ አውጪው አካል በአስፈፃሚው ላይ ያለውን የመቆጣጠር ሚና እንዲላላ ያደርጋል፣ ነፃ የፍትህ አካላት እንቅስቃሴዎችን ይገታል፣ የማህበረሰቡን እሴቶች በማበላሸት ዲሞክራሲን ያጠፋል፣*
- *ሙስና በዝቅተኛው የሕዝብ ክብር ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፣ በመንግሥት ላይ ያለውን መተማመን ያጠፋል፣*
- *ሙስና የፖለቲካ ተቋማትን ህጋዊነት ይቀንሳል፣ ይህም የመንግሥት የፖለቲካ፣ የልማትና የምጣኔ ሃብት ዓላማዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ይከብዳል፣ መንግሥት በሙስና ያጣውን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ ሲል ኃይል ይጠቀማል፣ ይህም ለፖለቲካ አለመረጋጋት ከፍተኛ ምክንያት ይሆናል፣*
- *ሙስና የምጣኔ ሀብት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ያበላሻል፣ የተሻለ አቅራቢውን ለመምረጥ ከመቸገር አልፎ አላስፈላጊና ተገቢ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ወይም ኮንትራቶች እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሙስና ለመጥፎ መንገዶች፣ ለዝቅተኛ የሕክምና አገልግሎቶች፣ ለደካማ ትምህርት ቤቶች፣ ለወደቀ የትምህርት ደረጃ መለኪያዎች፣ በገንዘብ የተደገፉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሳይደረጉ መጥፋት፣ ፕሮጀክቶች በማጠናቀቅ ሂደት መዘግየት መከሰት፣ የውጪ እርዳታ የዋለበትን ቦታ ያለመታወቅ፣ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች አነስተኛ መሆንና ከሀገር ውስጥ የሚወጣው ግን ከፍተኛ መሆን፣ የብሔራዊ ሃብትን የማጥፋት፣ በኢንዱስትሪው፣ በግብርናው እና በመሳሰሉት የማምረት አቅም መቀነስ፣ ወ.ዘ.ተ… ችግሮች እንዲከሰት ያደርጋል፡፡*
- *ሙስና ብዙ የምጣኔ ሃብት ወጪዎችን ያስከትላል፣ ሙስና የዋጋ ግሽበትን በማምጣትና ፍላጎት እንዲቀንስ በማድረግ የዜጎችን አጠቃላይ ደህንነት ይቀንሳል፣*
- *ለሕዝብ አገልግሎት ሙስና ዋና ችግር ፈጣሪ ነው፣ በመንግሥት ሠራተኞች ሞራል፣ በፕሮፌሽናሊዝም እና በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ከፍተኛ ችግር ያመጣል፣*

- ግለሰቦች ሙስናን በአዕምሮአቸው ከያዙ ለሥራ መደቡ ምንም ዋጋ አያስቀምጡም በተለይ የሥራ መደቡ ለሙስና የተመቸ ከሆነ ለምሳሌ፣ ጉምሩክ፣ አገር ውስጥ ገቢ ወ.ዘ.ተ... ይህ ሁኔታ የሠራተኞችን ጉልበትና ያሏቸውን እሴቶች ከታች ወደ ላይ በመቀያየር በማህበራዊ ጥሩ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ወዳልተመረጡ/ዝቅተኛ ወደ ሆነው የሙስና ተግባራት እንዲያመሩ ያደርጋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የመንግሥት የሥራ ቦታዎች ብቃት ላለው የሕዝብ አስተዳደር እንቅፋት ይሆናሉ፡፡
- ሙስና የአስተዳደር ብቃትንና ውጤታማነትን በመቀነስ የአስተዳደር ሂደቶችን ከማደናቀፋም በላይ በሁሉም የመንግሥት የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ያለመተማመን ስሜት ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም ለአፈፃፀም የሚሰጠውን የሥልጣን ውክልናን ያደናቅፋል፣
- ሙስና የታወቀውን የውሳኔ አሰጣጥ በመቀየር አድሎአዊነትና በዘፈቀደ የሚከናወኑ ሥራዎች እንዲሰፍኑ ያደርጋል፣ በዚህም ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አላስፈላጊ ይሆናሉ፣
- ሙስና የምልመላና የዕድገት ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፣ ለሙስና የተጋለጡ ሥራዎች በብዙ ሥራ ፈላጊዎች የሚፈለጉ ናቸው፡፡ በሙስና ምክንያት ብቃት ያለው ሠራተኛ ከሚመረጥ ይልቅ ችሎታ የሌለው በሰጠው ትልቅ ጉቦ ሊቀጠር ይችላል፡፡ ይህም በሕዝብ አስተዳደር ውስጥ ብቃትና ችሎታ የሌላቸው ሠራተኞች መሰባሰቢያ እንዲሆን ያደርጋል፣
- ሙስና የሕዝብ አገልግሎት አስተዳደርን ከሕዝብ አገልጋይነት (ሕዝባዊነት) በመነጠል የግል ትርፍ ለማግኘትና ራስን ለማበልፀግ በሚከናወኑ ሕገወጥ ድርጊቶች ላይ እንዲያጠነጥን ያደርጋል፣

በአጠቃላይ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ችሎታን ለማሻሻል እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር ሙስናን በተገቢው መንገድ ምላሽ መስጠት ዋናው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡

### 12.4 *የአስተዳደር ብልሹነት?*

በ Richard Crausman (1966) *አገላለጽ መሠረት "የአስተዳደር ብልሹነት? ማለት አድሎዎ/ወገንተኛነት፣ ችላ ማለት፣ ትኩረት አለመስጠት፣ ማዘግየት፣ ብቃት ማነስ፣ ያልተሟላና በዘፈቀደ የሚሰራ፣ ሞራልን ያልጠበቀ ባህሪና የመሳሰሉት ናቸው"፡፡*

*የአስተዳደር በደል የሚመለከተው በአስተዳደር መመሪያዎች ላይ የሚስተዋሉ ጉድለቶችን እንጂ በተሰጡ ውሳኔዎች ተገቢነት ላይ አይደለም፡፡ ሆኖም በመራጭ ኮሚቴው በመበረታታት ተከታታይ የሆኑ የእንግሊዝ የፓርላሜንታሪ ኮሚሽነሮች ትርጉሙን በማስፋት "መጥፎ ውሳኔዎች" እንደ አስተዳደር ብልሹነት? እንዲቆጠሩ አድርገዋል፡፡*

*ከላይ ያለውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በአብዛኛው በሕዝብ አገልግሎት ከሚስተዋሉ የአስተዳደር በደሎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፣*

- *ያለ ብቃት/ያለሜሪት/ ምልመላ፣ ምደባ፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ ሥልጠና፣*
- *ያልተፈቀዱ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎችና አበሎች፣*
- *መመሪያውን ያልተከተሉና ሕገወጥ የሆነ ከሥራ ማባረርና ወደ ተለያዩ የሥራ መደቦች ማዛወር፣*
- *የሠራተኛ ሪከርድ፣ ዶክመንቶችና የፋይሎችን አያያዝ በተመለከተ በስፋት የሚስተዋል ችግር፣*

*የአስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ ከሦስት ዓመት በፊት በቀድሞው የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሕዝብ አገልግሎት መሥሪያ ቤቶች የተካሄደው ምርመራና ምልከታ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ስትራቴጂ ፕሮፖዛልን ለመቅረፅ አስችሏል፡፡*

## 13. የሰው ኃብት ሥራ አመራር ስትራቴጂ ለሕዝብ አገልግሎት

*የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን በብዛትና በዓይነት ማሻሻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሲቪል ሰርቪሱ የዘላቂ የለውጥ ሂደቱ መቀጠል ይኖርበታል። እስካሁን ድረስ ቅድሚያ የተሰጠው ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት ላይ በማተኮር ሲሆን ይህም የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ወደውስጥ የሚያደርጉትን ምልከታ በመቀየር ደንበኞችን የማገልገል ዓላማን በዋነኛነት እንዲይዙ በማድረግ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ነው። ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ሂደት ደግሞ ለሰው ኃብት ሥራ አመራር ትኩረት በመስጠት ትክክለኛውን*

ሰው በትክክለኛው ቦታ በማስቀመጥ ጥራት ያለው አገልግሎት በማቅረብ የድርጅት ዓላማዎችን ማሳካት ነው።

አሁን ያለውን የሰው ኃብት ሥራዎች ተሞክሮ አስመልክቶ የጥራት/የመለኪያ የዳሰሳ ጥናት የተካሄደ ሲሆን ይህም ለሲቪል ሰርቪስ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ስትራቴጂን ለመቅረፅ እንደግብአት አገልግሏል።

የስትራቴጂው ዋና ግኝቶችና ማጠቃለያዎች የሰው ኃብት ሥራ አመራር ጉዳዮችን ስትራቴጂካዊና መዋቅራዊ ጉዳዮችን ሊመረምር ይገባል (HRM Strategy, FCSA, Draft Report, 2010)፡፡

1. **በሲቪል ሰርቪሱ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ላይ ዘላቂ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፣**
   - ❖ በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ስለሚኖረው የሰው ኃብት ሥራ አመራር ግንኙነት በተመለከተ ሚናዎችንና ኃላፊነቶችን ግልፅ ማድረግ፣
   - ❖ ትልቁን የሰው ኃይል ማለትም አስተማሪዎች፣ የጤና ባለሙያዎችና የልማት ወኪሎችን/ሠራተኞችን እንደ "መንግሥት ሠራተኞች" መቁጠር፣
   - ❖ የክልሎችን የሰው ኃብት ሥራ አመራር አሠራር ወጥነት እንዲኖረው ማስተባበርና መጠበቅ/መከታተል፣ ለምሳሌ፣ የፕሮፌሽናል ሥልጠናና ክፍያ፣

2. **በተለመደ ማዕቀፍ ውስጥ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሥልጣንን ማከፋፈል እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፣**
   - ❖ በፌደራል ደረጃ የሚያስፈልገውን በቀላሉ የመተጣጠፍ/የቅልጥፍና ፍላጎት ደረጃ በመለየት ተቋማትና መሪዎቻቸው ለሰው ኃብት ሥራ አመራር ተግባራቸው ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማስቀመጥና ያለውን አጠቃላይ ሥርዓት መጠበቅና በተመሳሳይም ለክልሎችና ለበታች የመንግሥት አካላት ጥቅም ላይ ማዋል፣

3. **የሰው ኃብት ሥራ አመራር በለውጥና በድርጅት ልማት ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፣**
   - ❖ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ሂደት ትግበራ ወቅት የድርጅት ለውጥ መጥፎ ጎኖች እንዳይከሰቱ፡ ብዙ

እርምጃዎች የተወሰደ ሲሆን ይህም የሠራተኞችን እምነት በመገንባት ከሲቪል ሰርቪሱ እንዳይለቁ አድርጓል፡፡

4. **የአፈፃፀም ሥራ አመራር ለውጥን በማጠናከር ረገድ ያለው ጠቀሜታ፣**
    - የሚዛናዊ ስኮር ካርድን ለመተግበር በተወሰደው እርምጃ የሠራተኛውን ችሎታና ብቃት ማሳደጉና ይህም የቁልፍ ሠራተኞችን የመልቀቅ ሁኔታን በመግታት ለውጭ ምልመላ የሚሰጠውን ትኩረት ቀንሷል፡፡
    - ተገቢ የሆነ የአፈፃፀም ደረጃ ለመቅረጽ ሠራተኛውን ሊያነቃቃ የሚያስችል ሥርዓት መገንባትና ይህንንም ከአፈፃፀም ስርዓት ጋር ማያያዝ፣

5. **ውጤታማ ስትራቴጂክ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ዕቅድ**
    - ከዋና የሙያ ሠራተኞች በስተቀር የሰው ኃብት ዕቅድ በአብዛኛው የለም፡፡ የሠራተኛ ገበያ ትንታኔና ተገቢ የሆነ የሠራተኛ ፍላጎት፣ የመልቀቅ ሁኔታ ግምት በአግባቡ አይሰራም፡፡ ውጤታማ የስትራቴጂክ ዕቅድ የሥልጠና፣ ሠራተኛን ለማቆየትና ለማነቃቃት የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት አቅጣጫ የሚያሳይ ነው፡፡

6. **የሥራ አመራርና የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሙያተኞች ልማት**
    - የሥራ መሪዎች አሁን የሌላቸውን የዘመናዊ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ችሎታ ሊያዳብሩ ይገባል፡፡ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሥልጣኖች ወይም ሃላፊነቶች ለመሥመራዊ የሥራ መሪዎች ተከፋፍሏል፡፡ በመሆኑም የመሥመራዊ መሪዎች ተጠያቂ የሚሆኑት ለምርታማነት ብቻ ሳይሆን ለሠራተኞች ችሎታ፣ ብቃትና ደህንነት ይሆናል ማለት ነው፡፡
    - የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሚና የማማከር ነው፡፡ በተጨማሪም ዕውቀቱ እነሱ ጋር ስላለ እንደ የውስጥ አማካሪ ሥራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡ በተፈለገ ጊዜ ደግሞ የሰው ኃብት ሥራ አመራር አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

7. **በሙያ ማህበራት የመወከል አስፈላጊነት**

- መምህራን፣ የጤና ባለሙያዎች እና ሌሎች የሙያ ማህበራት የአባሎቻቸውን ዕይታና አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲሁም የሥራ አመራር ካሪየር መዋቅርና የሙያ መግቢያ ደንቦችን የሚያንፀባርቁበት መድረክ ሊሆን ይገባል፣
- የቀጣሪ ተቋማትን ማደራጀትና የሠራተኛ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣

8. **ለሥራ አፈፃፀም እና የሠራተኛውን ችሎታ ለማሻሻል የአዲስ ሠራተኛ ትውውቅና የማቆያ ስርዓት**
   - የአዲስ ሠራተኛ ትውውቅ ማለትም ሥነ ምግባርን፣ እሴቶችና ደንቦችን፣ የአሰራር ስርዓት እና ቀስ በቀስ ወደ ሥራው ስለመግባት ጨምሮ በማስተዋወቅ የሚከናወኑ ተግባራት አፈፃፀምንና የሠራተኛውን የአገልግሎት ዘመን ለመወሰን ከሚረዱ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡
   - የአዲስ ሠራተኛ ትውውቅ እንዲሁም ሠራተኛው በስራ ላይ እንዲቆይ የማድረግ ልምዶች በትክክለኛው የቅጥር ወጪ ላይ ተፅዕኖ ያለው መሆኑ፣

9. **ከሽልማት ይልቅ ሥልጠና የሥራ አፈፃፀምን ለማሻሻል**
   - በአብዛኛው ሥልጠና በአቅርቦት ላይ የተመሠረተ እንጂ ፍላጎት ተኮር አይደለም፣ የሥልጠና ፍላጎት ጥናት አንድ የተለየ የሥራ መደብን ከግምት ውስጥ በማስገባት አፈፀምን ለማሻሽል በሚያስችል መልኩ ሊካሄድ ይገባል፣
   - በተጨማሪም የድርጅቱን አፈፃፀም ለማሻሻል ያግዛል በሚል ማበረታቻ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ሊበረታታ አይገባም፣

10. **በክፍያ ስርዓቱ ላይ መሠረታዊ ሥራ መሥራት**
    - እንደአብዛኞቹ ዓለም አቀፍ ስርዓቶች የሲቪል ሰርቪስ ክፍያ ሦስት ነገሮችን ይዟል፡፡ የአፈፃፀም ክፍያ የድርጅቱን ግብ ለማሟላት የሚሰጥ ማበረታቻ፣ የኑሮ ዋጋ ውድነት ላይ የተመሠረተ ማስተካከያ፣ በውጭ ካለው የሠራተኛ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችላል፣ እና በመጨረሻም የደመወዝ ስኬል ጭማሪ የሠራተኛውን ልምድ ለማቆየትና ተረጋግቶ እንዲሠራ ለማድረግ ያስችላል፣

- ጥቅማ ጥቅሞች አነስተኛ ክፍያን ለማካካስ ሳይሆን ራሱን ችሎ በመሠረታዊ ክፍያ ላይ ሊታይ ይገባል፣

11. **በዘላቂ የለውጥ ሂደት ውስጥ የሰው ኃብት ሥራ አመራር አስቸኳይ ጉዳዮች**

አዲስ የተዋቀረ ተቋምና የሥራ መዋቅር የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ቢያተኩር የተሻለ ይሆናል፣

- የሥራ ምዘናና ደረጃ አወጣጥ እና ለአዲስ የሥራ መደቦች የሚያስፈልገውን ተፈላጊ ችሎታ መለየትና ምላሽ መስጠት፣
- በፔርሶኔል ሥርዓት ምክር በመስጠት የለውጥ ትግበራ ሂደቱን መርዳት በተለይም የሠራተኛ መፈናቀል፣ ቅሬታ አቀራረብ ስልቶች ወ.ዘ.ተ...
- ከሚዛናዊ ሰኮር ካርድ ጋር የተሳሰረ የሥራ አፈፃፀም ሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ይህም ክፍያ ተኮር አፈጻጸምን በመዘርጋት ሠራተኛውን ያነቃቃል፣ እሴቶችን፣ እምነቶችንና አመለካከቶችን ለማሻሻል ይረዳል፣
- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የሠራተኛውን ችሎታና ብቃት ለማሳደግ፣
- የሥራ አመራርና የአመራር ልማት በማካሄድ የሥራ መሪዎችና በአመራር ላይ የሚገኙ የተለወጡ እሴቶች፣ እምነቶችና አመለካከቶችን በድርጊትና በቃል በተመሳሳይ ሁኔታ መፈጸም፣

## 14. ኢ-ሥነምግባራዊ ልምዶች በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ

በፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ጥላ ሥር በተካሄዱ ጥናቶች በሕዝብ አገልግሎት የሚስተዋሉ የሙስና ወይም ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራት ምንነት ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ እንደማጠቃለያ በፌደራል/በአዲስ አበባ ደረጃ በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራትና የሙስና አደጋዎች እንደሚከለተው ቀርበዋል፡፡

1. **ትምህርት**
    - በፈተናዎችና በተማሪዎች ውጤት ማጭበርበርና ተያያዥ ሙስናዎች፣

- ❖ በግልና በቡድን ለመኮረጅ ማሴር/መስራት፣
- ❖ መረጃዎችን ማሳሳት/የትምህርት ማስረጃ እና ሰርተፊኬትን በውሸት ማሰራት፣
- ❖ አስተማሪዎችን ለማሳደግና ለማሻሻል ጉቦ መስጠት፣
- ❖ ተማሪዎችን በመምረጥና በመገምገም ሂደት በወዳጅነት ወይም በጓደኝነት መስራት፣
- ❖ ሥልጣንን በመጠቀም ከሴት ተማሪዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ መፈለግ፣
- ❖ አስተማሪዎች አገልግሎታቸውን ወደ ግል ማስተማር የማዘዋወር ወይም ከትምህርት ቤት መቅረት፣

2. **የጤና አገልግሎት**
    - ❖ ተኝተው ለሚታከሙና በተመላላሽና ሕክምና ለሚያገኙ ለምሳሌ፣ ለራጅ፣ ለቀዶ ሕክምናና ለጉብኝቶች ሙስና መኖሩ፣
    - ❖ በሆስፒታል ተኝቶ ለመታከም ባለው መመሪያና ሂደት ላይ ወዳጅነትን ወይም ጓደኝነትን መጠቀም፣
    - ❖ ለሕክምና ትኩረት አለመስጠት ወይም ደካማ በሆነ ሁኔታ ማስተናገድ፣ እንክብካቤ ማድረግና ፋሲሊቲዎችን ማቅረብ፣
    - ❖ በቂ ያልሆነ ሙያተኞች፣ መድሃኒቶች፣ አቅርቦቶችና አምቡላንሶች፣
    - ❖ አላስፈላጊ የሆነ ምርመራ እና ከፍተኛ ገንዘብ መጠየቅ፣
    - ❖ ሆን ብሎ ህመምተኞችን ወደ ግል ክሊኒኮችና ፋርማሲዎች ለህክምና መላክ፣
    - ❖ ማጭበርበር፣ በስምምነት የሚሰጥ ጉቦ (ተቀባዩ ገንዘቡን አንድ ጉዳይ በማስፈጸሙ እንደ ኮሚሽን እንደሚወስድ)፣ ለተቆጣጣሪዎች/ኢንስፔክተሮች ጉቦ መስጠት፣ የመንግሥት ገንዘብ ማጉደል፣
    - ❖ ረጅም የመጠበቂያ ጊዜ፣ ሠራተኛው ከሥራ ገበታው መቅረት እና መለኪያ አለመኖር፣
    - ❖ ያለውን ገንዘብ በአግባቡ አለመጠቀም እና አቅርቦቶችን መዝረፍ፣

3. **ፖሊስ**

- የደህንነት ፖሊስ፣ ተጠርጣሪን ላለመያዝ ወይም ምስክርን ወደ ፍርድ ቤት ላለማምጣት፣ ጥቃቶችን ችላ ለማለት ወይም መረጃዎችን ለመቀየር ጉቦ መቀበል፣
- ትራፊክ ፖሊስ፣ ሕገወጥ የሆነ የአነዳድ ስህተትን በጉቦ መተው
- የእስር ቤት ፖሊስ፣ ለታራሚዎች አድሎ መፈጸም

4. **ፍርድ ቤቶችና ዓቃቤ ሕግ**
- ውሳኔዎችን ወይም ድርጊቶችን ለማስቀየር ክፍያ ወይም ጉቦ መጠየቅ፣
- ጉዳዮችን ወደ ክስ ለማቅረብ ወይም ላለማቅረብ ዓቃቤ ሕጎች ያላቸውን ሥልጣን በአግባቡ አለመጠቀም፣
- የሲቪል ጉዳዮች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሙስና ድርጊቶችን መፈጸም፣
- ዓቃቤ ሕግ የክስ ሂደቱን ደካማ አድርጎ የማቅረብ፣
- በዳኞች ላይ ተፅዕኖ ማድረስና ዝቅተኛ የዋስትና ገንዘብ እንዲጠየቅ ማድረግ፣
- በፍትህ አስተዳደሩ ላይ መዘግየትና ብቃት ያለመኖር
- ደካማ ውሳኔዎች፣ ሕጉ ተግባራዊ እንዲደረግ አለመፈለግ፣

5. **ንግድና ኢንቨስትመንት**
- ሕገወጥ የንግድና የሥራ ፈቃድ፣
- የአየር በአየር ንግድን የመቆጣጠሩ ሥራ አነስተኛ መሆን፣
- ከገበሬዎች በተሳሳተ ሚዛን ምርቶችን መግዛት፣
- ለዕቃው ከተከፈለው በታች ደረሰኝ ማቅረብ፣
- አርቲፊሻል እጥረትን ለመቆጣጠር የሚሰራው ሥራ ደካማ መሆኑ፣
- ቁጥጥር የማይደረግበት ከፍተኛ ዋጋ፣
- ሙያዊ ያልሆኑ የማሻሻጫ ማስታወቂያዎችን የመቆጣጠር እጥረት፣
- ውድድርን የሚፃረር ተጨባጭ ያልሆነ፣ የተሳሳተ፣ የተጋነነ እና አሳሳች ማስታወቂያዎች፣

6. **መሬትን ስለመከፋፈል /በዞን መከፋፈል/**

- መሬትን መከፋፈል፣ ጥሩ ቦታዎችን መምረጥ፣ የረዘመ ክፍፍል
- ለቤት ገንቢዎች ተገቢ ያልሆነ የመሬት አሰጣጥ
- የተሳሳቱ የመሬት ሰርተፊኬቶችና ዶክመንቶችን ማውጣት፣

7. **የመንግስት ኪራይ ቤቶች**
    - ቤቶችን ያለጨረታ ማከራየት፣
    - የተከራዩ ቤቶችን ሁኔታ የመከታተል እጥረት፣
    - የዘገዩ የኪራይ ክፍያዎችን ለመሰብሰብ በቂ ክትትል ያለማድረግ፣
    - ሕገወጥ ነዋሪዎችን፣ የቁልፍ ሽያጭ፣ ለሌላ ማከራየትን ያለመከታተል፣
    - ለሕጎችና ለደንቦች ተገዥ አለመሆን፣
    - የኪራይ ቤቶችን ዋጋ ለመተመን ወጥ አሰራር አለመኖሩ፣
    - የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት አለመኖር፣

8. **የመብራት፣ የስልክ፣ የውሃና-ፍሳሽና የፖስታ ግልጋሎቶች (Utilities)**
    - ግኑኙሮችን፣ መሳሪያዎችንና አቅርቦቶችን በወቅቱ ያለማቅረብ ችግሮች፣
    - የመብራት ኃይል፣ በተከታታይና ብዙ ጊዜ የመብራት እጥረት
    - የውሃ አቅርቦትና ፍሳሽ- የውሃ አቅርቦትና የፍሳሽ አገልግሎት እጥረት
    - የስልክ መስመሮችን መጠገን መዘግየትና የዘገመ የኢንተርኔት ግንኙነት
    - ፖስታ፣ አልፎ አልፎ በጣም የተለዩ እሽጎችን መሥረቅ፣
    - በመብራት ሃይል፣ በቴሌ እና በውሃ አቅርቦት መካከል ያልተቀናጀ የኮንስትራክሽን ሥራ፣

9. **የመንግሥት ግዢዎች**
    - ተገቢ ያልሆነ ጨረታ መስጠትና መሰረዝ
    - ከተወዳዳሪዎች መካከል የተወሰኑትን የመምረጥ ሂደቱ ተገቢ ያልሆነና ግልፅነት የጎደለበት አሠራር፣
    - ጥራቱ፣ ዋጋውና አቀራረቡ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ምርጫ ማካሄድ፣
    - ሕገወጥ ኮንትራቶችን ማደስ፣
    - በውል ውስጥ ደካማ አንቀፆችን ማስገባት፣

- የተዳከመ የግዢ መመሪያ፣ ምሳሌ ፕሮፎርማ መስጠት፣
- ከእያንዳንዱ ግዢ ሊገኝ የሚገባው ዝቅተኛ ዋጋና የሚገኘው ብቃትና ውጤታማ ደካማ መሆንና የጅምላ ግዢዎች፣

10. **ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ**
    - የጉምሩክ ቀረጦችን ለማስቀነስ ከጉምሩክ አስፈፃሚው ጋር በሚስጢር መገናኘት
    - የተሳሳተ የገቡ ንብረቶች ማሳወቂያ
    - ተገቢውን ክፍያ ሳይከፍሉ የተከለከሉ ዕቃዎችን ማስገባት/ ማስወጣት
    - ቫት /የሽያጭ ታክስ እና የታሪፍ ታክስን መካድ
    - የታክስ ክፍያን ማሳነስ
    - የታክስ ከፋዮች መረጃ ስርዓት ደካማ መሆኑ
    - የተሳሳቱ ግምቶችና የሂሳብ ስሌቶች
    - የደካማ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር
    - በቂ ያልሆነ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

11. **የመንግሥት ባንክና ኢንሹራንስ**
    - ተሰብሳቢን በመሰብሰብ ረገድ መዘግየት፣
    - ለብድር አገልግሎት ያለውን ንብረት በከፍተኛ ዋጋ መገመት፣
    - ማስያዣ፣ ለፎቆች የተሳሳተ የኢንጅነሪንግ ግምት መስጠት
    - የተሳሳቱ የሳይት ዕቅድ እና የመሬት ባለቤትነት ሰርተፊኬት ለባንክ ብድር መጠቀም
    - በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ መፈረም፣
    - ኢንሹራንስ ለማግኘት ተብሎ መኪናዎች ሆን ብሎ ማጥፋት ወይም ማበላሸት፣
    - ብድር ለማግኘት ያለው የአሠራር ሂደት መመሪያ በቂ አለመሆን
    - ብድር ያለመሬት ወይም ንብረት ማስረጃ መስጠት፣
    - ደካማ የመረጃ አያያዝ ስርዓት፣

12. **የመንግስት ኮንስትራክሽን**
    - ኮንትራቶችን በሙስና መስጠት
    - የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖር የኮንስትራክሽን ፈቃድ መስጠት፣
    - የኮንስትራክሽን ሥራ መዘግየት፣

- ጥራቱ ደካማ የሆነ የኮንስትራክሽን ሥራ
- ፕሮጀክቶችን አለመጨረስ
- የትዕዛዝ ልዩነትና የተጋነነ ወጪ፣
- በኮንትራክተሮችና በተቆጣጣሪዎች መካከል መመሳጠር መኖር፣
- ከሂደቱ ቀድሞ ምርጫ ማካሄድ፣
- ደካማ ቁጥጥርና ክትትል፣
- የመጨረሻ ተወዳዳሪዎችን ለመለየት ተገቢ አሰራርና ግልፅነት አለመኖር፣
- በአግባቡ ላልተሰሩ ዲዛይኖችና ላልተሟሉ ስፔስፊኬሽኖች ኮንትራት መስጠት፣
- በኮንስትራክሽን ዕቃዎች የሚስተዋል ሌብነትና ያለአግባብ መጠቀም፣
- ላልቀረቡ ዕቃዎች ክፍያ መፈፀም፣

13. ትራንስፖርት
    - በመለኪያዎችና በደረጃ አሰጣጥ ላይ ግልፅነት አለመኖር፡
    - የመንጃ ፈቃድን በጉቦ መውሰድ
    - በቦሎና በሊብሬ ሂደቶች የሚስተዋለውን የጉቦ ሁኔታ መቆጣጠር አለመቻል፣
    - የደንበኞች አገልግሎቶችና በሕዝብ ትራንስፖርት የሚጓጓዙት ዕቃዎችን በተመለከተ ያለው ቁጥጥር ደካማ መሆን
    - ቁጥጥር ያልተደረገበት እና ዝቅተኛ ጥራት ያለው ጥገና እና ከፍተኛ ዋጋ፣
    - በጥገና ጊዜ አዳዲስ መለዋወጫ ዕቃዎችን በአሮጌ መተካት፣
    - የመኪናዎችን የመጫን አቅም አስመልክቶ ቁጥጥርና ክትትሉ ደካማ መሆኑ፣
    - መኪናዎችን አወላልቆ ለሌላ ሥራ መጠቀም፣

14. ማዕድን ማውጣት
    - የፈቃድ ሁኔታዎችን አለማክበርና ደካማ የኢንስፔክሽን ሥራ
    - የማዕድን ገቢያ ማለትም ወጪዎች፣ ውጤቶችና ትርፍን አስመልክቶ የተሳሳተ መረጃ መስጠት፡

- በአካባቢው ለሚኖሩ ነዋሪዎች መፈፀም ያለባቸውን ግዴታዎች አለመወጣት፣ የካሳ ክፍያን አስመልክቶ ጉቦ መውሰድ እና መስረቅ፣
- በኮንትራክተሮችና በአቅራቢዎች መካከል በጨረታና በሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎች ላይ መመሳጠር፣

15. **ሆቴልና ቱሪዝም**
    - የሆቴል አገልግሎቶች ዋጋ ከፍተኛ ሆኖ ጥራቱ ግን ዝቅተኛ መሆኑ፣
    - በታክስ እፎይታ የመጡ መኪናዎችን ያአግባብ መጠቀም እና ሕገወጥ ጥቅሞችን ማግኘት፣
    - ከቤተክርስቲያኖችና ገዳሞች በጣም ውድና ታሪካዊ የድሮ ጊዜ ንብረቶች መስረቅ፣
    - ቱሪስቶችን በደካማ ሁኔታ ማስተናገድ፣ ደህንነቱ ደካማ መሆኑ እና መጥፎ መስተንግዶ መስጠት፣
    - በባህላዊ ማንነታችንና እሴቶችን ላይ የቱሪስት ተፅዕኖዎችን የመከታተልና የመቆጣጠር ሁኔታ አለመኖር፣
    - የቱሪስት ገቢዎችን ለመጨመር ጥንታዊ ልምዶችን እንደ መጥፎ መቁጠር/ማሳየት፣

16. **ኳራንቲን**
    - ያለተገቢው ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ የሚወጡ የግብርና ምርቶችንና የምግብ ተዋፅዖችን ላይ በቂ ቁጥጥር አለማድረግ፣
    - በጉቦ ምክንያት የተበላሹ የግብርና ምርቶችንና የምግብ ተዋፅዖችን ለሚገልጹ ሰነዶች ሰርተፊኬት መስጠት

17. **የቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች**
    - ተገቢ ያልሆነ መመሪያ እና ከፈቃድ ውጭ ነዋሪዎችን መጥቀም፣
    - ለአንድ ሚስት/ባል ሁለት ቤቶችን መስጠት፣
    - በቤቶች ግዢ ላይ የፕሮጀክቶቹ ሠራተኞች ተሳትፎ፣
    - የከተማ ነዋሪዎች ያልሆኑና ያልተመዘገቡ ነዋሪዎችን መጥቀም፣
    - ቤቶችን ለማስረከብ ረጅም ጊዜ መፍጀት፣

- ❖ ከቀያቸው/ከሰፈራቸው የተነሱ ነዋሪዎችን የመመዝገብ ሥርዓቱ ደካማ መሆን፣
- ❖ በገንዘብ አሰባሰብ መዘግየት መኖር፣

18. **ቀበሌዎች/ወረዳዎች**
    - ❖ ለቀበሌ /ወረዳ ተመራጮች የቤት ዕድል ማመቻቸት፣
    - ❖ ሕጋዊ የሆነ የቤት ባለቤትነት ሰነድ የሌላቸው የመኖሪያ ቤቶች/ዩኒቶች፣
    - ❖ ደካማ ሠራተኞችን መመልመልና መምረጥ፣
    - ❖ ገንዘቡን መመዝበርና ያለአግባብ ንብረቶችን መጠቀም፣
    - ❖ የተጠቃሚዎች/የነዋሪዎች ሱቆችንና ክለቦችን ያለአግባብ መጠቀም፣
    - ❖ በጉቦ ለግለሰቦች መታወቂያ ወረቀት ማውጣት፣ ሰርተፊኬት መስጠት ወ.ዘ.ተ…
    - ❖ ደካማ የጊዜ አጠቃቀም ለምሳሌ፣ በየጊዜው ስብሰባ ማካሄድ፣
    - ❖ በጨረቃ ቤቶች ግንባታ ላይ ወቅታዊ ቁጥጥር አለማድረግ፣

19. **ኢሚግሬሽንና ዜግነት**
    - ❖ ፓስፖርት ለመስጠት ረጅም ጊዜ መጠየቁ፣

20. **መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ማህበረሰቦች**
    - ❖ በቂ ያልሆነ ክትትልና ቁጥጥር[1]

ስለሆነም ሥነ- ምግባርን፣ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን በማስፈን ሙስና ካልቀነሰ ጥቂት የሕዝብ አገልግሎት ሪፎርሞች ብቻ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

---

[1] ምንጭ፣ (Compiled from studies of World Bank, Kilimanjaro International, AAU and FEACC 2004 and 2005 EC, Annaual Reports to Parliament)

# 15. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች

## 15.1 ማጠቃለያና መደምደሚያ

በአሠራር፣ በሁኔታ፣ በችሎታና በሥልጣን የሚለያዩ መሪዎችና ሠራተኞች እንዳሉ ቢሆንም ሥነምግባርና ተጠያቂነትን በሕዝብ አገልግሎት ማስፈን መልካም አስተዳደርን ለመመስረት/ለመገንባት እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነና ይህም ለልማት አስተማማኝ አቅም እንደሚፈጥር መረዳት ይቻላል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ጥናቶችና ዳሰሳዎች የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ የሥነምግባር ችግሮች አሉበት፡፡ ሆኖም እንደአብዛኞቹ የሰሃራ በታች አፍሪካ አገሮች የበዙ የተበላሹ ልምዶች ሳይሆን በሀገራችን የሚስተዋለው ብልሹ አሠራር በትናንሽ ሙስና ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

አሁን ያለው የሜሪት ልምድ የሚያተኩረው በሕጎችና ደንቦች ላይ ሆኖ ይህም የሰው ኃብት አስተዳደሩን ችሎታና የሥነምግባር እንቅስቃሴዎች የማጠናከር ፍላጎት አለው፡፡ በመንግሥት አስተዳደር እንደሚታወቀው ሕጎችና ደንቦች የግል ሥልጣን እንዳይስፋፋ ከሚያግዱ መከላከያ መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡

ምንም እንኳን የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ የደንበኞችና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ለማርካት ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም የተቋማትን አቅሞችን የማጠናከር ጥሪው እንደቀጠለ ነው፡፡ ጥሩው ዜና ማናቸውም የሪፎርም እንቅስቃሴ ቀጣይ ሂደቶች ሲሆኑ በሂደትም እየተሻሻሉ ሊጠናከሩ ይችላሉ፡፡ ጉዳዩም በመንግስት ዘንድ ዕውቅና አግኝቶ በቁርጠኝነት ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሥነምግባርና የተጠያቂነት ጉዳይ በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ ያለውን ሁኔታ ለመዳሰስ ጥረት ያደረገ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም፣

- የሕግ አውጪውን፣ የአስፈጻሚውንና የፍትህ አካላትን አቅም ማጠናከር እንዲሁም በአቅም ግንባታ ሂደት ውስጥ የሲቪል ማህበረሰቡን ሙሉ ተሳትፎ ማጠናከር፣
- በተጠያቂነት ረገድ ያለ የፖሊሲ፣ የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ ክፍተቶች መለየት፣

የመንግሥት የሥራ አመራር መሣሪያ በራሱ ኢ-ሥነምግባራዊና በሙስና የተጨማለቀ አይደለም፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች ሰዎች እና የሕዝብ አገልግሎት ለኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራት ያውሉታል፡፡

የቀድሞ የአቅም ግንባታ እና የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ እንዲሁም የአሁኑ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሁልጊዜም በጥሩ የሥነ-ምግባር መስፈርቶችና ባህሪያት የመንግሥት ሠራተኞች ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ይጥራሉ፡፡ በመንግሥት ሠራተኞች ላይ የተጣለው ቅጣቶች ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ፣ የመቅጣት፣ ከደረጃ ዝቅ የማድረግ እና እንደ ጥፋቱ መጠን ማሰናበትን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ሆኖም በሀገሪቱ የሕዝብ አገልግሎት የሐቀኝነት ሥርዓት ብዙ ባለድርሻ አካላት አሉ፡፡ እነሱም፣ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ፓርላማ፣ የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ዋናው ኦዲተር፣ እምባ ጠባቂ ተቋም፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የግል ዘርፉ እና ጠቅላላው ሕዝብ ናቸው፡፡

መንግሥት የሚተልመው ንጹህና በጣም ውጤታማ የሆነ የሕዝብ አገልግሎት አካል ሲሆን ይህም አካል ፖሊሲዎችን በመንደፍና ዓላማዎቹን ተግባራዊ በማድረግ የኢኮኖሚና የባህል ትሩፋቶችን የሚያስገኝ ነው፡፡ በተመሳሳይም የፌደራል መሥመራዊ ተቋማት ውጤታማና ተጠያቂ የሆነ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ማየት ይፈልጋሉ፡፡ ይህም ማለት የመንግሥት ሠራተኛ ሕጋዊ መብቶቹ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶቹ በተሻለ ሁኔታ በግልጽ እንዲቀመጡለት ሲሆን የግል ዘርፉ እና ጠቅላላው ማሕበረሰብ ደግሞ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ የመንግሥት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ መጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም ከቀድሞው በበለጠ የሙስናን ተግባራትን፣ የአስተዳደር በደልን እና ያለአግባብ የማስተዳደርን ለማጥፋትና የሥነ ምግባር መለኪያዎችን፣ ፍትህ እና ለብሔራዊ ልማት ታማኝነትን ለማረጋገጥና ለመመሥረት ሁሉን አቀፍ አካሄድ መከተል የተሻለ ይሆናል፡፡

## 15.2 የመፍትሄ ሃሳቦች

የሥነ ምግባር ጥሰትንና ተቋማዊ ሙስናን ለመከላከልና ሥነ ምግባርና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚከተሉት ጠቃሚ የመፍትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

1. በፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚተገበር ጠንካራና የተረጋገጠ የበላይ የፖለቲካና የመንግሥት አመራር ቁርጠኝነት እንዲሁም ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ ተቋማትን

በማጠናከር ኢ-ሥነምግባራዊ የሆኑ ልምዶችንና ሙስናን ለመዋጋት ዋናና ብቃት ያለው ድርጊት መፈጸም፣

2. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚያተኩር ቀጣይነት ያለው የሕዝብ አገልግሎት ሪፎርም፣ ይህም የሚመራው በስትራቴጂክ ዕቅድ እና በተገቢው ሁኔታ በሚተገበር የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ሲሆን ይህም የተሻለና ጥራት ያለው አገልግሎት እንደሚያስገኝና ሚዛናዊ ስኮር ካርድን በመጠቀም ደግሞ ጠንካራ የአፈፃጸም ሥራ አመራር እና የማበረታቻ ስርዓት ለመዘርጋት እንደሚያስችልና ይህም በዋናነት የሚደገፈው የሕዝብ አገልግሎት ተቋማትና ሠራተኞችን አቅም በመገንባት እንደሆነ፣
3. በማያቋርጥ ሁኔታ የመንግሥት ባለሥልጣናትንና ቁልፍ የመንግሥት ሠራተኞችን ገቢ፣ ንብረትና ዕዳዎች ይፋ ማድረግና መከታተል፣
4. ተገቢ ያልሆኑ ከፍተኛ የሕዝብ ሥራዎችና ግዢዎችን ለማስቆም የሚያስችል ጠንካራ የሕግ መለኪያዎችንና መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣
5. ለሙስና የተጋለጡ የሕዝብ አገልግሎት እንቅስቃሴዎችን ለማሳለጥና ብቃትና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣
6. ግልፅ የሆነና ተጠያቂነት የሠፈነበት የሕዝብ አገልግሎት የአሠራር ደንብ ማዘጋጀትና ደንቡም ነጻና ብቁ ለሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች የሚያገለግሉ የሙያ መሥፈርቶችን እንዲያካትት በማድረግ ተግባራዊ ማድረግ፣ ደንቡ ተቀባይነት ካገኘ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተግባራዊነቱን የመከታተል ሃላፊነት ቢሰጠውና በየጊዜው ትምህርትና ሥልጠና በማካሄድ ቢደገፍ፣
7. ከሕዝቡ የሚጠበቀውን መለኪያዎች ከፍ ለማድረግና የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ አሰራሮችን ለመለወጥ የሥነ ምግባርና የዜግነት ኃላፊነትን በተመለከተ በት/ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲዎች እና በማህበረሰቡ ትምህርት የመስጠቱን ሥራ ማጠናከርና መቀጠል፣
8. የመንግሥት ሠራተኞችና የሥራ መሪዎችን በተመለከተ የሥልጠና መርሆችን እንዲሁም ሥልጠናውን በየጊዜው ለማካሄድ የበጀት ሥልጣንን ያካተተ የሕዝብ አገልግሎት የሥልጠና ፖሊሲ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣
9. የመንግሥት ሠራተኞችን እና የከፍተኛ ኦፊሰሮች ደመወዝ አፈፃጸማቸውንና የሥራ መደቦቹን ኃላፊነቶች በሚያመላክት

መልኩ መዘጋጀቱን ማረጋገጥና በየጊዜው የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም የገበያ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣

10. የሥነምግባር መለኪያዎችን አስመልክቶ ለንቁ፣ ለተደራጁና ራሳቸውን መግለፅ ለሚችሉ የሲቪል ማህበረሰብና ጠንካራ የፕሮፌሽናል ማህበራት የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሩ የመጫወቻ ሜዳ ማዘጋጀት፣
11. የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግሥት ሠራተኞችን አዋጅ ለማስፈፀምና የሜሪት ሥርዓትን፣ ገለልተኛነትና ቀጣይነትን ከጠንካራ የተጠያቂነት መሣሪያዎች ጋር ለማጎልበት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና መተግበር፣
12. የተለያዩ የሪፎርም እንቅስቃሴዎችና መሣሪያዎች ማለትም የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ፣ ሚዛናዊ ስኮር ካርድ፣ ካይዘን ወ.ዘ.ተ… ከዕቅድ፣ ቅደም ተከተል ከማዘጋጀት፣ ከትግበራ፣ ክትትል ከማድረግ፣ ድግግሞሽን ከማጥፋትና ውጤታማና አመርቂ ውጤቶችን ከማስመዘገብ አኳያ ተገቢ የሆነ የቅንጅት አሠራርን መዘርጋት፣
13. በሙያዊ ጋዜጠኝነት የታጠቀ ነፃ ፕሬስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና ኢ-ሥነምግባራዊና የሙስና ልምዶችን በሕዝብ እይታው ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል፣
14. በሙስናና በማጭበርበር በተጠረጠሩ ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ የሆነ የምርመራ ዘዴዎችን ለማካሄድ እንዲቻል የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን የፎሬንሲክ ምርምራ አቅምን ማጠናከር
15. የሕዝብ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ዜጎችና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት በግልጽ የሚያስቀምጥ የዜጎች ቻርተርን ማዘጋጀትና መተግበር፣
16. በመንግሥት፣ በግል ዘርፍ፣ በሲቪል ማህበረሰብ እና በሌሎችም መካከል የፀረ-ሙስና ቅንጅትን መመሥረትና ማጠግከር፤

## 16. ዋቢ መጻሕፍት

AH Consulting (2010), Assessment of the Implementation of Civil Service Reform Program (CSRP) in Ethiopia, Draft Report

Atkilt, A. (2012), Advanced Leadership & BPR, Training Document, AACCSA.

Chandler, R.G. and Plano, I.C. (1982), Dictionary of Public Adminstration John Wiley & Sons.

FCSA, (2010), Human Resource Management Strategy, (Draft)

Kilimanjaro International Corporation Limited, (2012), Ethiopia Second Corruption Perception Survey, Final Draft Report, Volume 1.

The Association of Chartered Certified Accountants (ACCA), Professional Accountantant, 2 Central Quay, 89 Hyde Park Street, Glasgow, G3 8 BW, UK.

World Bank (2012), Diagnosing Corruption in Ethiopia, Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors.

ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚዳርጉ ሁኔታዎች ለመከላከል የተካሄዱ የአሠራር ማሻሻያ የጥናት ሪፖርት፣ የፌዴራል ሥነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ መስከረም 2002 ዓ.ም.

ሙስና በአገር እድገት ላይ የሚያስከትለው አደጋ፤ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል፤ ኢ.አ ሰኔ 1991 ዓ.ም.

የፌደራል የሥነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ያከናወናቸው ተግባራት ያስገኙት ውጤት ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም.

የፌደራል ሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን የ2004 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸም ህዳር 2005 ዓ.ም.

የፌደራል ሥነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን የ2005 በጀት አመት የ10 ወራት የእቅድ አፈጻጸም ግንቦት 2005 ዓ.ም.

ሥነ ምግባር መጽሄት ቅጽ 12 ቁጥር 3 መጋቢት 2005 ዓ.ም.

የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ፣ ሚያዚያ 1993 ዓ.ም.

የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ 515/1999 ዓ.ም.